

t.me/OLDBOOKSPDF

(c) ሜጋ አሳታሚ ድርጅት:- 1990
Mega Publishing Enterprise:- 1998

ስልክ:-11-31-90
Tel:- 11-18-25
12-86-41

ፖ.ሣ.ቁ
12684
P.O. Box

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::
All Rights Reserved

የሽፋን ስዕል ሙሉብርሃን በላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

## ማውጫ

| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| **አስቀ በቃ** | |
| ዳኛቸው ወርቁ | 3 |
| **መልስዎ ይኸው** | |
| ዳኛቸው ወርቁ | 13 |
| **የፍጻሜ መጀመሪያ** | |
| በአሉ ግርማ | 23 |
| **ከምቡጠርና አቶ አሳዛር** | |
| ስብሃት ገብረእግዚአብሔር | 36 |
| **ሌሊን ድንጋይ ያሰበስከ** | |
| ስብሃት ገብረእግዚአብሔር | 50 |
| **እነሱ** | |
| ባሴ ሃብቴ | 58 |
| **ጭጋግና ጠል** | |
| ባሴ ሀብቴ | 79 |
| **ዘሳን** | |
| አዳም ረታ | 109 |
| **ማን ያውቃል** | |
| ደምሴ ፅጌ | 143 |

t.me/OLDBOOKSPDF

**ብርቅዬ**

ሰርቅ ዳንኤል..............................................................171

**ፍርሃት**

ሰርቅ ዳንኤል..............................................................199

**ሒሳብ**

መሐመድ አሊ..............................................................219

**ሴሳው አባወራ**

ሰለሞን አያሌው..............................................................240

**አውሬሪስ**

ፍሬህይወት ተሰማ..............................................................257

**ቱሱ ፎርሳ** ..............................................................272

t.me/OLDBOOKSPDF

# ዳኛቸው ወርቁ

(1928 – 1987)



ዳኛቸው ወርቁ የካቲት 16 ቀን 1928 በደብረሲና ተወለደ። ከልጅነቱ ጀምሮ የአፈንጋጭነት ባህሪይ እንዳለው የሚነገርለት ዳኛቸው ወርቁ በረጅም ልብወለድ ደራሲነቱ (በአደፍርስና በ The Thirteen Sun) እጅጉን ይታወቃል።ይሁን እንጅ ዳኛቸው ወርቁ ፀሐፌ ተውኔት፣ ገጣሚ ፣ የአጫጭር ታሪኮች ደራሲና ተመራማሪም ነበር።

ዳኛቸው ወርቁ ድርሰት መጻፍ የጀመረው ከተማሪነቱ አንስቶ ነበር። ህዳር 22 ቀን 1987 በምግብ መመረዝ ከዚህ አለም በሞት እስከተለየበት ጊዜ ድረስ በመድረክ የታዩና ያልታዩ ተውኔቶች፣ የታተሙና ያልታተሙ ግጥሞች፣ የታተሙና ያልታተሙ ረጅም ልቦለዶች እንዲሁም ሌሎች ሥራዎች ጽፏል። ከእነዚህም መካከል *“ሰው አለ ብዬ አላምንም፣” “ሰቀቀንሽ እሳት፣” “ትበልጥ”* የተሰኙ ተውኔቶች፤*“እምቧ በሉ ሰዎች”* የግጥም መድበል፤*“አደፍርስ”*ረጅም ልቦለድ፤ “The Thirteen Sun”በእንግሊዝኛ የተጻፈ



t.me/OLDBOOKSPDF

ረጅም ልቦለድ፤ይገኙበታል፡፡ “The Thirteen Sun” በሦስት ቋንቋዎች (በጀርመን፣ በፖርቱጋልና በቻይና ቋንቋዎች) ተተርጉሞ ታትሟል፡፡

ከእነዚህም በተጨማሪ “የጽሁፍ ጥበብ መማሪያ” እና “የአማርኛ ፈሊጦች” ከዶ.ር አምሳሉ አክሊሉ ጋር አዘጋጅቶ አሳትሟል፡፡

ዳኛቸው ወርቁ ከላይ በጥቅሉ በቀረቡ ሥራዎቹ እጅጉን ታዋቂ ቢሆንም አጫጭር ልቦለዶችንም ይጽፍ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል ለዚህ መድበል የተመረጡት “አለቀ በቃ” እና “መልስዎ ይኸው” አጫጭር ልቦለዶቹ ይገኙበታል፡፡

ዳኛቸው ወርቁ ከአገር ውስጥ ባችለር ዲግሪ፤ ከውጭ አገር የማስተርስ ድግሪ የነበረው የዘመናችን እውቅ ደራሲ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# አለቀ በቃ

"ተረት ተረት"አሉ ባለቤቷ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ዕድሜ ያለው የሚመስል አንድ ወንድ ልጅ እየተመለከቱ፡፡ ቤቱ ሬሳ የወጣበት ይመስል ጭር ብሎ ነበር፡፡

ከባንኮው በስተውስጥ ቆመዋል ባለቤቷ፤ በስተውጭ በጉን በኩል ሁለት ትራስ ተደራርቦ እተመቻቸበት ሶፋ ላይ አንድ ረዘም ያለ ቀጭን ሰው እግሮቹን በሰፊው አራዝሞ ተቀምጧል፡፡ የራሱ ፀጉር ከግምባሩ መካከል አንስቶ እስከ ማጅራቱ ተረተር ድረስ በቀጭኑ ተመልጧል፡፡ በረጅም መቃ ዓይነት ነገር የተሰካ ሲጃራውን ባውራጣቱና በትንሽ ጣቱ መካከል አሾልኮ በሌባ ጣቱ ጫን እያለ ካለፍ አገደም ወደ አፉ በመውሰድ የጭስ ኩቦቹን እያስከታተለ ቡልቅ ቡልቅ ያደርጋል፡፡ ዓይኖቹ በር በሩን ይመለከታሉ፡፡

"ተረት ተረት" አሉ ባለቤቷ ደግመው፡፡ "የላም በረት" መለሰች አንዲቷ ቆንጆ፤ አንድዬ በብዙው አንድዬ በትንሹ ሲጃራዋን እየመጠጠች፡፡ እንደ ሰውዬው የጭስ ኩቦች ለመስራት ትደክማለች፡፡ አልፎ አልፎም ትን እያላት እንደሳል ያረጋታል፡፡ በስራው የሰለጠነው ቀጭኑ ሰውዬ የጉድን አየት እያደረጋት ሳቅ ይላል፡፡ እያከታተለ – አንድዬ በዝግታ አንድዬ በፍጥነት ኩቦቹን በማስወጣት፡፡

"ተረት ተረት" አሉ ባለቤቷ ለሶስተኛ ጊዜ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"የላም በረት" አለች መልሳ፣ ኩቦቹን ለመስራት እየታገለች ቆንጆዋ፡፡

"አንቺ አልተጠራሽም" አሉ ባለቤቷ ኮስተር ብለው፡፡

ትንሹ ልጅ እክፍሉ ውስጥ ከተኮለኮሉት ሶፋዎች መካከል ረጅሙ ሶፋ ላይ ተቀምጦ ካርታ በመደርደር ይጫወት ነበር፡፡ ቆንጆይቱ ድንገት ብድግ ብላ መጥታ ካርታውን ከልጁ እጅ መንጭቃ ወስዳ የካርታ ጥንቆላ ጀመረች፡፡

"ምነው አስረስ ተረቱን ንገረን እንጂ" አሉ ባለቤቷ ዋጋ የሚያስከፍል በሚመስል ድምፅ፡፡

"አንድ ቤት ሁለት ውሾች ነበሩ"ጀመረ አስረስ፤ "ቤቱ ቀዳዳ ነበር" ቀጠለ አስረስ የተነጠቀውን ካርታ እየተመለከተ "በቀዳዳው ወጡ፡፡"

"ታዲያስ" አሉ ባለቤቷ፡፡

"አለቀ በቃ" መለሰ አስረስ፡፡ ዓይኖቹ ከካርታው ላይ አልተነቀሉም፡፡

"እሺ ፍቅርስ እንዴት ያረጋል?"ቀጠሉ ባለቤቷ፡፡

"ያስለቅሳል" አለ አስረስ፤ እንባው እንደመጣበት ዓይነት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ያስለቅሳል? ከየት አመጣኸው ደሞ እንዲህ ያለውን መልስ?"

ከባንኮው ወደሶፋው መጥተው ቀና አርገው ዓይኑን ይመለከቱታል።

"ምነው ምን ሆንክ?"
"ያስለቅሳል"

"አይ ለቅሶ እዚህ የለም፤ የምን ያስለቅሳል ነው ደሞ" ይቀጥላሉ ባለቤቷ ቆጣ ባለ አንደበት፤ ወዲያው ፊቱን አበስ አበስ በማረግ "በል እንግዲህ አሁን ንገረኝ፣ፍቅር ምን ምን ይላል?" በማለት።

"ስኳር ስኳር አይል...ማር ማርም አይል..."

"ጋብዙኝ"አለች ድንገት እጉኔ ተሰጋ ካርታ ቀሚዋ። ስትጠጋኝ አላየኋትም።

"ጋብዙኝ" አለችኝ ደግማ።

"ቢራ ጠጭ" አልኳት።"እሺ" አለችና ትንሽ "ጅን" ጠብ ያለበት "ቤርሙጥ" አምጥታ እጉኔ ተመልሳ ተቀመጠች። ባለኩቡ እግሩን አንጠ ራርቶ ባንኮው ወገብ ላይ ወግቶ በመወጠር ተዝ ናንቷል።

"ድገሙኝ" አለችኝ፤ ስትጨልጠው አላየኋ ትም። ደገመች። ከሰውዬው ሲጃራ ለምና አመ ጣችና በመለኮስ ኩቦቹን ለመስራት ትፍጨረ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጨር ጀመር እንደገና። ለኔ ለማሳየትም ይሁን ነገሩ አልገባኝም።እኔ ለራሴ የሲጃራ ሽታ ያሰክ ረኛልኝ አልወድም። ደጉ ነገር ፈንጠር ብዬ ነበር መስኮት አጠገብ የተቀመጥኩት። የቀዬ አምፖል ብርሃን ውጋጋን ፊት ላይ በማይንተገ ተግበት በኩል። የምጠጣውም የጊዮርጊስ ቢራ ነበር።

"ቆንጆ ፎርም አለኝኮ" አለችኝ ቀስ ብላ።

"ጥሩ ነው" አልኳት ክጨሱ በመሸሽ።

"ላሳይህ" አለችኝ።

"እየሁትኮ" አልኳት።

"የለም አላየኸውም" አለችኝ።

"አልገባኝም" አልኳት።

"ሶስት ዊስኪ ብትገዛልኝ አሳይሃለሁ" አለ ችኝ።

"ምን? ልብስሽን..." አልኳት ዓይኔ ሳልወድ ጉርጦ።

"አዎ ምናለበት..."

"ኧረ ተይ..."

"ልታይ አይደለም"

"ሁላችንም እያለን?"

"ምንድነው ስድስታችን አይደለንም..." አለች እንደሷ ዓይነት ቆንጆ ጓደኛዋን እየተመለከ ተች።

"ታዲያ አትፈሪም?"

"ምን ታደርጉኛላችሁ? አትበሉኝ"

"በምን ታውቂያለሽ?"

"አይ ከበላችሁኝም ሕግ አለ"

"አሁን እውነት ካንጀትሽ ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

በቀኝ እግሯ መሬቱን መታ መታ እያደረ ገች፤ ሐሳቧ ርቆ የሄደ፣ ከንፈሯ ብቻ የሚንቀ ሳቀስ በሚመስል ሁኔታ፥

"አይ ለዊስኪው ሰስተህ እንደሁ ተወው" አለችኝ፡፡

"ሰውነትሽን በመጠጣት ለመርሳት ትፈልጊያ ለሽን?" አልኳት፡፡

"ሳልጠጣ ሰው መሆኔን አውቀዋለሁ መቼ አልኩህ?" ስትል መለሰችልኝ፡፡

"እኔ መቼም ሰው ነሽ እላለሁ" አልኳት፡፡

"ሰው ስለሆንኩማ መጠጥ እፈልጋለሁ፡፡"

"የሰው ምልክቱ መጠጥ ነው?"

"አይ ለዊስኪው ሰስተህ እንደሁ ተወው!"

"እውን አሁን ያልሽውን ታደርጊያለሽ?"

"ለምን አላደርግም"

"አይ እንዲያው አልመሰለኝም"

"እንዲመስልህ ከፈለግህ ዊስኪውን ግዛልኝ" መልስ ከመስጠቴ በፊት ብዙ ጊዜ ቆየሁ፡፡

"እንግዲያውስ ጠጪ" አልኳት፡፡ እንደ.ት እንደሄደች የምታውቀው ራሷ ናት፡፡አንድ ግማሽ ጠርሙስ ዊስኪና አንድ ብርጭቆ ይዛ መጣች፤ ቀዳች፡፡ ባንድ ትንፋሽ ጠጣችው፡፡ ደገመች፡፡ አሁንም ባንድ ትንፋሽ ጠጣችው፡፡የነፋስ ስልክም ነፋስ እንደሆነ አላውቅም፤ እውነትም ጠምቷት ኖሯል፡፡

አየት አደረገችኝ፡፡ "ትዊስት" የሚባለው የዳ ንስ ሙዚቃ መሰማት ጀመረ፡፡ ከወንበሯ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያለች እንቅስቃሴዋን ጀመረች:: ሶስተኛ ጊዜ ዊስኪዋን ቀዳች:: ገንዘቤ መሆኑ ተሰማኝ::

"ታዲያስ ተነሻ" አልኳት::

የምትንጠራራም መሰለኝ::ሰው የምትጠራም መሰለኝ::ሸንጥና ዳሌዋን ጣቶቿንና ክንዷን የም ታሳየንም መሰለኝ:: አንደኛውን ጫማዋን አወለ ቀች:: ሁለተኛውን ደገመች:: ከወገቧ ጉብደድ፣ ከሸንጥና ከዳሌዋ ጉበጥ፣ከደረትና ከትከሻዋ ቀና ብላ ግራ እጅዋን አራዝማ በቀኝ እጇ ከግራ እጇ መዳፍ ጀምራ ክንዷን፣ጡቶቿን እስከ ቀኝ ትከ ሻዋ ጫፍ ድረስ በቀስታ እየደባበሰች ታሪካዊ አነሳስ አሳየች::ወደፊቷም እንደመንደርደር ብላ አንገቷን ብቻ ዘወር በማድረግ አንድ ባንድ አየችን::ቀስ እያለችም ወደ እኔ ዞረች:: እጇንም በማሽቆልቆል ከቁርጭምጭሚቷ ጀምራ ባትና ጭኗን እየደባበሰች ወደ ደረቷ አመጣችው:: እግረ መንገዷንም ሰውነቷን ገለጠችው:: የባት ጡንቻ የላትም፤ ሙሉዋ ሙሉ ነው:: እንደገና አየት አደረገችኝ፣ሳቅ አይሉት ሳቅ ሳቀች፤ አስፈ ራችኝ::ወዲያውም "ልድገም ወይ" አለችኝ፤ ዓይን ዓይኔን እየተመለከተች::ባለ ኩቡ ቀድሞ ድገሚ አላት:: የሚሰራው የጭስ ኩብ ራሱ ላይ ይትጉለጉላል::እኔ ነገሩም አልገባኝ፤ እሷና እሱ ግን ተግባብተዋል:: የምትደግመው ያሳየችውን ትርኢት ሳይሆን ውስኪውን ኖሯል:: አራተኛው ብርጭቆ ስሙ እውነትም ድጋሞሽ ከሆነ ደገ መች:: ትርኢቱ ቀጠለ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ሶፋ ላይ ነበር የተቀመጥኩት—እግሮቼን አዝ ናንቼ:: መጣች—በኋላዋ ወደ እኔ:: እጭኑ ውስጥ ቀስ እያለች ገብታ ቆመች፤ ጭንና ጭኔን እየነ ካካች:: ቀስ እያለችም ፊቷን ወደኔ አዞረች:: እኔ አዟዟሯን ስመለከት ጹሮ ሹራቧን አውል ቃለች:: የት እንደወረወረችው ግን እግዜር ይወቅ::

ከላይ የለበሰችው ስስ ሽሚዝ ነው:: ጉርድ ቀሚሷ በሰፊ ቀበቶ ታስሯል:: ደረቷን ሰፋ አድ ርጋ ቆማ ቁልቁል ተመለከተችኝ:: ከመቅጽበ ትም በረጃጅም ጣቶቿ ጸጉሬንና አንገቴን ስትዳ ብሰኝና ቀሚሷ እጫማዬ ላይ ሲወድቅ አንድ ሆነ:: አይኔ አብሮ ወደ ሆዴ ገባ::ቱር ብላ ወደ ወለሉ ስትወጣ እንኳ የሚታየኝ እንደ ህልም ነበር:: ብንን ያልኩት ብቻ እሜዳ ላይ ሳያት ነው::

ተመስገን ነው:: ሆኖም ታዲያ የውስጥ ልብ ሷን አላወለቀችም::ብዙም ሳይቆይ ወደ እኔ ቀስ እያለች ተጠጋች::እንደ በፊቱ ግን አልተሞኘ ሁም:: እግሬን ሰብስቤያለሁ:: ምን ያረጋል እሶ ፋው ገባችና እግሯን ጭኔ ላይ ጥላ ጀርባዋን ሰጥታ ተቀመጠችብኝ:: የተወለወለ ነው ጀር ባዋ:: ጠባሳና ኸንጉርጉርነት አይታይባትም::

"ቁልፉን ከኋላዬ ፍታልኝ" አለችኝ::
"የምኑን" አልኳት::
"የጡት መያዣየን"
"እንዴት ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይዞህ ንፁህ ነኝ፣ምን አስፈራህ? ጡቴን ማየት ጠላህ እንዴ? የወደቀ መስሎህ እንደሆ" አለችኝ::

"የለም ለሱ እንኳን ..." ብዬ በመመለስ ራሴን ማደፋፈሪያ ነገር ስጀምር እንደትሬንታ የሚጮህ የካርታ ድርጅት ታርጋ ያለበት "ቼብ ሮሌት" አቶሞቢል ወደ ነበርንበት ገደማ መጣ:: ቆመ::

"ታዲያ ምንድነው ፍታልኛ" አለችኝ:: ልፈታ ስፈራ ስቸር ሁለት ፈረንጆችና አንድ ኢትዮጵያዊ እኛ ወዳለንበት ገቡ::ዱሮ በምታው ቅበት ዘዴ ጡቷን ነቅነቅ፣ ደረቷን ሰበቅ ስታደ ርግ ጡት መያዣዋ ጧ ብሎ ኖሯል:: ውጥር ጥር ያለ ጃኬት የለበሰው አንደኛው ፈረንጅ ፊቱ ድንገት ደም ለብሶ ተንደርድሮ መጥቶ ታቅፎ ሲያሽከረክራት ሁኔታው ታየኝ::

የቤቱ ውስጥ ባንዳፍታ ነፍስ ዘራ:: አንዲቷ ዙሪያ ጠረጴዛ መጥረግ፣አንዲቷ መቀመጫ ማስ ተካከል፣ አንዲቷ ክንድ መጥለፍ ጀመሩ:: ልጅ ቷን ጥርቅም አርጐ አቅፏት የነበረው ፈረንጅ ድንገት ለቀቃት:: በቅጽበትም አንድ ስቴካ "ዊንስተን" ሲጃራ ከጃኬቱ ውስጥ አውጥቶ ከፈ ተና እቤቱ ውስጥ ላለው ሁሉ ማደል ጀመረ– እየወረወረ::ያመለጠንም ብንኖር ከመሬት አንስ ተንም ቢሆን ሲጃራችንን እየኪሳችን እደረግን:: እኔ እንኳን አላጨስም ነበር፤ከማን አንሼ አልተ ግደረደርኩም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ኩብ ሰሪው ኢትዮጵያዊ ዱሮ ባኮውን ቀደደና ሲጃራውን ተያያዘው። የሱም ተማሪ ቀደደችና ተያያዘችው። "ስቴካው"ሲጃራ አላለቀ ኖሮ ድጋሚ ሊሰጠን ሲል ባለቤቷ ከባንኮው ወጥተው ነጠቁት። "ሌላ ባለ ሱስ ሞልቷል" ብለው። የተረፈውን በሙሉ አውጥቶ ጨመረላቸው።

ኢትዮጵያዊውና አንደኛው ፈረንጅ ተመቻችተው ተቀመጡና መሎቲ ቢራ ተቀዳላቸው። ጋባዣችንም ፈረንጅ ትንሽ ወዲያ ወዲህ ካለ በኋላ ተቀመጠ።

ግብዣዬን የተቀበለችው ወይዘሮ እግዜር ይስጥልኝ እንኳ ሳትል ዱሮ ሄዳ እሱው ላይ ተጠመጠመች። እጉኔ የነበረውን ወንበር ወደ ፊቴ አሽቀንጥሬ እግሬን እላዩ ላይ ዘረጋሁት — ዘርግቼ የማላውቀው ሰውዬ። ቢራዬንም ጭልጥ አደረግሁና "ውስኪ ብላክ ኤንድ ሁዋይት" አልኩኝ ድምጼን ከፍ አድርጌ። ውስኪው ተቀዳልኝ፤ ባንድ ትንፋሽ ጭው አረግሁት። "ድገሚኝ" አልኳት። ስትደግመኝ ሁለተኛው ቅጂ ተቀጣጥሎ ቀርቧል። "ደብል" አልኳት፤ ሳቅ ብላ "ደብል" ቀዳችልኝ።

"አስረስ" አሉ እመይቴ "ተረት ተረት"

"ባንድ ቤት ሁለት ውሾች ነበሩ።ቤቱ ቀዳዳ ነበር። በቀዳዳው ወጡ።"

"ታዲያስ"

"አለቀ በቃ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጋብዘኝ"ትላለች የኔ ተጋባዥ ታቅፋት የነ በረውን ፈረንጅ እያሻሸች:: ሲጃራዬን ከኪሴ መዠረጥሁት "ክብሪት እባክሽ" አልኳት::

እውጭ ስወጣ አጥሩ ሥር እነበረው ቁሻሻ ውሃ መውረጃ ውስጥ ልገባ ነበር:: ቀና አል ኩኝ:: አለፍ አለፍ እያለ የደመና ኩብ ይትጉለ ጉላል:: የቤቱን መንገድ ስያያዝ ማካፋት ጀመረ::



t.me/OLDBOOKSPDF

# መልስዎ ይኸው

"አሜሪካን ኢንስቲቲዩት፣ አእምሮን የሚያንፀው ትምህርት ነው።" ይል ነበር፣ከፒያሳ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንገድ ሲመጡ፣ራስ መኮንን ድልድይ አለፍ ብሎ ከትራፊኩ መብራት በስተቀኝ እሚገኘው ቤት ግንባር ላይ አግድም ተጽፎ የነበረው አርማ። አባቴ ፊታውራሪ አበበ ጉግሣ፣ ከፒያሳ ቤታችን ወደ እንግሊዝ ትምህርት ቤት በወሰዱኝ– በመለሱኝ ቁጥር አይኔ ተገልጦ ቀና የምለው እዚህ ትምህርት ቤት አጠገብ በደረስኩኝ ጊዜ ነበር። ወይ ካሁን አሁን ይቀየራል፣ የትራፊክ ቀይ መብራት ፍራቻ ፍጥነታችንን እንድንቀንስ ያደርገናል፤ወይ እንዳጋጣሚ ሆኖ ቀይ ይበራና ጨርሶ ያቆመናል፤ ወይም የእግር መንገደኞች እንዳሻቸው ማቋረጥ፣ በዝግታ አሻልተን ማለፍን ይጠይቀናል፤ እንዲያው ብቻ ነበረው ነገር፣እዚያ ስደርስ፣ ነቅነቅ አድርጎ ቀና የሚያሰኝ ምክንያት ስለማላጣ፣

*"አሜሪካን ኢንስቲቲዩት*
*አእምሮን የሚያንፀው ትምህርት ነው"*

ወይ ደግሞ ከግድሞሹ ጽሑፍ ሥር የነበረው ከብ ጽሑፍ

*"የአሜሪካን የእውቀት ማስፋፊያ ትምህርት ቤት"* ———

ወይ እበራፉ አጠገብ ይቆም የነበረው ማቃረቢያ

"*ኑና ተመዝገቡ*" ሲለኝ አገኘው ነበር።

እያደርማ፣ እዚያ እስከደረስሁበት ጊዜ ድረስ ተኝቼ–ወይ ድንገት የነቃሁ፣ወይ አይኔም እያዩ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ጆሮየም እየሰማ፣አእምሮየም እያሰበ፣እጄም የደብ ተር ኮረጆዬን እያሻሸ፣ ሁሉም ለየብቻቸው ስራ ቸውን ሲሰሩ ቆይተው፣ እዚያ ቦታ ሲደርሱ አን ድነት ለመሆን የሞከሩ፤ወይ የሰው እጅ አንገቴን ጨብጦ፣ ራሴን ደፍጦ፣ ተጭኖኝ እዚያ ስደርስ የለቀቀኝ፤ወይ ደግሞ አባቴ፣እናቴ፣ ወንድሞቼ፣ እንቶቼ አናደውኝ፣ አሳዝነውኝ ድንገት እዚያ ስደርስ የልብ ልብ በቅቶኝ፣ የምመነጭቃቸው፣ የምጥሳቸው፣ እኔነቴን የማሳያቸው፣ —ፈጥኜም— ግደለም፣እኔ እናንተን አይደለሁም፤ይቅር ብያች ኋለሁ በማለት፣ አንጀቴን አፍታትቼ፣ ልቤን ሞልቼ፣ ደረቴን አሳድጌ፣ አንገቴን አንጥሬ፣ግም ባሬን የማሳይም ይመስለኝ ነበር። ብቻ የሚመስ ለኝን ሁሉ ብደረድረው ምን ያደርጋል፤ ባጭሩ መስሎኝ የማላውቀው ነገር አልነበረም። በርግጥ ግን በተለይ እዚህ ሥፍራ ስደርስ የምቀናበት ምክንያት ይህኛው ነው ብዬ ላውቀው አልቻል ኩም ነበር።

አንድ ዓመት፣ሁለት ዓመት፣ ሶስት ዓመት፣ አራት ዓመት አለፈ፤ ማለቴ ነጋ —ጠባ! አእምሮ ዬም በዚሁ ምትሐት፣ ታይቶ በሚመስለኝ ነገር እየሞላ ሄደ።— እክፍል ውስጥ ስማር— ስበላ፣ ስጠጣ— ስጫወት፣ሌሊት ወይም ቧት ስነቃ ልዩ ልዩ መልእክቱን እየያዘ ሲታየኝ ቆዬ። ምን አለ ፋን ብቻ፣ በነደደኝ ጊዜ እንኳ ሳይቀር፣ "አሜሪካን ኢንስቲቲዩት!" ብዬ መጮህም እም ጥቼ ነበር።

እክፍሌ ውስጥ እዘጋና "አሜሪካን ኢንስቲ ቲዩት" በማለት፣እያንዳንዱን ፊደል ረግጬ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሽንጤ ብድግ፣ ቀኝ እግሬን ወርወር፣ ግንባሬን ኮስተር፣ ቀኝ እጄን ሰቀል፣ ግራ እጄን ረዘም አድርጌ፣ በዘመናዊ ያነጋገር ፈሊጥ ስናገረው ... ብቻ ምን ያደርጋል...ነበረው ብቻ ነገር፡፡ ነበረው ነገር፡፡

አባቴን ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ለመንኳቸው፤ ከእንግሊዝ ትምህርት ቤት አስወጥተው አሜሪ ካን ኢንስቲቱዩት እንዲያስገቡኝ፡፡ ደጋግመው እምቢ አሉኝ፡፡ ለትምህርት የነበረኝ ፍቅር እየ ተቀነሰ ሄደ፡፡ አስራ አንደኛ ክፍል ስደርስ ወደ አስራ ሁለተኛ ማለፍ አቃተኝ፤ ወደቅሁ፡፡ አባቴ ደግሜ እንድማር አስገደዱኝ፤ ደገምሁ፡፡ ደግሜ ወደቅሁ፡፡ አሜሪካን ኢንስቲቱዩት አስገቡኝ፣ አል ፋለሁ፣ አልኳቸው ላባቴ፡፡ አልመሰላቸውም፡፡ እንግ ሊዝ አገር ልከው ሊያስተምሩኝ በብዙ ደከሙ፡፡ አቃታቸው፡፡ እባክዎ አሜሪካን ኢንስቲቱዩት ልግባ ይፍቀዱልኝ፣ ግዴለዎትም፣ ይመኑኝ፣ አላሳፍ ርዎትም ብዬ እንባዬ እያቀረረ ነገርኳቸው፡፡ በተ ርም የሚያስከፍሉት ሀያ ብር ነው ብለውኛል፣ መናኛ ትምህርት ቤት መሆኑን ተረድቻለሁ አሉኝ፡፡ የነፍስ አባታችንንና እናቴን አማላጅ ላክሁ፡፡ እየተነጫነጩ፣ እያጉረመረሙ፣ ከንዴታ ቸው የተነሳ የመኪናው ማርሽ አልገባ እያላቸው፣ ካሁን አሁን ገንጥለውት ያርፉሉ እያልሁ ስፈራ ስቸር፣ መድረስ አይቀርም፣ ደረስን፡፡"መኪና መግ ቢያ" የሚል ጦር፣ "መኪና ማስገቢያ" ወደሚ ለው መራን፤ ገባን፡፡ አንዲት ኮረዳ ከደረጃ ደረጃ ዱብ ዱብ እያለች ወረደች፡፡ አባቴ፣ በኃይል አቁ መው፣ በሩን ከፍተው በመውጣት ቶሎ ብለው፤



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዴሬክተሩ አሉ እንዴ?" ብለው ልጅቱን ጠየቋት፡፡

"ባለቤቱ የሉም፤ ገንዘብ ተቀባይዋ አሉ" አለቻቸው፡፡

"ና እንጂ ውጣ ታዲያ ምን ይወዝፍሃል? " አሉኝ፡፡ ወጣን፡፡ ተከታትለን ደረጃውን ወጣን፡፡ እውስጥ አንዲት ሌላ ሴት ልጅ ተቀበለችን፡፡

"እዚህ ይሻላችኋል" አለችን-እኔን እንደምታውቀኝ ዓይነት ትክ ብላ በማየት፡፡ ተከትለናት ገባን፡፡ ያባቴ ፊት ትንሽ ፈገግ አለ፡፡ የእንግዳ መቀበያ ክፍሉን ንጽህና ሲያዩ በመደሰት መሰለኝ፡፡

"ምን ላምጣ" አለች ልጅቱ ተመቻችተን ከተቀመጥን በኋላ፣ እኔን እየተመለከተች፡፡

"ዲሬክተሩን ... ለማነጋገር..." ብለው ጀመሩ አባቴ፡፡
"የሚጠጡት ምን ላምጣ?" አለች ልጅቱ፣ አባቴ የጀመሩትን እንዳልሰማ ዓይነት————፡፡

"የምንጠጣው ... የምንጠጣው ..." አሉ አባቴ፣ አፍንጫቸውን እያቁነጠነጡ፡፡ወዲያውም ግንባራቸውን ኮስተር አርገው ቡና አሏት፡፡
"ለርስዎስ?" አለችኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሱ ሊመዘገብ የመጣ ተማሪ ነው፤ ምንም አይፈልግም" አሏት አባቴ፡፡ ዓይኗን ቦግ፣ አንገቷን ሰግደድ በማድረግ ሽንጧን መታ አድርጋ ተመልሳ ገባች፡፡ "አልጠላሽም ከቶ" የሚለው ሙዚቃ ድንገት ጀመረ፡፡ ያባቴ ዐይን ምናምን ያጥበረበረው መሰለ፡፡ ልውጣ ልውጣ፣ ቁጭ ብድግ፣ ይንቀጠቀጥ ጀመር፡፡ ድንገት ተነስተው ልጅቷ በገባችበት በር አንገታቸውን ሰከክ አር ገው ወዲያው ስግጥጥ ሲሉ አየኋቸው፡፡ ዐይናቸው ድንገት የተወጋ ይመስል፣እስከዚያን ያላየ ሁባቸው የተዛነፈ ቁመና፣ ድንገት ትከሻቸው ውድቅ ብሎ ወጡ፡፡ እኔም ምንነካቸው በማለት ተከተልኳቸው፡፡ከመከተሌ በፊት ግን እኔም እን ደሳቸው አንገቴን ሰከክ አደረግሁት፡፡ "መኝታ ቤት አለ" አለኝ እባንኮው አጠገብ በጉልህ ተጽፎ የተንጠለጠለው ጽሑፍ፡፡ ዝም ብዬ ቆምሁ፡፡ "ግቡ" አለችኝ ልጅቱ እየሳቀች፡፡ "ግቡ" አለችኝ ደግማ! መልስ አልነኩኝ ድንገት ከበሩ፡፡ "ሒሳብ፣ ሒሳብ!" አለችኝ ከማጅራቴ እየተከተለች "ሒሳቡን አልከፈሉም" አለችኝ፡፡ ዝም ብዬት ወጣሁ፡፡

አባቴ መኪናው መሪ ላይ አቀርቅረው ጠበ ቁኝ፡፡በሩን ከፍቼ ገባሁ፡፡ ሞተሩን አንቀሳቀሱ፡፡ ልጅቱ"ሒሳብ አልተከፈለም" አለች በማስታወስና በማዘዝ መካከል ባለ አንደበት ወደ አባቴ ቀረብ ብላ፡፡

"ምን?" አሏት አባቴ ደንገር ባለው፣በለዘበና ባዘነላት በሚመስል ድምፅ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሒሳብ አልተከፈለም" አለች እሷም፣ የቀ ድሞ እንደበቷን ቶሎ ለውጣ በለሰለሰ ድምፅ:: ቸኩል ብላ በመቀጠልም " ... ግዴለም ... " አለች አባቴን ዐይን ዐይናቸውን እያየች "... ቦርሳዎን እረስተውት እንደሁ ድንገት...ማለቴ በሌላ ጊዜ ይከፍሉኛል፤ ምንም አይደል ... "

"እረ የለም፣እረ የለም!" አሉ አባቴ ኪሶቻ ቸውን እየደባበሱ::

"... ግዴለም እውነቴን ነው፤ ግዴለም..." አለች ልጅቷ በተናገረችው በመጠንከር:: ዝር ዝር ፍራንክ አጡ መሰለኝ አንድ ብር አውጥ ተው ሰጧት::ወዲያው መኪናቸውን አንቀሳቀሱ::

"መልስ አለዎት!" አለች ልጅቱ የመኪናዋን መንቀሳቀስ ስታይ:: ለባቴ እንዳልሰሚት ዓይነት ቀጠሉ::"መልስ አለዎት" ብላ እንደገና ጮኸች መኪናዋን በመከተል:: አባቴ አሁንም ዝም ብለ ዋት ቀጠሉ:: ደጋግማ፣"መልስ አለዎት፤መልስ አለዎት" እያለች ተከትላ የሚያቆምላትም ሆነ የሚመልስላት በማጣቷ ዝም አለች:: ድንገት መለስ አልኩኝ—በሩን እንደወጣን:: "የመኪና ማስገቢያ" እሚለው በር ስር ቆማ በመገረም ስትመለከትና ወዲያው በቅጽበት ወደ ቤት ውስጥ ተመልሳ ስትሮጥ አየኋት::

አባቴ፣ ወደ ፒያሳ በመመለስ ፈንታ ወደ አራት ኪሎ ጠመዘዙ:: እንደልማዱ መብራቱ



t.me/OLDBOOKSPDF

አቆመን፡፡ እንደልማዴም ቀና አልኩኝ “አለም ማያ ቡና ቤት፤ የስልክ ቁጥር...” ሲለኝ አየ ሁት አግድሞሹ፤ ዓይኔን አፈጠጥኩበት፡፡ እስሩ የነበረው ክቡ ታወሰኝ-...

ልጅቷ በወዲህኛው በር ዱሮ ወጥታ—“መል ስዎ ይኸው! መልስዎ ይኸው!” እያለች በመ ጮህ ወደ ባቡር መንገድ ስታመራ፣ ብጫው መብራት በራ፡፡ የቤንዚኑን መስጫ ረገጡት አባቴ፣ ፍሬሲዎኑን ሳይለቁ፡፡ መኪናይቱ በሃይል እንክራፍታ መንገዱን ቀጠለች፡፡ የልጅቱንም ድምፅ ዋጠችው፡፡

ዝም ብለው ነዱ አባቴ፤ የነፃነት ሐውልትን አለፍን፤ ኮሌጁን አለፍን፤ ስላሴን አለፍን፤ የወ ጣቶች ልጆች ክርስቲያናዊ ማኅበርን አለፍን፤ የእንግሊዝ ት/ቤትን አለፍን፤ ዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታልን አለፍን፤የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨ ርሲቲን በቀኝ፣የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሆስፒታልን በግራ ትተን አለፍን፤ ውቤ በረሃን፣ አሮጌውን ማዘጋጃ ቤት አለፍን፤ የምኒሊክን ፈረስ በግራ፣ ጊዮርጊስን በቀኝ ትተን አለፍን፤ አዲሱን ማዘ ጋጃ ቤት አለፍን፤ ሄድን፤ ሄድን፤ ሄድን፤ ድንገት ቆምን፤ የመኪናይቱ ጩኸት ድንገት ተዋጠ-በማይዋጥ ነገር—መልስዎ ይኸው፤መልስዎ ይኸው—ይል መሰለኝ ይኸው ነገር—

“ያቺ ልጅ ... ያቺ ልጅ ... ”አሉ አባቴ ... መለስ ብዬ አየኋቸው፡፡ “ያቺ ልጅ ... ያቺ ልጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

..." አሉ አሁንም ደጋግመው ትክ ብለው በፊት ለፊታቸው እያዩ " ... እህትህን ትመስላለች" – አቤታችን ደርሰን ኖሯል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# በዓሉ ግርማ

(1930-1975)



በዓሉ ግርማ በ1930 በኢሉባቡር ሱጴ ከተማ ተወለደ:: በአባቱ ህንዳዊ በእናቱ ኦሮሞ (?) የሆነው በዓሉ ግርማ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በኢሉባቦር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በጄኔራል ውንጌት ተከታትሏል::የከፍተኛ ትምህርቱንም በመከታተል ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባችለር ከአሜሪካ ደግሞ የማስተርስ ድግሪ አግኝቷል::

በዓሉ ግርማ በሕይወት ዘመኑ የ "መነን" ና የ "አዲስ ሪፖርተር" መጽሔቶች፣ የ "አዲስ ዘመን" ና የ "The Ethiopian Herald" ጋዜጦች አዘጋጅ ሆኖ አገልግሏል:: በተጨማሪም የዜና አገልግሎት ሐላፊና የባህል ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪም ሆኖ ነበር::

በዓሉ ግርማ በአገራችን ስመ ጥር ከሆኑ ደራሲያች መካከል አንዱ ነበር:: የፈጠራ ድርሰቶችን ደጋግሞ በመጻፍና በማሳተምም ይታወ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቃል፡፡ "ከአድማስ ባሻገር"፣ "የህሊና ደወል"፣ "የቀይ ኮኮብ ጥሪ"፣ "ሀዲስ" (ከህሊና ደወል ጋር ዝምድና አለው?፣) "ደራሲው"ና "እሮማይ" በህዝብ ዘንድ በእጅጉ የሚታወቁ ልብወለድ ድርሰቶቹ ናቸው፡፡ በዓሉ ግርማ በተለይ በኦሮማይ በጊዜው የነበሩትን የደርግ ባለስልጣናት በማስከፋቱ ራሱን መስዋዕት ያደረገበት የመጨረሻው የታተመ ልብወለድ ድርሰት ነው፡፡

በዓሉ ግርማ የረጅም ልቦለድ ደራሲ ከመሆኑ በስተቀር በአጭር ልቦለድ ደራሲነቱ አይታወቅም፡፡ሆኖም"ኦሮማይ'ን በማሳተሙ ዋዜማ ላይ በየካቲት መጽሔት የወጣ አንድ አጭር ልቦለድ አለው፡፡ይኸው "የፍጻሜ መጀመሪያ" የተሰኘው በዚህ መድበል ውስጥ ይገኛል፡፡ በዓሉ ግርማ በታሪክ አወቃቀሩ፣ በግጭት አፈጣጠሩ፣ በገፀባህሪያት አሳሳሉ፣ በገለፃው፣ በቋንቋ ውበቱ በበርካታ ጀማሪ ደራሲዎች ስራዎች ላይ የጎላ ተፅእኖ ያሳደረ የፈጠራ ሰው ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# የፍፃሜ መጀመሪያ

የምሰጋ ሰው እንኳ አይደለሁም፡፡ግን በጣም ሰጋሁ፡፡ስለሰንታየሁ መስጋት ከጀመርኩ ሰንብቻ ለሁ፡፡እንደልማዱ ኩተሰወረ ቆይቷል፡፡ሶስት ወር አልፎታል፡፡መጨረሻ ያየሁት ምሽት የወትሮው ሰንታየሁ አልነበረም፡፡ ሳቂታ፤ ተጫዋች፣ ጠጡ ልኝ ብሉልኝ ማለት የማያታክተው ሰንታየሁ አልነበረም፡፡ ሲበዛ ቀልደኛ ነው፡፡ ያለሳቅ ህይ ወት ምንድነው! ማለት ይወዳል አዘውትሮ፡፡ እና ያቀልዳል፤ ያስቃል ... ሰቆ ያሳስቃል፡፡ ቀልድ ሲያልቅበት "ያ ቀልድ ትዝ ይልሀል?" ብሎ ይጠይቀኛል፡፡

"የቱ ልጅ"
"ሶስተኛው"

እና ሶስተኛውን ቀልድ እያስታወስን መሳቅ እንጀምራለን፡፡ለምናውቀው ቀልድ ሁሉ ቁጥር፤ ቁጥር አድርገናል፡፡ እኔ አንዳንዴ በቁጥሩ ቀል ዱን ማስታወስ ያሳነኛል፡፡ እሱ ግን ምንም አይ ረሳውም፡፡የሚደንቅ የማስታወስ ችሎታ አለው፡፡ ማስታወሻ አይዝም፡፡ከት/ቤት ጀምሮ ማስታወሻ ሲይዝ አይቼው አላውቅም፡፡ዓመት ሁለት ዓመት ቆይቶ ያን ቀን የተባለውን ወይም የተደረገውን ነገር ሲጠይቁት ግን አንድ ባንድ ዘርዝሮ ያስረ ዳል፡፡ ማንኛውንም ነገር እንደ ፎቶግራፍ ማንሻ ቀርጾ ለማስቀረት የሚችል ጭንቅላት አለው፡፡ ምናልባት ለዚህ ይሆናል ደራሲ የሆነው—አንድን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ደራሲ የሚያደርገው ምን እንደሆነ ባላው ቅም ቅሉ:: እንደ እድል ሆኖ ከስንታየሁ ቃለ ህይወት ሌላ ደራሲ በቅርብ የማውቀው የለኝም:: ሁሉም እንደስንታየሁ ከሆኑ ግን ከሩቅ ሊሸኟ ቸው የሚገባቸው ፍጡሮች ናቸው:: እውነቴን ነው:: ለጓደኝነት አንድ ደራሲ ይበቃል– እሱም በስንት መከራ::

አይ ስንታየሁ! ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ልክ የለውም::ሲጠጣ እንደ ዓሳ፣ሲወድ እንደ ጳጉሜ ውሻ፤ ሲቸር እንደ ንጉሥ፤ ሲያጣ እንደቤተ ክርስቲያን ዓይጥ ነው:: ለነገ የሚለው ነገር ከቶ የለውም:: የሚያደርገው ነገር ሁሉ ከልክ በላይ መሆን አለበት:: ከእሱ ጋር አብረውት እንዲስቁ ሲስቅ፤ከእሱ ጋር አብረውት እንዲያለቅሱ ሲያለ ቅስ፦ ይፈልጋል::ሕይወትን ካልኖርከው እንዴት ልታውቀው ትችላለህ? የሚል ፈሊጥ አለው:: ኃጢአት ነው የሚለው ነገር ያለው አይመስ ለኝም:: ሕይወት ያለ ኃጢአት ልትሰራ አትች ልም፤ ከኃጢአት ባሻገር ምንም የለም:: ሕይ ወት በራሷ ፍፃሜ ናት ባይ ነው:: እና ይኖረ ዋል::

መፃፍ ሲጀምርም እንደዚሁ ያበዛዋል:: ከእ ያንዳንዱ ቃላትና ከያንዳንዱ አረፍተ ነገር ጋር እየተጣላ፤ እየተጨቃጨቀ፣ አማን ሲወርድም እየተዋደደ፣ እህል፣ ውሀ ወይም ዕረፍት ሳይል ልቡ ውስጥ ያለውን ሀሳብ አውጥቶ በውበት ወረ ቀት ላይ ካላሰፈረ ቀና አይልም:: ሰው አያነጋግ ርም፤ ሌላ ደስታ አይኖረውም:: ከፈጠራ ስራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምትሀት ስር ይወድቃል። ለጥበብና ለውበት ፍፁም ተገዢ ይሆናል፤ አንዳንዴ ስመለከተው አንድ የማይታይ ኃይል የሚያመልከ ወይም የሚያነጋግር ይመስለኛል። የውበት አምላክ ካለ አንድ በቅጽበታዊ ጨረፍታ የማየው ከስንታየሁ ቆንጆ ገጽታ ላይ ነው። ቆንጆ ፊቱ አንዳንዴ ዝም ብሎ፤ ፀጥ ብሎ ይፈካል—ፈገግ፣ወከክ፣ፈካ እያለ፤ ፀዳል፤ ብርሀን እየሆነ ይሄዳል። ብዕሩ ይንደረደራል—ቀለሙ ይፈሳል።የሆነ ነገር ሲሰም ርለት ትንፋሽ ያለው መስሎ አይታይም።

'ልቡ ቆሞ ይሆን?' እላለሁ አንዳንዴ። ውበት ልብ ያቆማል ልበል! እና በውበት አምላክ ፊት ወጣት ይሆናል—ውብ ወጣት። አጠገቡ መኖሬን ፈጽሞ ይዘነጋል። እንዴ መጻፍ ከጀመረ ከድር ሰቱ ውጭ ላሉ ምንም ነገር ሕላዊ የለውም። እኔም ብሆን አላስቸግረውም። የፈጠራ ውበት፤ ጭንቀትና ደስታ ስለማይገባኝ ነው መሰለኝ፤ በልቤ ለምን ነው?ይህ ሁሉ ጭንቀት ምንድነው? እያልኩ ያደረበት ምትሀት እስኪያልፍለት ድረስ ዝም ብዬ እጠብቀዋለሁ። ምትሐቱ በላዬ ላይ እንዳለ ከቀጠለም ጥዬው እሔዳለሁ።

አንዳንዴ ቀና ብሎ በረጅሙ የደስታ ትን ፋሽ ከተነፈሰ በኋላ፤ "እለህ እንዴ?" ይለኛል።

"አዎ፤እንዴት ነው?"
"ውብ ነበር። ስንት ሰዓት ነው?" በማለት በደስታ እጆቹን እያሸ፤ "ውብ ነበር። ሔደን



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ቀን እናከብረው፡፡ ጂን ቶኒክ ለዘላለም ይኑር ... ታውቃለህ? ዛሬ አንድ ነገር ተረዳሁ ስለ ሰው ልጅ" ይለኛል፡፡

በየጊዜው ስለሰው ልጅ አንዳንድ ነገር ይረዳል፡፡

"ምን ልጁ?"

"ታውቃለህ? ውበትን ከማድነቅ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው በልቡ ክፉ አይደለም፣ሊሆንም አይችልም፡፡ አይመስልህም?"

"እውነት?"

"ለማንኛውም ነገር ዛሬ ካንዱ ባሕርይ የተረዳሁት ይህን ሀቅ ነው፡፡ ከምትፈጥራቸው ባህሪያት ተመልሰህ ትማራለህ– ከሚፈጥራቸው ባሕርያት ተመልሶ የማይማር ወይም ስለሰው ልጅ አዲስ ነገር የማይጽፍ ደራሲ የሞተ ነው፡፡ አይመስልህም? አሁን እሱን እንተወውና ሄደን እንጠጣ፤ ከሕይወት ጋር ፍቅር ይዞኛል፡፡ እና ለሕይወት ውበት መጠጣት እፈልጋለሁ፡፡"

ለምን በጂን ቶኒክ ለመስከር እንደሚፈልግ አይገባኝም፡፡ ዘላለሙን በሕይወት አረቄ እንደሰከረ ነው፡፡ ሲደሰት ብቻ አይደለም የሚጠጣው፡፡ ውበት አልታይ ያለው'ለትም ይጠጣል፡፡ከውበት ጋር ያልተሞሸረ'ለት ድንገት ያረጅብኛል፡፡ ውበቱ ከፊቱ ይጠፋል፡፡ጥርሱ ያገጣል፡፡ ግንባሩ ይቋጠራል፡፡ ሕይወቱ እውስጡ ታፍኖ ሊፈነዳ ይደርሳል፡፡እና ይጠጣል፡፡ ለውበት አምላክ ብዙ ጂን ቶኒክ ይለዋል፡፡ግን ብዙ የሚጠጣው አንድ መጽሐፍ ደርሶ ጨርሶ ሌላ አሳብ በሚፀንስበት



t.me/OLDBOOKSPDF

ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ያኔ ዝምታ ያበዛል፡፡ ዝምታው መጨረሻ የለውም፡፡በዚያን ወቅት ቢኮረኩሩትም አይስቅም፡፡ዝም ብሎ ይተክዛል፡፡ዝምታው ግሩም ነው፤ ውብ ነው፤ድንቅ ነው፡፡ እጭንቅላቱ ውስጥ ግሩም አሳብ ትርትር ሲል የሚሰማኝ ይመስለ ኛል፡፡ ብሩህ ገጽታው ላይ ችግር ምንድነው? የሕይወት ውበቷ ከመኖር ላይ ነው የሚል ይነበ በኛል፡፡እና ሁልጊዜ እንዲያስብና እንዲፅፍ እፈል ጋለሁ፡፡

ላናግረው አልሞክርም፡፡ አንድ ቃል ሳንለዋ ወጥ ብዙ ቀንና ምሽት አብረን እናሳልፋለን፡፡ እውቀዋለሁ፡፡ያውቀኛል፡፡ ዝምታችን በቂ ነው፡፡ የግድ መነጋገር የለብንም፡፡ አብረን እስከሆን ድረስ ዝምታችን ያስደስተናል፡፡እንደውነቱ ከሆነ በዝምታችን ውስጥ ብዙ የምንግባባበት ነገር እን ዳለ ይሰማኛል፡፡ እኔም ሆንኩ እሱ አንዱ ሌላ ውን ለማስደሰት የምናደርገው የተለየ ጥረት የለም፡፡ የልብ ጓደኞች ነን—በቃ፡፡

እኔ ለእሱ ከዚህም በላይ ነኝ—ማለቱ እኔ ለእሱ ከጓደኛም በላይ መሆኔን ብዙ ጊዜ ነግሮ ኛል፡፡የሚጽፈው ለኔ ነው፡፡እኔን ፊቱ ቁጭ አድ ርጐ ነው የሚጽፈው፡፡ ካለኔ ሌላ ታዛቢም፣ተመ ልካችም፣ አንባቢም ሆነ ሐያሲ አያውቅም፡፡

"አሁን የምጽፈው ነገር ሕሊናን ያረካው ይሆን?" የሚል ነው የመጀመሪያው ጥያቄ፡፡ በነ ገራችን ላይ ህሊና እባላለሁ፡፡ሕሊና ይፍረደኝ፡፡ የሚጽፈው ነገር እኔን የሚያረካኝ መስሎ ካልታ



t.me/OLDBOOKSPDF

የው ወይም ከተሰማው ባሳቡ ወደፊት አይገ ፋም፤ እዚያው ይገድለዋል:: በእኔ ምክንያት ስንት ጥሩ አሳብ ገድሎ እንደጣለ አላውቅም:: እርግጠኛ ነኝ ብዙ ናቸው:: ኃላፊነቱ ይሰማ ኛል፤ ይከብደኛል:: "እኔ ማን ነኝ? ሌሎች ታዛ ቢዎችን እያሰብክ ፃፍ:: እኔን ተወኝ" እለዋ ለሁ:: ምን ርግማን ብሆንበት እና ምን ቢጠላኝ ግን አይተወኝም::

"ምን ማለትህ ነው?"

"ደርቄአለሁ"

"አትቀልድ!"

"ቀልዴን አይደለም:: የምለው አዲስ ነገር የለኝም::ሌሎች ያላሉት፣ያልዳሰሱት ምን አዲስ ነገር ልል ወይም ልፈጥር እችላለሁ::ብዙ በጻፍ ክና ባነበብክ ቁጥር ብልህ ከሆንክ የምትገነዘበው ነገር ቢኖር ዝም ማለት የሚመረጥ መሆኑን ነው:: እውነቴን ነው:: የገደል ማሚቶ ከመሆን ዝምታ ይመረጣል:: በራስህ የዝምታ ጥልቀት ውስጥ መስመጥ ራሱ ውበት ነው::" አለኝ::

"ሶስት ልቦለድ ብቻ ጽፈህ እንዴት እንዲህ ማለት ትችላለህ?እኔ ካንተ ብዙ ነገር ነበር የም ጠብቀው" አልኩት::

"ከሶስት ልቦለድ በላይ ልሔድ የማልችል ቢሆንስ?ማንም ከልኩ አያልፍም::አንዳንድ ሰዎች አንድ ልቦለድ ጽፈው ያቆማሉ:: እንደኔ ያሉት ሶስት ጽፈው ያቆማሉ::ሌሎች የታደሉ ደራሲያን አሥር፣አሥራ አምስት ወይም ከዚያ በላይ ይሄ ዳሉ:: አዲስ ነገር ለማለት ወይም ለመፍጠር



t.me/OLDBOOKSPDF

እስኪችሉ ድረስ ቢቀጥሉ ጥሩ ነው፡፡ እኔን የሚ
ያሳዝኑኝ ምንም አዲስ ነገር ለማለት ወይም
ለመፍጠር ሳይችሉ ለመቀጠል የሚፈልጉ ጅሎች
ናቸው፡፡ጥቅሙ ምንድነው? አዳዲስ ነገር ለማበ
ርከት የማይችሉ መሆናቸውን በወቅቱ ተገንዝ
በው ዝምታን የሚመርጡ እንዳልኩህ ብልሆች
ብቻ ናቸው፡፡እኔም ብልህ ነኝ — ጉረኛ ባትለኝ”
ብሎኝ ዝም አለ፡፡

በልቤ ዛሬ አልለቅህም አልኩና፣ “እንደ እው
ነቱ ከሆነ ልጅ ነህ!” ብዬ ጮኩበት...፡፡

“እንዴት እስቲ ንገረኝ” አለኝ፡፡

ነገርኩት፡፡ታላቅ አብዮት በመካሄድ ላይ ይገ
ኛል፡፡ አሮጌው ስርአት እየሞተ አዲሱ እያቆጠ
ቆጠ ሲሔድ እናያለን፡፡ ማኅበረሰቡ እንዳለ በእን
ቅስቃሴ ላይ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቀን በእውነት
አዲስ ነው — ማለት የተፈጥሮን ህግ ተከትሎ
መሽቶ የሚነጋ ተራ ቀን አይደለም፤ ወይም አይ
መስለኝም፡፡ እኔ...እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ካለፉት
ስምንት አመታት ጀምሮ ሰለቸኝ፤ ረዘመብኝ
ያልኩት ቀን ትዝ አይለኝም፡፡ እያንዳንዱ ቀን
የራሱ ገድል የራሱ የሆነ ሽንፈትና ድል፤ የራሱ
የሆነ ውበት አለው፡፡

ኢትዮጵያ ላይ በዘልማድ ነግቶ የሚመሽ ቀን
የለም፡፡ታዲያ ይህ ሁሉ ምንድነው? ለደራሲያን
ከዚህ የበለጠ የወርቅ ማዕድን፤ ከዚህ የላቀ
ልምድ፤ከዚህ የተሻለ ታላቅ ትምህርት ቤት ምን



t.me/OLDBOOKSPDF

አለ? ሂድና ጻፍ! ብትፈልግ ዝፈን:: ቢሻህ አል ቅስ::ግን ጻፍ:: ሁሉም በመረጠው መልክ መታ ገል አለበት! ትግል የሌለበት ሕይወት የለም:: ግን ትግል ሲባል መጀመር ያለበት ከራስ ነው:: ትልቁ የሰው ልጅ ፈተና– ትግል ከራስ::

ሂድና ፃፍ! ቃላት ኮረት ወይም ድንጋይ አልሆኑም:: ውበት ሞታ አልተገነዘችም:: አዲስ ውበት–አዲስ ሐቅ– አዲስ ተስፋ ሞልቷል–በየመ ንገዱ– በየፋብሪካው–በየማሳው::ሂድና ጻፍ! በዚህ ጊዜ ብዕሬን ካፎቱ ልክተት የሚል ደራሲ–:: እኔ እንጃ ... በማለት ነገርኩት፤ ጨቀጨቁት::

“ደርቄ አለሁ አልኩህ አትሰማኝም? የውበት አምላክ ፊቱን አዙሮብኛል-ብቃ”

“አላምንም፤ ወይስ ሌላ ምክንያት አለህ?”

“ምን ሌላ ምክንያት ይኖረኛል?”

“ምናልባት አብዮቱ አስጠልቶህ እንደሆን? የፈጠራ ሰዎች ስትባሉ መቸም ስሜታዊ ናችሁ ... ”

“በአብዮት ላይ እምነት📖 ለሰው ልጅ ፍቅር እንዳለኝ ታውቃለህ ... ”

“ታዲያ ምንድነው?”

“ደርቄአለሁ ስልህ ለምን አይገባህም!”

“አይገባኝም!”ብዬው ከፊት ለፊታችን የተደ ረደሩትን የአረቄ መለኪያዎች ደፍቼ ተነሳሁ::

ዓይኖቼን ለማመን ያቃተው ይመስላል:: አንዴ ወደ ፈሰሰው ጂን አንዴ ወደ እኔ እያፈ



t.me/OLDBOOKSPDF

ራረቀ ሲመለከት ቆየ፡፡ እንዲህ ሆኜ አይቶኝ አያውቅም፡፡

"ዛሬ ምን ነካህ?" አለኝ፡፡

"ምን ሆኛለሁ?"

"ተለወጥክብኝ፡፡"

"ያው የድሮ ሕሊና ነኝ"

ግራ እንደተጋባ ከፊቱ ላይ ይነበብ ነበር፡፡

"ጥሩ ጂን ለምን ታፈሳለህ ጃል?" አለኝ ሊያረሳሳኝ፡፡

"ከእንግዲህ ይበቃል! እኔ ያንተ አስታማሚ አይደለሁም፡፡ ከፈለክ ጂን ከተጠመቀበት ጋን ውስጥ ገብተህ ልትሰምጥ ትችላለህ፡፡ድንገት ምን ፈሪ እንዳደረገህ አላውቅም፡፡ ደፋር ትመስለኝ ነበር፡፡ ገደል ግባ" አልኩት የምሬን፡፡

"የት ልትሔድ ነው?"

"ጂን የሚጠጣ ሌላ ጓደኛ ፈልግ!"

"ያልገባህ ነገር አለ ... "

"አዎ፤ ከእውነት አትሽሽ" ብዬው ጥየው ሄድኩ፡፡

ይህ ከሆነ ቆይቷል፡፡ ምናልባት ዘላለሜን እንድሰቃይ ፈልጎ ይሆናል—የትም ሔዶ ጠፍቶ የቀረው፡፡ ብቸኛ ተደራስያኑ አይደለሁ! እየተሰቃ የሁ እንድኖር ፈልጎ ነው፡፡ወደሞት ሰደድኩት፡፡ የሞተ ምናለበት? አረፈ ተገላገለ፡፡ ቀሪው ይጭነ ቀው፡፡ ምነው ባልተናገርኩት፤ ኃጢአቱ ከበ ደኝ፡፡ ሳይታወቀኝ እንባዬ መጣ፡፡ ባንድ ፊት ደግሞ ንዴት አደረብኝ፡፡ የምን አትርሱኝ ነው እሱ! ሆን ብሎ ይሆናል እንዲህ ያደረገው፤



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘላለሜን እንድረሳው? ማን ተረስቶ ለመቅረት ይፈልጋል–ከሞቱም በኋላ በተለይም ደራሲያን፣ ይሁን፡፡ ግን አሁን ምናለበት ጠያቂ አድርገኝ ባይጠፋ! ሰይጣን! የመጣው እንባዬ አልወረደም፤ ዓይኔ ላይ ደርቆ ቀረ፡፡ ድንገት የቤቱ በር ሲንኳኳ ሰማሁ፡፡

"ማነው? ይግቡ፡፡"

ስንታየሁ ነበር፡፡ ውበት የተላበሰ ጤናማ ወጣት መስሏል፡፡

"የት ነበርክ አንተ!"

"ረጅም ሱባዔ ገብቼ ነበር..."

"መጥፎ ስጋት ላይ ጥለኸኝ ነበር፡፡ ምነው ምን አደረኩህ ጃል? ምን በደልኩህ?"

"አንተም ለሰው ትጨነቃለህ እንዴ?"

"ምን ማለትህ ነው ልቤ ከድንጋይ የተሰራ መሰለህ?"

"ስለሰው ደንታ ያለህ አይመስለኝም ነበር..."

"ይህን ሁሉ ዘመን አብረን ስንኖር ስለኔ ያለህ ግምት ይህ ነበር?ይገርማል፡፡ ለምን ልጄ? ምን እንዲህ አሰኘህ?"

"ግን አሁን ተለውጠሀል" አለኝ ...

"እንዴት እስቲ ንገረኝ" አልኩት፡፡

"አሁን ስሜት አለህ፡፡ በፊት ሁሉንም ነገር ከርቀት የምትመለከተው ትመስለኛ ነበር፡፡ ደንታ አለህ ለካ! ስሜት እንዳለህ አላውቅም ነበር፡፡ ተደራሲ ሁሉ ደንታ ያለው አይመስለኝም ነበር፡፡ ለማንኛውም ነገር አመሰግናለሁ..."

"ስለምኑ ልጄ?"

"የውበት አምላክ ታርቆኛል..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"አዲስ ሥራ ጀመርክ?"

"ስለእሱ ኋላ አጫውትሃለሁ፡፡ ቆንጆ—ውብ አሳብ ነው፡፡አሁን እንሂድና ይህን ምሽት እናክብረው" አለኝ፡፡

ጊዜ አላጠፋሁም፡፡ ስለአዲስ ስራው ለመስማት ቸኩዬ ነበር፡፡ ተያይዘን ወጣን፡፡ እንደወተት የነጣ የጨረቃ ብርሃን ጭለማው ላይ ነግሶ አል፡፡

"ማሩም አይደለች?" አልኩት፡፡

"ማሩም ናት፡፡ ውብ ናት፡፡ ዓለም ከእሷ ጋር ይስቃል፡፡ኮከቦቹን እያቸው፡፡ ሰማዩን ተመልከተው፡፡ እና እኔንም" አለኝ፡፡

ሁሉንም ተመለከትኩ፡፡ እሱንም ጭምር፡፡

"መኖር ደግ ነው፡፡ ቆንጆ ነው" አልኩት፡፡

"መኖርና መጻፍ— አዎን ውብ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ፈሪ አይደለሁም" አለኝ፡፡

ፈገግታ ብቻ ሆኖ ነበር...፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ስብሃት ገብረ-እግዚአብሔር
(1928 — )



ስብሃት ገብረ-እግዚአብሔር ሚያዝያ 27 ቀን 1928 በትግራይ ብሔራዊ መንግስት በአድዋ አውራጃ ርባገረድ በተባለ ስፍራ ተወለደ። በአስር አመቱ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ለአንድ አመት በስዊድን ሚሽን ትምህርት ቤት፤ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን አዳሪ ት/ቤት ተከታትሏል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከትምህርት ፋካልቲ በባችለር ድግሪ ተመርቋል። ለተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት አሜሪካና ፈረንሳይ አገር ተልኮ ፍላጎቱና ትምህርቱ ስላልተጣጣሙለት ትምህርቱን ሳይጨርስ ተመልሷል። ለሁለት አመታት ያህል በአስፋው ወሰን ት/ቤት የእንግሊዝኛ መምህር የነበረው ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር ከፈጠራ ጽሁፍና ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር የተዋወቀው ገና ተማሪ ሳለ ነበር።።በጋዜጠኝነት ሙያው፣ "የመነን"፣ "የቁም ነገር"ና የሌሎች መጽሔት አዘጋጅ ሆኖ አገልግሏል።።በወቅቱ አማርኛ ለፈጠራ ድርሰት ብቃት የለውም ከሚሉት ወገኖች በመሆኑ የፈጠራ ድርሰት የጀመረው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሌሊቱም አይነጋልኝ" የተባለውን ያልታተመ ድርሰቱን አሜሪካን አገር እንዳለ ሰላ ገጾች ያህል በእንግሊዝኛ ከጻፈው በኋላ አማርኛ ለሥነ ጽሁፍ ቋንቋ ብቃት እንዳለው በመረዳቱ ፈረንሳይ አገር እያለ በአማርኛ ቋንቋ ጨርሶታል፡፡

ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር የሚጽፋቸው ድርሰቶች እጅጉን ከአገራችን ባህልና ወግ ጋር የሚጣሉ በመሆናቸው ሥራዎቹ ያልታተሙለት ብዙ ነው፡፡ ከጻፋቸው አራት ረጅም ልቦለዶች መካከል "ሌሊቱም አይነጋልኝ" እና "ትኩሳት" ረቂቃቸው ሲኖር ቀሪዎቹ ሁለቱ የት እንዳሉ አይታወቁም፡፡ ስብሃትም እንደተሳካላቸው ድርሰቶች ስለማይቆጥራቸው በመጥፋታቸው እጅግም አይቆጭም፡፡

ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር በአጫጭር ታሪኮቹና በመጣጥፎቹ ባብዛኛው በአንባቢያን ዘንድ ይታወቃል፡፡

"አምስት ስድስት ሰባት" በሚል ርዕስ የወጣ የታተመ የአጫጭር ታሪኮች መድበል አለው፡፡ ካልታተሙ የአጫጭር ታሪኮቹ መካከል ሁለቱ በዚህ መድበል ይገኛሉ፡፡

ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር ከፈጠራ ድርሰት ደራሲነቱም በተጨማሪ ተዋናይም ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ከምቡጠርና አቶ አላዛር

የደስ ደስ ቀን በሰአት አይለካም – በደስታ ዎች እንጂ፡፡ሙሴ አድሀርያን ሶስተኛዩቱን ዚያ ስተፈስህ ፊያሸኮ ካሰናበቱዋት በኋላ "አየህ ከም ቡጠር፣ ባለፈው ህይወት አዲስዩስ ብልሀተኛው መለኛው ግሪክ የጦር ጀግና አልነበርኩም?" አሉ፡፡

"ነበሩ"

"ለወራት ጦርነት የዘመትኩ፣አገሬ – ቤቴ ለመመለስ ሃያ አመት አልወሰደብኝም፧ አገሬ ስደርስ ያልጠረጠረ ተመነጠረ እንዳይሆን ብዬ ከአደጋ ለመሰወር ስል ጭርጭስ ያለ ድሀ ሽማ ግሌ መስዬ መጣሁ፡፡ ራሴን እስከገለጥኩ ድረስ ማንም አላወቀኝም፡፡ ያ ጡብደል ውሻዬ፤ ቡችላ እያለ ትቼው የወጣሁ ስመለስ አርጅቶ፤ ግማሽ ታውሮ አገኘሁት፡፡በጠረኔ አወቀኝና ዘሎ እጆቼን ትከሻዬ ላይ ጫነብኝ፡፡ እና 'እቺን ቀን ካየሁስ ሌላ ቀን ማየት አልፈልግም' ያለ ይመስል ከትከ ሻዬ ወርዶ እግሬ አጠገብ ተጋደመና እዚያው ሞተ፡፡ ሄደ፡፡"

"እንዲህ ነው ከሞቱ አይቀር!" አለ ከምቡ ጠር፡፡

"አንተ ግን ከሰላሳ ሶስት አመት በኋላ ስመ ለስ እንኳን ዘለህ አቅፈኸኝ ልትሞት ቀርቶ የሰ ላምታ እንኳ አንዴ አልጮህክም፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሟች ውሻ አይደለሁማ፡፡ ተመላላሽ ውሻ ነኝ፡፡"

"ቢሆንም፡፡"

"ይልቅ ጠረን ብትሉ፡፡ እቺን የልደት ኬክ ያመጡልኝ'ኮ እትያልታየ ናቸው፡፡"

"ተው'ንጂ፡፡የተዘባረቀብህ ይመስላል፡፡ እትየ ልታየ እኛው ታያቸዋለህ አይደለም'ንዴ እየፈ ተሉ?"

"እሱ የተረት ሰፈር አድባር ሲሆኑ አድባ ራቱ የምትለብሰው የዘወትር ልብሷ ነው፤ ናቸው ማለቴ፡፡ ዛሬ አድባራቱ የክት ልብሷን ለብሳ እቻ ትሎት፡፡"

"እሷማ ማርያም መግደላዊት ናት እ.የ ልኩህ!?"

"እንዲሁም እትያልታየ ናት፡፡ ጠይቋት፡፡" አቶ አልአዛር አይን አይናን እ.ያዩዋት "በፊት የማውቅሽ ይመስለኛል፡፡ንገሪኝ' ስቲ፡፡እኔ ምንም ሊገባኝ ያልቻለ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለሁት፡፡ ትንሽ ብርሀን ልትፈነጥቂበት ትችያለሽ?"

ሙሴ አድህሪያን "ከምቡጠር" አሉ በህዋር ያዊ ድምፅ "ዛሬ ልደትህ ብቻ ሳይሆን የተመላ ላሽነት ስራህን የምትሰራበት ቀን ጭምር ነው፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ለሰላሳ ሶስት አመት አንተም ኑብስ ህም ከዚህ ክፍል አትወጡም፡፡ አልአዛር ድሮ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከኛ ጋር አብሮ የኖራቸው ግን እሱ የሚረሳቸው ስላለ—ታሪካችንን አጠር አርገህ ንገረን።ማርያም የኔ 'መቤት በገናሽን በለስላሳው እየደረደርሽልን" አሉ።ተነስተው ወጥተው በገናዋን አምጥተው እጅ እየነሱዋት አቀበሏትና ተመልሰው ተቀ መጡ።

ከምቡጠር ቀጠለ። ይሁዳ፣ አልአዛር እና ኢየሱስ የትምህርት ቤት ጓደኞች ነበሩ። ገና ጨቅላ ተማሪዎች እያሉ መምህራቸው ረቢ ሂለል ሶስቱንም ለብቻ ወሰዱዋቸውና እንዲህ አሉዋ ቸው።

አላውቅም'ንጂ ከሶስት አንዳችሁ ሕዝበ እስ ራኤል ለዘመናት ሲጠብቀው የኖረው መሲህ ነው። ማንኛችሁን እንደሆነ አላውቅም'ንጂ ከሶስ ታችሁ አንዳችሁን ነው። ስለዚህ ከሶስታችሁ ማንኛችሁም ቢሆን ሁለታችሁ እስከመጨረሻው እንድታገለግሉት ሶስታችሁም ቃል ኪዳን ግቡ።

ሶስቱ ጓደኞች ቃል ኪዳን ገቡ። አልአዛ ርና ይሁዳ በየበኩላቸው በልባቸው እንዲህ ብለው አሰቡ።"ረቢ ሂለል'ከ ማንኛችን እንደሆነ አውቀ ዋል። ጊዜው ሲደርስ እሱ ራሱ ይንገራቸው ብለው ደምድመው ነው'ንጂ ያልነገሩን"

አመታት አለፉ። ሶስቱ ጓደኞች አደጉ፣ ጐረመሱ፤ የሰላሳ አመት እድሜም አለፋቸው። መጥምቁ ዮሀንስ የበግ ለምድ እንደለበሰ ከም



t.me/OLDBOOKSPDF

ድረ በዳ ወጥቶ መጣና በዮርዳኖስ ወንዝ ኢየሱ ስን አጠመቀው፤ መሰከረለትም፡፡

"ወንድሜ አልአዛር፣ሀገረ ሞት ሂድና ሙሉ የቃፌር ስለላ ፊዕመሀልኝ ትመለሳለህ" አለ ኢየ ሱስ፡፡

"ባልከኝ ጊዜ ለመሄድ ዝግጁ ነኝ"
"መሞት አትፈራም?"
"ምን ያስፈራኛል? ስንቱን ከሞት ስታስነሳ አይቶንህ አይደለ?"

እንግዲህ አልአዛር ሞተ፡፡ ሶስት ቀን ይወስ ድብታል ተብሎ የነበረው ተልእኮ አራት ቀን ወሰደበት፡፡ ለዚያውም ኢየሱስ ጮሆ አልአዛርን ጠርቶ ከሞት መንጭቆ ሲያወጣው፣ ሞት አልለ ቅም ብሎ የአልአዛርን ግራ እግር እስከ ቁርጭ ምጪሚቱ ድረስ እንደጉረሰ ስለነበረ እግር እስከ ቁርጭምጭሚት እዚያው ቀረ፡፡

"እኛ ደህና እንሁን ንጂ አንድ እግር እስከ ቁርጭምጭሚት ምናችን ነው?" አለ አልአዛር "ጠሳችንን እንደወሰደ እዚያው ይቅር!"

"አየህ ከምቡጠር" አሉ ሙሴ አድሀሪያን በሀዋርያነታቸው ከተኮፈሱበት "እኔም ማርያም መግደላዊትም ከኢየሱስ ጋር ኖረናል– የኖርነውን ሁሉ እናስታውሰዋለን፡፡ አልአዛር ግን በእግር ከነቁርጭምጭሚቱ በኩል እየነፈሰበት ከአንድ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው እድሜ ርቆ ወደ ትላንት አይታየውም፤ አይታወሰውም::"

"ለምን አይታወሰውም?"

"ተኖረ'ንጂ አልተመዘገበም::"

"ዘይገርም!"

"በዚህም በዚያም ዘይገርም ነው ይኸው ልህ:: በል አንተ ታሪክህን ቀጥል::"

የአልአዛር ተልእኮ እጅግ ከመሳካቱ የተነሳ የይሁዳ ተጨማሪ ስራ አላስፈለገም ነበር:: ይሁዳ ግን ሰስታችን ጨቅላ ተማሪ ሆነን በገባነው ቃል ኪዳን መሰረት እኔም ወደ ተልእኮዬ እንድሄድና ሀገረ ሞትን ሰልዬልህ እንድመለስ ፍቀድልኝ አለ:: ተፈቀደለት:: ተሰቀለ በገመድ::

ቃፊር ይሁዳ አገረ ሞት የገባው በጓሮ በር ሾልኮ ነበር:: ስንትና ስንት ምስጢራዊ መረጃ ሰብስቦ እንደተመለሰ አልተመዘገበም:: ለምንስ ይመዘገባል?

ጊዜ ማለፉን ቀጠለ–ሲል ቀጠለ ከምቡጠር–ጊዜው ሲደርስ ጌታ ሀዋርያትን ወደየአገሩ ሲልካቸው አብሮ አደጉቹን አልአዛርን እና ይሁዳን እና ማርያም መግደላዊትን እንዲህ አላቸው:: "ወደ ቅድስታገር ሂዱና ወንጌልን ስበኩላቸው:: አስተምራችሁ ካበቃችሁ በኋላም እስከመለስ ድረስ እዚያው ቅድስቷገር ቆዩኝ" አላቸውና፤ ባረካቸውና ላካቸው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ማርያም የምታስተምርበትና የምትኖርበት አምባ መቅደላ ይባል ነበር፤ መግደላዊት የሚ ለው ቃል በሀገርኛ ቃል ነብስ ሲዘራ፡፡

አልአዛር፣ ይሁዳ፣ ማርያም— እነዚህ ሶስቱ ዘወትር ይገናኛሉ፣ከህዝበ ክርስቲያን አይገናኙም እንጂ፡፡

ማርያም በገናዋን ለምእመናን ተወችላቸውና መንገዷን ቀጠለች፡፡ያንን በገና ማንም ሰው ቢደ ረድረው ልክ ማርያም ራሷ እንደምትጫወተው ሰማያዊ ሙዚቃ ይንቆረቆራል፡፡ የሷ ማስታወሻ ስጦታ ነዋ፡፡

እንዲሁም አለ አንድ መሰንቆ፡፡ የመጨረሻ ባለቤቱ ያወርስሀል፡፡ ያንን መሰንቆ ስትጫወት አንተ ሳትሆን መሰንቆው ድንቅ ያገርኛ ዘፈና ችን ይጫወታል፡፡ አንተማ እጅ ብቻ ነህ ድምፁን እንዲያወጣ የሚገለገልብህ፡፡ የዚያ የመሰንቆ ጭራ የማርያም መግደላዊት የፈረስዋ ጭራ ነው፡፡ መሰንቆው ነው' ንጂ ዘፋኙ ማንም ሰው ሊሆን ይችላል፡፡

እንዲሁም አለ የማርያም መግደላዊት መፅሀፈ ፀሎት፡፡

ቀኑ ፋሲካ ነበር፡፡ ህልማለም አልቤርጐ ስምንት ቁጥር ውስጥ አቶ አልአዛር ለውሻቸው ለከምቡጠር በካቲካላ የተዘፈዘፈ ክትፎውን አቅር



t.me/OLDBOOKSPDF

በውለት ለራሳቸው በቅቤ ያበደች፣በአይብ የታጀ በች ዶሮ አስመጥተው ሁለቱም ከተቋደሱ በኋላ፣

"ከምቡጠር፣ ተጫወት" አሉት፡፡

"ሙሴ አድሀርያን ዛሬ ሊመጡ ይችላሉ"

"ኧረ ባክህ!?"

"ላይመጡም ይችላሉ፡፡አንዳንዴ ማንም የሚ ችለውን እሳቸው አይችሉትም፡፡ አንዳንዴ ደሞ ማንም የማይችለውን እሳቸው ይችሉታል፡፡ ባለ ፈው ምድራዊ ህይወታቸው ኦዲስዩስ ,የ ብልህ ግሪክ ጀግና ሆነው ነበር የኖሩት፡፡ ኦዲስዩስ ለአ ጭር ዘመቻ የወጣ፤ ዘመቻው አስር አመት ሙሉ ፈጀበት፡፡ ይሄ ብቻም አይደል፣ ከትሮይ ዘመቻ ሲመለስ የሚወዳት ሚስቱ ናፍቆው እየ ቸኮለ፣ ,የ ህፃን እያለ ትቶት የዘመተው ልጁ አድጐ ምን አክሎ እንደሆነ ለማየት ጓጉቶ እየ ተጣደፈ መርከቡን ተሳፈረ — እንዲህ እየተጣ ደፈ አገሩ ለመድረስ ሌላ አስር አመት ወሰደ በት፡፡

"ሙሴ አድሀርያን ኦዲስዩስ ናቸው?"

"ነበሩ"

"አሁንስ?"

"አሁን'ማ ሙሴ አድሀርያን ናቸው"

"አትዘባርቅ' ንግዲህ!"

"እኔ'ማይደለሁ — ሃቲሃላይቱ እንደሆነች'ንጂ"

"ክትፎይቱስ?"

"እንክት እንጂ! ኧረ ክትፍ ክትፍትፍ!"

አቶ አልአዛር በሳቅ ተንከተከቱ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይኸን ጊዜ በድንገት በሩ ብርግድ ብሎ ተከ ፈተና "ሰላም ለክሙ!" አላቸው በዜማ፤ የሀዋ ር.ያ መጐናፀፊያ ለብሶ የቆመው ሰውዬ።።

አቶ አልአዛር "ዴርዴሪክ!" ብለው እየጮሁ ዘለው አቀፉዋቸው።። ከዚ.ያ ራቅ አርገው እያዩዋ ቸው "በድምፅህ አወቅኩህ'ንጂ መልክህ ግን በጣም ተለውጧል።።እንኳን አርመን ፈረንጅ አት መስልም።።"

"ምን እመስላለሁ?"

"ወይ ዐረብ ወይ ይሁዲ ወይ የሆነ ሴማዊ ነው 'ምትመስለው ከነጊምህ።።አቤት ደሞ ጠጉርህ እንዴት አምሮብሃል! ከትከሻህ አልፎ ወርዶ ብቻ – ምን ልበልህ፤ ዘናጭ ሃዋር.ያ መስለሀል"

"ነኝ 'ንጂ"

"እንዴት ማለት?"

"አላወቅከኝም'ንዴ? እኔኮ አብሮ አደግህ ይሁዳ ነኝ"

"እኔ ይሁዳ የሚባል አብሮ አደግም የለኝ"

"ማን የሚባል አብሮ አደግ ነው ያለህ?"

"ዴርዴሪክ አድሀር.ያን ነዋ!አብሮ አደግ እና አብሮ አደን አልነበርንም? በጉርምስና ሙቀት ሴት ልጅን ለመጐናፀፍ ስንወጣ?ታስታውሳለህ?"

"አስታውሳለሁ።።ሁሌእንደቀደምኩህ ነበር።።"

"የምን መቅደም?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ድንኳናን በውብ ቃላትና ፈገግታዎች አስከፍቼ ገብቼ የውበቷን ሙቀት ስኰናፀፍ- አንተ ገና ውጪ ቆመህ በአምሮት እየተንዘፈ፤ ፍክ ረኸርም ልመና ታዜማለህ፤ ላሊበላ ይመስል"

"ያንተ ፈጥኖ የሚቀናህ'ኮ አስቀያሚዋን ስለ ምትመርጥ ነው"

"በል ተወው፥አልአዛር፡፡የሴት አስቀያሚ የለ ውም—የውበት አይነት ይለያያል'ንጂ፡፡የቀይ ሴት ውበት፥የጠይምሴት ውበት የጥቁር ሴት ውበት፥ የቀጭን ሴት ውበት፥ የወፍራም ሴት ውበት፥ የኰረዳ ውበት፥የአሮጊት ውበት፥እያቀፍከው ያለ ውበት፥እያስታወስከው ያለ ውበት፥ እየናፈቅከው ያለ ውበት—ውበት! ውበት! ለምሳሌ ለናሙና ያህል'ንኳ እስቲ ወደ ሀሳብህ ዳስ ግባና እዚያ ከምታገኛቸው ሴቶች ሁሉ የተዋበችውን ሴት አውጣትና አስተዋውቀን፡፡ እንያት እስቲ ውብ ትን፡፡

ከአቶ አልአዛር ሀሳብ እትያልታየ ወርቃማ ብርሀን ፈገግታቸው እየታየ ወጡና እጨዋታችን ውስጥ ገቡ፡፡እትያልታየ ሲታዩ ወደ አንድ በኩል ተቀምጠው የዳመና ክምር ከሚመስል ጥጥ የእድሜዎቻችንን ክሮች እየፈተሉ ይመስላል - እንደ ወደ ግማሽ ልቃቂት ደርሰዋል፡፡ ሙሴ አድሀርያን በሀዋርያዊ መልካቸው ሶፋው ላይ ተኮፍሰው ውዲቱን ወይኒቱን በያስተፈስህ ፈገ ግታ እየተገኰነጪት ነው—እንደ ወደ ግማሽ ፊያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽኮ ደርሰዋል፡፡ አቶ አልአዛርና ከምቡጠር ለዚህ ጉዞ ቀደም ብለው ስለተነሱ ግማሽ ሞቅታ ደርሰዋል፡፡

"ተጫወት ከምቡጠር" አሉት፡፡

"ሙሴ አድሀርያን ስማቸውን ስናነሳ የመ ጡት ለምን ነበር?"

"እድሚያቸው ረዥም ስለሆነ"

"ሀራምባና ቆቦ አሉ እትያልታየ፡፡እኛ እዚህ ሆነን ስማቸውን ስናነሳ ጊዜ ድንገት ደረሱና እድሚያቸውን አረዘሙት?"

"የሰው ልጅ ሀሳቦች ግንኙነት ነው፡፡ አንተ ውሻ ነህ፡፡ከኛ ጋር ስለኖርክ ሰውኛ የገባህ ይመ ስልሀል'ንጂ ሰውኛ ግን ውስብስብ እንቆቅልሽ መሳይ ነገር ነው፡፡ ለማንም አይገባውም፡፡ ገብቶ ትም አያውቅም፡፡"

ዝም ዝም ሆነ፡፡ ጊዜ እያለፈ ሄደ፡፡ እትያል ታየም ልቃቂታቸውን ለቀቁና መፍተላቸውን በመቀጠል ድጋሚ ግማሽ ልቃቂት ደረሱ፡፡ሙሴ አድሀርያንም ያስተፈስሀን አንድ ፊያሽኮ ተኩል ያህል አድርሰዋታል፡፡

በሩ ተንኳኳ፡፡ "ግቡ!"

በሩ ተከፈተ፡፡ ቀይቱ የውብት እመቤት የለበ ሰችው የሀገር ልብስ ቀይ ጃኖ ጥለቱ አንድ ክንድ ስፋት ያለው ነው፡፡ ሶስት አዳዲስ ሻማ የበቀለበት የሚመስል የልደት ኬክ በሁለት እጆ ችዋ ይዛ ገብታ ከምቡጠር አጠገብ አኖረችውና "መልካም ልደት ከምቡጠር!"አለች እንደ መልኳ



t.me/OLDBOOKSPDF

የደስ ደስ ባለው ድምጿ፡፡ "ከስጋ የተሰራ ኬክ ነው፡፡"

አቶ አልአዛር እንደዚች አይነት ሁለመናዋ ውበት የተሞላበት ሴት አይተው አያውቁም፡፡ በዚያ ላይ እንደ እህታቸው አይነት ነገር ሆና ነው ወደልባቸው የገባችው፡፡ እቺ ሴት ውብ ናት፣ ከውብ አልፋ ውበት ናት፡፡እዝጌርየው እን ዲህ አርጎም ይፈጥራል፡፡

እቺ ውበት ሶስቱን ሻማዎች እየለኮሰች "ሶስት ጊዜ አስር ሻማ እና ሶስት ሻማ ነው ያበ ራሁልህ፡፡ ለሰላሳ ሶስተኛ ልደትህ እንኳን አደረ ሰህ" አለች፡፡

"በብርሃንነታቸው ሰላሳ በሰምነታቸው ሶስት ናቸው" አለ ከምቡጠር፡፡

"ትክክል!" አለች አጠገቡ በርጩማ ላይ እየተቀመጠች፡፡

ሙሴ አድህርያን ከመኮፈሳቸው ተነስተው እየመጡ "መልካም ልደት፣ ከምቡጠር!" ብለው ገፀ በረከት እፊቱ አስቀመጡለት፡፡ እጅግ በጣም የተለየ የመነፅር መያዣ ይመስላል፡፡

ውቢቱ እመቤት "አቤት ማማሩ!" እያለች ገፀ በረከቱን አነሳችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የወርቅና ብር ሀረጎች አላዩ ላይ ተገማምደ ውበት በአልማዝና እንቁ ተንቆጥቁጧል፡፡

ከፈተችው፡፡

መነፅሪቱ ሁለመናዋ እንደ መያዥያዋ በጥቃ ቅን ክቡር ድንጋዮች ተንቆጥቁጧል፡፡ከዚህ ከመ ንቆጥቆጥም የበለጠ ልዩ የሚያደረጋት ታድያ፣ አይኖቿ ከመስተዋት ሳይሆን ከሚያምር እን ጨት የተሰሩ ናቸው፡፡

"ይኸውልህ ከምቡጠር" አሉ ሙሴ አድህር ያን"በዚች መነፅር ችሎታ ውባለም ዘጠኝ ጠጅ ቤት በዘጠኝ ቁጥር ውስጥ ይህን ሰላሳ ሶስት አመት ወደ ውጭ ሳልወጣ እዚያችው ክፍሌ ውስጥ እየዋልኩ እያደርኩ፥ እግዚአብሔር ይመ ስገን—የምበላው የምጠጣው እየተላከልኝ ኖሪያ ለሁ፡፡እኔ መነፅሪቱን የወረስኳት ከማርያም መግ ደላዊት ነው፡፡እሷም በበኩሏ ለምክንያትዋ ከዚያ በፊት በዚች መነፅር ሀይል ለምለም ቂጠማ መኝታ ቤት በአስር ቁጥር ውስጥ ሰላሳ ሶስት አመት ከኖረች በኋላ ጊዜው ሲደርስ መጥታ ለኔ አወረሰችኝ፡፡

"እኔ ደሞ ጊዜው ሲደርስ መጣሁና ይኸው እንካ ውረስ እያልኩህ ነው፡፡ መነፅሩን ታረግና በሀሳብህ የት መሄድ እንደምትፈልግ ትነግረ ዋለህ፡፡ የምትፈልገውን በቅፅበት ያመጣልሀል፡፡ አርጊለትማ ማርያም የኔ መቤት"



t.me/OLDBOOKSPDF

አረገችለት፡፡ በዝምታ ጠበቁት፡፡ "ለቅምሻ ያህል በቂ አይተሀል ወይ? ሌሎቹም እንዲያዩት ብዬ ነው፡፡ አውልቂለትና ለአልአዛር አስሞክ ረው፡፡ይኸውልህ አልአዛር፣በምድራቱ ላይ እንደ ልብ እንመላለሳለንንጂ ይህን መንገድ እንዲ ሄደኸዋልና በድጋሚ መሄድ የለም የሚለን የለም፡፡ የመነፅራቱ ስልጣን በጊዜ ውስጥ እንደ ልብ ትመላለስ ዘንድ ያስችልሀል፡፡ እስቲ ለም ሳሌ የኔን ሰርግ እለት አስባትና ሂድስቲ"

አቶ አልአዛር መነፅሩ ከተደረገላቸው በኋላ እንደተባሉት አሰቡ፡፡ ልክ ያን ጊዜ የነበረው ሰርግ ወለል ብሎ ታያቸው፡፡ በሲኒማ እንደሚያ ዩት ሳይሆን እውስጡ ገብተው እንደሚኖሩት ነው፡፡መነፅሩን አውልቀው ለውቢቱ የልብ እህታ ቸው አቀበሉዋት፡፡ ሁሉም እየተቀባበሉ የከምቡ ጠርን ተእምራዊ መነፅር ከሞከሩዋት በኋላ ውቢት ወደ መያዣዋ መለሰቻትና ዘግታ ከምቡ ጠር የፊት እግር አጠገብ አኖረቻት፡፡ ከዚያ ወደ መጠጣቱ ተመለሱ፡፡

"እሺ ከምቡጠር፣ተጫወት"

"አልበርት አንስታይን በሶስተኛው ሰማይ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ግን አስተማሪነ ታቸው እንደ መነፅራችን ለየት ያለ ሳይሆን አልቀረም፡፡ተማሪዎቻቸውን፣ ድሮ ቀረ፤ አንተ ተጉልተህ ምንም ሳታዋጣ መምህርህ ከየትም አሳድዶ እውቀቱን ባፍባፍህ የሚያጉርስህ፡፡እሱ ፋራ አስተማሪ ነው፡፡አራዳ ይሁዲ የሆነ ፕሮፌ ሰር ግን እንዲህ ይልሀል፡፡ እነሆ የቤት ስራ፡፡ የቤተመፃህፍትና በተለይም የጭንቅላት ስራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው፡፡አንድ ስፋትዋ፣ ቁመትዋ፣ ወርድዋ እኩል አንድ ሴንቲሜትር የሆነ አንዲት አንኳር እጣን እውስጧ ስንት ጭስ ይዛለች? መለኪያው ወይ መቁጠሪያውስ ምንድነው? ሁለት-መቅደስ ውስጥ በቀንዲል የሚበሩት ሰባት ሻማዎችስ እውስጣቸው ስንት ብርሃን ይኖራል? መለኪያውስ ምን ይሆናል?"

"ፕሮፌሰር አይንስታይንን ታውቃቸዋለህ?"

"ለምን አላውቃቸውም?"

እንዲህ ጨዋታቸውን ሲቀጥሉ እንተዋቸዋለን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ኤሊን ድንጋይ ያለበሰክ

የአሮጊት ድምፅ "ተመልከት! አንተ ሰው ተመልከት! ወደኋላ ተመልከት!" አላቸው አቶ ወንዳፍራሽን ዘወር ብለው ቢያዩ::

ግፊያ ጥድፊያ ነው መንግሥተ ሰማያት ለመግባት::የአቶ ወንድአፍራሽን ታላቅ ወንድም ጋሼ መላኩን ሰዎች እየቀደሙዋቸው ያልፋሉ:: ጋሼ መላኩ በንዴት፣

"አቶ ናደው አንጋደደው"ብለው ጮሁበት:: ሳያይ ረግጧቸው ያለፈው አንካሳ ሰማዕት መሳይ ሳይሰማቸው አለፈ:: "ስንቱ ጉድ አለ እናንተ! ኸረ አሳልፉን? ጾመናል፣ ፀልየናል፣ መጽውተናል፣"እያሉ እያጉረመረሙ፤እየተጓሸሙ ትልቁ በር ደረሱ– ጋሼ መላኩ::

መዝገብ አንባቢዎች አትገባም አሉዋቸው::

"ምነዋ?"

"ልጅህ ረግሞሀል"

"ምናባቱን ቆርጦት"

"እንጃባቱን"

"እኮ ቀስ አትሳደብ:: ልጄ ዲዳ ነው:: ምን ብሎ ረገመኝ?"

"መሬት አትቀበልህ፣ ፈጣሪ አይማርህ" ብሎ::

"ዲዳ ነው እያልኳችሁ"

"እናውቃለን ዲዳ ነው:: ደንቆሮም ነው::"

"እኮ እንዴት አባቱን ብሎ ረገመኝ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሱ አዝኖ አለቀሰ፡፡ አዋቂዎች ኃዘን ለቅሶውን ወደ ቋንቋ ተረጐሙት፡፡ መልአክ በመዝገብህ አሰፈረው፡፡"

"ሀሰት"

"ሀሰት? ይህ ደፋር!"

"ያዘው—ግለው" አሉና ይዘው ከገደሉ አፋፍ ወደ ገሃነም ቢወረውሩዋቸው ጋሼ መላኩ "ኡ ኡ ኡ" እያሉ፣ እየጮሁ፣ሲወድቁ ... ሲወድቁ ብንን ብለው ነቁ አቶ ወንዳፍራሽ እኚህ ፍራሽ አዳሽ፡፡

"በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ እከህደከ ሠይጣን" አሉ አቶ ወንዳፍራሽ እያማተቡ በሌሊቱ፤ በውድቅቱ፡፡ እንደ ተጋደሙ ስለዚህ ህልም እያሰቡ ረዥም ጊዜ ቆዩ፡፡ ወንድማቸው ጋሼ መላኩ ከሞቱ ሰባት ዓመት አልፏቸዋል፡፡ ዛሬ መምጣታቸው ምን ይባላል?ደሞስ የምን ዲዳ ልጅ ነው እሱ?

ጋሼ መላኩ አልወለዱ ምን ማለት ይሆን?

እንዲህ እያሰላሰሉ ቀስ በቀስ እንቅልፍ ሸለብ እያደረጋቸው ገና ጨርሶ ሳይወስዳቸው ሌላ ሕልም ድቅን አለ ከፊታቸው፡፡

ጋሼ መላኩ ባህታዊ ሆነው፣ከስተው፣መንም ነው፣ አጥንት ብቻ ቀርተው በዘንጋቸው ወደዋሻቸው በኩል እየጠቆሙ፡- "ና ልንገርህ ወንዳፍራሽ" አሉዋቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ ወንዳፍራሽ ፈርተው "እምቢ" ሲሉ ፈለጉ፡፡ ጋሼ መላኩ እየጐተቱ ወደ ዋሻው አስገቡዋቸው፡፡ ዋሻው ውስጥ እንደገቡ አሁንም የአሮጊት ድምጽ "ስማ አንተ ሰው ስማ ወደኋላ ስማ" አላቸው "ፈጣሪም ሴት ልጁን ሕይወትን ለሞት ዳረለት፡፡ ሞትም ሠይጣንን ሚዜ ሁነኝ አለው፡፡..."

እርጅና ጨምዳዳ አፉን እያጣጣመ ወደ አቶ ወንዳፍራሽ በኩል ሲመጣ አቶ ወንዳፍራሽ ሊሸሹ ዘወር ቢሉ ጋሼ መላኩ የዋሻውን በር በትልቅ ድንጋይ ድፍን ሲያረጉባቸው እርጅና ሊይዛቸው እጁን ሰደድ አድርጐ አፈፍ ሲያረጋቸው ሲል ብንን አሉ አሁንም ከእንቅልፋቸው፡፡

"በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ እክህደከ ሰይጣን" አቶ ወንዳፍራሽ ሌላ ሕልም እንዳያዩ ፈሩ፡፡ተነስተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ፡፡ ከቅዳሴ በኋላ ወደቤታቸው ሲያዘግሙ ድንገት ድንግጥ አሉ ስለሰሙት ያንን ያሮጊት ድምጽ፡፡ በሕልማቸው 'አንተ ሰው ተመልከት! አንተ ሰው ስማ' ያላቸውን ድምፅ አሁን በውናቸው ስለሰሙት ደነገጡ፡፡ የጀመሩትን እርምጃ ሳይጨርሱ መሀል ቤት ድርቅ ብለውቀሩ፡፡

ያ ያሮጊት ድምጽ በዝግታ በቀስታ እንዲህ ይላል፣ "ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ፣ እውር አሞራን የምትመግብ አምላክ፣ ዮናስን በዓሣ ሆድ ያኖርክ፣ የጠበቅክ አምላክ፣ እኔንስ አለሁ አትለኝም ወይ? ምሳዬን አትጥልልኝም ወይ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

አቶ ወንዳፍራሽ በፍርሃት እየተርበተበቱ ወደ ድምጹ በኩል ዘወር አሉ፡፡ከስልክ እንጨት ሥር አንዲት አሮጊት ቁጭ ብለው ይለምናሉ፡፡ እውር ናቸው፡፡ የአላፊ አግዳሚውን ኮቴ ሲሰሙ "ስለማርያም ስለመብረሃን"ይላሉ ጮክ ብለው፡፡ አቶ ወንዳፍራሽ ቀስ ብለው ከመንገድ ወጥተው አሮጊቷ አጠገብ ቆሙ፡፡ አላፊ ሳይኖር አሮጊቷ እንደገና ፈጣሪን በዝግታ ሲያነጋግሩት ይቆዩና ሰው ሲያልፍ ሲሰሙ ጮክ ብለው "ስለመብረሃን ጣድቃኖቹ ማርያም አለሁ ትበላችሁ፤ እምዮቹ ስለአዛኘቱ" ይላሉ፡፡ሰው በማያልፍበት ጊዜ ደሞ ፈጣሪን እንዲህ ይሉታል፡፡ "ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ፣እውር አሞራን መጋቢ፣ጫጩትን በእን ቁላል ውስጥ ያሰፈርክ፣ እኔንስ ረሳኸኝ ወይ? ስጠራህ አለሁ አትለኝም ወይ?አቤት ባይ፣ስጠኝ ባይ በዛብህ ወይ?"

"ስለማርያም! ማርያም ትለመናችሁ ጣድቃ ኖቹ! "፣ ሲሉ አቶ ወንዳፍራሽ ኪሣቸው ገቡና መጀመሪያ እጃቸው የያዛትን ፍራንክ አወጡ— ስሙኒ፡፡

"እንኩ እማማ"

ድንግጥ አሉ አሮጊቷ፡፡ የተዘከራቸው ሰው አብሯቸው የቆየ መሆኑ ተሰማቸው፡፡ እጃቸው ስሙኒውን አወቀው፡፡ ዝም ብለው ቆዩ ቆዩና፥

"ማን ነህ?" አሉ በለስላሣ ድምፃቸው፡፡ዝም አሉ አቶ ወንዳፍራሽ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማን ነህ 'እንኩ እማማ' ብለህ ስሙኒ የሰጠ ኸኝ?"

"እኔ ነኝ፤ እዚህ ቆሜ ስሰማዎት ነበር።"
"ሰማኸኝ? ... እህ" አሉ ለብቻቸው እንደሚ ያሰላስሉ ዓይነት።

"እንዴት ነው እዚህ የደረሱት?" አሉ አቶ ወንዳፍራሽ አሮጊቷ አጠገብ ድንጋይ ላይ እየተ ቀመጡ። የጧት ፀሐይ ደስ ይላል።

"አዬ ልጄ! የኔማ ታሪክ እንደተረት ነው።"
"ይንገሩኝ እስቲ።"
"ይኸውልህ ሰባት ወለድኩና ሰባቱም ሞቱ። ስምንተኛ እንደወለድኩ አዋቂ ቤት ሄድኩ። አዲስ አበባ እሚሉት ሀገር ሂጂ እዚያ ሞት የለም አሉኝ።አንድ ቀን ሳልውል፣ስንቁን ጨር ቁን ሳልል ተነሣሁና ወደ አዲሳባ መንገዴን አቀናሁ።ሞት እንዳይደርስብኝ፣ልጄን እንዳይወ ስድብኝ ስሄድ ሰንብቼ ስሄድ ከርሜ፣ ምግቤንም መጠጊያዬንም እየለመንኩ ስሄድ ከርሜ ሰኔ ሚካኤል ካገሬ የወጣሁ ለህዳር ተክለሃይማኖት አዲሳባ ገባሁ።

"እንዳሉትም አዲሳባ ሞት የሌለበት አገር ሆነና ልጄ አደገልኝ። እንጨት ከጫካ እየለቀ ምኩ፣ጠላም ከገብስ እየጠመቅኩ፣እንጀራም በየ ልት እየሸጥኩ አሳደግሁት። ሰው ሆነ። ለሰው ወግ ደረሰ፤ ሚስት አገባ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከዚያስ"

"ዋ ልጄ!ከዚያማ ሚስት ሳትፈልገኝ ቀረች:: ከንግዲህ ምን ልረባ ለራሴ አሮጊት? ቤት ከማጣ በብ፣ እንጀራ ከመፍጀት አልፌ ምን ልጠቅ ማት? አልፈጭላት፣አልጋግርላት:: አንድ ወለደ ችና ባል ልጁን መውደዱን እርግጠኛ ከሆነች በኋላ እቺን አሮጊት ካላስወጣህልኝ ፍታኝ አለ ችው::"

"እና አስወጣዎት?"

"እኔ ወጣሁለት እንጂ ለምን ላስኰንነው? የልጅ ፍቅር አይደል አገሬን፣ ጐረቤቴን ጥዬ እንድኮበልል ያደረገኝ! እሱንም የልጅ ፍቅር እና ቱን እንዲያባርር ያረገዋል አልኩና የገዛ እናቱ ኃጢአት ኩነኔ ከምሆን ብዬወጥቼ ጠፋሁበት::"

ልጃቸውን ሞት እንዳይበላው ካገራቸው ከወ ንዛቸው ኮበለሉ፣ ገሃነም እንዳይበላው ደሞ ከል ጃቸው ከራሱ ኮበለሉ፤"እውነትም የናት ፍቅር" ብለው አሰቡ አቶ ወንዳፍራሽ:: "ታዲያ ፈጣ ሪዬ ጥሎ አልጣለኝም" አሉ አሮጊትዋ "እሷ መሰላት እንጂ እኔስ ይኸው የሱን ጸሐይ እሞቃ ለሁ፤ይኸው ከሰው ጋርም እጫወታለሁ::"

ዝም ብለው ጥቂት ጊዜ አለፈ:: አቶ ወንዳ ፍራሽ በዝግታ ድምጽ "ኤሊን ድንጋይ ያለበስክ አሉ ከዚያ ምን ነበር?"

"እውር አሞራን መጋቢ፣እንኮይን በገደልየተ ከልክ፣ደመናን እንደ ጥጥ ሰብሳቢ ረሳኸኝ ወይ? እለዋለሁ::አቤቱታ በዛበት፤የሚጠራው፣የሚለም ነው በዛ::ምን ያርግ ብለህ ነው?ስንቱን ይስማ?



t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ይቆይ ይቆይና አለሁ ይለኛል፡፡እየዞሽ ይለ ኛል፤ ረስቶ አይረሳኝም፡፡

"እንደዚህ እንደ አሁኑ ይሰጠኛል፡፡ ባንተ እጅ ሆነ እንጂ ሰጪው እሱ ራሱ ነው፡፡ ማደሪ ያም ሰጥቶኛል፤አንድ አረብ አለ እርጅናዬንና የሰው አገር ሰው መሆኔን አይቶ መጠጊያ ሰጥቶ ኛል፡፡ የሠፈሩ ሴቶች ደሞ ቡና ያጠጡኛል፤ የሚቀመስ ይሰጡኛል፡፡ እሱው ይመስገን የጐደ ለኝ የለም፡፡ መሪ እንኳ ሳይቀር ሰጥቶኛል፡፡ እዚህ ሰፈር ተረኛ የሆኑ ሁለት ፖሊሶች አሉ፡፡ ጧት ወደዚህ ወደ ልመናዬ ቦታ መርተው ያመ ጡኛል፡፡ ሲመሽ ወደ ማደሪያዬ መርተው ይወሰ ዱኛል፡፡ እሱ አልተወኝም፡፡ይኸውልህ እንዲያው አንዳንዴ ብቸኝነት ሲሰማኝ አነጋግረዋለሁ እንጂ በደንብ ይጠረኛል፡፡ ምስጋና ይግባው፡፡ ዛሬ ደሞ ከሰው ጋር መጫወት እንዳማረኝ አይቶ ይኸው አንተን ላከልኝ፡፡ እንደዚህ ነው የሱ ነገር፡፡"

አቶ ወንዳፍራሽ ካሮጊትዋ ጋር ሲጫወቱ አርፍደው ወደቤታቸው ሲያዘግሙ አንድ መልስ የሌለው ጥያቄ እየተመላለሰ መጣባቸው፡፡ አሮጊ ትዋን ዛሬ ጧት ሊያገኙ የአሮጊትዋን ድምጽ በትላንት ማታ ሕልም መስማታቸው ምን ማለት ይሆን?



t.me/OLDBOOKSPDF

# ባሴ ሀብቴ

(1942 —— 1988)



ባሴ ሀብቴ በአማራ ብሔራዊ መንግስት ጎጃም ውስጥ በ1942 ተወለደ፡፡ ከዚህ አለም በሞት እስኪተለየበት እስከ 1988 ድረስ በመጀመሪያ በመምህርነት ቀጥሎ በማዕድን ሚኒስቴር በቀያሽነት አገልግሏል፡፡

ባሴ ሀብቴ"ውሸንፍር"፣"ቃል"ና"ጠብታ ማር" (ከደምሴ ፅጌ ጋር) ልቦለዶችን፤ "ሲራም ደቨርገፎራክና" እና "ሮሚዮና ዡልየት" የተሰኙ ተውኔቶችን ተርጉሟል፡፡ ባሴ ሀብቴ ወጥ የሆኑ አጫጭር ልቦለዶችንም ይጽፍ ነበር፡፡ከዚህ አለም በሞት ከተለየ በኋላ "ደራ ጎን"፣"ድንገት"፣"ሀበሻ" የተሰኙት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትመዋል፡፡ ከአጫጭር ልቦለዶቹ መካከል "እነሱ እና ጭጋግና ጠል" የተሰኙት በዚህ መድበል ውስጥ ይገኛሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# እ ነ ሱ

ያልሆኑት ነገር እንዴት ይጥማል! አሁን እነ ዚህ ሁለት ልጆች እንዲህ ሲሆኑ እንዲህ መሆኑ እነሱን ያልሆነን ሰው የሚጥመውን ያህል ይጥማ ቸው ይሆን? ልጅቱ ጠይም ናት፡፡ብሩህ ጠይም ናት፡፡እውስጧ አምፖል ነገር አለ መሰል፡፡ ወደ ውጭ የምትረጨው ጨረር እንዲህ አይደለም፡፡ ልጁም ለግላጋ ነው፡፡ጥሩ ምግብ እየበላ ባያድግ ኖሮ ጥቁር ነበር እሚሆን፡፡ ግን ጥቁር አይደ ለም፡፡ ደስ ይላል፡፡ አነጋገራቸው ውብ ነው፡፡ ድምፃቸው እንዴት ነው እሚለሰልሰው፡፡ኬክ እየ በሉ፤ ቡና በወተት እየጠጡ፤ ፍቅር እየተጫ ወቱ፤ ደስታን እንደጠበል ሲረጩ የረከሰ ሁሉ ይቀደሳል፤ ደስታ ናቸው፡፡

እንዲያ እያወሩ ደስታ ሲረጩ ቆይተው ለጥቂት ጊዜ በዝምታ አውርተው– ተያይተው፤ ተያይተው፤ እየተያዩ ተነጋገሩና ተግባቡና ሂሳባ ቸውን ከፍለው ወጡ፡፡እነሆ ደስታ አካል ሠርቶ ገዝፎ ሲወጣ ታዬ፡፡ ብሩህ ፊቷ ከተቀመጡበት ወንበር ላይ ቀረ፡፡ እነሱ ግን ወጡ፡፡

* * *

ሰው ይወጣል ይገባል፡፡ ድምር ሰው ነው፡፡ ኬኒ ሮጀርስ ይዘፍናል፡፡

Promis me son
not to do the things I done
walk away from trouble
if you can...



t.me/OLDBOOKSPDF

የቡና መኪናው ይንፈቀፈቃል፡፡ ቴፕ ሪከርደሩ ይዘፍናል፡፡

It doesn't mean to be weak

To turn the other cheek

የፊቷ ብርሃን እየጨለመ ሄደ፡፡ዓይኖቿ ጉልተው ይታያሉ፡፡ ሰው ይወጣል ይገባል፡፡ ወንበራቸው ባዶ ሆነ፡፡እሷም ጥላው የወጣችው የፊት ዱካም ሄዱ፤ ቀስ እያሉ ጠፉ፡፡ የቡና መኪናው ይተነፍ ሳል—የፏጫል-ይንፈቀፈቃል፡፡ኬኒ ሮጀርስ ይዘፍ ናል፡፡

There is someone for every one

S'tomy ....

*　　*　　*

"ይህኛውን ኬክ ቅመሺውስኪ ይጣፍጣል፡፡ ... አላት" እነዚህ ሁለቱ ደሞ መቼ መጡ!? እነ ዚያ የቅድሞቹ እነበሩበት ቦታ ላይ ነው የተቀ መጡ፡፡ ሰው ይወጣል ይገባል፡፡ ያሳያትን ኬክ አነሳችና ቀመሰችው፡፡ ፊቷን ኮምጠጥ አድርጋ ምጣ-ምጣ እያለች አጣጣመችው፡፡በመጠኑ ፊቷ መለስ አለ፡፡ በመጠኑ ፈካ አለ፡፡ጣፈጣት፡፡ ግን አላረካትም ጣዕሙ፡፡

"አዎ ጥሩ ነው" አለች፡፡ ግን በፊቷ አላደነ ቀችውም፤ ጣዕሙን፡፡

"አዎ ደህና ነው፡፡ ... ግን እንደድሮው አይ ሆንም" አለች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይጣፍጥም?" አላት፡፡ይጣፍጣል ብትለው ደስ ይለዋል፡፡ ፊቱ ያንን ነገራት፡፡

"ይጣፍጣል፡፡ ግን እንደዱሮው አይደለም" አለችው፡፡ ቅር አለው፡፡እሷ እንዲያ ብትልም እሱ ግን ጣፍጦታል፡፡

"እንደዱሮው ተጨንቀው፤ተጠንቅቀው አይ ሰሩትም" አለች፡፡ ቅር አለው፡፡ የሷን ዱሮ አያ ውቀውም፡፡ ሊያየው አልሞከረም፡፡ ዝም ብሎ ኬኩን ይበላል፡፡

ቴፕ ሪኮርደሩ ይዘፍናል፡፡ድምር ድምፅ ይሰ ማል፡፡ ሳቅ፣ ሹክሹክታ፣ ድሪያ፣ የቴፕ ዘፈን፣ የቡና መኪና... ከውጭ የመኪና ድምፅ፡፡

የውቢቷ ልጅ ብሩህ ፊት እነበረበት ቦታ ላይ ነው የተቀመጡ፡፡ ልጁ ቆንጆየ ነው፡፡ እሷ ቀይ ናት፡፡ የእሱን ዱሮ እንጅ የእሷን ዱሮ አያውቀውም፡፡ ዓይኖቿ ሞጭሙጨዋል፡፡

"ይሽኛውን ኬክ ቅመሰው፡፡ ሳይሻል አይቀ ርም ክሬሙ ነው መሰለኝ" አለችው፡፡ዓይኗ ሰው ያፍራል፡፡ ፍርሃትስ ያለባት አይመስልም፡፡

የጀመረውን ጨረሰና ባለክሬሙን መብላት ጀመረ፡፡ እሷ ሻይዋን አንስታ መጠጣት ጀመ ረች፡፡ታየዋለች፡፡አይታ አትጠግበውም፡፡ክብ ፊቱ እንዴት ደስ ይላል፡፡ኑሮ ምንም ዓይነት መስ መር አልተለመችበትም-በፊቱ ላይ፡፡ ችግር አልገ



t.me/OLDBOOKSPDF

ረፈውም፡፡ አልተሰቃየም፡፡ገና ነው፡፡ለዚያ አልበ ቃም፡፡ልጅ ነው፡፡ ታየዋለች፡፡ አይታ አትጠግበ ውም፡፡ መንፈሷ ሁሉ ተረብሿል፡፡

"ይኸ ነጩ ምንድነው?" አላት ክሬሙን እያሳያት፡፡

"ክሬም"አለችው ያሳያትን እንደዘበት አየት እያደረገች፡፡ ዓይኗ ሰው እሚያፍረው ለምንድ ነው? ... ፍርሃትስ የለባትም፡፡

"ይጣፍጣል" አለ ክሬሙን እንደብርቅ ነገር እያዬ፡፡

"እንደዱሮው አይደለም" አለችና ዱሮን ለማ የት ምትሞክር መሰለች፡፡ "በዚያ ላይ ደግሞ አንዱን ሠላሣ ሳንቲም ይላሉ፡፡"

መንፈሷ ሁሉ ተረብሿል፡፡ ነፍሷ ተከዛለች፡፡ እሱ ክብ ፊቱ እንደቅድሟ ልጅ ብርሃን ይረ ጫል፡፡ግን እሱ ቀይ ነው፡፡ ጠይም አይደለም፡፡ ይችኛዋ ኑሮን ኖራዋለች፡፡ኑሮ ገርፏታል፡፡ ውሉ የጠፋ ልቃቂት ይመስላል ኑሮዋ፡፡

ፊቷ ይናገራል፡፡ ሙሉ መጽሐፍ ነው፡፡ የወ ጡት ልጆችና አብሯት ያለው ልጅ ያላዩት ብዙ ጉድ አይቷል ፊቷ፡፡ እና ያየውን ሁሉ መዝግቦ ተጣጥፏል፡፡

"ክሬሙ እንኳ አይጣፍጥም"እያጥላላች ተና ገረች፡፡ ዝም አለ፡፡ ግን ከፋው፡፡ እሱን ኬኩ ጣፍጦታል፡፡ ኬኩን አንስታ እየተፀየፈች በፊት ጥርሷ ጫፉን ገመጥ አደረገችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ውድ ነው?" አለ። ስለዋጋ ብዙ ነገር አያውቅም።

"በጣም እንጂ። ያውም ለዚህ!"

እየናቀች አሳየችው። ቅር አለው። ግጥጥሞ የለም እንግዲህ!

"ለኔ ግን ጣፍጦኛል።"

"ከጣፈጠህ ደግ።"

በዝግታ ነው እሚነጋገሩ። የሷ ድምፅ ትንሽ ሻከር ያለ ነው። ከሻይው ፉት አለችለት። እሱ በወተት እየማገ ኬኩን ገመጠው። ታየዋለች። አይታ አትጠግበውም።ቅላቱ ድንቅ ነው። ከውስጡ የሚወጣው ብርሃን ሳታስበው ፈገግ ያረግ ሀል።አይኖቹ ጥቁር ቡናማ ናቸው።የጠራ ጥቁር ቡናማ አይን ያለው ሰው ደስ ይላል።እሷም ቀይ ናት።ያ ሁሉ ሰንበር እስኪወጣባት ችግር ገርፏት እንኳ የቅላት ውበቷ ያስታውቃል።ግን የውሰጧ መብራት ተቃጥሏል።እሳቷን ኑሮ አክስሎታል። እፊቷ ላይ ብርሃን የለም።ቀና ብሎ አያት። የሱን ብርሃን ሲቀበል ፊቷ ትንሽ ፈካ አለ።አይኖቿ ግራጫ ናቸው፤የግሪክ ክልስ ናት መሰል። ሰበር እያት ነው እንጂ ፊት ለፊት ማየት አትችልም።የሚያሽቆጠቁጥ ሰው ለብዙ ጊዜ አስጨን ቋታል። ያን ያህል ችግር ገርፏትም ቅላቷ ያባብላል።

ቋ...ቀሽ

ገ ገ...ግርግጭ ገ

ገርገ...ቀጭ

ሽሽሽ...



t.me/OLDBOOKSPDF

የቡና መኪናው ያፋጫል፣ ይንፈቀፈቃል፡፡ ቴፕ ሪኮርደሩ ይዘፍናል፡፡ ልቧ ወደ ቴፕሪኮርደሩ ሄደ፡፡

እሱ ኬኩን ይበላል፡፡ ከወተቱ ፉት እያለ፡፡ ኬኩ ጣፍጦታል፡፡ዘፈኑን እየሰማች ስለሆነ የሚበላውን ነገር ለመንቀፍ ጊዜ የላትም፡፡ ቅድም የነቀፈችውንም ረስቶታል፡፡ደስ ብሎታል፡፡ዘፈኑን አይሰማም፡፡ የሚበላውን ነገር ያጣጥማል፡፡ ኬኩን ያየዋል፤ እያየ ይበላዋል፡፡

*"ካላማሸው አካል፤...በልቤ ላይ..."*

"ባህታ!" አለች፡፡

ዝም ብሎ ይበላል በወተት እየማገ፡፡ ሰምቷታል፡፡

"ቆንጆ ዘፈን ነበር" አለች፡፡

ዝም አላት፡፡

"ይኸን ዘፈን ለረጅም ጊዜ ነበር ምንሰማው፡፡"

ዝም ብሎ ይበላል፡፡

"የዚህ ዘፈን ትዝታ የበላይነህ ትዝታ ነው፡፡"

ዝም አለ፡፡ቤቱ ይንሾካሾካል፤ያወካል፡፡ የመኪናው ክላስክ ከውጭ ከሞተሩ ድምፅ ጋር እየተደባለቀ ይገባና እቤቱ ውስጥ ያለውን ሹክሹክታና ሁካታ ይውጥና ያልፋል፡፡

*"ታሰኘኝ ጀመረ ደሞ – ደሞ ... "*



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጁ ወለላ ነው፡፡ ሲበላ ደስ ይላል፡፡ እሷ ቀይ ናት፡፡ ትዝታ ውስጥ ገብታለች፡፡ ራቁቷን ገባች፡፡ትዝታ ውስጥ ገብታ ስታዝን እንዴት ደስ ትላለች፡፡የተጨማደደ ቆዳዋ በጥቂቱ ይለጠጣል፡፡ ታምርና ታሳዝናለች፡፡ውብ አሳዛኝ ፊቷን ማየት ያባባል፡፡

እንዳ ደመቅ ያለ ሁካታ ይሰማል፡፡ልጁ እግ ድግዳው ላይ የተለጠፈውን ሥዕል ያያል፡፡ ዋል ያው እተራራው ጫፍ ላይ ቆሞ ልጁን በጽሞና ያየዋል፡፡ወይም ፎቶ ግራፍ ለመነሳት ተጠንቅቆ የቆመ ይመስላል፡፡ የጢስ አባይ ፏፏቴ የተሰጣ ጨርቅ መስሏል፡፡ቀኑ ፀጥ ያለ ነው፡፡ ስለዚህም የተሰጣውን ጨርቅ ነፋስ አያውለበልበውም፡፡ ቴፑ ይዘፍናል፡፡ ዘፈኑም ትዝታ ነው፡፡ ድምፅ አመጣጡንም ለስላሣ ነው፤ የትዝታ እንቅልፍ ያስወስዳል፡፡

ለስላሣ የትዝታ ሀዘን!

እንዲያም ለስላሣ የትዝታ ሀዘን እያዘነች፤ ፊቷ መስመር ለብሷል፡፡እንዲያም ሰንበር ለብሳ ቅላቷ አልደበዘዘም፡፡ ውብ ናት፡፡ በትዝታ የተ ከዘ ውብ ፊቷ ያሳዝናል፡፡

"ይሄ ቤት ሀ ብሎ ሲከፈት አውቀዋለሁ፡፡ እንዲህ እንደዛሬው ማንም አይገባበትም ነበር፡፡ ግን የሁለት ወር ደሞዙን እንደተቀበለ ይዞኝ መጣና ተጫወትን፤ እወደው ነበር!"



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝም አላት፡፡ እጣቶቹ ላይ የቀረውን ክሬም ላስ ላስ አደረገ፡፡ ወንበሮቹን አያቸው፡፡ረጃጅም መከዳ ባይኖራቸው የጠጅ ቤት አግዳሚ ወንበር ነበር እሚሆኑ፡፡ ግን እንደዚያ ዓይነት ወንበር አይቶ አያውቅም፡፡

ቴፕ ሪኮርደሩ ይዘፍናል፡፡

"ካላጣሽው አካል ..."

አየችውና ፍዝዝ አለች፡፡

ልጁ ቆንጆ ነው፡፡ ፀጉረ ሉጫ ነው፡፡ ቡናማ ሉጫ ፀጉር ደስ ይላል፡፡ አበባ ነው፡፡ ያደረገው ሸራ ጫማ ቆሽሿል፡፡ አንድ ትልቅ ሳቅ አንዴ በቤቱ ውስጥ ተወናጨፈ፡፡የሴት ልጅ ሳቅ ነው፡፡

"ያኔ ሴት ልጅ ከወንድ ጋር ደፍራ ካፍቴ ሪያ አትገባም ነበር፡፡ ከገባችም በጣም ትፈራ ነበር፡፡ አቤት እንዴት ነበር የፈራሁት ያንለት እዚህ ቤት ይዞኝ ሲገባ!"

ለሱ አልነበረም እምትናገረው፡፡ እሱ አንድ ነገር ሊነግራት ፈልጓል፡፡

"ሕልም አየሁ" አለ፡፡

ዝም ብላ አየችው፡፡እንዲቀጥል በዐይኗ ጋበዘ ችው፡፡

"ዛሬ በሕልሜ አንድ ሰው ሆዱን ታሞ ሲሰ ቃይ አየሁ፡፡"

"ማነበርሱ?"

"አላውቀውም"



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘፈኑ አለቀ፡፡ቴፕ ሪኮርደሩ ቃቃ ደሸ! አለ፡፡
"እና?"
"ምኑ?"
"ህልምህን?"

"ስነቃ ሆዴን በጣም አመመኝ"
ቴፕ ሪኮርደሩ መዝፈን ቀጠለ፡፡ስሜቷ ወደዘፈኑ ሄደ፡፡

"ጀመረ ደሞ ደሞ እንደምናለሽ!"

ሰፌ መነፅር ያደረገች ልጅ ሙሉ ሳቅ እየሳቀች አለፈች፡፡የለበሰችው ቢጫ ባጊ ንፁሕ ነው፡፡ አብሯት የገባው ወንድ ልጅ ግማሽ ሣቅ ይስቃል፡፡ ወንዱ ልጅ ሰፌ መነፅር አድርጋ ሙሉ ሳቅ እየሳቀች ንፁሕ ቢጫ ባጊ የለበሰችውን ልጅ ክንዷን ይዞ ግማሽ ሳቅ እየሳቀ ... እንደ ሰደርያ ሁሉ ክናድ የሌለው ጃኬት ለብሷል፡፡ "ጃፖኒ ይባላል" ብላ ነበር ሸዊት፡፡ ንፁህ አረንጓዴ ባጊ ሱሪና ንፁሕ ቢጫ ሸሚዝ ለብሷል፡፡ እሷ ሙሉ ሳቅ እምትስቀው የወይንጠጅ ሊፕስቲክ በተቀባ ከንፈሯ ነው፡፡ ሹራቧ ቀይ ነው፡፡

ልጁ አዝኗል፡፡ ጓጉቷል፡፡ ለመብላት አይደለም፡፡
"አባባ ያንተ አባት አይደሉም አለችኝ፡፡"
"ማ!"
"ማርታ፡፡"
በርጎራሄ አየችው፡፡ በንዴት አየችው፡፡ በሀዘኔታ አየችው፡፡ የቡና መኪናው ይጮሃል፡፡ ቴፕ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሪከርደሩ ይዘፍናል፡፡እንዳዳ ሁካታ ይሰማል፡፡ ልጁ አዝኗል፡፡ተጨንቋል፡፡ሲጨነቅም ቆንጆ ነው፡፡ግን እንዲያ ቆንጆ ሆኖም ያሳዝናል፡፡

መንፈሷ ለሁለት ተከፍሏል፡፡ እሷም ጨንቋታል፡፡
"ኬክህን አልጨረሰክም?"
"አዎ!"

ኬኩን እየቆጠበ ይበላል፡፡ እየሳሳ ክሬሙን ከኬኩ ላይ ይልሳል፡፡

*"እይዋት ስትናፍቀኝ..."*

እንደገና ወደ ትዝታዋ ተመለሰች፡፡ ልጁ ኬኩን እየቆጠበ ይበላል፡፡

እሷ ተከዛለች፡፡ፊቷ የችግር መጽሐፍ ነው፡፡
*"በዐይን እየተያዩ..."*

በኃይል ተነፈሰች፡፡ ቀና ብሎ አያት፡፡ፊቷን አለሰለሰችው፡፡ እንዲያ ችግር ሁሉ የቀረጸው፤ ወይም ችግር እንዲያ አድርጎ የቀረጸው ፊቷ ቀይ ነው፡፡ ውብ ቅላቷ አልደበዘዘም፡፡

*"... የመናፈቅ ጣጣ"*
ቴፕሪከርደሩ ይዘፍናል፡፡
*"በኔ ላይ ነው እንጂ ..."*
እንደገና በኃይል ተነፈሰች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይቶ አይጠግበኝም ነበር።" ሩቋን እያየች፤ እወዲያ ከዚች ቅጽበት ወዲያ– ወዲያ በጊዜ ዓለም ተጓዘች።

"ይኸን ዘፈን ሲሰማ ያቅፈኝና፤ አቅፍ ያረገኝና ከጥላሁን ጋር አብሮ ይዘፍን ነበር።"

"ማነው እሱ?"

ደንገጥ አለች። ዝም አለች። አየችው። የፊቱ ብርሃን ነዐብራቅ ፊቷን አበራው። ትወደዋለች። አይታ አትጠግበውም። ልጁ ቆንጆ ነው።

"ለዘውትር እየየሁሽ..."

ልጁና ትዝታዋ ... ወደ ዘፈኑ፤

ልጁና ዘፈኑ... ወደትዝታዋ... ተመለሰች መለሷት።

"ጓደኞቹ ያሙት ነበር።...ሪቮሉሽነር ሮማንቲክ መሆን የለበትም ይሉ ነበር። ሰው ይንገረኝ እኔ ልስማቸው ትዝ አይለኝም... ያሙት ነበር። እሱም የሚያቅፈኝ፤ የሚዘፍንልኝ በፊታቸው ነበር።

"ግን አንዳቸውም እምትሠራው ትክክል አይደለም ብሎ እፊቱ አይነግሩትም ነበር። ይፈሩት ነበር፤ ያከብሩት ነበር ... ደቃቃ ነበር። ግን ደሞ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያከብሩት ነበር፤ ይፈሩት ነበር።።አሥራ ሁለተኛን ክፍል አልፌ ኮሌጅ ስገባ..."

"ማነው እሱ?" ግራ እየተጋባ ጠየቃት።። ግራ ገብቶታል።።ሲያያት ደነገጠ።።ድንጉጥ ነው።። ደነገጠች።። ትፈራዋለች።። ትሸሸዋለች።። በሀዘኔታ አየችው።።በፍቅር በርኅራኄ አየችው።።አይቷት አት ጠግበውም።።ትወደዋለች።።ትናፍቀዋለች።።አብረው እያሉም ናፍቋታል።።

"ኬኩን ጨረስክ?"

ቡና በወተቱን አልጨረሰውም።። ፉት አለና ከንፈሩን ላሰ።። ከንፈሩ እንዴት ደስ ይላል።።

"እዩአት ስትናፍቀኝ..."

የትኩስ ኬክ ሽታ ቤቱን አወደው።።እሷ ዘፈኑን ትሰማለች።። ልጁ እኮርኒሱ ላይ የተሳለውን ስዕል እንጋጦ ይመለከታል።። እስዕሉ ላይ ያሉ ሰዎች እግር የላቸውም።።

"መጽሐፍ ማንበብ አስለመደኝ" አለች።።
"መጽሐፍ ማንበብ እወዳለሁ" አለ።።

"ትወዳለህ?...ጥሩ ነው።።እሱም መጽሐፍ ማን በብ ይወድ ነበር።። አንዳንዴ ሳያናግረኝ...ሳላናግ ረው ለብዙ ሰዓት እናነብ ነበር።። ... መጽሐፍ ማንበብ ጥሩ ነው።።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማርታ ደሞ መጽሐፍ ማንበብ መጥፎ ነው አለችኝ::"

"አለችህ?"

"አዎ! እሷም የታሰረችው ይኸን መጽሐፍ አንብባ አንብባ ነው አለችኝ"

ዝም አለች::ግን ከፋት::

"ይኸን መጽሐፍ ማንበብህን ካልተውክ ወይ ታብዳለህ ወይ ትታመማለህ ወይ ትታሰራለህ:: አለችኝ ..."

"አለችህ?!"

"አዎ!...አባቴ እብድ ነው?"

"ይኸንንም የነገረችህ ማርታ ነች?"

"አይ ማርታ አይደለችም:: እማዬ ናት::"

"እማዬ!?"

"አዎ!...ብርጭቆ ሰበርኩና ተናደደችና እብድ ልጅ– እብድ.. እንደአባትህ እብድ" አለችኝ::

ዝም አለች:: አዘነች:: በፊቷ ላይ የሚገኙ ሥሮች ተጠጋጉ፤ ፊቷ ሰፌድ መሰለ:: የተዘበራ ረቀ ዙር ያለው ሰፌድ መሰለ::

"አባባን አባቴ እብድ ነወይ ብየ ጠየኳቸው:: ማነው እንዲህ ያለህ አሉኝ::እማየ አልኳቸው ...ውሸቷን ነው አሉኝ::አባትህ እኔ ነኝ አሉኝ:: እና ሳሙኝ::ግን ተናደው ነበር::አባትህ እኔ ነኝ አሉና ሳቁ:: እኔ ግን ፈራኋቸው:: ምክንያቱም



t.me/OLDBOOKSPDF

ተናደው ነበር፡፡ ማርታ ደሞ አባባ አባትህ አይደ ሉም ትላለች፡፡"

"ማርታ!..." አለች፡፡

ለልጁ አልነበረም እምትነግረው፡፡ እያሰበች ነው መሰል፡፡ የፌዝ ፈገግታ ፈገግ ብላ ታስባ ለች፡፡ ልጁ ቡና በወተቱን አነሳና ጨለጠው፡፡

ከፊት ለፊታቸው በርካታ ወጣቶች፤ ጥንድ ጥንድ ሆነው፤ጥቂቶች ደግሞ፣ነጠላ ነጠላ ሆነው ...ሲገቡ፣ሲወጡ፣ሲነሱ ሲቀመጡ፣ ሲበሉ ሲጠጡ ይታያሉ፡፡ አዲስ የገቡት በፊንታቸው የሚፈልጉ ትን ያዛሉ፤ትርምስ ነው፡፡

"ስማ!...ይህን ውሰድና ቦቅሰኛ አድርግልኝ"
"ቦቅሰኛ ምንድነው?" አለ ልጁ፡፡
"ኬክ" አለች፡፡
"አንድ ኬክ ልብላ?" አለ ልጁ፡፡እየፈራ ነው የጠየቃት፡፡

"ብላ!...የኔ ወንድም እባክህ አንድ ኬክ ጨም ርልን" ስትል አሳላፊውን በትህትና ጠየቀችው፡፡ ትህትና ነው እንጂ ፍርሀት አልነበረባትም፡፡
"ኬክ ከዳቦ ይሻላል" አለ፡፡

አልመለሰችለትም፡፡ዘፈኑን ታዳምጣለች፡፡ ከዘፈኑ ጋር ያለፈውን ዘመኗን ትኖራለች፡፡

"ዳቦ..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"'ዳቦ ለተራበ!' አሉ ፈረንሳዬች" አለች አቋርጣው፡፡ ዝም አለ፡፡ አልገባውም፡፡ እንዳልገባው እፊቱ ላይ ይታወቅበታል፡፡ ከየት መጣሽ ያላት ፈገግታ እከንፈሯ ላይ መደነስ ጀመረች፡፡ ልጁ ባንድ እጁ የገመጠለትን ኬክ ይዞ በሌላው እጁ እጠረጴዛው ላይ የተዘሩትን የኬክ ፍርፍሮች እየደፈጠጠ ይጫወታል፡፡ ኬኩን ያያል፡፡ እሷ ደረቱን ታየዋለች፡፡ ቴፕ ሪኮርደሩ ይዘፍናል፡፡

*"ምነው ተለየሽኝ መስከረም..."*

ልጁ የኬኩን ፍርፋሪ እንደቁንጫ ያፍተለትላል፡፡

*"እንቋጣጣሽ ብለን ..."*

እሷ በሀሳብ ተውጣለች፡፡

"የኛ ኑሮ ትግል ነው አለኝ፡፡ አመንኩት፡፡ ምርጫ አልነበረኝም፡፡አመልከው ነበር፡፡እኔ ብቻ ሳልሆን ጓደኞቼም ያመልኩት ነበር"

በጠያቂ አይን አያት፡፡ በጥርጣሬ አይን አያት፡፡ በፍርሀት አይን አያት፡፡ በስጋት አይን አያት፡፡ሲሰጋም አይኑ ያምራል፡፡ ቆንጆ ልጅ ነው፡፡

"ፈራሁ!" አላት፡፡ ፈርቷል፡፡

"ምን ፈራህ"አለችው፤ ደንግጣለች፡፡ መደንገጧ ይታወቅባታል፡፡

"የምትነግሪኝ ነገር ያስፈራኛል"አላት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝም አለች፡፡በስጋት አየችው፡፡ይናፍቃታል፡፡
"ምን ነገርኩህ?"አለችው፡፡

"እንጃ" አላት፡፡እቅፍ አርጋ ሳመችው፡፡ አፍ ንጫዋ ቆንጆ ነበር፡፡ ፊቷ እንዲያ ሰንበር ብቻ ሆኖ እንኳ አፍንጫዋ ደስ ይላል፡፡ ቴፑ ሽሽ...ጧ አለ፡፡

ከውጭ ሲጢጥ የሚል ድምፅ ተሰማ፡፡ ጧ! የጥይት ያህል ጮኸ፡፡

"ሰው ገጨ?"
"እንጃ!"

በቤቱ የቀረ ሰውም ያለ አልመሰለ፤ እየተን ጋጉ ወጡ፡፡

"ልውጣ "አለ፡፡ ከገቢ ወጪው ወሬ አንድ ሰው ሳይሞት አልቀረም፡፡
"አርፈህ ተቀመጥ!"አለችው፡፡

ልጁ መውጣት አምሮታል፡፡እሷም መውጣት አምሯታል፡፡ የሞተውን ሰው እንዲያይ የፈለገች አትመስልም፡፡

* * *

ይኸ ሰው መቼ ገባ? እልጁ አጠገብ ነው የተቀመጠው፡፡ እሱ ሰውየውን ያያል፡፡ ሰውየው ሊያግባባው እየሞከረ ነው፡፡ ልጁ ግራ ተጋብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቷል፡፡ ወይም አፍሯል፡፡ እሷ ነጠላዋን ታራግፋ ለች፡፡

"ኬክ ትወዳለህ?"አለ ሰውየው፡፡

ቴፕ ሪኮርደሩ ሽሽሽሽ...ይላል፡፡

"አንድ ማኪያቶ!"አለ ሰውየው "ጠቆር ያለ" ይኸ ጎርነን ያለ ድምፅ ነው፡፡ መነፅር የደረገ ቀጭን ሰውየ፡፡ ነጠላዋን እያራገበች ሩቅ ታያ ለች፡፡ ከግድግዳው ወዲያ ነው የምታየው፡፡እን ዲያውም ህዋን ሳይሆን ጊዜን ነው የምትመ ለከተው፡፡

"ምን ዓይነት ኬክ ይምጣልህ?" አለ ሰው የው፡፡

"የዚህ ዓይነት"

"ኬክ አምጣ!" አለ ቦዩን፡፡

"ምን ዓይነት ኬክ ይሁን?"ሲል ጠየቀ ቦዩ፡፡

"ሁለት ክሬም ኬክ አንድ ቦምቦሊኖ" አለ ሰውየው፡፡

*"እኔስ መስሎኝ ነበር..."*

አንዲት ዘለላ ቡናማ ጥቁር ፀጉር ወደ ግን ባሯ ተነጥላ በፊቷ ላይ ወርዳ አንገቷን አልፋ እደረቷ ላይ ወድቃለች፡፡ፀጉሯ ወዙን አጥቷል፡፡ የቡና መኪና ይጮሃል፡፡እግድግዳው ላይ ያለው ልጅ ይስቃል፡፡

*"እኔስ መስሎኝ ነበር..."*



t.me/OLDBOOKSPDF

ቴፖ ናፍቆቷን ዘፈነላት፡፡ አባበላት፡፡ ጊዜን አፈጠጠችበት፡፡ ጊዜን ግን ትዝ ያለችው አይመስልም፡፡ ቴፖ ጊዜን አልዘፈነውም፡፡

"ይኸው!" አለ ቦዩ የታዘዘውን እያቀረበ፡፡

"ጥሩ፤ ውሀ በብርጭቆ አምጣልኝ" አለ ሰውዬው በምስጋና አይነት፡፡

እሱ ኬኩን በናፍቆት አየው፡፡ ኬክ ይወዳል፡፡ ኬክ ከዳቦ ይሻላል፡፡ ሸሚዙ አዲስ ነች፡፡ ደስ ትላለች፡፡ ጃኬቱ አልተቀለፈም፡፡ ግድግዳው ውሃ ሰማያዊ ቀለም ተቀብቷል፡፡ እሷ ውሃ ሰማያዊ በተቀባው ግድግዳ በኩል በሃሳብ ጭልጥ ብላ ሄዳለች፡፡ አዝናለች፡፡ የናፍቆት ሀዘን አዝናለች፡፡ ሰውየውና ልጁ የተግባቡ ይመስላል፡፡ ይተያያሉ፡፡

"ብላ እንጂ"

"እሺ!"

ኬኩን በቁጠባ መልክ ትንሽ ገመጥ አደረገው፡፡ ቀና ብሎ ሰውየውን ያየዋል፡፡ደስ እያለው ያየዋል፡፡ ኬኩን ደስ እያለው ይበላል፡፡ ኬክ ይጣፍጣል፡፡ ራብ ያስጠላል፡፡

ልጁ ሰውየውን አየው፡፡ ሰውየው ደግ ነው፡፡ እያፈረ ሳቀ፡፡ ፈገግ አለ፡፡ ሁለት የፊት ጥርሶቹ የፈረንጅ ባቄላ ያካክላሉ፡፡ነጭ ናቸው፡፡ቴፖ ይዘፍናል፡፡ አየችው፤ኬክ ይበላል፡፡ ሰውየው አያት፡፡ አየችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምን...ቅድም..."

ልጁ ፈራ፡፡ ቀና ብሎ አየት፡፡ በብሩህ ቀይ ኮከብ ፊቱ ላይ የፍርሃት ዘር ተበትኖበታል፡፡

ሰውየው በመነፅሩ ውስጥ አሾልቆ አየት፡፡ ከበዳት ሰውየው፡፡አያስፈራም፡፡ግን በጣም ይከብ ዳል፡፡ ግርማ ሞገስ አለው፡፡ ቴፕሪኮርደሩ የተቆ ራረጠ ድምፅ ያወጣል፡፡

ትን አላት፡፡ መሳል ጀመረች፡፡

ሰውየው ፊቱ ልውጥ አለ፤ ፊቱ ቅጭም አለ፡፡ፊቱ ቅጭም ሲል ይበልጥ ርህሩህ ይሆ ናል፡፡ቆንጆ ነው ሰውየው፡፡

ያስላታል!... ትን ብሏት፡፡ ... ያስላታል፡፡
ልጁ መብላት አቁሟል፡፡ ያያታል፡፡ በጣም አልደነገጠም፡፡ ግን ዐይኑ ሰግቷል፡፡ሲሰጋ ያሳዝ ናል፡፡ ሲያሳዝን እንዴት ነው የሚያምረው!

"አይዞሽ...አይዞሽ!...ምነው ምን ነካሽ?" አላት ሰውየው፡፡ፊቷ ከሰውየው ሸሸ፡፡ ልጁን አየችው፡፡ ሰግቷል እጁን አንስታ አረጋጋችው፡፡ በአንድ እጁ ቡናማ ፀጉሩን እያሻሸች ልታረጋጋው ሞከ ረች፡፡ ግን ሳሉ አስቸገራት፡፡ እሱ ግን አይና ገር፣አይበላ፣ጨንቆታል፡፡ሰውየውም ጨንቆታል፡፡
ይኸን የመሰለ ዘፈን ይደምስሱት!



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይዞሽ ትንታ ነው። ትንፋሽሽን ቁጠር አድርጊና በኃይል ወደ ውጭ ተንፍሺ!"

ሰውየው ምክርም ርዳታም እየሰጠ ያጽናና ታል። ደግ ነው።

ልጁ አፉን ያንከላውሳል!

እህ! እህ! እህ! አሁ! እህ!

የቡና መኪናው ቱፍ ... ቱፍ ...ግሽሽ...ቱፍ...ቱፍ ይላል።

ያስላታል።...ትን ብሏት ያስላታል።...

ቴፑ ይዘፍናል። እሷ ሳሉ ጋብ እያለላት ነው። ልጁ እየደነገጠ አፉን ያንከላውሳል። የሰውየው ፊት ዘና ብሏል። ፈገግ ሳይልም መደሰቱ ይታወቅበታል።

"አልቻልኩም መረረኝ እኔን..."

እሷ ቴፑን አታዳምጥም። ፊቷ ቀይ ይሆ ናል። ደረቷን ገልጣ በነጠላዋ ታራግባለች። ልጁ ኬኩን አልጨረሰም። ከኬኩ ላይ ክሬሙን ይልሳል። ሰውየው ቦምቦሊኖውን ጨርሶ አፉን በናፕኪን ይጠራርጋል።
"ጨርስና እንሂድ"
"ና... ቦይ... ና!"
"ሂሣብ ስንት ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"በጠቅላላ ነው?"

"የእኛን እኛ እንከፍላለን" አለች እሷ፡፡

"በጠቅላላ...አዎ! በጠቅላላ ስንት ነው?" አለ ሰውየው፡፡

"ሁለት ከአምስት"

"የእኛን እኛ እንከፍላለን"

ሰውየው እኪሱ ገባ፡፡እሷ መሐረብ መፍታት ጀመረች፡፡ መሐረቡ ጠብቆ ነው የተቋጠረው፡፡ እሷ ልትፈታ ትታገላለች፡፡ ሰውየውን አልወደደ ችውም፡፡ ቦዩ ዕቃውን እያነሳሳ ጠረጴዛውን ይወለውላል፡፡ ልጁ እጣቱ ላይ የቀረውን ክሬም ይልሳል፡፡ ሰውየው አምስት ብር አውጥቶ ሰጠው፡፡

"የእኛን እኛ እንከፍላለን፡፡"

"የጠቅላላ ሒሳብ...፤ መልስ አምጣ"

እሷ የተናደደች ትመስላለች፡፡ዕውነቷን ነው የተናደደችው፡፡ ቦዩ ለሰውየው መልሱን ሰጠው፡፡

"የእኛን እንካ!"

"ተከፍሏል፡፡"

ቴፕሪኮርደሩ ይዘፍናል፡፡ ሰውየው ተነስቶ ልጁን ጉንጩን ስሞት ወጣ፡፡ እሷም እየተከዘች ተነሳች፡፡ ልጁ ደስ ብሎታል፡፡

ወጡ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ጭጋግና ጠል

በግንቦት አስራ ሁለት/1983– ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ ሬዲዮ– "ከመንግስት ምክር ቤ/ት የተሰጠ መግለጫ ስላለ እንደደረሰን እናሰማለን" አለ፡፡

"ደግሞ ዛሬ ምን ሊያወሩ ይሆን"

"ምኑ ይታወቃል–ሆኖም ማዳመጡ ይሻላል"

ትንሽ ሆቴል ናት መኖሪያችን፡፡ – እንግዳ ይኖራል፡፡ ማን ምን ተናገረ አይፈይድም፡፡

"ሰውዬው ጠፍቷል የሚል ጭምጭምታአለ"
"ማን– ቾምቤ"
"አዎ አላመንኩምንጂ ወሬ ሰምቻለሁ"

"ያኔም ከሥልጣን ወረድኩ ይላል ብለን ስን ጠብቅ ነው የታሪክ አስተማሪ ሆኖ ቁጭ ያለው፡፡ ዛሬ ደግሞ ስለጠርነት ምንነት ፍልስፍና ያስተም ረን ይሆናል"

"ደፋር ናት'ኮ! አ–አይ ቾምቤ!"

አንድ ሽማግሌ አሉ– ቢራ በጣም የሚወዱ፡፡ እና ትናንሽ ልጃገረዶችን የሚጋብዙ፡፡– ሴት ካዩ የሚያቁነጠንጣቸው፡፡አንዳንድ ቀን ባምስት ሰዓት መጠጣት ይጀምራሉ፡፡ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አካ ባቢ መጠጣትና ትናንሽ ልጃገረዶችን መጋበዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያቆማሉ፡፡— ብዙ ገንዘብ ይከፍላሉ፡፡— አንድ መካከለኛ ቤተሰብን ወር የሚይዝ ገንዘብ— ያን ያህል፡፡...

የሬድዮውን መግለጫ ሲሰሙ ዘለሉ፤ ፈነ ጠዙ፤ እምቦሳ ሆኑ — ያን ያህል መደሰትና ያን ያህል መዝለል የሚችሉ መስለውኝ አያውቁም ነበር፡፡— ደስታቸው በጣም አስገረመኝ!— መደሰት መቻላቸው ልበል ይሆን?—የቀላመዱም መሰለኝ፡፡ ምክንያቱም ባለፈው ጊዜ ጠጥተው፥ ጠጥተው፥ ሰክረው—

"ጀግና ማለት እሱ ብቻ ነው— ጀግና ማለት መንግሥቱ ኃይለማርያም ነው! — የነቴዎድሮስ፣ የነአሉላ አባነጋ አምሳያ ጀግና! ... " እያሉ እየጮሁ፥በሱ ጀግንነት እየኮሩ ሲናገሩ ሰምቻቸው ነበር፡፡

እኒህ ሰውየ ፈሪ ናቸው ብዬ አስቤ ነበርና— መንግሥቱ ከሥልጣን ወረደ መባልን ሰምተው፤ እንደሚጋብዟቸው ሴቶች ወጣት ሆነው ሲፈነጥዙ ሳይ ገረመኝ፡፡—

ከሁለት ቀን በኋላ በስድስት ሰዓት ላይ ሬዲዮ— ... መንግሥቱ ኃይለማርያም ...

"ስማ! ጓድም ቀረ!..."

...በደቡብ ክፍላተ ሀገር የሚገኙ የጦር ማሰልጠኛ ተቋሞችን የሚጉበኝ በማስመሰል...



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሰማ ! ... አንተ አሉቾኮ..."
... በአውሮፕላን ወደ ኬንያ ኮብልሏል...
"ፓ!... እነዚህ ሰዎች ናቸው!"
"አንተን ምን እንዲህ አደረገህ!"
"እንዴት አንተ ይሉታል?–ነውር አይደለም እንዴ?"
"ሰው ሁሉ አንተን'ኮ ነው የሚያየው!–"
"የትኛው ሰው?– የምን ሰው?– ሰውእ?–"
"ቆይ..."
"ቆይ ማለት አያስፈልግም–እኛ ባህል ያለን ሕዝብ ነን፡፡ መዲና እንዲህ ይላል፡፡–

'አንቱ ያልኩትን ሰውዬ
አላቃልልም አንተ ብዬ
አባይ ይጎድላል እንኳን ሰው
ጊዜ ሲያዋርደው–'

ይኸኮ ቀላል ነገር አይደለም"
"አጠፋአ ታዲያ ... "
"ያጥፋአ ... አላጠፋም አላልኩም፡፡ እኔ በበኩሌ መንግሥቱ ሲያለማ አይቼው አላውቅም፡፡ይህን ያህል ዓመት አንቱ ይሉት የነበረው እያጠፋ ነው፡፡... መንግሥቱ'ኮ ባሥራ ሰባት ወይም ባስራ ምናምን ዓመት ውስጥ አንድን አገር እደሌለች አድርጐ ያፈረሰ ሰው ነው፡፡... እንዲያውም በኔ አስተሳሰብ... አንድ ንጉስ ይቺን አገር ላጥፋ ብሎ አቅዶ፥ተዘጋጅቶ ቢነሳ እንኳ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን ያህል ተሳክቶለት ሊያፈርሳት እንደማይችል አውቃለሁ፡፡ ... ይህን እያደረገ አንቱ ሲሉት ኖሩ፡፡ዛሬም ያው ጥፋቱን ቀጠለ፡፡– እንዲያውም ዛሬ አጠፋ ማለት አይቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልም፡፡ለቆ መሄዱ አልቀረት ይቀንሳል እንጂ የሚ ያደርሰው ጥፋት የለም፡፡— የመጀመሪያውን ትክ ክለኛ ነገር የሰራለት ጋዜጠኛ ሆዬ አንተ ብሎት ቁጭ! — እና ..."

"በቃ ተወው..."

"የለም፥አልተወውም፡፡ ያሞግሱት ማለቴ ግን አይደለም፡፡ አንቱ ይበሉት፡፡ አንቱ ባለ አፋቸው ጥፋቱን ይዘርዝሩ"

"አንቱ እያሉ ጥፋቱን ቢዘረዝሩ— ያው አንተ ይሆን የለም!— ... ዳሩ መንግሥቱ ካጠፋቸው ነገሮች አንዱ ባህል ነው፡፡— ባህል የሌለው ራቁት ሕዝብ ሆንን፡፡—መስረቅ የማይቀፈው፥ድሀን ገፍፎ ልብሱን ሸጠ መጠጥ መጠጣት ኃጢአት ቀርቶ ወንጀልነት የሌለው ድርጊት የሚመስለው ... ኧረ ስንቱ! —የ— ባዶ አደረገን'ንጂ፡ ... ዳሩ መንግ ሥቱ የዘራውን አጨደ፡፡—"

"ግን አንተኮ! ..."

"እኔ መንግሥቱን አንድም ቀን አንቱ ብየው አላውቅም፡፡መንግሥቱ ለኔ ቆሻሻ ነው፡፡— ጥራጊ ነው፡፡ — ለባህላችን እንጂ ለመንግሥቱ አላዝ ንም፡፡ ... "

በዚህ ቀን ማታ ቪ.አ.ኤ.



t.me/OLDBOOKSPDF

"... 'ቆራጡ፥ ብልሁ፥ አስተዋዩና ገናናው መሪ' ሲላቸው የነበረው የኢትዮጵያ ሬዲዮም አንተ እያለ ነበር እንዴት እንደጠፉ የሚያትተ ውን መግለጫ ያስተላለፈው" ሲል ተናገረ፡፡ በልቤ፡-

እናንተ ካገር ስለራቃችሁ፥ መንግሥቱ የረ ጨው ፀረ ባህል መርዝ ስላላገኛችሁ እንደባህሉ ማለት ቻላችሁ አልኩ፡፡

ሐሙስ ወደ ማታና አርብ- አዲስ አበባ በተ ጕሳቆለ የመንግሥት ወታደር ተሞላች፡፡ ሁለት አውቶማቲክ ጠመንጃ በቀኝና በግራ ትከሻቸው ያነገቱ፥ ላውንቸር የተሸከሙ፥ ባዙቃ ተሸክመው አውቶማቲክ ጠመንጃ የደረቡ፥ ... ሁለት አውቶ ማቲክ ጠመንጃ አንግተው ሶስተኛውን መሬት ለመሬት የሚጕትቱ ቸር – ር ... ር ... ር ... ር ... ር... እያደረጉ የሚጓዙ...

... ወታደር ... ወታደር ... ወታደር አዲስ አበባ ወታደር በወታደር ሆነች፡፡– ጕልተው የሚ ታዩበት ምክንያት እንግዳ ስለሆነ ይሆናል ነገሩ፡፡ ... ወይም ብዛቱ ... ወይም ...

ወታደር – ያደፈ ፊልድ ጃኬት፥ የተበጣጠሰ ፊልድ ጃኬት፥ የወየበ ፊልድ ጃኬት፥– ያደፈ ቅጠልያ፥ የተበጣጠሰ ቅጠልያ፥የወየበ ቅጠልያ – አፈር የመሰለ ቅጠልያ–



t.me/OLDBOOKSPDF

አፈር የመሰለ፥ የተጎሳቆለ ወታደር መጥቶ ፈሰሰ፡፡ አይኔ እሰው ላይ ባረፈ ቁጥር ያ ሰው ወታደር ሆነ፡፡—

አዲስ አበባ ሰጋች፡፡ — ስጋት ላይ ወደቀች፡፡ አንዱ "ይኸ የገባው የኛ ወታደር ነው ብላችሁ ነው? ... እነሱ ናቸው፡፡ በቃ ከተማውን ያዙት" ይላል፡፡

ሌላው — "ይኸ ሞራሉ የወደቀ ወታደር ፈጀን፡፡ ወታደር ሞራሉ ወድቆ ከሥርዓት ውጭ ከሆነ፥በዚያ ላይ ተርቧል፥ይህ ሁሉ ሆኖ መሳሪያውን እንደያዘ ነው፡፡ አስቡት፤ — አለቅን፥ ..." ይላል፡፡

ሶስተኛው ደግሞ— "አብረው ገብተዋል ወያኔ ዎች፡፡— ይህ የመንግሥት ወታደር ብቻ አይመስ ለኝም" ይላል በሩቅ አሳቢ ቁም ነገር ተመስጦ፡፡ ሌላው ሌላ፥ሌላው ሌላ ... ሆኖም አብዛኛው ሰው ደንዝዟል፤ ስጋቱ ቢኖረውም ስጋቱን ደብቆ በግ ብኑ በሰላም የሚኖር ይመስላል፡፡

የሚጠጡ ይጠጣሉ፡፡ ... ሴተኛ አዳሪዎችም ከወንድ ጋር ያድራሉ፡፡ ... ስካርም አለ፡፡ — ወሬ ግን እየተሽከረከረች አዲስ አበባ ሁኔታ ላይ ትነጥባለች— ፍርሃት ላይ!

ወያኔ ስትገባ የምታጎሳቁለን፡- ሞራሉ የወደ ቀው ወታደር የሚያደርሰው ግድያ— ዘረፋ! ...



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ግን ዘረፋ አልነበረም፡፡ — የተስፋዬ ገ/ኪዳን ሕፃን መንግሥት ወታደሩን ሰብስቦ ጃንሜዳ እንዲያርፍ አደረገ፡፡ ወይም ሞከረ እንበለው? — የደከመ፥ የተራበ፥ የተጉሳቆለ፥ ያፈረ — ሞራሉ የወደቀ ወታደር ...

ሁሉም ጃንሜዳ አልገባም፡፡

"እኛ ሰፈር አንድ ትልቅ ሜዳ አለ፤ እዚያ ሰፍረዋል"

"እነማን?"

"የኛ ወታደሮች"

"እ—ሺ!"

"ሕዝቡ ምግብ እያዘጋጀ ወስዶ ያበላቸዋል"

ካዲስ አበባ ደቡብ የመጣ ሰው የነገረኝ-

"ጉለሌ ውስጥ በየቤቱ እየዞሩ ይለምናሉ"

"መለመን - መለመን?"

"አዎ፡፡ ስለምንተ ማርያም ብሎ መለመን!"

እኛ አካባቢ —

"ባለቤቱ አለ?"

"የለም፤ ምነው?"

"ቢኖር ጥሩ ነበር፡፡ ባይኖርም- እስኪ እንዲህ አርጉልን እባካችሁ፡፡ አንድ አስር እንጀራ ቀበሌ ድረስ አምጡና ስጡልን"

ቀበሌ በትህትና ሲናገር— ለመጀመሪያ ጊዜ፡፡ በትህትና ተናግሮ እንደሄደ —

"ለወታደሮቹ መሆን አለበት"- ባዘኔታ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እዎ ልጄ፥ ለነሱ መሆን አለበት፡፡ ጃንሜዳ ሰብስበዋቸዋል አሉ" የአዲስ አበባ ሕዝብ ለመጀ መሪያ ጊዜ ሰው ሆነ፡፡ ለተቸገረ አዘነ፡፡ እንጀራ እያዋጣ ለወታደሮቹ ሰጠ፤ መመገብ ጀመረ፡፡

እኔ ክፉ ነገር አሰብኩ፡፡መብላታቸውን ባልጠ ላውም ፈራሁ፡፡ የራባቸው ነገር ብዙ ሊሆን ይች ላል ብዬ ገመትኩ— እና እንጀራ ሲጠግቡ ሌላው ረሀብ ይከተል ይሆናል የሚል ጥርጣሬ መጣ ብኝ፡፡

ይኸ የዋህ ሕዝብ ቀልቦ ጉልበት ሰጥቶ መሣ ሪያ በያዘ፣ሞራሉ በወደቀ ወታደር ይጎሳቆል ይሆን?—ፈራሁ፡፡ ፀለይኩ፡፡ ይህ አይሁን፥ከሆነም አታሳየኝ ስል ፀለይኩ፡፡

አዲስ አበባ አፈር መሰለች፥ከሳች፡፡ ቀን ቀን ወሬ እንደሳት ፍንጥርጣሪ ይበራል፡፡ ይለበልባ ታል፡፡ ሌሊት በጥይት ትታረሳለች፡፡ ከሳች— አዲሳባ፡፡

"ወያኔ ተቃርባለች አሉ"
"የት ደረሱ?"
"አምቦ- አምቦ ደርሳለች ይባላል"
"አምቦማ ... አምቦ ከገቡማ ቆዩ"
"መቂ — መቂ— "
"አዲስ አለም — አርባራት —"

ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ሱቆች ሁሉ ተዘጉ፡፡ — ድንገት በዚህም በዚያም የብረት መጋረጃዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

ወረዱ፡፡ ዠርጠጥ –ሲጢጥ ዠርጠጥ –ገው+ድው ... ችኮላ ... ጥድፊያ ... ደፋርነን የሚሉ ተዘጋ ጅተው እሱቃቸው በር ላይ ቆመዋል፡፡ አልተሸ በርንም ለማለት የሚሞክሩ ይመስላሉ፡፡ ሆኖም እጅግ ተሸብረዋል፡፡ እጃቸው ቁልፎቻቸውን መርጦ አዘጋጅቷል፡፡ እኛም መዝጋት ይኖርብን እንደሆነ ለማጣራት እንዲህ ሆነው ከቆሙት አንድ ሁለቱን ለማነጋገር ሞከርኩ – ልብ ብሎ የሚመልስ ሰው አልነበረም፡፡ – በሌላ ቀን ምን ያህል እንደሚያከብሩኝ ስለማውቅ አልተቀየም ኩም፡፡

አዲስ አበባን አየኋት፡፡ ጭጋግ ለብሳ ታየ ችኝ፡፡ ብሩህነት፥ድምቀት፥አልባብ አልባብ መሽ ተት ስሜት ይሆናል- ምናልባት፡፡

"ለምን አትዘጉም?" አለኝ አንዱ ባለመዝጋ ታችን እየደነቀው፡፡

"ምን እንደተፈጠረ አልገባኝም"

"ዘረፋ ነዋ – ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?"

"የሰማሽው ነገር አለ?"

"የሰማሁት እንኳ የለም፥ ግን ..."

"ምንድነው ነገሩ" – ለማጣራት ወጣ ብዬ፡፡

"መርካቶን ዘረፉት!"

"እነማን? — "

"ታጠቅ ተያዘ አሉ"

"ታጠቅ፥ እዚህ?"

"ተያዘ አሉ"



t.me/OLDBOOKSPDF

ከአርብ ማታ ጀምሮ የአዲስ አበባ የሌሊት ሰማይ በጥይት መታረስ ጀምሯል፡፡ ቅዳሜ'ለት ተኩሱ የጀመረው አንድ ሰዓት ሳይሆን ነው፡፡ አርብ'ለት ከሶስት ሰዓት በኋላ ነበር፡፡—

የተስፋዬ የይድረስ ይድረስ መንግሥት ሰዓት እላፊን ሶስት ሰዓት ከምሽቱ— አውጆ ሰንብቷል፡፡

ቅዳሜ ስምንት ሰዓት አካባቢ ሞቅ ያለው ወታደር ባካባቢው ታዬ ተባለ፡፡ አንድ ሰው በመ ንገድ ሲያልፍ በሰደፍ መትተው ጣሉት- ሁለት ወታደሮች የሚል ወሬም ተሰማ፡፡ለምን እንደሆነ ስጠይቅ መሣሪያ ሸጡልኝ ብሏቸው ነው ሲሉ ነገሩኝ፡፡ ይህ የሞራል መውደቅን ሳይሆን ክብር መጠበቅን ያሳያል የሚል ሃሳብ ታየኝ፡፡

ቅዳሜ እጅግ ፈጣን ነበር፡፡ ወደምሽት ላይ የወታደሩ ቁጥሩ እየበረከተ ሄደ፡፡የከተማው ዱርየ ከሚያውቀው ወታደር ጋር እየተጣመረ ሲዞር ይታይ ጀመር፡፡ቅዳሜ እጅግ አስፈሪ ሆነ፡፡ ሁል ጊዜ ከመምጣታቸው የተነሳ ከደንበኝነት ወደጓደ ኝነት የተቀየሩ ሁለት የማውቃቸው ሰዎች እየ ሮጡ ገቡ፡፡ ምን እንደሆኑ ስጠይቃቸው—፡

“አሁን ሲተኮስ ሰምተሃል? በኛ ላይ ነው'ኮ የተኮሰብን፡፡ የሚገርም ነው”

“አብዮት ጠባቂ ነው?— ሰዓት ገና አይደ ለም'ንዴ?”



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን አብዮት ጠባቂ አለ– ወታደር ነው'ንጂ! አብዮት ጠባቂውማ ሲተኩስብን እያየ ማዶ መንገዱን ይዞ ዝም አለ፡፡"

"ለምን ይተኩስባችኋል?"
"ገንዘብ አምጡ ነዋ!"
ገንዘብ ሰጥተው እንደተገላገሉ ነገሩኝ፡፡

ቅዳሜ የመሣሪያ ሽያጭ እንደተጧጧፈም ተሰማ፡፡ "በሰላሳ ብር ምን የመሰለ ክላሽ ከመቶ ጥይት ጋር ትገዛለህ?" ጥያቄ ቀረበልኝ፡፡– እንደ ማልፈልግ ተናገርኩ፡፡ ሰው ግን እስካፍንጫው እንደታጠቀ ሰማሁ፡፡ – ወያኔ ስትመጣ ሊያዋጋ የሚችል መሣሪያ አለ ይላል ወሬው፡፡ – ወያኔን ወግቶ የሚመልስ ነገር ቢመጣ ደስ ባለኝ ... ደስ ባለኝ፡፡ሆኖም የተደራጀ÷የሰለጠነ÷ቅንጅት ያለው ወታደርን አሸንፎ የመጣ ወያኔ መሣሪያ በያዘ÷ የጉበዝ አሊቃ እንኳን በሌለው ሕዝብ እንዴት ሆኖ ሊወጋና ሊቸነፍ ይችላል? በዚያ ላይ ከብበ ማዳከም የሚሉት ታክቲክ አለ፡፡– ወያኔ በአዲስ አበባ ተጠምጥሟል – እንደዘንዶ፡፡ ምንም ነገር እንዳይገባ ከልክሎ ከቦ ቁጭ ቢል እንኳ ያቸን ፋል... ስል አሰብኩ፡፡ ስለዚህ የፊት የፊቱን ነው ወያኔ ቢገባ ይሻላል፡፡ባበደ ወታደር ሳንጃ ያለም ክያት ከመሞት÷ ያው በለመድነው የኮሙኒስት ጭቆና መማቀቅ ይሻላል – መጨረሻውን እግዜር ያውቃል፤ አልኩ፡፡ የወያኔን መምጣት መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡–



t.me/OLDBOOKSPDF

የዘረፋ ታሪኮች ተሰፋፉ፤ ባንዶገን ሕዝቡ፥ ባንዶገን ወሮበላው፥ ባንዶገን ወታደሩ – ዘረፋ፥ ዘረፋ፥ዘረፋ፥! ቀበሌ ተዘረፈ....

እየቆየ መሣሪያ የያዘና ሞቅ ያለው ወታደር እየሁ የሚለው ሰው ቁጥሩ ጨመረ፡፡ወሬው እየተ ጋነነም፥ እየተጨማመረም መድረስ አመጣ፡፡ (ሆቴሏ የጓደኛዬ ናት፡፡ ብዙ የሚሸበር ሰው አይደለም፡፡ ወሬም ያዳምጣል እንጂ አያንኳኳም ... ያየውን እኳ ለመንገር ጊዜ ይፈጅበታል፡፡)

"እነዚህ ዱርየዎች ሊበጠብጡን ነው ማለት ነው" አለኝ፡፡

"ምን ሆነ?"

"አንዱ አሁን ወታደር ይዞ መጥቶ አስቸገ ረን "ከ"

"ምንድን ነው የሚሉት?"

"አልጋ፤ ..."

"የለም ብሎ መመለስ ነዋ"

"እሱማ እንዲያ ነው ያደረግነው፡፡ ... ግን ትንሽ አስቸገረ – ወታደሩ"

ሰማሁ፡፡ – 'አልጋ የለም' ሲሉት ቢራ ስጡኝ ብሎ ይቀመጣል፡- ወታደሩ፡፡ 'ቢራ የለም' የሚል መልስ ሲሰጠው 'ይኸ ሁሉ ሰው እየጠጣ እንዴት የለም ትሉኛላችሁ' ብሎ ይጮሃል፡፡

"መሣሪያውን እንዴት እንዴት እንዳደረገው ሊገባህ አይችልም!" እየመራ ያመጣው በሰፈሩ ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት ሞራል አልባው መንግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥት ከፈለፈላቸው እልፍ አእላፍ ሚጨት ሌቦች አንዱ እንደነበረም ተነገረኝ፡፡ እንደሚያውቁት ስጠይቅ – የዚያ ቀበሌ ሊቀመንበር ልጅ እንደሆነ ነገሩኝ፡፡– ቤተሰቡ በልጁ ላይ ዛተ፡፡ "አንድ ግርግር ከተነሳ አስቀድሞ እሱን ቀንዱን ማለት ያስፈልጋል- ምንም ርህራሄ ማድረግ አያስፈልግም!"

ነገሩ ሽብር ነበር፡፡ –አገሩ ተሸብሮ ነበር፡፡– የሰው ልብ ይሸበር ነበር፡፡ እኔም ... የኔ ሽብር ቀዝቃዛ ነበር፡፡–ከሁሉ የፈራሁት ግን ዱርየውንና ወታደሩን ነው፡፡ –መግደልም አያስፈልግም፡፡ ... ወሬው ደግሞ ፍርሃቴን አገነነው፡፡...

"ጉለሌ አካባቢ ዱርየውና ወታደሩ ገጥመው ብዙ ቤት ዘረፉ"

"ቄራ አካባቢ ሶስት ቤት በፈንጂ ተመታ"

እዚህ አካባቢ እንዲህ ያለ የዘረፋ ድርጊት ተደረገ፡፡... አዲስ አበባ በዘረፋ ወሬ ተናወፀች፡፡

"ወርቅ ቤቶች ... ሱቆች ... ሀብታሞች ... ምንም ሽቀጥ የላቸውም"

"ምን ሆነ? – ተዘረፈ?"

"ከመዘረፉ በፊት እያሉ ወደመኖሪያ ቤት አጓጓዙት"



t.me/OLDBOOKSPDF

" ... ወርቅ ቤቶች በጆንያ እየሞሉ ሲያግዙ ነበር"

"በጆንያ ? – ወርቁን?"

"ይሆናላ!" ... ወርቅ በጆንያ!

"ምንድነው? ሰው እስካፍንጫው ታጥቋል ይባል የለምንዴ!?"

"ቢታጠቅስ? – ለምን አይከላከልም ለማለት ነው? – ፈንጂ ይዘው አይደለም እንዴ ለዘረፋ የሚሰማሩት! ... "

ይህ እየሆነ ሳለ – የወያኔ ወሬም ይሰማል-

"ደብረዘይት ተያዘ አሉ"

"ኤየር ኃይሉስ?"

"ታፈነ! ... ሌሊት ገብተው በየተኙበት አፈኗቸው አሉ - ያው ጠቋሚ አላቸው አደል"

"ዘብ የለምንዴ? - አየር ኃይልን ያህል"

"ምን ዘብ አለ!... አየር ኃይል ሥራ ያቆመ ድሮ ግንቦት ስምንት...በነአምሣ መገደል አኩርፎ ከዚያ ወዲህ ... "

"ገባኝ ... "

"አየር ኃይል ቢዋጋ ኖሮ ወያኔ ይህን ያህል ትናጥጥ ነበር? አይዋጋምኮ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሣሚት ይሆናል – አልተሸነፍኩም ... አልተሸነፍንም ለማለት"

"አይምሰልህ – አንድ መቶ አለቃ ጓደኛዬ ያጫወተኝ ነገር አለ። ...

... "የኔን ፖዚሽን ነገርኩት፥ የነሱንም ነገር ኩት–እና በሳቸው አልኩት።ዝም ብሎኝ አለፈና ቦምቡን እሜዳ ላይ አፈሰሰው። በመነፅር አይቼ ልክ እንዳይደል ሬዲዮ ሳደርግለት መልስ ሳይሰ ጠኝ ለቀቀው። ይህን ሳይ ተናደድኩና ተነጫነ ጮኩ።የዚህን ጊዜ ወያኔው መስመሩን በኔ አስተ ካክሎ ይከታተለኝ ኖሮ– ከት ብሎ ሳቀብኝ። 'ልታስመታኝ ነበር አደል?' ብሎ ተሳለቀብኝ። ከችንፈቱ ይልቅ የሱ ሳቅ አናደደኝ። ሠራዊቱ አንድ አልሆነም ... "

በዚያም ብሎ በዚህ ደብረዘይት ተያዘች።

የአየር ኃይል ቦምብ እሜዳ ላይ መጣል፤ የደብረዘይት መያዝ፤ የአየር ኃይሉ መታፈን – መታረድ እየተደጋገመ ሲነገረኝ–

"ታዲያ... እኔ ያልገባኝ ደብረዘይትም ትያዝ ግን ያየር ኃይል መኮንኖች መታረድ ምንድ ነው?– ማለት ቦምብ እሜዳ ላይ ከጣሉ ባለውለታ አይሆኑም እንዴ ለወያኔ" ስል ጠየቅኩ።

"ወያኔ! ... ወያኔ ምን ውለታ ያውቃል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ወያኔ ሰው አይደለምንዴ?– ባይሆን ከሙኒስት ናቸውንጂ መቼም ሰው ናቸው፡፡ ... ከሙኒስት ደግሞ... "

"ትግሬ ... ትግሬ መሆናቸውንም አትርሳ!"

ይኼ ግን የሚያናድደኝ ነገር ነው፡፡ አንድ ቀን ተናድጄ መንገድ ላይ የጮህኩት ትዝ አለኝ፡፡

አንዱን ትግሬ ነገር ቆስቁሰው ሰዎች ሲደበድቡት አየሁ፡፡ለምን እንደሆነ ስጠይቅ "– ይበሉት— ትግሬ ነው" አሉኝ የማላውቃቸው ሰዎች፡፡ ያኔ ጠፍኩ፡፡

"ሰው ምን ነካው!" አልኩ፡፡ "መንግስቱ ኃይለማርያምና መለስ ዜናዊ ቢጣሉ፣ ቢዋቀሩ፣ ቢቀጣቀጡ ለሥልጣናቸው መሆኑ እንዴት ይጠፋዋል!– የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህና ገዢ፣ደግ ገዢ ነው እንጂ–ትግሬ ወይም ኦሮሞ ወይም ወላይታ ወይም አማራ አይደለም የሚፈልገው!"አልኩት፡፡ አብሮኝ የነበረው ሰው ፤

"ባገር የመጣ ነው፤ አንተን ምን እንዲህ አደረገህ!" አለኝ፡፡

"እየህ ፖለቲከኞች ለማጋጨትና ወደ ሥልጣን ለመውጣት ይህን የክልል፤ ይህንን የብሔር ግጭት ይጠቀሙበታል፡፡ ግን ... "



t.me/OLDBOOKSPDF

"የነበረው ነገር ባንተ መናደድ አይሠረዝ! ስለዚህ...ብትተወው ይሻላል"– ጓደኛዬ መከረኝ፡፡ እኔ ግን ቀጠልኩ፡፡

"ትማርን እንል የለምንዴ! ... አዲሳባ አደለ ንም እንዴ! ... የዘር ልዩነትን የተውነው ሚስት ለመምረጥ ብቻ ሆነ ማለት ነው!?– ደንቆሮነት ነው! ... እብደት ነው! ... የፖለቲከኛ አርጩሜ መሆን ነው!"

ያን ሰሞን ጠቡ በረከተ፡፡ እዚህ ቦታ እንዲህ ያለ ትግሬ ተደበደበ፡፡... አንድ ትግሬ "ገና እንገ ዛሻለን" ብሎ ደሜን አፈላው፡፡ ... አንድ ሰውዬ ሲያልፍ ትግሮች ይዘው ቀጠቀጡት...

ከተማዋ የጦርነት ቦታ ሆና ቆየች፡፡ እኔም እበሽቅ ነበር፡፡... አፌን ግን ተው አልኩት፡፡– መናገሩ ዋጋ አልነበረውም፡፡ ሕዝብ መንጋ ሆኖ ሲያስብ አእምሮው ይታወራል፡፡ – እንደነዱት የሚነዳ መንጋ ይሆናል፡፡– ወይም ሲንጋጉ ሲያይ የሚንጋጋ ... ነገር ይሆናል፡፡

ወደዚህ ሰሞን ሁኔታ ልመለስ – ሰው ሁሉ ሰኞን ይጠብቃል፡፡ ለንደን ላይ በኢትዮጵያ መንግስትና በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የሰላም ውይይት ይደረጋል፡፡

በአቶ ተስፋዬ ዲንቃ የሚመራ ቡድን ወደ ለንደን ሄዷል፡፡ በሌላ በኩል "ወያኔ አቃቂ ደር ሷል፤ ወያኔ ሰበታን ይዛለች...! ወያኔ ሆለታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገነት— ገብታለች... ወያኔ ይኸን ሥፍራ ያዘች" የሚለው ወሬ በርክቷል፡፡

የወያኔ ሬዲዮ ቀደም ብሎ አዲስ አበባ ዋና ዋና ቦታዎች ላይ በሩቅ የሚመታ ከባድ መሣሪያ ደግኖ እንደሚጠባበቅ አስረድቶ የአውሮፕላኖችን እንቅስቃሴ አግዷል፡፡ አየር አዲስ አበባ አይገባም አይወጣም፡፡

ሰኞ— ምሽት አሥራ አንድ ሰዓት—

"ቤት ዝጉ፡፡ አልጋ ማከራየትም አያስፈልግም!"

ሰሞኑን ዘግተን ብንሰነብትም ቀስ እያልን— ለምናውቀው — አልጋ ስናከራይ ነበር የሰነበትነው፡፡ ዛሬ ግን ከልብ ወዳጆች የቀረበልን ምክር — ዝጉ! የሚል ነው፡፡

ከተማዋ በተኩስ ተደባልቃለች፡፡የሸሸው ወታደር ጠግብ ሲል ይበልጥ ለመጥገብ ፈልጓል፡፡ አውቶማቲክ የአዲስ አበባን ፀጥታ በታተከው፡፡ ሰላም ቡትቶ ጨርቅ መስላ ታየችኝ፡፡ ወሮበላው ከወታደሩ ጋር ይንከወከዋል፡፡

"ይኸው — ይመልከቱ ጋሼ — ከእገሌ ጋር ሁለት አሉ" አለኝ — አንዱ አሳላፊ "እገሌ" ያለው አንድ የምናውቀው የሰፈር ቦዘኔ ነው፡፡ ቤታችን ደርብ ነገር ስለሆነች — የውጪንም በር



t.me/OLDBOOKSPDF

ቆልፈን ነበርና፤ በደርቡ መስኮት ቆሞ ነው ይህን የሚለኝ፡፡

"ምን ይሰራሉ?"

"አንዱን ሰውዬ አስቁመው ይጠይቁታል... ይኸው... ይመልከቱ! ፈተሸው!"

"ይቅርብህ – መጋረጃውን ዝጋው ይተኩስብ ሀል ካየህ፤"

አንድ ስዓት አካባቢ – ተኩስ ለደቂቃ ያህል ሲቆም እንኳ ጭንቅ ጭንቅ ይለኝ ጀመር፡፡ጆሮዬ ድምፁን ተላመደው፡፡ የሰው ተፈጥሮ የሚገርም ነው! እስቲ ተኩስ ይለመዳል? –

ሶስት ስዓት – ምሽት– መብራት ጠፋ፡፡

አዲስ አበባ በጠቅላላ መብራት ጠፋ፡፡ ቢያ ንስ በመስኮት ቆሜ ያየሁት አካባቢ መብራት አልነበረውም፡፡ በማግስቱ እንደተረዳሁት ደግሞ ጠቅላላ ከተማይቱ መብራት አልነበራትም፡፡ ደግ ነቱ ጨረቃ ወለል ብላለች፡፡ ሙሉ ጨረቃ – ደብዛዛ ቀስተ ደመና የከበባት ጨረቃ– ወይም የተቃጠለ እና አመዱ የቀረ ቀስተ ደመና ልበለው? ... ያ ከቧታል፡፡

ምልኪው ጦርነት ነው፡፡ ... ብጥብጥ ነው፡፡... ነፋሱም ...
"ነፋሱ ደግሞ ምንድ'ነው?"አለ አስተናጋጁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሰሞኑን ሁሉ እንዲሁ ነው የሰነበተው" አልኩት፡፡

"ዱሮም በግንቦት እንዲህ ያለ ነፋስ አለ?"

"አልመሰለኝም፡፡ ... በግንቦት ... በግንቦት ወበቅ'ንጂ ነፋስ ትዝ አይለኝም"

"ታዲያ ነፋሱ ..."

"ጦርነት፤ ነፋስ ብጥብጥ ነው ጦርነት ነው-ይላሉ"

"እውነት ነው?"

"እኔ'ንጃ"

ለሊት አስር ሰዓት አካባቢ ተኩሱ ለየት አለ፡፡ ከባድ መሣሪያ መሰማት ጀመረ፡፡ ዘፈቀደ ሳይሆን ልውውጥ ያለው ተኩስ ሆነ፡፡ አልፎ አልፎ ተረረም ተረረም ተረረም የሚል በኖታ የሚተኮስ የመሰለ አውቶማቲክ ሲሰማ ነበር፡፡ ያሁኑ ግን ደንበኛ ልውውጥ መሆኑ ያስታው ቃል፡፡ ከባድ መሣሪያም ተራውን እየጠበቀ ያነቃ ንቀናል፡፡

በመስኮት ቆሚያለሁ፡፡የኢሠፓ ስብሰባ አዳራ ሽና ፓርላማው ይታዩኛል፡፡ የጥይት ውራውርት ብልጭልጭ ሲሉ አያለሁ፡፡ በስብሰባ አዳራሽ አናት ላይ ያ ብልጭታ ይታየኛል፡፡ መትረየሱና አውቶማቲኩ ፋታ የላቸውም ... ፈንዲሻ ሲቆላ! የተኩስ ድምፅ ያንን ይመስላል፡፡

እኔ በመስኮት ቆሜ እጠብቃለሁ ... አንድ ነገር እጠብቃለሁ፡፡ ምንድነው እምጠብቀው? ድንገት ይህንን ጥያቄ አቀረብኩ ለራሴ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የምጠብቀው ነገር አስገረመኝ!

የምጠብቀው የኢሠፓ ስብሰባ አዳራሽ ሲፈ ራርስ ለማየት ነበር፡፡ ገረመኝ ደነገጥኩ፡፡

የደነገጥኩት በሀሳቤ አልነበረም፡፡ ስብሰባ አዳ ራሹን አልወደውም ነበር፡፡ ብዙ ምክንያቶች አሉኝ፡፡ የመጨረሻ የኢትዮጵያ በሽታ፣ የዚች ሀገር ተፃራሪ ዛር– ወይም መቃብሯ እሚቆፈረው እዚያ ውስጥ ስለሚመስለኝ ነው፡፡ መጥፎ አዋጅ በወጣ ቁጥር (ለነገሩ ምን መልካም አዋጅ ወጥቶ ያውቃል) ያ ቤት ትዝ ይለኛል፡፡ አዋጁ ጥቁር ጭስ መስሎ ይታየኛል– ስለዚህ የስብሰባ አዳራ ሹን መፍረስ መጠበቄ አላስደነገጠኝም፡፡

ያስደነገጠኝ፣– አልፎ ፓርላማውን ያፈርሰው ይሆን? የሚል ጥያቄ ስለመጣብኝ ነበር፡፡ እስከ ዚያ ሰዓት አልተኛሁም፡፡ የፓርላማውን የሰዓት ታወር መመታት ህሊናዬ ውስጥ ተመለከትኩኝ፡፡ ድንገት የስላሴ ቤተክርስቲያን ትዝ አለኝ! ደርሶ ደካከመኝ– እግሬ ተብረከረከ፡፡ እንቅልፌ ስለመ ጣም– ስለደከመኝም ሊሆን ይችላል– ተኛሁ፡፡

በሀልሜ–ትርኢት የምታሳይ ጥቁር ፍየል አያ ለሁ፡፡ፍየሏ ባንኮኒ ተደግፋ ቆማ ከራባቷን ባንድ እጅዋ እያስተካከለች ፊቷን በመስተዋት እያየች ሳለ ቤቱ አውቶቡስ ይሆናል፡፡ ሾፌሩ ፍየሏን እያየ በሳቅ ይንከተከታል፡፡

"ጋሼ ይምጡና ይመልከቱ!" ይለኛል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጋሼ! ጋሼ! ... ጋሼ እረ ተነስተው ይመልከቱ– በእናትዎት" ሳቅ– ከት– ከት– ከት!

"ጋሼ! ... ጋሼ!" ብንን አልኩ፡፡ እስተናጋጁ ነበር፡፡ የመኝታ ቤቴን በር እየቆረቆረ–

"ጋሼ! ... ይነሱ!" አለኝ፡፡
"ምነው? ምን ተፈጠረ?"
"ኧረ አመለጠዎት – ይነሱ ሰው ሁሉ ተሰብ ስቦ እየተመለከታቸው ነው"

"ገቡ?–"ተጣድፌ ተነሳሁ፡፡በመስኮት ሄድኩ–

... ባላገር ቀጫጭን ባላገር– ጠንካራ፤ ጨፍ ራራ፤ አጫጭር ባላገር... መትረየስ፤ አውቶማቲክ ጠመንጃ፤ ላውንቸር፤ ባዙቃ – የያዘ ... ቡትቶ በራሱ ላይ የጠመጠመ– ወይም ባንገቱ ላይ–ወይ ትከሻው ላይ ጣል ያደረገ– ባላገር ...

በቅሎ – ስንቅ የተጫነ በቅሎ ፋንድያ ...

"ወይኔ! እነዚህ ናቸው ያሸነፉን?" አለ ልጁ ከጎኔ፡፡ ይህን ጥያቄ ከዚያ በኋላ ብዙ ጊዜ ሰማ ሁት፤– ደጋግሜ ሰማሁት፡፡ ምን ተሰማኝ?– ደስ አለኝ?– ከፋኝ?–

... ምናልባት ደነዘዝኩ፡፡ – ምናልባት...

ከዚህ አንድ ወር ቀደም ብሎ –ወይም ሁለት ሶስት ወር ...



t.me/OLDBOOKSPDF

"እልቂት ይታየኛል!"
"የምን እልቂት?– የት?"
"እዚህ አዲስ አበባ፡፡ – ይታየኛል"

...እንዲህ የሚሉ በርክተው ነበር፡፡ሰው ሁሉ ባህታዊ መስሎ ይታየኝ ጀምሮ ነበር፡፡– ወይም ነቢይ– መጣብህ! የሰው ልጅ መዓት መጣብህ! ... የሚል ባህታዊ፡፡... አምላክ በተግባራችሁ እጅግ ተቆጥቷል...እናንተ የተረገማችሁ ያዲሳባ ልጆች ሆይ!ከቶ ምን ይውጣችሁ ይሆን?–የሚል ነቢይ፡፡

ሕዝቡ ፈርቷል፡፡ የንግርቱ አይነት በዛ፡፡- የገመተውን ንግርት የሚለው እንደአሸን ፈላ፡፡ የንግርቱ ዓይነት ስል ግን-የሚነገርበት መለያየት ማሳየቱ እንጂ ፍሬ ነገሩ አንድ ነው፡፡

... ከፍተኛ እልቂት ይሆናል፡፡...ሞቃዲሾ ገና አውሎ ነፋስ ውስጥ ገብታ ትወራጫለች፡፡ ሞቃ ዲሾ እዚህ ትደገማለች ብሎ ያልሰጋ ይኖር ይሆን? የማይኖር ነገር ስለሌለ ይኖራል ማለት ይቀል ይመስለኛል፡- ስጋት–ስጋት– ስጋት– ደግ ነቱ የደነዘዘ ስጋት ነበርና ሽብር አልታየም፡፡ ስጋት ጎልቶ አልወጣም፡፡– ወሬ ግን ይወናጨ ፋል፤ ይወናጨፋል – ስጋት የተሸከመ ወሬ፡፡
"ህዝቡ ጥራጥሬ እየገዛ ነው፡፡"
"ጥራጥሬ - ለምን? -ሊዘምት ነው?"
"ምን ለምን ትላለህ - ረሀብ ፈርቶ ነዋ!"
"ጦርነቱ እዚህ ደረሰ'ንዴ?"
"ምን ቀረው! መርሀቤቴ ደብረብርሃን ..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"በሶ! ዋናው አስፈላጊ ነገር በሶ ነው"
"በሶ?"

"አዎ በሶ! ... አያችሁ በሶ ውሃ ብቻ ነው የሚፈልገው፡፡ በሶ ነው ዋናው"

"ጥራጥሬም ቢሆን ..."

"የለም ጥራጥሬ እንዲያው ነው! ዋጋ የለ ውም፡፡ለምን ብትሉ —ጥራጥሬ እሳት ይፈልጋል፡፡ —ማገዶ ደግሞ ላይኖር ይችላል፡፡ ... ስለዚህ ዋናው በሶ ነው፡፡"

ሰው ጥራጥሬ ይሸምታል፡፡... ባለሱቆች ጥራ ጥሬ በጆንያ በጆንያ እየሞሉ በሱቃቸው ውስጥ ገሽረዋል፡፡ በሽቀጣሽቀጥ ሱቆች ውስጥ ማካሮኒና ፓስታ በብዛት ይታያሉ፡፡-

ፃድቃን ህልም ማለም አብዝተዋል፡፡- ከእግ ዜር ጋር በልባቸው ይነጋገራሉ፡፡ አንዱ እንዲህ አለኝ-በነቢይ ድምፅ "ልቤ በኃይል ይሰማዋል፡፡ እግዜር' ኮ ለኔ ችግር ሲመጣ ይነግረኛል፡፡- እሱ በመከለያው ይከልለን እንጂ፤ ከመዓቱ ጥላ ከለላ ሆኖ ይሰውረን'ንጂ — እኔ'ንጃ ዘንድሮ በጣም ፈርቻለሁ፡፡— በጣም"

በልቤ — ፍርሃት እውነት ነው፡፡ከእግዜር ጋር የተደረገውን ውይይት ግን እጠራጠራለሁ — ስል አሰብኩ፡፡ በድምፅ ግን ምንም አስተያየት አልሰጠሁም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ደግሞ ህልም አይቻለሁ" አለኝ፤ድምፁ ያው የነቢያት ድምፅ ነበር።ያየውን ህልም ነገረኝ፡-

መንግሥቱ ኃይለማርያም አንድ ቤት ውስጥ ታሥሮ ይመስለኛል—የገጠር ቤት— ክብ የሆነ አለ አይደል?— እሱ ውስጥ። — እምሰሶው ላይ ታስሮ ሲወራጭ ይታየኛል።- ምን ሆኖ ይሆን? እያልኩ ሳስብ ድንገት በሬ ይሆናል።በሬ ሆኖም መንግስቱነቱ አልተቀየረም። ጥቁር በሬ ይሆናል፡- ቀንዱን ታስሮ፤ አረፋ ደፍቆ፤ በእግሩ መሬቱን እየፎገረ፤ "ቡ" ይላል። በእግሩ ይፎግል፤ ይፎግ ልና ጎንበስ ብሎ ወለሉን በቀንዱ ይቆፍረዋል። ሌሎች በሬዎች ዙሪያውን ይለምኑታል።እሱ ግን መጥቶ ካልፈጀኋቸው እያለ ይፎገላል። ወዲያው ሸሸት ይላሉ። ሊበጥስና ሊፈጃቸው ነው ብየ ስፈራ— ብንን አልኩ። በላብ ተነክሬአለሁ፡-

"ይሽ የሚገርም ህልም ነው" አልኩት "ፍቺው ምን ይሆን?"

"ቀላል ነው፤ ግልፅ ነው በቃ ጨረሳቸው ማለት ነው ፈጃቸው!"
"ወያኔዎችን ማለትህ ነው?"

"የምን ወያኔ! ... ወያኔ በአሻጥር እንዲገባ የተደረገ ነው። ማን ይችለዋል። አሁንማ መሳሪ ያው— የኛ መሣሪያ ሁሉ በሱ'ጅ ነው ያለው!"

"ታዲያ እነማንን ነው የሚፈጃቸው?"
"ባለሥልጣኖችን ነዋ"


t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ ህልም ሁለት ሶስት ቀን በኋላ ፍሥሀ ደስታና ለገሠ አስፋው ጡረታ መውጣታቸውን የኢትዮጵያ ሬዲዮ ተናገረ፡፡—

"አውቆ ነው... ሆኘ ብሎ ነው" አለኝ " ሆኘ ብሎ ነው፤ሕዝቡ የት ደረሱ እንዳይል ነው በጡረታ አስመስሎ ያገለላቸው"

"አልገባኝም"

"እንዴት አይገባህም፡፡— ሁለቱን መርጦ ጡረታ ሲያወጣ እንዴት አይገባህም፡፡ ፍስሐ ትግሬ ነው! የወያኔ ክንድ ነው፡፡ ለገሠ ደግሞ ከወያኔ ደላር ተቀብሎ ትግራይን ለቆላቸው የወጣ የወያኔ ግገር ነው"

ይህ የሰው ግገር ጉዳይ አልገባኝ እያለ ጥያቄ ደጋግሜ ጠይቄ ያገኘሁት ምላሽ በአመዛኙ ቁጣ፤ ጥቂት፤ ደግና ቀላል ነገር የማይገባኝ ደደብ በመሆኔ ትዝብት፤ ጥቂት በአይጠረጥሬነቴ ሀዘን ቢጤ —ስለነበር ላነሳው አልፈለግኩም ስለዚህም— ሌላ ጥያቄ ጠየቅኩ —

"የም ሆኖ ጡረታ መውጣታቸው ይበልጥ ነፃ እንደሆኑ የሚያሳይኝጂ እንደሚፈለጉ የሚያሳይ አይመስለኝም—"

"ለመግደል ነዋ! ... ሲጥ ለማድረግ፡፡ — ሲጥ ያደርጋቸዋል፡፡— ምናለ በለኝ"

"ያልገባኝ ኮ—"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ቆይ እኮ— አየህ በስልጣን ላይ ካሉ ስማ ቸው በሬዲዮ መነገር፣በጋዜጣ ላይ መውጣት አለ በት:: በቴሌቭዥን መታየት አለባቸው:: ጡረታ ከወጡ ግን – አዲዮስ::— ስማቸው ባይጠራም የት ሄዱ የሚል ሰው አይኖርም:: ለምንስ ይጠይ ቃል?"

ይህን መቀበል ለኔ ከባድ ሆነብኝ:: መንግስ ቱን የማውቀውን ያህል ይህን ያህል የሚሰራ አልመሰለኝም:: ስለዚህም— "አይመስለኝም" አል ኩት "ምክንያቱም መንግስቱ አንተም እኔም እን ደምናውቀው ለመግደል ፈርቶም ገደልኩ ለማለት አፍሮም አያውቅም::... አየህ መንግስቱ የመግ ዛት እጣ ወድቆበት እንጂ የመግዛት ጥበብ የሚ ባል ነገር የለውም:: ጠላቱን በድብቅ ሲጥ የሚያ ደርግኮ ብልህ መሪ ነው!" ስል ተናገርኩት::

"አይምሰልህ – አሁን ታክቲኩን እየለወጠ ነው:: ሰውየው እየተለወጠ ነው" አለኝ::

ከሁለት ቀን በኋላ መንግስቱ ለገሠና ፍስ ሐን፤ ፍቅረስላሴ ወግደረስን አፍኖ የት እንዳደ ረሳቸው አይታወቅም የሚል ወሬ ነፈሰ:: – ስስ ወሬ ነበር:: –

"አላልኩህም!"

"ግን እኮ ዋጋ የለውም:: ሠራዊቱ ሞራሉ ውድቅድቁ ከወጣ ከተበተነ በኋላ—ሽር ይሰሩ ነበር ቢባል'ንኳ የነሱ መሞት ዋጋ የለውም:: መንግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስቱም በስልጣን ላይ አይቆይም፤ ወያኔ መግዛቱ አይቀርም፤ ኤርትራም ከመገንጠል አትድንም—"

"ልክ ነህ!... ግን... ግን እንደተጫወቱብን ሊቀሩ—"ገባኝ:: ሀገር ማዳን ሳይሆን በቀል ነው፤ ስል አሰብኩ፤ በቀል ነው::መንግስቱ ደግሞ መሪ ሳይሆን አርጩሜ ነው:: — የበቀል አርጩሚ ነው::

ግንቦት አሥራ ሦስት መንግስቱ ኃይለማ ርያም ከስልጣን ወርዶ ሀገር ለቆ ወጣ:: በዚያ ሣምንት የአዲሳባ ስጋት መደንዘዝ ወጣ ብሎ መንቀሳቀስ ጀመረ::— ህዝቡ ለመመሸግ ዝግጅ ቱን ተያያዘው::

ፀጥተኛውን ሽርጉድ ስመለከት አንድ ሚካ ኤል አንጀሎ ስእል ትዝ አለኝ::የጥፋት ውሃን የሚያ ሳይ ሥዕል ነው::አገር ሁሉ ውሃ በውሃ ሆኗል::አንድ ሰፋ ያለ ቋጥኝ ገና አልሰመጠም:: እላዩ ላይ ብዙ ሰዎች ሰፍረውበታል::— ስለጠበ ባቸው ቆመው እርስበእርስ ተያይዘዋል፤ አንዲት መቆ ሚያ ነጥብ የለችም::ግን ገና እቋጥኙ ላይ የሚንጠላጠሉ አሉ::— ወደ ቋጥኙ የሚመጡም ይታ ያሉ::—መቼም ድንቅ ስዕል ነው::ያን ስዕል ሳይ— እስከመቼ?— የሚል ጥያቄ ነበር የተሰማኝ::

የአዲስ አበባ ገበያ መራቆት ጀመረ::— በሁለት ቀን ውስጥ ዋጋ ጨመረ::
"ፓስታ ይኖራል?" ትላለህ::
በመጀመሪያ ትጠናለህ — ከዚያ —



t.me/OLDBOOKSPDF

“ሰባት ብር – እሸጉ”
የሚል መልስ ይሰጥሀል
“የቱ?
“እሸጉ – ”

“አምስት መቶ ግራም?– ምነው ትናንት– ማለት ከትናንት ወዲያ አራት ከሃምሣ ገዝቼ!”

“ሰባት ብር”–

ይህ ሐሙስ'ለት ነው፡፡ ዓርብ'ለት አሳላፊውን ጠርቼ – ፓስታ እንዲገዛልኝ ጠየኩት (ሀይለኛ ጨጓራ በሽታ ስላለብኝና ስለተነሳብኝ ፓስታ ነው የምበላው ሰሞኑን)



t.me/OLDBOOKSPDF

# አዳም ረታ
(1950 _ )



አዳም ረታ በ1950 በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ:: በትምህርት አለም- በጂኦግራፊ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተቀብሏል::ሁለተኛ(የማስተርስ)ዲግሪውን ደግሞ በውጭአገር አግኝቷል::

የሚፅፈው በአብዛኛው አጫጭር ልቦለዶችን ቢሆንም ግጥሞችንም ይፅፋል:: ከዚህ ቀደም በተለያዩ መፅሔቶች ላይ ግጥሞቹ ታትመዋል:: ያልታተሙ ግጥሞችም አሉት::

አጭር ልቦለዶቹን በተለያዩ መፅሔቶች ለአንባቢ አቅርቧል:: በመፅሐፍ – ከሌሎች ደራሲያን ጋር "አባደፋርና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች" በሚለው የአጭር ልቦለድ መድበል ውስጥ ሥራዎቹ ለህትመት በቅተዋል::ከዚያም በ1981 በግሉ "ማህሌት" የተሰኘውን የአጭር ልቦለድ መድበል አሳትሟል:: ከዚህም ሌላ ብዛት ያላቸው ያልታተሙ አጭር ልቦለዶችና ግጥሞች አሉት:: ከአዳም ረታ ያልታተሙ አጫጭር ልቦለዶች መካከል ዘላን ለዚህ መድበል ተመርጧል::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዘላን

ተሻለ አደፍርስ በግንቡ ላይ በእጆቹም፣
በእግሮቹም እየቧጠጠ ወጣና አንድ ክንድ ያህል
ወደ ጐን ስፋት ያለው ቦታ አግኝቶ ተጋደመ፡፡
አጠገቡ የቆሙት የዕድ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸውን
እያወናጨፉ ባሌ የሚደንሱ ሎጋ መናፍስት ይመ
ስላሉ፡፡ የግንቡ ቅዝቃዜና ሽካራነት በአንድ ጎኑ
አላስተኛ አለው፡፡ በሆዱ ተንጋለለና ፊት ለፊቱ
ተመለከተ፡፡ በአጥሩ በር መግቢያ ዳርና ዳር የተ
ተከሉት የደረቀ ዕንባ የሚመስሉ መስታወት የለ
በሱ አምፑሎች ጨለማ ውስጥ ጥቁር ካባ ተሸ
ፍኖ ብቻውን እንደሚሳብ የጋኔን ዐይን ያበ
ራሉ፡፡

ሙቅ ፈሳሽ ከልቡ ሥር ወደ ሆድቃው በቀ
ጭኑ የሚንጠባጠብ መሠለው፡፡ አይኖቹ እንባ
አፈለቁ፡፡ ከጓደኞቹ ጋር ተሰባስቦ የሚያወራው
የሠይጣኖች ታሪክ ትዝ አለው፡፡ ምናልባት ከአ
ጥር ግቢው ውስጥ ረዥም ጥቁር ነገር በቀስታ
እየተራመደ በሚያቃጥል ጅራፍ ጀርባው ላይ
ቢገርፈውስ? ቁጭ አለ፡፡ ከሁዋላው መጥቶ ቢገፋ
ውስ? ቆመ፡፡ ዙሪያውን በፍርሃት እየዞረ ተመለ
ከተ፡፡ ፀጥታ ብቻ ነው፡፡ ቡናና ቃጫ ጭነው
የሚያልፉ ከወልቂጤ የሚመጡ የጭነት መኪና
ዎች ብቻ ይሰማሉ፡፡አንዳንዴ ውሾች ይጮኻሉ፡፡
ተመልሶ ተጋደመ፡፡

ርጥብ የጥቅምት ሌሊት ከእንቅልፉ ቀሰቀ
ሰው፡፡እንደ ማንኛውም ቀን ፀሐይ የምትወጣበት



t.me/OLDBOOKSPDF

የምሥራቅ ሰማይ ነጥቶአል፡፡ ልብሱ በጫዛ ረጥቦ አል፡፡ዙሪያውን ቀና ብሎ አየ፡፡ቤቶች በየቦታው ሲከፈቱ ድምፅ ይሰማል፡፡ አንዳንድ ማድቤቶች ይጨሳሉ፡፡

እንደራበው አወቀ፡፡

ከተቀመጠበት ግንብ ወርዶ እግሩ ወደጣለው መሄድ ጀመረ፡፡

ቤቱን ከሩቅ እያየ ቆመ፡፡ የፊት ለፊቱ በር አልተከፈተም፡፡ ነጭ ጢስ ከቤቱ ጓሮ ይፈል ቃል፡፡ ትኩስ ሻይና ዳቦ ማግኘት አለበት፡፡ ወደ ቤቱ ጓሮ በቀስታ እርምጃ ሄደ፡፡ እናቱ ምድጃ ዳር ተቀምጣ ሻይ ታፈላለች፡፡ ትኩስ ድንቾች በነጭ ሳህን ላይ ተቀቅለው እንደ ዕንቁሉት ይትጎለጎላሉ፡፡

ፊቱን በጨረፍታ እያሳያት ቆመ፡፡

"የት አደርክ?"

ዝም፡፡

"ሆድህን ልትሞላ ነው የመጣኸው አይደ ለም?"

ክርኑን አከከ፡፡ ዐይኖቹ ተቅለበለቡ፡፡ የሚመ ልሰው ጠፋው፡፡ ሳትረበሽ ፊቷን ዞር አርጋ አየ ችው፡፡እሱም በዐይኑ ትክ ብሎ አያት፡፡ በመደ ናገጡ፣ ዕርዳታ በማጣቱ የሳቀችበት መሠለው፡፡ እየሮጠ ወጣ፡፡ በእግሩ-ወደ መርካቶ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘርፍጥ ብላ ተቀምጣለች፡፡በእጣን ሽታ የታ ፈነው ቤት ወይ መቅደስ ወይ የዛር ሴቶት ያስ ታውሳል፡፡ ከእስዋ ፊት ለፊት ነጫጭ ነጠላ የተ ከናነቡ ቤቶች እግሮቻቸውን ወደ ፊት ዘርግተው የተረጨ ፈንድሻ መስለዋል፡፡

"ልጅሽ የት ሄደ፤ አሁንም አትቆጭውም?"

"ስንት ጊዜ ልቆጣው፡፡ ሴት ሆኜ እንደአባት ደብዳቤ ነው!"

"ትምህርት ቤት ለመሆኑ ይሄዳል?"

"ለወር ያህል ይሒድ አይሂድ አላውቅም"

"እኔ የምልሽ ጋሼ አለማየሁ ያሉትን ልንገ ርሽ...መቼም..."

"ሰምቼዋለሁ እባክሽ ተሻለ ሰረቀ ቢሉ እኔ አላምንም፡፡ አሁን የሚበላው አጥቶ ነው?"

"ምን አረገ?" አሉ ሌላኛዋ ሴት ወፍራም ጣቶቻቸው መሀል ጥንግ ካከለችው ስኒ ርጥብ ፊኛ በመሰሉ ከንፈሮቻቸው ቡና እየሳቡ፡፡

"የጋሼ አሰፋ ሚስት ከገበያ መጥታ ዘንቢሏን እግሯ ሥር አስቀምጣ ኩሊ ስትጠራ 'አለሁ' ብሎ መጣ፡፡"

እናቱ ነገሩ እንዳልጣማት ፊቷን ጭፍግግ አረገች፡፡

"'የሚያሳዝን ነው፤አንተ የቡርቱካን ልጅ አይ ደለህም' ብትለው 'አይደለሁም' አላት፡፡ 'አይ



t.me/OLDBOOKSPDF

አውቅሃለሁ ባለኔ...ምን የምትበላው አጣህ?' ብት ለው 'አይደለሁም ምን አገባሽ' ብሎ ድርቅ፡፡ 'አይ ዞር በል፤ ደግሞ ልጄን አሸከምሽው ተብዬ ስሜ ይነሳ!' ብላ ሌላ ለመጥራት ስትከጅል ከገዛ ችው ፓስታ አንዲት ወረቀት ይዞ ሮጠ፡፡"

"ምን ሊያደርገው?" አሉ አንዷ አሮጊት ድር ጊቱ ሳቅ ፊታቸው ላይ አምጥቶባቸው፡፡

"ሆቴል ሄዶ በርካሽ ሸጦ ፓስታ በላበት፡፡ ይኼን እንኳን የነገረኝ ልጄ ነው" አለች፤ ያስደ ነቀ ወሬ እናቱ ፊት እያዘነች ማውራት በመቻሏ ኩራት ተሰምቶአት፡፡ ጆሮዎቿ ላይ ያንጠለጠ ለቻቸው ሎቲዎች ጕንጮቹዋን ይገርፉሉ፡፡የቀይ እጅዋ ጀርባ ላይ ድፍን ክብ ንቅሳት ተጠቁራ ለች፤ —ጎራዳ ሴት፡፡ ጫማዋን አውልቃ እግሯን ጉያዋ ከተተች፡፡ በአቀማመጧ ተደስታ ይሁን ድካምዋ ቀንሶላት ከልብዋ ተነፈሰች፡፡

"ለአስተማሪዎቹ መንገር ነው፡፡ለመሆኑ ይማ ራል?" አሉ ወፍራሙዋ አሮጊት ከስኒው ሥር የቀረውን የስኳር ደለል እንጋጠው እየጠጡ፡፡

"ምን ያርጉ እነሱ፡፡ የገዛሁዋት ደብተር ትሸ ጣለች፤ በበነጋታው እርሳሱ አንድ ቀን አያድር፡፡ ዕብድ እኮ ነው፡፡የት እንደሚያድር አላውቅም፡፡ አስተማሪ ይመልሰዋል እሱን?"ለራስዋ ከንፈርዋን መጠጠች— ብርቱካን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሱን ለማስተካከል ጀርባው ላይ ያልጨረሰ ኩት ባህር ዛፍ የለም"

"እንደገና ደግመሽ ንገሪ፤ ለዲሬክተር ቢሆን ይሻላል"

"ከገዛሁለት አምስት ደብተሮች ያቺ ናት የቀረችው" አለች ልባስ የሌላት በቁመቷ ለሁለት የታጠፈች ደብተር እያሳየቻቸው።

"እኔ የማድረው የኪራይ ገንዘብ እየለቀምኩ ነው። እሱ ደሞ እንደአባቱ እርኩስ ነው" ልቅሶ እንደሚጀምራት አይነት ንግግርዋን አቁማ ራስዋን ደፋ አረገች።

"ሁለተኛው ቡና አልደረሰም?" አሉ ወፍራሟ ሴት አርዕስት ለመለወጥ– እንዳልደረሰም ቢያውቁ።

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ነገሠ። የተሻለ እናት ሁለተኛ ትንሽ ልጅዋ እየሮጠ መጥቶ እግርዋ ሥር ተቀመጠ።

ወፍራሙዋ ሴት አዲስ የተላጨ ጭንቅላቱን አርዕስት አርገው ለማሳቅ ሲሉ፥

"ይሕቺ እናትህ ናት እንደው ዳግመኛ እንዳ ይበቅል አርጋ ከሥሩ የላጨችህ? ቁንጮም አታስቀር?" አሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ከአርዕስት መራቁ ወሬውን የሚገለው የመሰላት ጎራዳዋ ሴት ብቻዋን አኩርፋ ነጠላ ዋን መዳበስ ጀመረች፡፡

"ነገ ደግሜ እነግራለሁ ለትምህርት ቤቱ፡፡ ከዚያ በሁዋላ ይበቃኛል፤ እንደሆነው ይሁን"

"ልጅ ይሳሳታል ... ልጅ ካላጠፋ ደግሞ ... ያውም ወንድ ልጅ"አሉ ወፍራምዋ ሴት በተከፈ ተው በር ወደ ውጭ እያዩ፡፡

"የሱ አቻ የለውም ኧረ! ሲወለድ አሰጨን ቆኝ፡፡ አሁን ደግሞ ያቃጥለኛል፡፡ ማን ይሙት አሁን ሳልታገስ ቀርቼ ነው?" አለች እናቱ ጀበና ውን የፈላ ውሀ እየሞላች፡፡

አንድ ጥላ ሞት በቀስታ እየተሳበ መጥቶ በሩ አጠገብ ቆመ፡፡ ብርቱካን ጭንዋ ላይ የተቀ መጠ እስዋን የሚመስል ሁለተኛ ልጅዋን አቅፋ ለች፡፡ ጠይምዋ ሴት አንገታቸውን ቀና አርገው የአደፍርስን ፎቶ ግራፍ ይመለከታሉ፡፡ከባድ ሳቅ ይስቃል፡፡ አምስት የሚደርሱ የፊት ለፊት ጥር ሶቹ ሀጫ በረዶ መስለዋል፡፡ የእሳት አደጋ ልብ ሱን እንደለበሰ ነው፡፡እንደመሰጣት ሁሉ ለረዥም ጊዜ አይንዋን ከሰውየው አልነቀለችም፡፡

"የድሮ ባልሽ ቆንጆ ነበር" አለቻት፡፡

"ያንሳው እቴ ... ይኼን ሰጠኝ ሄደ...ከፋት... እንደ እሱ ከፋት፡፡በማን ወጣ ቢሉ ይኼ-



t.me/OLDBOOKSPDF

በአባቱ” አለች ፎቶግራፉንም ለማየት ቀና ሳትል፡፡

"አሁን የትነው ያለው?"

"እንጃ አባቱን"

"ተጣልታችሁ ነው? ወይስ ምንድን ነው?"

"አንቺ ደግሞ ምንድነው ያለፈ ነገር እያነሳሽ የምትጨቀጭቂአት፡፡እንዳው እኮ እናንተ ... አሁን ምን ይባላል" አቋረጧት ወፍራምዋ ሴት፤ ውይይታቸው ወደማያምር ጭቅጭቅ እንዳይለወጥ፡፡

"አንቺስ የማንሽ?" አለች ጠይምዋ ሴት አሳንብሳ ወደ አቀፈችው ሕፃን ልጅ ጉንጩን ለመንካት አመልካች ጣትዋን አሹላ፡፡

"ኦ ሆይ!" አሉ ወፍራምዋ ሴት ቀደም ሲሉ ያቋረጧት የዳይሬክተሩ ጉዳይ ተመልሶ እንዳይመጣ በመፍራት በብስጩ አባባል ነገሩን መግታት ፈልገው፡፡

ሴትዬዋ የደነገጠች ያፈረችም አልመሰለች፡፡

"እንዴ ማነህ አንተ?" አሉ ወፍራምዋ ሴት በር አጠገብ ሳይነቃነቅ ወደ ቆመው ጥላ እየተጣሩ፡፡

ተሻለ ፊቱን ብቻ አሳይቶ ወደ ሁዋላ ተመለሰ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ና...እንዴ ና እንጂ ምን ትፈራለህ?" አሉ አሮጊቷ ከተቀመጡበት ለመነሳት ምድርና አየር እየጨበጡ፡፡

"ልጅሽ ተሻለ ነው" አሉ ወፍራምዋ ሴት፡፡ መቅረቱን ሲያዩ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ እሱ ሄዱ፡፡

"ና ልጄ...ና ቤትህ አይደለም?" ራሱን እ.ያ ሻሹ እጁን እየጐተቱ አስገቡት፡፡ እናቱ ደብቃው የነበረ ቂጣዋ ገነፈለባት፡፡

"አንተ ደሞ ዞር በል!" እምቦሳ ልጃን ከላ ይዋ ላይ አንስታ ወለል ላይ አስቀመጠች፡፡

"ተይ አንቺ ደግሞ አትቆጪው" አሉ ወፍራ ምዋ ሴት የገፅዋን ሁኔታ አንብበው፡፡

"የት ጠፋህ የት አደርክ፡፡ ደሞ ዛሬ የሚባ ላም አውሬ የለም?" አለች እናት፡፡

"ተይ እንጂ አንቺ...እንዴ? ሕፃን ነሽ እንዴ! ከልጅ ባስሽ፡፡ና ልጄ፣ምሳህን እስክትሰጥህ ከዚህ ቡና ቁርስ ቅመስ" አሉት፡፡ ወንበር ላይ አስቀም ጠው በስፌት ላይ ደረቅ የስንዴ ቂጣዎች አምጥ ተውለት፡፡

"አትናገርም ... የሆዱማ ነገር ይሆንልሃል፡፡ የት አደርክ?" መብላት የጀመረውን ዳቦ የሚ ቀማ ስለ መሰለው እንደምስጢር የደበቀውን ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ማውጣት ነበረበት፡፡ከተናደደች ደግሞ ተመሳሳይ ነገር ሊደርስበት ይችላል፡፡

ዝም አላት፡፡ አፉ ውስጥ የከተተውን ጉርሻ ማላመጥ አቆመ፡፡ ጉሮሮው ደረቀበት፡፡

"እዩኝ እንግዲህ … ትንኮል ነው ይሄ አይደ ለም?"

"ተይው በቃ አንቺ፡፡ብላልኝ ልጄ" አሉት አፋቸውን ለማባበያ አሞጥሙጠው እየተናገሩ፡፡
"የት አደርክ አትናገርም?"
"እ … እ …" መናገር ፈራ፡፡
"እሺ በል" በጉጉት፡፡
"እሳቸው ቤት" አለ ወደ ወፍራምዋ ሴት እያየ፡፡
"እንዴት … እኔ ቤት?" አሉ በመገረም
"ማታ ኩሽናችሁን ከፍቼ ገብቼ … "

እጃቸውን አገጫቸው ላይ አስደግፈው በሃዘን አዩት፡፡እናቱ በንዴት በእፍረት ፊቷ ሲቀላ ይታ የዋል፡፡ ስፌቱ ላይ የቀረችውን ትርፍ ዳቦ በሌላ እጁ አንስቶ ያዘ፡፡

እናቱ አጠገቧ የነበረ አንድ ስኒ በእሱ አቅ ጣጫ ወረወረች፡፡ አንገቱ ላይ አገኘው፡፡

ከተቀመጠችበት ተነስታ ልትይዘው ወደ እሱ ተንደፋደፈች፡፡ከእጁ የተፈናጠረውን ቂጣ አንስቶ ወደ ውጭ ወጣ፡፡ ወፍራምዋ ሴትና ጓደኛቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

በድንጋጤ ባሉበት ፈዘው ቀሩ፡፡ እናት የአደፍ ርስን ፎቶግራፍ ከተሰቀለበት ምስማር ላይ አው ልቃ በሩጫ ተከተለችው፡፡

"የእዚህ ሽንት አይደለም መጀመሪያውኑስ... እ ... እ ጠብቀኝማ አንተ አንተን ሳልገል"

የቤቷ በረንዳ ላይ ስትደርስ አጥር ውጭ ደርሶአል፡፡ በእሱ አቅጣጫ፣ አምዘግዝጋ ወረወ ረች፡፡ ለጭቃ መከለያ ግቢው ውስጥ የተደለደለ የድንጋይ መንገድ ላይ ተሰባበረ፡፡

አይኗ ውስጥ የበቀለው ጥላቻ ቤቱ ዙሪያ ተንዘረፈፈ፡፡ የሰዎቹ መኖር ትዝም አላላት፡፡ አሮጊቶቹ ተከትለዋት ወጡ፡፡

ተሻለ አልነበረም፡፡ የተዘበራረቀ ነጠላዋን እያስተካከለች ተመልሳ ገባች፡፡

...ከሃያ አመት በፊት እንዲህ እንደ ዛሬ ፊቷ የግራር ቅርፊት ሳይመስል ከዚህ ልጅ አባት ጋር ተጋባች፡፡ የእሳት አደጋ ሰራተኛ ነበር፡፡ እዚህ አሁን አለችበት ቤት ሰርቃ ለማከራየት ከመም ጣቷ በፊት ምግብ ቤት ነበራት፡፡

ኮንትራት በወር እየከፈላት የሚመገብ ደንበ ኛዋ ነበር፡፡

ምግብ ቤቷን ከሰራች ጀመሮ ሓሳብዋ ሌላ ቦታ ሄዶ አያውቅም፡፡ ሽሮ ማገንፈሉን፣ ምስር



t.me/OLDBOOKSPDF

መክካቱን፣ ጠላ መጥመቁን፣ ውሐ መቅዳቱን ርቃ እጅና እግሯን አቅፋ ገንዘብ ለማግኘት የሚከ ራይ ቤት ለመስራት ነበር– አላማዋ፡፡

እያንዳንዲቱን ሳንቲም ወደ ሳጥንዋ ወይም ወደ ባንክ ትወረውራለች፡፡ ከተመደበው በላይ ሺህ ደንበኛ ቢሆን አንዲት ጭልፋ ወጥ አትጨ ምርም፡፡ ትንሽ የሚጐዳ ስህተት ገረዷ ስትሰራ ብታያት አንገትዋን ይዛ ትሞህባታለች፤ ወይም ከስራዋ ታስወጣታለች፡፡ ከወንዶች ጋር ፍቅር እንዳትሞክር የእስዋ ምግብ መወዳኛ እንዳይሆን ትጥራለች...

"አይ ይሐ ምግብ ቤት እንጂ መዳሪያ አይ ደለም–" በቁጣ ሳይሆን በሳቅ፡፡

"አንቺ ነይ እስኪ ወደዚህ ይሐ ..." ገረድዋ ወደ እስዋ ስትመጣ፤

"ይሐ ማዕድ ዙሪያ መላፋቱን መሳሳቁን ተይ አላልኩሽም፡፡ ሁለተኛ ልይሽ ..." ከጨለማ ጓዳ ብቅ ብላ ሰዎቹን እያየች፤

"ብሉ እንጂ ይጨመራል...በዚህች ሽንኩርት ገዝተሽ ነይ"

"እለ እኮ እትዬ"

"ግዢ አልኩሽ ግዢ" ደምበኞቿ መጠራቷን በሌላ እንዳይጠረጥሩ መላክዋን ልታሳያቸው –



t.me/OLDBOOKSPDF

"በዚህ ነይ እንጂ... በሰዎቹ በኩል ያስፈራል እንዴ?" ወደ ሰዎቹ እየሄደች-እንዲሰምዋት፡፡

እስዋ ሳታውቅ ግን እሳት አደጋ ጣቢያው ውስጥ አንድ የወሲብ ጀብደኛ እሷን ማሳሳት እን ደሚችል ተወራርዶአል፡፡

ብረት ባርኔጣውን በብብቱ ይዞ-

"እንዲህች አይነት ሴት ቀላል ናት" አለ፡፡ አጭር ቁመና አለው፡፡ አፍንጫው ስር የተከረ ከመች ሽንጉበት አለችው፡፡ ተላጭቶት ሁለት ሳምንት የሚሆን ፀጉሩ ያብለጨልጫል፡፡ ዐይኖቹ በቅንድቡ ትልቅነት ተሸፍነው በአይኑ ፈንታ የሚታየው ጥቁር የጉን ቀዳዳ ነው፡፡ጉራውን ተና ግሮ ሲስቅ በሰውነቱ ሙሉ የተሸከመው ወፍ ራም ስጋ ተንቀጠቀጠ፡፡

"የሚቀጥለውን ወር እቁብ ካልቻልኩ እከፍላ ለሁ ከቻልኩ ትከፍላለህ"

የዚህችን የእቁብ ውርርድ አልሰማችም፡፡

ቅዳሜ ማታ የኩልፌ የእህል በረንዳ ከቀን ትርምስዋ ስትፀዳ አንድ የጂን ጠርሙስ ይዞ እቤቷ ሔደ፡፡በዚያን ሰዓት የሚገለገል ሰው ስላል ነበር ተዘግቶአል፡፡ በር አንኳኳ-ግራ ሳትጋባ አል ቀረችም፡፡ ከጥቂት ዝምታ በኋላ ማንነቱን ጠየ ቀች፡፡

"ማነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ አደፍርስ ነኝ"

"እንዴ በዚህ ሰዓት ምነው ... እንደምዘጋ እያወቅህ" ተከፍቶለት ገባ፡፡

"እራቴን ልበላ ነው የመጣሁት-" በወረቀት እንኳን ሳይሸፍን ብብቱ ሥር እያሞቀ የያዘውን ጂን ተሸክሞ ዘወትር ወደ ሚመገብበት ወንበር እየሔደ፡፡

"ቢያልቅስ" አለችው፡፡

"ትንሽ ሽሮም ቢሆን አፍይልኝ እኔ ሥጋ ውን አላሰኘኝም፡፡ ሌላ ቦታ አጣሁኝ፡፡ አንቺን ከማስቸገር ብዬ አንድ ምግብ ቤት... የሚበላ እኮ አይደለም ያው አንቺ ትሻይኛለሽ ብዬ መጣሁ፡፡ ሰራተኛሽ ባትኖርም ላስለፋሽ፡፡ የእኔ እህት-" ልመና ለማስመሰል በልምምጥ እንደሚጠይቃት እያረገ፡፡

ትዕቢቷን ስላበለፀገላት ወደ ጓዳዋ ገባች፡፡ አንዳንዴ ብቻ ለሚጠይቃት እየመለሰችለት ቆዩ፡፡

"ለመሆኑ አረቂውን ለምን ያዝከው?"

"እረቄ አይደለም ጂን ነው" አለማወቋዋን ሊነግራት፡፡

"ጂንም ይሁን አረቄ ለምን ያዝከው?"

"ምን እባክሽ..."ዝም አለ፡፡

"ምን አልከኝ?"

"ምን ያረግልኛል" አላት፡፡

"እስከዚህ ከባድ ነገር ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"መናገር አፍሬ ነው"
"ምን የሚያሳፍር ነገር አለው፡፡"

"አንዲት ጓደኛዬ አለች፡፡ ከእስዋ ጋር ተቃጥሬ ነበር እጋብዝሻለሁ ብዬአት-" ከሰል ምድጃዋ ጋ ተቀምጣ ቅር ያለው ፊቷን ወደ እሱ አዞረች፡፡ አላያትም፡፡

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ፡፡

የሬድዮኑን የዘፈን ሳል የሚያሸንፍ የሚቁላላ ሽንኩርት ድምፅ ይሰማል፡፡ የከሰል ምድጃዋን ይዛ ወደ ሳሎን መጣች፡፡

"እንዳልተኛ አረግሽኝ" አለችው፡፡
"መቀመጥ ከደከመሽ ትራስሽን አምጭና ምድጃሽ አጠገብ ጋደም ብለሽ ስሪው" አላት፡፡

የምትጠቀምባቸውን እቃዎች በሙሉ ከጓዳዋ አምጥታ ምድጃው ዙሪያ ደረደረቻቸው፡፡ ለወጥ ስራ አንዳንዴ ብቻ የምትጠቀምባቸው ቅመሞች፣ ቁሳቁሶች ሁሉ አልቀሩም፡፡

"ምንድነው ይሔ ሁሉ"
"ወጥ እኮ ነው የምሰራው" አለችው፡፡

የጂኑን ጠርሙስ ወደ አፍንጫው ወስዶ አሸተተና እነበረበት መለሰው፡፡
"እሱ ነገር ያው አረቄ ነው፡፡ አይደለም?" አለችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"የ·ተለየ ነው።ይሔ ከፈረንጅ አገር የሚመጣ ነው።...የአማርኛ ዕሉፍ እንኳን የለውም"አላት። ቅመም መበተን፣ በርበሬ መርጨት፣ ድስቷን ማማሰል ቀጠለች። ጠርሙሱን ከፈተው።

"ምነው?" አለችው።

"ትንሽ ልጠጣለት" አላት ብርጭቆ ወደተደረደረባቸው ቡፌ እየሄደ። ትልቅ ብርጭቆ አንስቶ ሊቀዳበት ሲል-

"መለኪያው አይሻልህም?"አለችው።
አንድ መለኪያ ይዞ ሄዶ እነበረበት ተቀመጠ።

ባትጠጣም ለስላሳ መጠጥና ጠላ ብቻ ይሸታት የነበረች ቤትዋ ጅን ስለገባባት ብርቱኳን ደስ ተሰኘች።

"በሁዋላ ሰክረህ እንዳትረብሸ" አለችው በሳቅና--በቀልድ።

"ይሔ!" አላት ጮክ ብሎ "ይሔ እኮ አያሰክርም ... የአገራችንን ዳግም አረግሽው እንዴ? ለምን አትሞክሪውም ብርቱካንዬ" ቁልምጫውን እንዳልሰማች ሁሉ ድስቷን በኃይል ማማሰል ቀጠለች።ራሱ ተነስቶ ሔዶ ሌላ መለኪያ ሞልቶ ሰጣት።

የአመልካች ጣትዋን ጥፍር ነክራ ላሰቻት። ለመቅመስ የአጠጣጥዋን ስልት ሞራል ለመስበር



t.me/OLDBOOKSPDF

አፉን በርግዶ በሳቅ ተንዘፈዘፈ፤እንደ ጅል ዐይ ንዋን አቁለጨለጨች፡፡

አሁንም በኃይል ማማሰል ቀጠለች፡፡

"እንዴ ጠጪው እንጂ" አላት እየሳቀ፡፡ መልስ አልሰጠችውም፡፡

የራሱን መለኪያ ይዞ ወደሚነደው ከሰል ቀረበ፡፡

"ምንም ጨርቅ ብደራርብ ብርዱ አልለቀኝ አለ"

ከሰሉን እያራገበች ቀና ብላ አየችው፡፡ መለኪያውን በእጁ አንስቶ እየሰጣት÷

"እጮኛዬ ትቆጣኝ እንጂ እንደ እናት ለም ታበላኝ እህቴ ጂን ጠርሙሴን መከፈቴ አይ ቀር" አለ፡፡

በር ከፍቶ ወደ ውጭ ወጣ፡፡ ሲመለስ የካፖ ርቱ ቁልፍ ተከፍቶአል፡፡

"የት ሔደህ ነው?" አለችው፡፡

"ሽንቴን ልሸና" አላት ጠረጴዛ ላይ ያስቀ መጣትን መለኪያ ጨልጦ ሌላ እየቀዳ፡፡ ያጋመሰ ቻትን መለኪያ ሞላላት፡፡ አልተግደረደረችም ...



t.me/OLDBOOKSPDF

ራት ሲደርስ አብረው ከበሉ በሁዋላ በስካር እንደ ደከመ ሁሉ እጅዋን ያዛት...

ተሸክሞ መኝታ ቤቱ ሲወስዳት ከማልቀስ በስተቀር ምንም አልተናገረችም...

ሰኞ ጠዋት ስራው ሲመለስ እቁቡን እንዲከ ፍል ጓደኛውን ጠየቀው፡፡

አንድ ወር ያህል አብረው ቆዩ፡፡ ፀነሰች፡፡ ተሻለን ፀነሰች፡፡ የእሳት አደጋውም ሰው እንደለ መደው በየመንደሩ የተዳፈኑ ፍም ሴቶችን ለማ ቀጣጠል እስዋን ዘንግቶአት ተሰማራ፡፡

አምስት ዓመት እዚያ አካባቢ ከነገደች በሁ ዋላ ጎፋ መጣች– ከልጅዋ ጋር፡፡ እያደገ ሲሄድ መልኩ ሁሉ እሱን መሰለ፡፡ አደፍርስ ከሌላ ሴት ጋር ተቃቅፎ ባለችበት መንገድ ሲያልፍ – እን ደማያውቃት ሁሉ የሚሰራው ስራ ትዝ እያላት የወለደችለትን ጠላችው፡፡

የሕይወትን ትብትብነትና ሸር እያወቀች ስት ሔድ በዚያች ዕለት ምሽት የሰራት ስራ ሁሉ ተንኮልና ማስመሰል እንዳለበት ስታውቅ አንዳ ንዴ ታለቅሳለች፡፡

ቤት እያከራየች መኖር ስትጀምር የልጅዋን ት/ቤት ርዕሰ መምህር ውሽማ አድርጋ ያዘች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ትናንትና ት/ቤት ዴስክ ላይ ተኝተህ ... እንደሌላ እንደሚያስቆጥርህ አታውቅም?" አለው ዳይሬክተሩ በቁጣ እያየው።

ሌሎች ሁለት አስተማሪዎች ርዕሰ መምህሩ ጠረጴዛ ፊት ለፊት የብረት ወንበሮች ላይ ተቀ ምጠዋል።ተሻለ ከእነሱ ራቅ ብሎ ግድግዳ ጥግ ቆሞአል።

ርዕሰ መምህሩ መላጣ ነው። ሉጫ ፀጉሩን ከሁዋላ ጎትቶ በማበጠር ግንባሩን ለመሸፈን ሞክ ሮአል። ከቀጭን ጠፍጣፋ የፀጉር ጣውላ ሥር የጭንቅላቱ ቆዳ አልቦታል።

"አትናገርም?"አለ ደገመና ሁለት ክንድ ርዝ መት ያለው እንደ መግረፊያ የሚያገለግለውን ቀጭን የመኪና ጎማ ቁራጭ እያወዛወዘ።

"ማደሪያ የለኝም"

"እናትህ ከእስዋ አልፎ ለሌሎች ማደርያ ትሰጥ የለም?"

"እፈራለሁ" አፍንጫውን እያከከ።

"ምን ያስፈራሃል?" አለ ሌላው አስተማሪ ዐይኖቹ ሸውራራ። መሬት ሲያይ ጣሪያ የሚ ያይ፣ ጣሪያ ሲያይ መሬት የሚያይ የሚመስል። ትልቅ ፍልስፍና እንደተናገረ ሁሉ እናቱን አመ ልካች ጣቱ ላይ አስደገፎ፥



t.me/OLDBOOKSPDF

"የጠፋኸው ከሌለ ምን የሚያስፈራህ አለ?"

"ይሔ የማይሰራው የለም፡፡ባለፈው ጊዜ ..." ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ልጁ ሄደ፡፡

አይኖቹ ተቅለበለቡ፡፡ እጆቹን አንድ ጊዜ እግሩ መሃል ያደርጋል፤ አንዴ ራሱን ያከባቸ ዋል፡፡

የርዕሰ መምህሩ ረኻርም ሰውነት እላዩ ላይ የወደቀበት መሠለው፡፡ ማልቀስ ጀመረ፡፡

"ደብተሩን ይሸጣል!" አለ፡፡ ወደ ጠረጴዛው ሔዶ ጉማውን ለመውሰድ፡፡

"አል-ተ-ገ-ዛ-ል-ኝ-ም"

"ደብተር ተሸከመህ ትመጣ የለም ት/ቤት-በፊት" አለው ሶስተኛው አስተማሪ በስካር ብዛት የተጣመመ የሚመስል ፊቱን፣ የደፈረሰ ዐይኑን እያገለባበጠ፡፡
"የእኔ አይደለም"
"ታዲያ የማነው?"
"የልጆች፣ የጓደኞቼ ነው"
"እንዴት?" አለ ዳይሬክተሩ፡፡
"ኪራይ...ስሸከምላቸው እንዳጠናበት ያውሱ ኛል"

ሰካራሙ በተደነቀ አይነት አንድ ጊዜ አስተ ማሪውን ሌላ ጊዜ ርዕሰ መምህሩን አይቶ፡-



t.me/OLDBOOKSPDF

"እናትህ ጠዋት መጥተው እንደሚገዙልህና በትክክል እንደሚያስተምሩህ ነው የተናገሩት፡፡" የርዕሰ-መምህሩንና የእናቱን ወዳጅነት ያውቃል፡፡ ለእሰዋ ለምን እንደሚያደላ አልገባውም፡፡

ከሚቁለጨለጩ ለማኝ አይኖቹ ዕንባ ፊቱን ሰንጥቆ ወረደ፡፡

"ለመሆኑ ባለፈው ሴሚስተር እንዴት ነው ማርክ...እየው እስኪ" አሉ ወደ ሆምሩም ቲቸሩ (ወደ ሰካራሙ) ዞር ብለው፡፡

"ስምህ ማነው አንተ?"አለው ሰካራሙ ቲቸር በላዩ፡፡ ተሻለ ከተቀመጠበት ተነስቶ የተማሪዎች ሪፖርት ካርድ ወደሚቀመጥበት ሄደና በላስቲክ ገመድ የታሰረ ጥራዝ ይዞ መጥቶ ስሙን መፈለግ ጀመረ፡፡

"ማን አልከኝ?...ተሻለ?"

ሪፖርት ካርዱን ገልጦ ራሱ ሲያነብ ቆይቶ
"አማርኛ = 65
እንግሊዘኛ = 78
ታሪክ = 82"

"ዝም በል ተወው በቃ ..." አሉ ዳይሬክተሩ ሪፖርት ካርዱን ከአስተማሪው ነጥቀው ወደ ጠረጴዛው በመወርወር እየመለሱ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ደብተር ከሌለው ... እቤቱ አድሮ የማያጠና ይሔንን ማርክ የሚያገኘው ኮርጆ መሆን አለበት ... ወይም አንተም ዞሮብህ ስትደምር ተሳስተህ ይሆናል" አሉቸው ዳርና ዳር ምራቃቸው ደርቆ የሻማ ቅራፊ መስሎአል፡፡

ቲቸር በላይ ስለተወረፈ በእፍረት ተሻለንና ሌላውን አስተማሪ እያየ በአረቄ የተመሳለጠ ከንፈሩን ነከሰ፡፡ መልስ አልሰጠም፡፡

"ውጣልኝ አሁን" አሉ ጮክ ብለው ክፍሉ ውስጥ ያሉት በሙሉ እስኪረበሹ ድረስ፡፡ "ዳግመኛ ስለአንተ ነገር እቤቱታ ብሰማ ከትምህርት ቤት ትወጣታለህ" አሉት፡፡

አንገቱን በፍርሃት ሰብሮ ከክፍሉ እየሮጠ ወጣ፡፡ የአሥራ አንድ ሰዓት ፀሐይ ፊቱ ላይ አበራች፡፡ አባራማ ፊቱን ሰንጥቀው ያለፉት የእንባ ጠብታዎች የሰሩት መስመር ጠቆር ብሎ ይታያል፡፡

ወደ ኮቶኒ አካባቢ ጉዞውን ጀመረ፡፡

"ተሻለ መጣህ!" አሉት አንድ ሽማግሌ አዲሱን የግንብ መኖሪያ ቤት የሚያቆሙት የቀን ሠራተኞች አባት የሚሏቸው፡፡

"አዎ!አባት"አላቸው ድምፁን ዝቅ አድርጎ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀና ብለው አዩትና "ለምን ዘገየህ?... ሰዎች ሁሉ ወደየቤታቸው ሄደዋል... ራትህ እዚያ ዘንድ አለልህ ብላ፡፡ሂሳቡን በሁዋላ አብረን እናሰላለን" አሉት፡፡

ያጋጠመውን ሊነግራቸው አልፈለገም፡፡ራቱን ለመብላት በር አጠገብ ቁጭ አለ፡፡

"ዕቃዎቹን እኔ አስገባልዎታለሁ እርስዎ ይተኙ" አላቸው፡፡

'አባት' የሚቆረቆረው አዲስ ቤት የሚሰራበት ዕቃ እንዳይዘረፍ ቤቱ ጀርባ የቆርቆሮ መጠለያ ቆምላቸው የሚጠብቁ ዘበኛ ናቸው፡፡ አንድ ቀን ሊነጋጋ አካባቢ በማያርፍ የዘበኛ እግራቸው በግ ቢው ውስጥ ሲመላለሱ የሲሚንቶ ክርታስ አን ጥፎ ተኝቶ ያገኙታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከተ ሻለ ጋር ይተዋወቃሉ፡፡ ለቀን ሰራተኞች እያፈሉ የሚሸጡትን ሻይና ዳቦ ሂሳብ እያሰበላቸው አብ ረው ይኖራሉ፡፡

"ሰማህ ተሻለ እኔ ከዚህ አካባቢ ሌላ ቦታ እንደው ማለቴ ከዚህ ትምህርት ቤት ርቄ ብሔድ ትመጣለህ?"የጦር ሠራዊት ብርድ ልብስ ውስጥ ተጠቅለው ተቀምጠው፡፡

ጉንጩን የሞላው ዳቦ አላናግር ስላለው ራሱን ብቻ በአዎንታ ነቀነቀ፡፡ እንደበፊቱ ብቻ ቸውን ጨረቃ ላይ አያፈጡም፡፡ ብቻቸውን የኮ ሽታ ምንጭ ለመፈለግ ጓሮና ስርቻ አይገቡም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ብቻቸውን የሲሚንቶ ቀረጢት ለቅመው ጉልትና አውቶቡስ ማቆሚያ ሄደው አይቸገሩም፡፡ የሚወ ዱት እንጉርጉሮአቸው ለባዳ አየር አይጮህም፡፡

ሲመሻሽ ስሌታቸውን ጨርሰው በትርፋቸው ከረኩ በሁዋላ እንደለመዱት በር ላይ ቆመው መንገደኛ ለመመልከት፣ መኪና ለማየት ሲመጡ ተሻለ እቤት ቀረ፡፡

ከደብተሩ ወረቀቶች ቀዶ መጻፍ ወደሚያካ ክሉ ትናንሽ ወረቀቶች ሸነሸናቸው፡፡ መማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉትን የዴስኮች ብዛት በአእም ሮው አሰላስሎ የሲማንቶ መያዣ ቀረጢት ከሚ ሰራባቸው በርብርብ ከተጠረዙ ወረቀቶች ያልተ በላሹትን እየቀደደ እያወጣ ከከረመ በሁዋላ እላያ ቸው ላይ መፃፍ ጀመረ፡፡

'አባት' አልጋ ላይ ወገባቸውን ለማሳረፍ ሲመጡ ቁጭ ብሎ ሲፅፍ ያገኙታል፡፡

“እንዴ ዛሬስ አላበዛኸውም?” አሉት፡፡ማንበብ እንደሚችሉ ወደሚጽፍበት ወረቀት አጉንብሰው እስከርቢቶው ያተማቸውን ፊደሎች እየተመለ ከቱ፡፡

በጥዋት ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡ ክፍሉ ውስጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ዴክስ ላይ አንዳንድ ወረቀት አስቀምጦ ወጣ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የትምህርት ጊዜ ሲጀመር፣ ደወል ሲደወል ተማሪዎች መግባት ጀመሩ፡፡እሱ ከሁሉ መጨረሻ ግን ከአስተማሪው ቀደም ብሎ ገባ፡፡

በክፍሉ ውስጥ ትርምስና ሳቅ ጢም ብሎ አል፡፡

"ምንድነው?" አለው አጠገቡ የሚቀመጠውን ብዙ ጊዜ በሸክም ኪራይ ደብተር የሚያውሰውን ልጅ፡፡

"እየውማ ይኼን ተፅፎ አገኘን" አለው፡፡ከሲሚንቶ ቀረጢት የተቀደደ ወረቀት እያሳየው፡፡

ቀድሞ እንዳልተመለከተው ማንበብ ጀመረ፦

*ማስታወቂያ*

*የዳይሬክተሩ መላጣ ያስጠላል፡፡ የቡርቱካን ውሽማ ናቸው፡፡*

*ቲቸር በላይ ሰካራም ናቸው፡፡የኮታቸው ኪስ ተቀዳዶአል፡፡*

*ሆምሩም ቲቸራችን አይናቸው በመንሸዋረሩ ያስጠላሉ፡፡*

አስተማሪው በር በርግደው ሲገቡ የክፍሉ ዕርጭታ ተረብሾአል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ብጫቂ ወረቀቷን፣ይዘው ሳቅ ይለዋወጣሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ሆናችሁ?" አሉ ወደ ጥቁር ሰሌዳው እየሄዱ። አንድ አይናቸውን ጣሪያው ላይ አንድ አይናቸውን ተማሪዎች ላይ አርገው።

ተሻለ አጠገብ የሚቀመጠው ልጅ በወረቀቱ ላይ ስላነበባቸው ነገሮች አስተማሪው ምንም ባለ መረዳት የሚያረጉት ንቅናቄና በድብቅ መደፈራ ቸው ሳቅ አስመለጠው።

ሰው ሁሉ እሳቸውን ሲያይ በሸውራራነታቸው የሚስቅ የሚመስላቸው አስተማሪ ፊታቸውን ቁጣ ቀብተው ወደ ልጁ ተጠጉ።

"ምን ያስቅሃል?" አሉት።

ከተወሸቀበት ዴክስ ወደ ላይ አንጋጦ በፍር ሃት አይኑን አቁለጨለጨ። ዝቅ ብለው እጆቹን ሲያዩ ብጣሽ ወረቀት ላይ የተፃፈ ጽሑፍ ተመለ ከቱ። ከልጁ አደነጋገጥ ያሳቀው ጉዳይ እዚያ ውስጥ መሆኑን ጠርጥረው ተጭኖ የያዘበት እጁን አንስተው ወረቀቷን ወሰዷት። ተማሪዎች ደነ ገጡ።

ጀርባቸውን አዙረው እያነበቧት ስለሄዱ ተማ ሪዎች የሆምሩም ቲቸራቸውን ስሚት ማወቅ አል ቻሉም። ወረቀቷን ኪሳቸው ከተው ዞር አሉ።

"ማነው የፃፈው?"—ተሻለ ጓደኛ ላይ አፍ ጠው።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ አንጃ ... እ ... እዚህ ጠረጴዛ ላይ ነው የገኘሁት" አለ።

ወደተሻለ ቁጣቸውን አቦሩ። ተሻለ አልተረበሸም።

"እኔ እንደውም ሲያዩ ነው የመጣሁት... አር ፍጁ ነው" አላቸው።

"ደሞ ... ሁሉም ጠረጴዛ ላይ ነበር" አለ ልጁ። ንዴታቸውን ውጠው በተመሰቃቀለ አይናቸው ሲያዩት ቆዩና "ተውት በቃ መገኘቱ አይ ቀርም..." አሉ። ከተቀመጡበት ተነስተው ቾካቸውን ይዘው ወደ ብላክ ቦርዱ ዞረው መፃፍ ጀመሩ።

## መልመጃ

1. የዩኒቨርስቲው ዳይሬክተር ለማዳ ውሻ አላቸው።
2. ከሰካራም ሰው ቁም ነገር አይጠበቅም።
3. ሆሜር እውር ከመሆኑም በላይ ፈላስፋ ነበር።
4. ሚስት ያላገባ ሰው ውሽማ መያዙ አይቀርም።
5. የሸዋረገድ የኮት ኪስ ቀዳዳ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

6. ሕፃናት የሚያስጠሉት ሰው ከሰው በላይ አይደለም፡፡
7. የዕድራችን ዳኛ ቲቸር መስፍን ናቸው፡፡

(ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች ባለቤትና ተሳቢውን ለይ)

"ለፈተና የሚደመር ስለሚሆን አስባችሁ ስሩ" ብለው ተቀመጡ፡፡

መማሪያ ክፍሉ ውስጥ የተፈጠረው ውጣ ውረድ ከስሞ ተማሪዎች መልመጃቸውን ለመስራት አገነበሱ፡፡

የመልመጃውን ጥያቄ ገልብጠው ጨርሰው መልስ መስጠት ሳይጀምሩ አስተማሪው እየከሩ ወረቀቱን ሰብስበው ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አሉ፡፡ አሩብ ሰዓት ያህል ተደፍተው የተማሪዎቹን ፅሑፍ ከተበተነው ወረቀት ጋር ሲያስተያዩ ቆይተው ተሻለ ላይ አፈጠጡ፡፡

ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የቆዳ አለንጋ ይዘው ወደ ተሻለ መቀመጫ ሄዱ፡፡ ተማሪዎች ሁሉ ፊታቸውን ወደ እሱ አዞሩ፡፡

"አንተነህ አይደል የፃፍከው?"

ዝም አላቸው፡፡ወደ ላይ አንጋጦ እያየ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ውጣ!" አንገቱን ይዘው ክፍሉ ፊት ለፊት አቆሙት፡፡

ለቅሶ እንደሚከጅለው ሁሉ አፉን እያንቃነቀ አስተማሪውን ማየት ጀመረ፡፡

"አትሰማም...ደንቆሮ ነህ? አንተነህ የፃፍከው አይደለም?"

"አዎ!"

የቆዳ ጅራፍ ጀርባው ላይ እየደጋገመ ወደቀ፡፡ አላለቀሰም፡፡

"ዱርዬ ... አንተ መቼ ይሰማሃል ... ዳይሬክተሩ ጋ ነው መውሰድ" ብለውት እያዳፉ ይዘውት ወጡ፡፡

"ይሔ ለራሱም፣ ለቤተሰቡም፣ ለአገርም አይሆን" አሉ ዳይሬክተሩ-ለአስተማሪው፡፡

የሰጣቸውን ወረቀት ካነበቡ በሁዋላ የጉማ አለንጋቸውን እያመቻቹ በእጃቸው ጠሩት፡፡

"እጅህን፣እጅህን" አለ ሌላው አስተማሪ የጀርባው መገረፍ በደንብ ያልተሰማው መስሎት፡፡

"እጅህን ዘርጋ፡፡" የጨው ውሃ ውስጥ ተዘፍዝፎ የደረቀ ጥቁር ጨርቅ እስኪመስል ገረፉት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ውጣ" አሉት ዳይሬክተሩ እርግጫ ሰን ዝረው፡፡

በድርጊታቸው የተገረመ የመሰለው አስተማሪ አስተሳሰቡ ፊቱ ላይ እንዳይታወቅበት ቶሎ ብሎ—

"ለእንደዚህ አይነቱ ልጅ ቤተሰቡን አልሰማ ካለ፣እኛን አልሰማ ካለ ማታ ተማሪዎች ከመበተ ናቸው በፊት ተማሪው ፊት ይቅርታ እንዲጠይቅ እናደርጋለን"አላቸው፡፡ በብስጭት ማዕበል ውስጥ ሆነው ሊያስተምርና መንፈስን ሊቀጣ የሚችለ ውን ይህን ዘወትር የሚጠቀሙበትን ጥበብ ቀዝ ቀዝ ብሎ ሲቀማቸው ሲሰሙት ተበሳጭተው ለጥ ቂት ጊዜ ተከራከሩት፡፡

"ምን እንዲህ አይነቱ ሲኦል ምድጃ ዳር አስ ቀምጠው ልገፋህ ነው ይቅርብህ ቢሉት አይተ ውም፡፡ እሺ አንተ ሸውራራ ነህ እሽ እንትናም ሠካራም ነህ፡፡ ... የእኔ ለእናቱ ውሽማ መሆን ምን አመጣው? ... ከየት አየው ... አሁን ይሔ ለአገሩም አይጠቅም ... ለራሱም አይሆን ...እንደ አባቱ ነው ያረገኝ... አባት ለዚህ? ... አሁን እን ዴት ይሁን? ... " ከወንበራቸው ተነስተው እየተ ንጐራደዱ፡፡

"አስተማሪዎችን ስለሰደበ አስተማሪዎች ይቅር እንዲሉት፣ የጓደኞቹን አስተማሪዎች በመ ጥሮ በመጥራቱ ተማሪዎችን ይቅር እንዲል፡፡..."



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩ ጥሩ ቢመስልም አንዲት ክፍል ውስጥ የተፈፀመውን አንድ ሺ የሚሆኑ ተማሪዎች እን ዲሰሙት ማድረግ ወሬውን ማስፋት መሰላቸው፡፡

"ወሬው የሚዛመት መስሎዎት ፈርተው እንደ ሆነ እሱ አይቀርም" አላቸው፡፡

"ማን አለህ እሱን፡፡ እኔ የማስበው ሌላ ነበር፡፡ ይህች ሀገር እንዲህ አይነቱን ንፍጣም የምታሳድግ ከሆነ የት ነው...የምትደርሰው? ንጉሰ ነገስቱም የሚለፉት እንዲሁ ቀረ እኮ ማለት ነው" አሉና "ልክነዎት!" የሚል መልስ ከአስተ ማሪያቸው ጠብቀው ሲያጡ —

"ማታ እንዳትረሳ...ተማሪዎች ቀድመው ከክ ፍል ይውጡ" አሉት፡፡ ወንበራቸው ላይ ተቀም ጠው በወፍራም እጃቸው መጨፍለቅ የለመደ ብዕራቸውን አነሱ፡፡

ከአንድ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪ ዎች በሙሉ ወጥተው ሰንደቅ አላማ መስቀያው ፊት ለፊት ተሰልፈዋል፡፡

ቲቸር በላይ በሰልፉ መስመር ፊት ለፊት ተሻለን እየጐተቱ አውጥተው አቆሙት፡፡

ሁለት፣ ሶስቴ አጨብጭበው የተማሪዎች ጫጫታ ረጭ ሲል ንግግራቸውን ጀመሩ፡፡—



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኛ እዚህ ትምህርት ቤት የምንመጣው ለመማር ነው፡፡ለሌላ አይደለም፡፡ ቤተሰቦቻችንና አገራችንን ንጉሰነገስታችንን ለማገልገል ነው፡፡ ነገር ግን ከሰንጴ መሃል እንክርዳድ እንደማ ይጠፋ ሁሉ ጨዋ ተማሪዎች መሃልም ባለጌዎች አይጠፉም፡፡ (ተሻለ አንገቱን ደፋ፡፡ ፊት ለፊቱ የቆሙት ተማሪዎች ሁሉ እሱ ላይ አተኮሩ፡፡) አስተማሪ ባይወልድም አባት ነው፡፡ ከእውቀት ምግብ ከእውቀት ማእድ ያበላል፡፡ አንድ አትክ ልት ተኮትኩታ እንደምታድግ ሁሉ እሱም ተማ ሪዎችን ይኮተኩታል፣ ውሃ ያጠጣል፡፡

"ነገር ግን አንዳንድ ባለጌዎች (የአስተማሪው የመናገር ስሜት እየጋለ ሲሔድ በልጆቹ ፊት ላይ የመመሰጥ ስሜትም ይታያል) ዱርዬዎች ማለት ይሻላል ቤተሰባቸውን ከማስቸገር አልፈው ትምህርት ሳይከታተሉም አስተማሪዎቻቸውን ይሰ ድባሉ፡፡

"ተማሪ ተሻለ እውቀት የሚሰጡትን አስተ ማሪዎች አንዳንዶቻችሁ በተለይ ፋይቭ— ኤ ያላችሁ ሳትሰሙ አትቀሩም ተሳድቦአል፡፡ ይሔ ንን አስነዋሪ ስራ እሱም ይሁን ሌሎች ይመሰክ ራሉ... (ተማሪዎች እስኪሰለቻቸው ድረስ ንግግራ ቸውን ቀጠሉ)"

(አንጴ አስተማሪውን አንጴ ተሻለን እያፈ ራረቁ የሚያዩት የተማሪዎች ጥንድ አይኖች ለመጨረሻ ጊዜ ተሻለ ላይ አረፉ)



t.me/OLDBOOKSPDF

ቲቸር በላይ አለንጋቸውን እያነሱ እግሩ ላይ፣ ጀርባው ላይ፣አንገቱ ላይ ይጥሉ ጀመር፡፡

ተሻለ ማልቀስ ጀመረ፡፡ የአስተማሪው የመግ ረፍ ስሜት እያደገ ሔደ፡፡ተሻለ ሲበዛበት መሬት ላይ ቁጭ አለ፣የሚያቃጥለውን እጁን፣እግሩን፣ አንገቱን እያከከ፡፡

"ይለምድሃል?" አሉት ዳይሬክተሩ በቆሙበት የባንዲራ ምሰሶ አጠገብ፡፡ የልቅሶው ሲቃ 'በል' ላሉት ቃል መልስ ለመስጠት ትንፋሽ አልሰ ጠውም፡፡

"ይለምድሃል?" አሉት ደግመው፡፡ ከተቀመ ጠበት በግድ ጐትተው እያቆሙት፡፡

"አይለምደኝም!" አለ፡፡ ዛሬ የሚከዳው ግን እሱን የማይሸሸው የነገው ሁኔታ ትዝ ብሎት ማልቀስ ጀመረ፡፡
"ጮኸ በል!"
"አይለምደኝም! አይለምደኝም!"...

ዳይሬክተሩ ባንዲራ ማውረጃውን መዝሙር በመዘመር ተማሪዎችን መምራት ጀመሩ...

*ደሙን ያፈሰሰ ልቡ የነደደ*
*ባርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ...*



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰልሰቱ ቀለማት በሰንደቁ ላይ ቁልቁል በቀስታ ሲንሸራተቱ የተሻለ ልቅሶ ጩመረ–የተማሪዎች የጩኸት ድምፅ ገነነ፡፡

ለተሻለ ሰቆቃ ማንም ጆሮ አልነበረውም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ደምሴ ፅጌ

(1948 –   )



ደምሴ ፅጌ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋና ሥነ ጽሁፍ የባችለር ድግሪ አግኝቷል::

ደምሴ በመጀመሪያ በመምህርነት ቀጥሎም በቱሪዝም ኮምሽን በሚዘጋጅ በዜና ቱሪዝም ጋዜጣ በረዳት አዘጋጅነት አገልግሏል:: ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ከተዛወረ በኋላ የዛሬይቱ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል::በአሁኑ ሰዓትም የአዲስ ዘመን ዋና አዘጋጅ ሆኖ በመስራት ላይ ይገኛል::

ደምሴ ከጋዜጠኝነቱ በተጨማሪ “ፍሊጋ” የሚባል ኖቬላ ደርሶ አሳትሟል:: እንዲሁም “ትንግርት” ና “ጠብታ ማር”(ከባሴ ሀብቴ ጋር) የተሰኙ ትርጉሞች አሉት:: ደምሴ ፅጌ ከኖቬላ ወጥ ድርሰቱና ከትርጉም ሥራዎቹም ሌላ አጫጭር ልቦለዶችንም ይጽፋል:: ጥቂቶቹ በተለይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትመው ለንባብ በቅተዋል:: በዚህ የአጫጭር ልቦለዶች መድበልም “ማን ያውቃል” የተሰኘው አጭር ልቦለዱ ይገኛል::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ማን ያውቃል?

ነገሩ የተጀመረው በለጠና ዘቢባ ሊጋቡ አንድ ወር ብቻ ሲቀራቸው ነው፡፡ አንድ ቀን በለጠ በድንገት ከአጋሮ መጣ፡፡ ገና ሳየው ደነገጥኩ፡፡ ብዙ ተለውጧል፡፡ ያ ደስ የሚል ወዛም ጥቁረቱ አመድ ለብሶ ፊቱ ገርጥቷል፡፡ ለሳምንታት እህል ሳይቀምስ የተኛ በሽተኛ መስሏል፡፡ አይኖቹ በጣም ከመቅላታቸው የተነሳ ነጭና ጥቁር መሆናቸውን መለየት አይቻልም፡፡ በለጠ እንደወትሮው ስንገናኝ ሞቅ ያለ ሰላምታ አልሰጠኝም፡፡

"ታዲያስ ደህና ነህ?"ብሎ ነው ቁጭ ያለው፡፡

"ምነው ምን ሆነሀል?" ብዬ ጠየቅሁት በድንጋጤ፡፡

"ምንም አልሆንኩ!"አለኝ ግንባሩን ጨምደድ አድርጎ፡፡

"ደህና አይደለህም እንዴ?" ስለው የባሰ እንደ መቆጣት አለና፥

"ምን አየህብኝ!" ብሎ አፈጠጠብኝ፡፡

ያንዳንድ ሰዎች ፊት በውስጣቸው የሚሰማቸውን ስሜት ለመደበቅ አቅም የለውም፡፡ ነገሩን ለይቶ ባያሳውቅ እንኳ ከውስጥ ያለውን የስሜት መነካት አውጥቶ ያሳያል፡፡ የበለጠ ፊት የዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይነቱ ነው፡፡ ሲደሰት፣ ሲያዝን፣ወይም ሲናደድ በቀላሉ ይታወቅበታል፡፡ ከፊቱ ላይ የሚታየውን ነገር በቀላሉ አንብቤ ስለምደርስበት በለጠ ከኔ ምንም መደበቅ አይችልም፡፡ አሁን ግን በጣም ተለውጧል፡፡ በውስጡ እየፈላ ሲገነፍል የተቃረበ ውን ስሜት አፍኖ ለመያዝ ይታገላል፡፡ ግን አል ሆነለትም፡፡

ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለን ተያየን፡፡ሲጋራ አው ጥቶ ለኮሰና ጭሱን በሃይል ወደውስጥ ማግ ማግ እያደረገ፣ ከኔ አልፎ ጣራ ጣራውን ይመለከት ጀመር፡፡ የሚያስጨንቀው፣ ግን ሊነግረኝ ያልፈ ቀደው ነገር እንዳለ ተሰማኝ፡፡

"ምንድነው? ለምን አትነግረኝም?" ብዬ ጠየ ቅሁት፡፡

"ምን እነግርሀለሁ?ምንም አልሆንኩ አልኩህ! ምንም አልሆንኩ!"

"ዝግጅቱ እንዴት ነው?አንድ ወር ብቻ እኮ ነው የቀራችሁ፡፡"

"ልደግስም ላልደግስም እችላለሁ"

"ምን ማለትህ ነው?" ደነገጥኩ፡፡ ከሳምንት በፊት ስለሰርጉ ዝግጅት በጉጉት ሲያወራኝ የነበ ረው በለጠ፤ከሳምንት በፊት የሚያጅቡትን የመኪ ናዎች ብዛት ሲቆጥርልኝ የነበረው በለጠ፤ ደጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግሞ ደጋግሞ አደራ አደራ ይለኝ የነበረው በለጠ፤ እንደዚህ ሲናገር አስደነገጠኝ፡፡

"ምን ተፈጠረ?"

"ለፍቅርም ሆነ ለትዳር መተማመን ያስፈል ጋል፡፡"

"ታዲያ – ታዲያ በዘቢባ ላይ ይህን እምነት ሊቀንስ የሚችል ምን ነገር አጋጠመህ?" አል ኩት፡፡

"ዝም ብሎ ሲጋራውን ይምግ ጀመር፡፡

"በለጠ ለምን አትነግረኝም? ምን የሰማኸው ነገር አለ?" በማለት ጠየኩት በድጋሚ፡፡ ብድግ ብሎ ወጣ፤ መልስም አልሰጠኝ፡፡

በለጠ ድንጉጥ ነው፤ አንድ ነገር ሲሰማ ወይ ያምናል ወይ አያምንም፡፡ የነገሩን እውነትነት ወይም ሀሰትነት ለማጣራት የሚሞክረው በኋላ ነው፡፡ በዚህ ጠባዩ ብዙ ጊዜ ያፍርበታል፤ ስህተ ቶችን ደጋግሞ ከፈፀመ በኋላ ነው ራሱን ወይም ሌላውን ይቅርታ የሚጠይቀው፡፡

ይህን ነገር ማስወገድ አለብኝ ሲል ዘወትር እሰማዋለሁ፡፡ ግን ደጋግሞ ሲናገረው እንጂ ሲያ ስወግደው አላየሁም፡፡ ድንገት ፈራሁ፡፡ የነገሩን ምንነት ሳያጣራ አንድ ነገር ቢያደርግ ቢያንስ ቢያንስ የሁለት ሰው ህይወት መበላሸቱ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በፍጥነት ልብሶቼን ቀያይሬ በለጠን ፍለጋ ወጣሁ:: ከቤቱ አላገኘሁትም፤ ከናቱም ቤት ብሄድ አጣሁት:: ታክሲ ይዤ ወደ እነዘቢባ ቤት በረርኩ:: እዚያም የለ:: ዘቢባንም አላገኘኋት:: ግራ ገባኝ:: ይህን ሰው ምን አገኘው?

በለጠና ዘቢባ የረጅም ጊዜ ፍቅረኞች ናቸው:: ዛሬ ቀለበት አስረው ለጋብቻ እስከደረሱበት ድረስ ብዙ መሰናክሎችን አልፈዋል::ብዙ ጊዜ ተጣልተው፣ብዙ ጊዜ ታርቀዋል:: ብዙ ጊዜ ተለያይተው እንደገና ተገናኝተዋል:: በመጨረሻው ተለያይተው መኖር የማይችሉ መሆናቸውን ካመኑበት በኋላ ነው ሊጋቡ የቆረጡት::

ለጋብቻቸው መፍረስ ዋናው መንስኤ ከእነሱ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ነበር:: በለጠ የክርስቲያን ልጅ ነው:: ዘቢባ የእስላም:: የሁለቱም ቤተሰቦች የጋብቻቸውን እቅድ ሲሰሙ አሻፈረኝ ብለው ተነሱ::

"እንዴት ልጃችን ክርስቲያን ታገባለች? ተበላሸች! ሀራም ነው!"

"እንዴት ልጃችን ሙስሊም ያገባል? ረከሰ" ብለው እሪ አሉ::

በመጨረሻ በለጠ እዘቢባ ቤተሰቦች ዘንድ ሲሄድ ሙስሊም ሊሆን፤ ዘቢባም እሱ ቤተሰቦች ዘንድ ስትሄድ ክርስቲያን ልትሆን ከተስማሙ



t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ሰላም ወረደ፡፡ የበለጠ እናትማ ዘቢባን ዘነ በች ብለው መጥራት ያዙ፡፡

በለጠ ዘቢባን ምን ያህል እንደሚወዳት አው ቃለሁ፡፡ ጆማ በነበረበት ጊዜ አንድም ቀን ሳያ ያት የዋለ እንደሁ ያቁነጠንጠዋል፡፡ከሥራው እን ደወጣ ልብሶቹን ቀያይሮ፣ ሁለት እጆቹን እኪሱ ከቶ እያፏጨ ወደ ዘቢባ ይሮጣል፡፡ሲኒማ ቤት፣ ኳስ ሜዳ፣ መናፈሻ ቦታ፣የትም የትም ሲሄድ ዘቢባ ከጐኑ አትለይም፡፡ እጓደኞቹ ቤት ለካርታ ጨዋታ ሲሄድ እንኳ ዘቢባ ተለይታው ከቀረች በሙሉ ልቡ አይጫወትም፡፡የትም ቦታ እሷ ከሌ ለች በራሱ ሙሉነት ተማምኖ አይቀመጥም፡፡ ዘቢባ በሌለችበት ቦታ ሁሉ ቀልቡ አይኖርም፡፡

ዘቢባም እንደዚሁ ነች፡፡ አንድ ቀን ሳታየው የዋለች ለት ትረበሻለች፡፡ መምጣት በሚገባው ሰዓት ሳይመጣ የቀረ እንደሁ ሱቁን ለእህቷ አስ ረክባ በለጠን ፍለጋ ወደቤቱ ትገሰግሳለች፡፡እዚያ ባታገኘው የጓደኞቹን ቤት ሳታዳርስ ተመልሳ ከቤቷ አትገባም፡፡

በለጠ በዘቢባ ምክንያት ይህን ያህል ሲና ደድ አይቼው አላውቅም፡፡ ምን ሰማ? ለወትሮው ምስጢሩን ደብቆኝ አያውቅም፡፡ ለምን ሳይነግረኝ ቆየ?

ፈልጌ ስላጣሁት ከመናፈሻ ገባሁና ቡና አዝዤ ቁጭ አልኩ፡፡ የበለጠ ሁኔታ በጣም አሳሰ በኝ፡፡ ዛሬ ለሰርጉ በሚዘጋጅበት ወቅት፣ ከአንድ ወር በኋላ የሚወዳትን ልጅ ሙሉ በሙሉ የራሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

አድርጐ ደስታው ፍጹም በሚሆንበት ወቅት ምን አጋጠመው? ምን አይነት ሰይጣን በመሀከላቸው ገባ? ጠንካራ የሆነውን ማህበረሰባዊ ግድብ ጥሶ ከዚህ ደረጃ የደረሰውን ፍቅር ማን የጥርጣሬ መርዛማ ፍሬውን ዘራበት?ላውቀው አልቻልኩም።

የኬቶ ወንዝ ምንም ሳያግደው ፀጥ ብሎ ቁል ቁል ይፈሳል። ፍቅርም እንደወንዝ ውሀ ነው። ምንም እስካልገባበት ድረስ ሳይደፈርስ ፀጥ ብሎ ወደ ፍቅረኞቹ ይፈሳል። አንድ ነገር የገባበት እንደሆነ ግን በቀላሉ ሊደፈርስ ይችላል። ... አርፎ መቀመጥ አልቻልኩም።ይህን ነገር ማቆም አለብኝ።

በለጠ የሚያዘወትራቸውን ቡና ቤቶች ሁሉ አዳረስኩ። ላገኘው አልቻልኩም።ተሰፋ ቆርጬና ደክሞኝ 'ጅማ ሆቴል' ቡና ለመጠጣት ስገባ ተስፋ ዬን አገኘሁት። ገና ሲያየኝ እንደመደንገጥ ብሎ ግንባሩ ላይ የተለያዩ ስሜቶች ተፈራረቁበት። ሰላም ብየው ተቀመጥኩ።

"በለጠን አላየኸውም?" ብሎ ጠየቀኝ።
"እኔም እሱን ነበር የምፈልገው የት ገባ?"

"በአስራ ሁለት ሰዓት ቀጠሮ ነበረን" ብሎ ሰዓቱን ተመለከተ።

"አስራ ሁለት ተኩል ሆኗል። እዚሁ ነበር ቀጠሯችን"



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሁኔታው የበለጠን ነገር ሳይሰማ እንዳልቀረ ተጠራጠርኩና፣ "ምንድነው የሆነው? ዛሬ ጤነኛ አይመስለኝም?" ብዬ ጠየቅሁት፡፡

"ምን እባክህ በጣም የተወሳሰበ ነገር ነው፡፡"

"እንዴት?"

"የልጅቷን ነገር አልሰማህም እንዴ?"

"የዘቢባን?"

"አዎ የዘቢባን፡፡ሳትጫወትበት የቀረች አይመስለኝም፣"

"ምን ማለትህ ነው? ምን አደረገች?" ስለው ሳቅ ብሎ ተመለከተኝ፡፡

"ሌላ ወንድ ይዛለች ተብሎ ነው የሚወራው፡፡"

ሳቂ መጣ፣ ተናደድኩም፡፡ ዘቢባን አውቃታለሁ፡፡ እንዲህ አይነቱን ነገር፣ ለዚያውስ ሊጋቡ አንድ ወር ሲቀራቸው? የምታደርግ ልጅ አይደለችም፡፡ በበለጠ ተናደድኩበት፡፡ ለኔ ሊነግረኝ ያልቻለውን ሚስጢር ትናንት ላገኘው ጓደኛው በመንገሩ አዘንኩበት፡፡

"በዚህ ነው ይህን ያህል የተበሳጨው?"

"እንዴት እንደ ቀላል ነገር ታየዋለህ?"አለኝ ተስፋዬ፤ ወደፊት ያገጠጡ ጥርሶቹን በምፀት ፈገግታ እያሳየ፡፡ "እንዴት እንደዚህ ትላለህ?



t.me/OLDBOOKSPDF

ምንነቷን ሳያውቅ ቢያገባት ህይወቱ ተበላሽቶ መቅረቱ ነው እኮ፡፡"

"ከተገናኙ አመታት አልፈዋል" አልኩት በን ዴት ከንፈሮቼ እየተንቀጠቀጡ፡፡ "ዘቢባና በለጠ የተዋወቁት ትናንት አይደለም፡፡"

"ብዙ ጊዜ አብሮ መቆየት የሰዎችን ምንነት ጨርሶ ሊያሳውቅ አይችልም፡፡"

"አዎ" አልኩት በውስጤ የተቀጣጠለው ቁጣ ሊገነፍል እየተናነቀኝ፡፡

"አዎ!ቢሆንም በለጠ የዘቢባን ምንነት ማወቅ የሚገባው አሁን አይደለም፡፡ ደግሞም ያውቃ ታል፡፡በደንብ ስለሚያውቃት ነው ሊያገባት ቃል የገባው" ስለው ተስፋዬ ሳቀብኝ፡፡

"ሰውን" አለ ተስፋዬ "በተለይም ሴቶችን እድሜ ልክህን እንኳ አብረሀቸው ብትኖር መቶ በመቶ አውቃቸዋለሁ ማለት አትችልም፡፡ ዛሬ ይሄ ነው ያልከውን ሰው ነገ ሌላ ሆኖ ልታገኘው ትችላለህ፡፡"

ቁጣዬ እየጨመረ ስለሄደ መልስ ልሰጠው አልቻልኩም፡፡

"ታዲያ-ታዲያ ዘቢባ ሌላ ወንድ ይዛለች፤ እርግጠኛ ነኝ ነው የምትለው?!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደዚያ አላልኩም፡፡ እርግጠኛ ባልሆንም እጠራጠራለሁ፡፡"

ተነስቼ ሳንቀው ምንም አልቀረኝ፡፡ የሰራ አካሌ ተንቀጠቀጠ፡፡ ተስፋዬ ሳደርገው ያሰብኩ ትን ከሁኔታዬ የተረዳው ይመስል ወዲያው ለወጥ ብሎ ቀዝቀዝ አለ፡፡ ፊቱ 'በቃ ተወው' በሚል አይነት ፈገግታ ተሞላ፡፡

"መቼም እኛ ያለብን የጓደኞችን የወደፊት ኑሮ እንዳይበላሽ ማድረግ ነው፡፡ በተቻለን ሁሉ ልንረዳውና ከጐኑ ልንቆም ይገባናል" አለኝ፤ ምንም አልመለስኩለት፡፡ ትንፋሽ አጥሮኝ ዝም አልኩት፡፡ካንድም ሁለቴ – ሶስቴ 'ሰይጣኑ አንተ ነህ፣በመሀከላቸው የገባህ!' ልለው ቃጥቶኝ ነበር፡፡ የቀዘቀዘውን ቡና አንስቼ ስጨልጠው ነው ትንሽ ጋብ ያለልኝ፡፡

"ዘቢባ እንዲህ ታደርጋለች ብዬ አላምንም፡፡ ለዚያውስ ከማንጋ?ጅማ ትንሽ ከተማ ነች፡፡ ዛሬ እሷ ከሌላ ወንድ ጋር ብትወጣ ወሬው ወዲያው ነው የሚሰማው፤ ይሄ ሁለቱን ለማለያየት በተለ ይም ሰርጋቸውን ለማበላሸት ሆን ተብሎ የተወራ ወሬ ነው፡፡"

"ቢሆን ደስ ይለኛል" አለና ተስፋዬ የሁለት ቡና ሂሳብ ከፍሎ 'ቀጠሮ አለብኝ' ብሎ ጥሎኝ ወጣ፡፡ ከነበርኩበት ሳልነሳ ረዘም ላለ ጊዜ ተቀ



t.me/OLDBOOKSPDF

መጥኩ፡፡ ብዙም አሰብኩ፡፡ የነገሩ መንስኤ ግን ሊታየኝ አልቻለም፡፡

ተስፋዬ የበለጠ አዲሱ ጓደኛው ነው፡፡ በንጋ ነው የተዋወቁት፡፡ ዛሬ በጣም የቅርብ ጓደኞች ሆነዋል፡፡ በለጠ የትም ሲሄድ ዘቢባ አትለየው እንደነበር ሁሉ ዛሬ ተስፋዬም ከጐኑ አይጠ ፋም፡፡ እኔም አንድ ሰሞን የበለጠን ፍቅር ስለተ ጋራኝ ቀንቼበት ነበር፡፡

* * *

ሌሊቱን እንቅልፍ የሚሉ ነገር አላየኝም፡፡ በሀሳብ ስወራጭና ስገላበጥ አደርኩ፡፡ በለጠ ማታ ውኑ ወደ አጋሮ ተመልሶ ሳላገኘው በመቅረቴ ጭንቀቴን አባባሰው፡፡ ሲነጋ አካባቢ ሰውነቴ ደክሞ ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርገኝ የመ ኝታ ክፍሌ በር በሀይል ተንኳኳ፡፡ ደጋግሞ ተን ኳኳ፡፡ እየተጐተትኩ ተነሳሁና በሩን ስከፍት ዘቢባ "ዳዊት! ዳዊት!" ብላ እላዬ ላይ ወደቀች፡፡

ልብስ እንኳ በደንብ አልለበሰችም፡፡በላይዋም ላይ ጣል ያደረገችው ስስ ቀሚስ ከሰውነቷ ጋር በብርድ ተጨማዷል፡፡የሰራ አካሏ ይንቀጠቀጣል፡፡ ታለቅሳለች፣ትናገራለችም፡፡ የምትለው ባይገባኝም የኔና የሌሎች ጓደኞቻችንን ስም ደጋግማ ታነሳ ለች፡፡በጉንጮቿ የሚንዠቀዠቀው እንባ አይኖቿን ፈንቅሎ ለመውጣት የሚታገል ይመስላል፡፡ ያቺ ቆንጆ፣ ያቺ በመንገድ ላይ ያያትን ሁሉ አፍዝዛ ቆሞ እንዲመለከታት የምታስገድደው ውብ ልጅ


t.me/OLDBOOKSPDF

የጥቅምት ብርድ እንደመታው ቅጠል ጭርምት ምት ብላ ጠቁራለች፡፡ ለሊቱን ሙሉ ስታለቅስባቸው ያደረችው አይኖቿ ውበታቸው ሁሉ ተገፎ፣ በጣም ቀልተው እንባ ብቻ ለማፍለቅ የተፈጠሩ ይመስላሉ፡፡ የምይዘውን አጣሁ፡፡ እማደርገው ጠፋኝ፡፡የሚዝለፈለፈውን ሰውነቷን እንደ ምንም ደጋግፌ ከአልጋዬ ላይ አስቀመጥኳት፡፡

"ዳዊት! ዳዊት!" አለች ዘቢባ "ምን– ምንድ ነው የሆነው? ለበለጠ ምን አወሩለት?" አለችኝ፡፡ የምመልስላት አልነበረኝም፡፡

"እኔእኮ አልገባኝም ዳዊት ምንድነው ነገሩ?"

"አይዞሽ ተይው ምንም አይደል፤ ቀላል ነገር ነው"፡፡ከዚህ በላይ መናገር አልቻልኩም፡፡ በለጠ ለኔ የነገረኝ ነገር የለም፡፡ ወሬውንም የሰማሁት ከተስፋዬ ነው፡፡

"ባዶ ወሬ ነው" አልኳት የምለው ቢጠፋኝ፡፡

"ማ– ማ– ማን እንዲህ አይነቱን ወሬ ያወራ ለታል? ዳዊት ማነው?!"

እንባ ከሚተናነቀኝ በቀር ልረዳት አልቻልኩም፡፡ ዘቢባ ጭንቅላቷን በሁለት እጆቿ ደግፋ አቀረቀረች፡፡እንዴት አድርጌ ላፅናናት? እንዴት አድርጌ በልቧ ውስጥ የገባውን ፍርሀት ላውጣው?



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ በበለጠ ላይ? እኔ— እኔ— በሱ ላይ እን ደዚህ አደርጋለሁ? ዳዊት ዛሬ ወግ ማዕረግ በማ ይበት ጊዜ! ዛሬ ለሰርጌ ሌት ከቀን በማስብበት ጊዜ እንደዚህ አደርጋለሁ?! በለጠን ምን ያህል እንደምወደው ታውቃለህ! ዳዊት እኔ እ—እ— እኔ!?"ሲቃ እየተናነቃት መናገር አልቻለችም፡፡

"በለጠን መተው ብፈልግ ኖሮ፣ ሌላ ወንድ ብወድ ኖሮ ለምን ቀለበት አሰርኩ? ለምን ላገባው ቃሌን ሰጠሁት?ሌ— ሌ— ላ ወንድ ብይዝ ኖሮ በቃኝ አልፈልግህም አልለውም ነበር? ወላጆቼ፣ዘመዶቼ፣ ጓደኞቼ ሁሉ እንዴት አንድ ምስኪን ክርስቲያን ታገቢያለሽ እያሉ ሲያወ ግዙኝ፤ የሰፈሩ ሰው እንደ እርኩስ እያየ ልጆቻ ችንን እንዳታበላሽ ከቤታችን እንዳትገባ እያሉ ሲያርቁኝ፣ ይሄን ይሄን ሁሉ ችዬ ከሱ ጋር ለመ ጋባት መቁረጤ ሌላ ወንድ ብወድ ነው ዳዊት? እ— እ— እኔ— እ— እ—"

"በቃ ተይው ሁሉም ከንቱ የሰው ወሬ ነው፡፡በለጠ ነገሩን ሲደርስበት ይተወዋል፡፡ እስ ከዚያ ቻይው፡፡"

ዘቢባ በድንገት "ዳዊት!ዳዊት!"አለችና ብድግ ብላ ከጉልበቴ ላይ ወደቀች፡፡

* * *

ይህን ነገር ማቆም አለብኝ፡፡ የጓደኛዬንና የእጮኛውን ሕይወት ለማበላሸት የተነሳውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰይጣን ማጋለጥ አለብኝ፡፡ ለጊዜው በዚህ ውሳኔዬ ተፅናናሁ፡፡ ግን ምን ማድረግ እንደምችል ጥቂት እንኳ ፍንጭ አልታየኝም፡፡ ማን ይሆን በመሀከላቸው የገባ?አንድ ጓደኛዬ እንዳለው በር ግጥ አንዳንድ ሰዎች የሚፈጠሩት የሌላውን ጥሩ ፍቅር፣የሌላውን ጥሩ ህይወት ለማበላሸት ይሆን?

ይህን ነገር ባጭሩ መቅጨት አለብኝ፡፡ ዛሬ ውኑ አጋሮ ሄጄ በለጠን ለማግኘት ወሰንኩ፡፡ ከሰአት በኋላ በበራሪ ሊዎንችና እየከነፍኩ ብሄድ ሳላገኘው ቀረሁ፡፡

መስሪያ ቤቱ ሄድኩ፡፡ ላንድ ሳምንት ፈቃድ ወስዶ መሄዱ ተነገረኝ፡፡ በለጠ ይህን ሁሉ ካደረገ በርግጥ ያገኘው ፍንጭ ይኖራል፡፡ልቤ ግን ይህንን ማመን አልቻለም፡፡

ከአጋሮ እንደተመለስኩ ከቤቱ ስሄድ አገኘሁት፡፡ ሁኔታው ከበፊቱ ቀዝቀዝ ብሏል፤ በቀዘቀዙ አይኖቹ እያየ ቀዝቃዛ ሰላምታ ሰጠኝ፡፡ አጋሮ እሱን ፍለጋ መሄዴን ስነግረው እንኳ ምንም አልተሰማው፡፡ለጥቂት ጊዜ እኔ እያየሁት እሱ አይኖቼን እየሸሸ ቁጭ አልን፡፡

"ትናንት ፈልጌህ ነበር"

"ለምን?"

"ተስፋዬን አግኝቼዋለሁ" ስለው አይኖቼን መሸሹን ትቶ ግንባሩን ኮስተር አድርጐ ተመለከተኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"የሰማኸው ወይም የደረስክበት ነገር ካለ ለምን አትነግረኝም?"

"ምን ያደርግልሀል?" አለኝ ቆጣ ብሎ፡፡ "ነገርኩህ አልነገርኩህ ምን እምታደርገው ነገር አለ?"

"በለጠ ከዚህ በፊት የሚያጋጥምህን ችግር ሁሉ ከማንም ይልቅ ለኔ ነበር ቀድመህ የምት ነግረው፤ ዛሬ ግን ..."

"ዛሬ ግን ልነግርህ አልፈለኩም!" አለኝ ነገ ሬን ከከንፈሬ ላይ ቀልቦ፡፡ "እኔው ጀምሬዋለሁ እኔው እጨርሰዋለሁ!"

"ዛሬ ሰርጋችሁ አንድ ወር ብቻ ሲቀረው፣ ዛሬ ሁለታችሁም ሁሉን ነገር ረስታችሁ ለጋ ብቻ መዘጋጀት በሚገባችሁ ወቅት እንዲህ አይ ነቱን ወሬ እንዴት ታምናለህ? ቢወራስ የተወራ ሁሉ እውነት ነው? ከዚህ በፊት ወዲያው ሰም ተህ ወዲያው ያመንካቸው ወሬዎች ከምን ላይ ነው ያደረሱህ? መልሰህ ከማፈር ለምን በመጀ መሪያ አታጣራም፡፡ ያንተንና የሷን መጋባት የማይፈልጉ፣ ባንተም በሷም የሚቀኑ እንዳሉ አታውቅም?ባልተጨበጠ ወሬ ራስህንም እሷንም ማሰቃየቱ ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ..."

"አ– ሀ– ሀ–" ሳቀብኝ በለጠ፡፡

"ያልተጨበጠ ወሬ!ዛሬስ የተጨበጠውን ይዤ ነው የተነሳሁት፡፡ ባልተጨበጠ ወሬ የምወዳትን



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅ የማስቀይም ይመስልሀል?! ነገ ሊፈጸም የተቃረበውን ሰርጌን የማበላሽ ይመስልሀል? ያልተጨበጠ ወሬ!? ዛሬስ የተጨበጠውን ይዤ ነው የተነሳሁት!"

ተናደድኩ፡፡

"ካመንከበት ለምን ሁላችንንም ታስጨንቀናለህ? የሆነውን፣ የፈጸመችውን ለምን አትነግረንም?"

"ለናንተ የምነግራችሁ ነገር የለኝም፡፡ ጊዜው ሲደርስ ለሷ ቁርጧን እነግራታለሁ፡፡"

"አንድ ወር ብቻ እኮ ነው የቀራችሁ"

"አንድም ቀን ይቅረን!እኔ ካልፈለኩ የሚሆን ነገር የለም፡፡ አንድ ሰአትም ሲቀረው ላፈርሰው እችላለሁ" ብሎ አቀርቅሮ ያስብ ጀመር፡፡

ቆይቶ በድንገት ቀና አለና ትኩር ብሎ አይን አይኔን እያየ ከት ብሎ ሳቀ፡፡ደጋግሞ ሳቀ፡፡በዚህ ሁኔታ አነጋግሬ ላሳምነው እንደማ ልችል ታየኝ፡፡ተስፋ ባልቆርጥም ለጊዜው ከመ ጨቃጨቅ መተውን መረጥኩ፡፡ ደህና ሁን ብዬ ተሰናብቼው ልወጣ ስል"ጥኑ ወዳጅ ጥኑ ጠላት ይሆናል አሉ" ብሎ ተረተ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

*   *   *

በለጠ ይርቀኝ ጀመር፡፡ እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም ጓደኞቹን ጠላ፡፡ ሁሌ የሚታየው ከተስፋዬ ጋር ነው፡፡በመንገድ ላይ ሲሄድ፣ ቡና ቤት ሲቀመጥ፣ማታ ማታ ሲጠጣ ከጎኑ የማይ ለየው ተስፋዬ ብቻ ሆኗል፡፡ ብዙ ይጠጣል፤ ብዙም ያጨሳል፡፡ሰውነቱ እየከሳ፣ መልኩ በይበ ልጥ እየጠቆረና አመድ እየመሰለ መጣ፡፡

ሁላችንም ባለን አቅም የሁለቱም ቤተሰቦች ወሬውን እንዳይሰሙ ተከላከልን፡፡ ሆኖም የወሬ ህይወቱ ከቦታ ቦታ መዛመቱ ነውና ከሁለቱ ቤተሰቦች ዘንድ ለመድረስ ጊዜ አልወሰደበ ትም፡፡

የዘቢባ ቤተሰቦች ወሬውን ሲሰሙ ደስ አላ ቸው፡፡ "አላልንም ድሮስ ክርስቲያን አምና መጠጋቷ ይበላት!" እያሉ ያፌዙባት ጀመር፡፡

የበለጠ እናት ወሬውን ሰምተው ቢደነግጡም እኔና ጓደኞቹ እየሄድን ስለምናፅናናቸው ዝግጅ ቱን አላቋረጡም፡፡

የበለጠ ሁኔታና የወሬው መዛመት ዘቢባን የበለጠ አዳከማት፡፡ ተስፋ ቆረጠች፡፡በሀሳብ የቆ ሰለው አንጀቷ እህል እንደልብ ስለማይቀበላት ጠወለገች፡፡አስራ አምስት ቀናት ብቻ የቀረውን ሠርጓን በጉጉት ከመጠበቅ ይልቅ ሀዘንና ለቅሶ ብቻ ታቅፋ ቀረች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

* * *

አንድ ቀን እሷ ጋ ውዬ ስመለስ 'ግቤ ሆቴል' ፊት ለፊት ወርቅነህን አገኘሁት:: ቡና እንጠጣ ብሎኝ እበረንዳው ላይ ቁጭ አልን:: ወርቅነህ በበለጠ ሁኔታ በጣም ከሚጨነቁት ጓደኞቻችን አንዱ ነው::በለጠ እንደሁላችንም እየራቀው እስከሄደ ድረስ የተለየ ምስጢረኛው አድርጎት ነበር::የበለጠና የዘቢባ መቃቃር ከሁላችንም ወርቅነህን የበለጠ አሳስቦታል:: ብዙ ጥሯል፤ ሁለቱ ቀኑ የተቃረበ ሠርጋቸውን አላግባብ እንዳያበላሹ፣በዚያም ሳቢያ አስከፊ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ያላደረገው ነገር የለም::

ወርቅነህ ከሁላችንም አብልጦ በለጠን ይወደዋል:: በለጠን የማይወድ ማን አለ? በደግነቱ፣ በሰው ወዳድነቱ፣ ለጓደኛ ሟች በመሆኑ ... እሱንማ የማይወደው አለ? ሁላችን ለሱ ለየት ያለ ፍቅር ነው ያለን:: እሱም የሚወደው እንጂ የሚጠላው ሰው የለውም::ከኔ ጋር ስንተዋወቅ ረዘም ያለ ጊዜ ነው:: ታዲያ አንድ ቀን እንኳ እገሌን እጠላዋለሁ ሲል ሰምቼው አላውቅም:: የበደሉትን እንኳ ስቆ ከማሳለፍ አልፎ ቂም ይዞ፣ጥላቻ አርግዞ፣ጥርሱን ሲነክስ አይቼው አላውቅም::

“ለምን ዝም ትላላችሁ ዳዊት?የበለጠን ጉዳይ አንድ ነገር እናድርግ እንጂ” አለኝ ወርቅነህ::

“ምን ማድረግ እንችላለን?እኔ በበኩሌ የምችለውን ሁሉ ሞክሬያለሁ::በለጠ ለኔ ምንም ሊነግረኝ አልፈቀደም:: ዘቢባን በማን እንደጠረጠራት እንኳ አልነገረኝም::”



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለኔም አልነገረኝ" አለ ወርቅነህ "በፊት በር ግጥ ያገኘው ነገር ያለ መሰሎኝ ነበር፡፡ ዘቢባን ካንዴም ሁለቴ— ሶስቴ ከቤቴ መጥታ አነጋግሬ ያታለሁ፡፡ ያገኘሁባት ፍንጭ የለም፡፡"

"ታዲያ ምን እንዲህ ያደርገዋል? ድፍን ያለ ነገር እኮ ነው የሆነብኝ፡፡"

"በጥርጣሬ ይመስለኛል" አለ ወርቅነህ "ያፈቀረ ሰው አላፊ አግዳሚውን ይጠረጥር የለ? በጣም ስለሚወዳት ማንንም ቀና ብላ ባየች ቁጥር ሊጠረጥራት ይችላል፡፡ በለጠን ታውቀዋለህ፡፡ የገመተውን ቀርቶ የሰማውን ሳይጠረጥር የሚያምን ሰው ነው፡፡ አንድ ነገር ሰምቶ ይሆናል? ማን ያውቃል? ገርኒቱን ያወቀ..."

"በጥርጣሬ ብቻ እንደዚህ ያደርጋል? ደግሞስ ማን በመሀከላቸው ገብቶ ወሬ ሊያቀብለው? አይመስለኝም፤ ያየው ነገር መኖር አለበት፡፡"

"እንጃ" አለ ወርቅነህ "ያየው ነገር ቢኖር ይነግረኝ ነበር፡፡"

ግራ ተጋባሁ፡፡ በለጠ በጥርጣሬ ብቻ ነው የሚወዳትን ልጅ ለመተው የተነሳው? በጥርጣሬ ብቻ ነው ስንት የደከመበትን ሠርግ ለማበላሸት የሚጥረው? አልመሰለኝም፡፡

"በመጠኑም ቢሆን ዛሬ አንተን ነው የሚቀርበው ለምን አታነጋግረውም?" አልኩት ወርቅነህን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ያልሞከርኩት ነገር አለ? በተለይ ዘቢባ ካንደ₌ም ሁለቴ – ሶስቴ ከቤቴ መጥታ ሁሉንም ነገር ካጫወተችኝ ወዲህ ነገሩ ተጨባጭ አለመ ሆኑንI መሰረት በሌለው ጥርጣሬ የራሱንና የሷን ህይወት እንዳያበላሽ ደጋግሜ ነግሬዋለሁ፡፡ግን አልሰማኝም፡፡አትቸኩል፣ አመዛዝን፣ነገሩን ከተለ ያየ አቅጣጫ እየው እያልኩ ብዙ ወትውቼዋ ለሁ፡፡ አሁንማ ያባስ ብሎ ያሸሸኝ ጀመር፡፡ሰሞ ኑን እንደሰማሁት ቀለበቴን አስመልሳለሁ እያለ ይፎክራል አሉ፡፡ እስከዛሬም በኔ ብርታት ነው የቆየው፡፡ እኔ እምፈራው ቀለበቱን 'ማስመለሱን' ብቻ ሳይሆን በራሱም ሆነ በሷ ላይ አደጋ እንዳ ያደርስ ነው፡፡"

"ታዲያ ምን እናድርግ ትላለህ?"

"በጣም ነው የጨነቀኝ፡፡ የበለጠን ነገር ሳስ በው አንጀቴ ነው እሚቃጠል" አለኝ ወርቅነህ እሱም እንደኔው ግራ ተጋብቶ፡፡የምንወደው ጓደ ኛችን ህይወት አይናችን እያየ ገደል መግባቱ ነው፡፡ የኔን ጭንቀት በወርቅነህ ፊት ላይ ተመለ ከትኩት፡፡ ምነው በለጠ የምንወደውን ሁሉ ባያሳ ዝነንና ባያስጨንቀን?

"እኔን ምን እንደሚያስጨንቀኝ ታውቃለህ?" አለኝ ወርቅነህ "ለበለጠ ወሬ የሚያቀብለውን ማወቅ ቀርቶ መጠርጠር አለመቻሌ ነው፡፡"

"ወሬኛ የት ይታጣል፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሱስ እውነትክን ነው" አለኝ ወርቅነህ "ለራሳቸው ባይጠቀሙም ሰውን በመጉዳት የሚረኩ ሞልተዋል።ባል በማግኘቷ የሚቀኑባት ጓደኞቿም ሊሆኑ ይችላሉ።ወይም ፈልጓት ያቃተው ወንድ ሊሆን ይችላል" ብሎ ፈገግ አለ።

"ጓደኞቿ? ጓደኞቿ!እነ ዘሀራ?አያደርጉትም። ለዚያውስ እሷንና በለጠን አለያይተው ምን ሊያገኙ? እሷን ትቶ እነሱን አያገባ።"

"በማለያየታቸው ብቻ ረክተው ቢቀመጡስ!" ደነገጥኩ።እንዲህ አይነቱን ክፋት ለማንም ልሰጠው አልተዘጋጀሁም።

"ለምን የመጨረሻ ሙከራ አናደርግም?"አልኩት ወርቅነህን የመነመነ ተስፋውን ጨርሶ ሳይገለው አንድ ነገር እንዲያደርግ በማሰብ።

"አንተ በለጠን እንደምንም ብለህ አግኘውና አነጋግረው።እኔ ዘቢባን አነጋግራታለሁ።መቼም ለሷ ከማን ጋር እንደጠረጠራት ሳይነግራት አይቀርም።ሳንተም አንድ ፍንጭ ይሰጥህ ይሆናል።"

"እኔ ዝግጁ ነኝ" አለ ወርቅነህ በኔ ውስጥ ያንሰራራው ደካማ ተስፋ ወደሱ እየተጋባ።

"በለጠን ለማዳን አድርግ ያልከኝን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ። ከፈለግህም አብረን እናነጋግረው።"



t.me/OLDBOOKSPDF

"የለም ብቻህን ብታነጋግረው ነው የሚሻል፡፡ ከኔ ጋር ብዙ ተነጋግረናል፡፡ አሁንማ ሊያነጋ ግረኝ ቀርቶ ሊያየኝ ይቀፈዋል፡፡ አንተ ሞክር..."

ከወርቅነህ ጋር ብዙ ተነጋገርን፡፡ በመጨረሻ ነገሩ መፍትሄ እስኪያገኝ የሠርጉ ዝግጅት ጨርሶ እንዳይቋረጥ የተቻለንን ሁሉ ለማድረግ ተስማምተን ተለያየን፡፡

የሚጋቡበት ቀን እየቀረበ በመጣ ቁጥር በለ ጠና ዘቢባ እየተራራቁ ሄዱ፡፡ በለጠ እኛን እን ደሸሸ ሁሉ እሷንም ይሸሻት ጀመር፡፡ የፈቃዱ ቀን ቢያልፍም ከሥራው ተመልሶ አልገባም፡፡ ውጪም መታየቱን አቁሞ ከቤት ይውል ጀመር፡፡ በተስማማነው መሰረት ወርቅነህ ሊያ ነጋግረው ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ፡፡እኔም ከዘቢባ ምንም ፍንጭ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ሁኔታው እንቆቅልሽ አይነት ሆነብን፡፡

ዘቢባ የሰውን አይን ማየት ስላልቻለች ሀፍረ ቷን ታቅፋ ከቤት ውስጥ ቀረች፡፡ ወጣ ስትል የሚያያት ሁሉ ስለሷ የሚያወራና የሚጠቃቀ ስባት ስለሚመስላት የሰውን አይን ሸሸች፡፡

የሠርጉ ዝግጅት ከሁለቱም ቤት ቀዘቀዘ፡፡ ሁላችንም ተስፋ ቆረጥን፡፡ የሚሆነው ነገር ሁሉ አላግባብ መሆኑን ብናውቅም መንስኤውን ልን ደርስበት ስላልቻልን የሁለቱን ፍቅረኞች ህይ ወት ይዞ ወደ መቀመቅ የሚንደረደረውን ሂደት



t.me/OLDBOOKSPDF

ልንገታው አልቻልንም፡፡ ቢሆንም እስከ መጨረ ሻው መታገል ነበረብን፡፡ እንደአማራጭ የወሰድ ነው በሁለቱም ቤተሰቦች በኩል የሚደረገው ዝግጅት ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ማድረግ ነበር፡፡ መጨረሻውን ብናውቀውም ይኸኛው ጥረታችን ከሞላ ጎደል ተሳክቶልናል፡፡

"ኢያጎ ነው!"አለ ቀልደኛው ጓደኛችን ጠጅ ነህ፤አንድ ቀን ከኔ ቤት ቁጭ ብለን ካርታ እየተጫወትን የበለጠንና የዘቢባን ጉዳይ አንስ ተን ስንጫወት፡፡

"ከመሀከላቸው ገብቶ ያለያያቸው ኢያጎ ነው!" ሲል ደገመና ተናገረ፤ ነገሩ ሁላችንንም አሳቀን፡፡

"አይደለም! አይደለም!" አለ ጠጅነህ እንደ ገና ሀሳቡን በመቃወም አይነት፤ አንድ ነገር እንደታየው ሁሉ የያዘውን ካርታ እጠረጴዛው ላይ ወረወረው፡፡
"ማ መሰላችሁ ማ መሰ..."

የሳሎኑ በር በድንገት በሀይል ተበረገደ፡፡ ሶስ ታችንም በድንጋጤ ፈዘን ቀረን፡፡በለጠ በቁጣና በደስታ መሀል ተወጥሮ ወደ ውስጥ ገባ፡፡

"ጠላቴን አገኘሁት! ጠላታችንን አገኘሁት!" እያለ ከፊታችን ቆመ፡፡ በቀኝ እጁ ትንሽ አው ቶማቲክ ሽጉጥ ይዟል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጠላቴን አገኘሁት፡፡ ዳዊት ጠላታችንን ተበቅየዋለሁ!" ብሎ ሰንጢውን እጠረጴዛው ላይ ወረወረው፡፡ ለምን ያህል ደቂቃ እንደሁ አላውቅም በቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ፡፡

"ዘቢባን!? ዘቢባን!? ...ዘቢባን ገደልካት" ብዬ ልጮህ ስል በለጠ፤

"ይኸውልህ እየው!" ብሎ አንድ የተጨማደደና በላብ የራሰ ደብዳቤ ከኪሱ አውጥቶ ሰጠኝ፡፡

"አንብበው፡፡ ጠላታችን እሱ ውስጥ ነው ያለው!"

ደብዳቤውን በሚንቀጠቀጡት እጆቼ ይዤ በሚንቀጠቀጡት ከንፈሮቼ ለማንበብ ሞከርኩ፡፡

*ጥር 1—1965 ዓ.ም.*

*በለጠ እንደምናለህ*

*ይህንን ደብዳቤ በችኮላ ነው የጻፍኩልህ፡፡ ያንን ጉዳይ ሌት ከቀን እየተከታተልኩ ነው፡፡ ዘቢባ ያንተ እግር ከጅማ ወጣ ሲል የምትውለው ከዳዊት ቤት ነው፡፡ማታ ማታም እያመሸች ሲሸኛት አይቻቸዋለሁ፡፡*



t.me/OLDBOOKSPDF

*ዳዊት በጣም የቅርብ ጓደኛህ ስለሆነ ሌላ ሰው ላይጠረጥራቸው ይችላል፡፡ ለኔ ግን ሁኔታ ቸው አላማረኝም፡፡*

*በመሀከላችሁ እንዲህ አይነት ነገር እያለ ብትጋቡ ትዳራችሁ ትዳር ስለማይሆን በቶሎ መጥተህ ሁኔታውን ራስህ ብትከታተለው ይሻ ላል፡፡ በዚህ አይነት ብዙ የተቃለሉ ወንዶች ስለማውቅ በጉዳዩ አስቤበታለሁ፡፡ በቶሎ ናኗ እኔ እስከዚያው ክትትሌን እቀጥላለሁ፡፡*

*ወንድምህ*
*ወርቅነህ*

አንብቤ እንደጨረስኩ ሳላውቀው ቁጭ ብድግ አልኩ፡፡ እነጠጅነህም እተቀመጡበት በድን ሆነው ቀሩ፡፡

"ዳዊት አትደንግጥ!" አለኝ በለጠ፡፡

"እውነተኛውን ጠላቴን አግኝቼዋለሁ፡፡ አንተ ሳትሆን ወርቅነህ መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡ ደስ አይልህም ዳዊት፤ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻዬን የነገሮችን እውነትነትና ሀሰትነት ለማረ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋገጥ በመብቃቴ! ደስ አይልህም?! … ” አለኝ
በለጠ በተጨነቀ ፊቱ ፈገግ ብሎ፡፡ አመድ በለ
በሰው ፊቴ ፈገግ ብዬ አዎንታዬን በአገጩ የገ
ለፅኩለት መሰለኝ እርግጠኛ አይደለሁም

ቆይቼ እፊቱ የወረወረውን ሴንጢ ገርመም
አደረግሁና በለጠን ዞር ብዬ ተመለከትኩት፡፡

“አይዞህ! አትደንግጥ አልገደልኩትም” አለና
ሳቀ፡፡

“እንዴት? ብለህ አትጠይቀኝ እንጂ ጠላታ
ችን እሱ መሆኑን ስደርስበት በቀጥታ ወደቤቱ
ገሰገስኩ፡፡በሩን በርግጄ ስገባ አልጋው ላይ በጀ
ርባው ተንጋሎ ጣራ ጣራውን እየተመለከተ በሀ
ሳብ ወደሰማዩ ሰማያት የዘለቀ ይመስላል፡፡
መለስ ብሎ ሲያየኝ ከዓይኖቹ የወጣው ድንጋጤ
እኔንም አስደነገጠኝ፡፡በዚያች ቅፅበት ያደረገውን
ሁሉ እንደደረስኩበትና ምንም ነገር ሊደብቀኝ
እንደማይቻለው ሲያውቅ ነው እንደዚያ የደነ
ገጠው፡፡

“ተንደርድሬ ከተንጋለለበት በሸሚዙ ኮሌታ
አንገቱን አንቄ አነሳሁት፡፡ ጥቂት እንደተፋጠ
ጥን ለሁለታችንም ወንበር ስቤ ፊት ለፊት ተቀ
መጥን፡፡ ለምን ያህል ደቂቃ እንደሁ እንጃ ያለ
ድምፅና ያለ ቃላት በአይኖቻችን ብቻ እውነ
ቱን ተለዋወጥን፡፡ ስንጨርስ ብድግ ብዬ ሴንጢ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዋን ከኪሴ አወጣሁና 'አበቃልህ! ልገልህ ነው ተዘጋጅ!' ስለው ምንም ሳይናገር ከትከት ብሎ ሳቀና 'እረደኝ' ብሎ እጠረጴዛው ላይ በግንባሩ ተደፋና ማጅራቱን ሰጠኝ:: በጣም ያስገረመኝ ይሄ መሰለህ? አሁንም ሳስበው የሚደንቀኝ እን ደዚያም ሆኖ በሳቅ መንከትከቱ ነው ... "

"ግን ለምን አደረግሁት አለህ?"

"ምንም ምክንያት አልሰጠኝም::'በቃ አድርጌ ዋለሁ:: አሁን የፈለግኸውን ማድረግ ትችላለህ!' አለኝ::"

"ምን እንደያዘኝ እንጃ! የሴንጢውን ስለት እማጅራቱ ላይ ላሳርፈው ሁለት ሶስቴ ቃጥቶኝ ነበር:: ተውኩት:: ድንገት አንድ ሀሳብ መጣል ኝና 'ቀና በል' ስለው ቀና አለ:: እንዴት እንዳ ደረግሁት? ወይም እንዴት እንደተደረገልኝ አላ ውቅም ብቻ አንድ ጆሮውን ጐትቼ ከፊሉን ቀነ ጠስኩለት::

"'በዚህ ክፉ ሥራህንና እኔን ለዘላለሙ ታስ ታውሰናለህ!' ብዬው የጆሮውን ቁራጭ አፍን ጫው ላይ ወርውሬለት ተንደርድሬ መጣሁ::"

"እና ለድርጊቱ ምንም ምክንያት አልሰጠ ኝም ነው እምትለኝ?!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምንም" አለኝ፡፡ ወዲያው ወርቅነህ 'በሚያ ደርጉት ክፉ ነገር ምንም ባይጠቀሙም ሌሎ ችን በመጉዳታቸው ብቻ የሚረኩ ሰዎች አሉ እኮ' ያለኝ ትዝ አለኝ፡፡ ምናልባት እሱ ራሱ ከእንዲህ አይነቶቹ ሰዎች አንዱ ይሆን? ማን ያውቃል!?...



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሰርቅ ዳንኤል

(1958 — )



ሰርቅ ዳንኤል በ1958 በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ፡፡ የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በካቴድራልና በቅዱስዮሴፍ ት/ቤቶች ካጠናቀቀ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመግባት በሳይኮሎጂ የትምህርት ዘርፍ የባችለርና የማስተርስ ድግሪ ተቀብሏል፡፡

ሰርቅ ዳንኤል አጫጭር ልቦለዶችንና ግጥሞች መጻፍና መግጠም የጀመረው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ ቆይቶም "ቆንጆዎቹ" የተሰኘ ረጅም ልብወለድ ድርሰት አሳትሟል፡፡"ቆንጆዎቹ" በአተራረኩና በአነሳው አህጉራዊ ጭብጥ ብዙ ያወያዩ፤ በሬዲዮ ተተርኮም ከፍተኛ ተነባቢነት ያተረፈ ወጥ ድርሰት ነው፡፡

ሰርቅ ዳንኤል ለህትመት ያልበቁ በርካታ የግጥምና የአጫጭር ልቦለድ መድበሎች አሉት፡፡ ከአጫጭር ልቦለዶቹ መካከል "ብርቅዬ" እና "ፍርሃት" የተሰኙት ለዚህ መድበል ተመርጠው ቀርበዋል፡፡ሰርቅ ዳንኤል በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት በማገልገል ላይ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ብ ር ቅ ዬ

"ብርቅዬ!"
"ወዬ!"

"ይሰንጥቅሽ!" አለ በቀኝ እጁ የበሩን መቃን ይዞ በፕላስቲክ ቦት ጫማው ላይ የተደፈደፈውን ጭቃ በእንጨት ደፉ ላይ እያላከከ፡፡

"ልሳንህን ይዝጋው አንት ጅራታም ቡዳ!"

"አሜን ብርቅዬ አሜን እሱ ነው ከሰው እያ ጣላ ያጠፋኝ...ሀ! ሀ! ሀ!..."

እስከወገቡ ጉንበስ ብሎ እንዳች የሚያክል ገላውን ወደቤት ውስጥ አዘለቀው፡፡

"ስብሀት ለአብ! ምን ያክላል?"

ዙርያዋ በጭቃ ተገርፎ ከውስጥ ግድግዳዋ በጋዜጣ ወረቀት ወርቅ ተደርጋ የተለበደችው የብርቄ እናት ጐጆ አንድ ክፍል እንድትሆን ታስባ የተሰራች ብትሆንም መሀል ለመሀል ከጥግ እስከ ጥግ የተንጠለጠለው ያደፈ ባለአበባ ሰማያዊ መጋረጃ፣ባለሁለት ክፍል ቪላ አድርጓታል፡፡ ከመጋረጃው ጀርባ ሽንሽን አረንጓዴ ባለሽንተረር የአልጋ ልብስ የደረበ ድንክ አልጋ ተዘርግቷል፡፡ ብርቄ ከእናቷ ጋር የምትተኛበት ነው፡፡ግን ይኼ ሁሌ አይደለም፡፡ የብርቄ እናት ከሚሰሩበት የሳሙና ፋብሪካ ባለተረኛ በሚሆኑባቸው ለሊቶች



t.me/OLDBOOKSPDF

ብርቄ ብቻዋን ትተኛበታለች፡፡ግን ይሄም ሁሌ አይደለም፡፡ አንዳንዴ ብርቄ አምስት ብር ይዞ ከተፍ ከሚል ባለተረኛ ጋርም ትተኛበታለች–ግን አደራ ይሄ ምስጢር ነው፡፡ እናቷ አያውቁም፡፡ "... ሆሆ ... ጉመን በጤና" አሉ ...

ከወዲህኛው ክፍል በቀኝ በኩል ጥጋቱን ይዞ አንድ አካለ ስንኩል እግረ ሽንካላ ሶፋ ወንበር ብጫ አይሉት ቡና፣ ቡና አይሉት ግራጫ ቀለሙን የማይለይ ጨርቅ ለብሶ ተኮፍሷል በኩራት፡፡ በተለይ ለሊቀ ደንበኞች፡፡ ከበሩ በኩል ከመስኮቱ በታች ደግሞ ተራርቀው በተተከሉ ሁለት ጉማጅ ግንዶች ላይ የተዘረጋ ጣውላ ቢጤ አለ፣ ለምዕመናን፡፡

"እናትሽ ዛሬ ባለሽፍት ናቸዋ?" አለ ዋኬኔ ጥያቄ ሳይሆን ተራ ዓረፍተ ነገር በመሰለ አነጋገር፡፡

"እሱን አረጋግጠህ ነዋ የመጣኸው?" አለች ብርቄ፤ የሷም መልስ የሚሻ ጥየቄ አልነበረም፡፡

ብርቄ የለበሰችውን ጠቆር ያለ፣ ስስ፣ ወይን ጠጅ፣ እጅጌ ጉርድ ቀሚሷን ከቋንጃዎቿ ስር ወሸቅ አድርጋ ቁጢጥ ብላ ለማታው ገበያ የምታ ቀርባቸውን የአረቄ መለኪያዎች ውሀ በተሞላ ድስት መሳይ የእንጨት ቁና ውስጥ ነክራ እያገ ቦራጨቀች ታወጣለች፡፡ ተራ በተራ እየፀዱ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ኢይ እንዲያው ... ሆን ብዬ ነው::" አለ ግድግዳ ላይ የተለጠፉትን ስዕሎችና ማስታወቂያ ዎች ከዚያ በፊት አይቶ እንደማያውቃቸው ሁሉ አንድ በአንድ እያጠናቸው— 'ባለ አምስት ብሩን ሎተሪ ገዝተው እድልዎን ይሞክሩ!' 'ካፌኖል— ለራስምታት!' ...

ብርቱ የታጠቡ መለኪያዎቿን በየጣቶቿ ሰክታ ቁጢጥ ካለችበት ተነሳች:: በዋኬኔ ጀርባ በመሰቡ በኩል ወደ መደርደሪያው ስታልፍ አፈፍ አደረጋት:: ልፊያ እየቃጣው::

"ኡፍ ... ልቀቀኝ" አለች::

"በቃ...እናትሽ ዛሬ አይመለሱማ...?" ዳበሰ::

"ልቀቀኝ! እየው ዛሬ እነዚህ መለኪያዎች ይሰበሩና..."

"ታዲያ ለምኑ ነው እዩዩው ይንኮታኮቱ አ!" አለ በጉርናና ድምጹ::

"ኧረ ያንተው ጀርባ ይንኮታኮት:: ደንደሳም ጃውሳ ... አሁን አንዷ ብትሰነጠቅ ወር ትጠፋ ለህ::"

"ማ...እኔ ዋኬኔ? እንኳን ለአንድ አረቄ መለ ኪያ ለሴላም ለሴላም እተርፋለሁ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንግዳው ወንድ እስቲ አንዷን ጦሽ አድር ጋት ... እስ ... ቲ ዋኬንዬ በሞቴ አንዷን ... " አጉል ተፈታተነችው ለቀቃት፡፡

ጥቁር ነው ዋኬኔ፡፡ ጨለማ፡፡ ፈካ ብሎ የሚ ታየው ቀን ቀን ነው— የወፍጮ ቤቱ ዱቄት ሲቦንበት፡፡ጆንያ ሙሉ ዱቄት ሲያወርድ፣ ጆንያ ሙሉ ዱቄት ሲገለብጥ፣ ጆንያ ሙሉ ዱቄት ሲጭን የሚውል ገላው ጠብድሎ ያንኑ ወፍጮ ውን አክሏል፡፡በዛ ሰውነቱ ተፍ ተፍ ሲል የሚያ ዩት የወፍጮ ቤቱ ደንበኞች — "አደራህን ዋኩ ተሳስተህ ወፍጮውን እንዳታነሳው" እያሉ ይቀል ዱበታል፡፡

ሽከሙ ብቻ አይደለም እንዲህ ያጠበደለው፡፡ እረፍት ባገኘ ቁጥር አለዛም "ዋኬንዬ ይቺን አስ ፈጭና ቆየኝ" የሚለው ሲያጣ አድራሻው ከማማ ስንዱ ቤት ነው፡፡

"እማማ ቅቅል አለ?" ይላል— በዚህ ሰዓት ቤት እጠብቅሀለሁ ያለው ይመስል— ቅቅል፡፡ አንድ አይናማዋ እማማ ስንዱ "አለም" የለ "የለምም" የለ ከምድጃው ላይ ወደማይወርደው ጥቀርሻ ድስታቸው ጭን መሳይ ክንዳቸውን ይል ኩና በቀሚሳቸው ጫፍ ክዳኑን ካነሱ በኋላ "እፍ ... እፍ" እያሉ በረጅሙ ጭልፋቸው ከሽ ኽናው ሾርባ ይቀዱለታል፡፡

"ተው...እንጂ... አይመልሱት እማማ ስንዱ?" ያልጉመጉማል ዋኬኔ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

“ታዲያ በስሙኒ ሁለት ሸኽና ልትውጥ አማረህ ...? ምነው ስንዱ ...እንደው አሁንስ ...” ይላሉ ቱግ ብለው፡፡

“እሺ ሰላሳ እከፍላለሁ”

“ሀምሳ!”

“እሺ አርባ”

“ሀምሳ አልኩ ሀምሳ”

“እሺ! እሺ! እከፍላለሁ” ይላል ድስቱን ሲከ ድኑት ሲሉ ተሽቀዳድሞ፡፡

አንድ ሸኽና ይጨምሩለታል፡፡

“አሀ! በሉ እንጂ ከመረቁም ይጨምሩበት” ይላቸዋል፡፡

ዋኬኔ ያንን ልድልድ ቅባት የሸኽና ሾርባ ግጥም አድርጐ ከጠጣ በኋላ ላንቃው ላይ የተጋ ገረውን ሞራ በምላሱ እየቧጠጠ ተነስቶ ይወ ጣል፡፡ ሽልንጉን ከፍሎ፡፡ ጠብድሎ፡፡

“ብርቅዬ አንድ አረቂ ቅጂልኛ” አለ አግዳ ሚው ጣውላ ላይ እየተቀመጠ፡፡

ዋኬኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነብርቄ ቤት መመላለሱን ተያይዞታል፡፡ብርቄን እንኳን የሚያ ውቃት፣በአይን ይሁን እንጂ፣ቀደም ብሎ ከምት ኖርበት ከአጎቷ ቤት ከደብረ ማርቆስ አልፎ አልፎ እየመጣች እናቷን ስትጠይቅ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ባለፈው ግንቦት እኚሁ አጐቷ ሲሞቱ ግን ከልጆቻቸው ጋር ስላልተስማማች ነው አሉ መጥታ ከእናቷ ጋር ተዳበለች፡፡ ስትመጣ ትንሽ ምናምን ይዛ ነበር መሰለኝ የናቷን ቤት እንደ ነገሩ አሳድሳታለች፣ከውስጥም ግድግዳው በጋዜጣ ወረቀት የተለበደው ያን ሰሞን ነው፡፡ በኋላም እናቷ ያዝ ለቀቅ ያደርጉት የነበረውን የማታ መሸታ፣አንድ ክፍል ቤታቸውን በመጋረጃ ሁለት አድርጋ፣ በቅጡ ተያይዛዋለች፡፡

ከዚያ ወዲህ ነው ዋኬኔ እግር ያበዛው፡፡ ምን እሱ ብቻ እነ ዱባለ ኮርቻውም የዘንዬን ቤት እብድ ውሻ የታሰረበት ይመስል እርግፍ አድር ገው የተውት ከዚያ ወዲህ ነው፡፡

እንጃ ብቻ ለምን እንደሆነ፣ መልኳ እንኳን– የብርቂ– ያን ያህል የሚስብ አይደለም፡፡ ጠየም ከማለትም አልፎ ጠቆር ያለው ገጽታዋ ከሳቅና ከፈገግታ ይልቅ ፌዝና ማሽሟጠጥ ይቀናታል፡፡ ጐመድ ብሳ ወርዳ ከወደጫፏ ቀና የምትለው አፍንጫዋ የእርሷ አትመስልም፡፡ የሌላ የአሻን ጉሊት ትመስላለች፣የቀበጥ አሻንጉሊት፡፡ሞላ ሞላ ያሉት ከንፈሮቿም ያን ያህል የሚስቡ አይደ ሉም ...እንትን አስመስለዋታል፡፡ አይኖቿ አንድ ነገር አላቸው፡፡ መስታወ ...ት ይመስላሉ ልበል? ብዙ ጊዜ ፊት ለፊት ሰውን አያዩም፣ ሲያዩ ግን አንድ ዓይነት ሚስጢር የሚያስተላልፉ ይመስ ላሉ– ያ ነገር እኔና አንተ ብቻ የምናውቀው ...የ ... " አያሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ገላዋ ቀልጣፋ ነው፣ ቀጠን ብሎ ጥምጥም ያለ፡፡ጉች ጉች ያለች አይን አውጣ ጡቶቿ ማፍ ጠጣቸው በጀ እንጂ እንደሁኔታዋስ ለግላጋ ወጣት ወንድ ነው የምትመስል፡፡

ብቻ እንጃ ባጠቃላይ ገጽታዋ ያን ያህል አይደለም፡፡ ግን ወንዶች ይወዷታል ... እንግዲህ የሚያውቁት ነገር ቢኖር ነው...ህእ፡፡

ወር በገባ ከአምስት እስከ አስራ ሁለት'ማ? በዚያ ሳምንት የብርቄ እናት ከሚሰሩበት ፋብ ሪካ የሌሊት ተረኛ አይደሉ? አይነሳ፡፡ የኑብርቄ ቤት ጢም ይላል፡፡ ከዚያማ ... መፋጠጥ ነው፣ "መሸብህ ሂድ" መባባል፡፡ዛሬ ግን ልብስ ሰፊው ዘለቀ የናቱን የወይዘሮ ዘርፈሽዋልን ሙትአመት ሰንጋ ጥሎ ስለደገሰ ሰው ሁሉ እዛው ተሰብ ስቧል፤ የኑብርቄም ቤት ያለልማዱ አየር ገብቶ ታል፡፡

ዋኬኔ ዛሬ ቆርጦ ነው የመጣው፡፡ቀን እማማ ጌጤነሽ አስፈጭልኝ ብለው የሰጡትን በርበሬ እንኳን ከቤታቸው አላደረሰም፤ ከራሱ ቤት ነው አስቀምጦት የመጣ፡፡ ምን ያድርግ መሸበት፡፡

ዋኬኔ፣የብርቄ እናት ከፋብሪካው እንደሚያ ድሩ አጣርቷል፡፡

"ብርቅዬ አንድ አረቄ ቅጅልኛ" አለ አግዳ ሚው ጣውላ ላይ ተቀምጦ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ብርቄ እጆቿን በቀሚሷ ካደረቀች በኋላ ከመደርደሪያው ላይ የአረቄ ጠርሙስና መለኪያ አንስታ ተጠጋችው:: መለኪያውን ከፊቱ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ የጠርሙሱን ክዳን በእርጋታ ከከፈተች በኋላ ጉንበስ ብላ አረቄውን ትቀዳለት ጀመር::

"አቤት ተንኮል! አሁን ምን ትጠቀሚያለሽ?" አለ ዋኬኔ በልቡ በቀሚሷ ክብ የደረት ቅድ አሾልኮ ወደ ውስጥ እየተመለከተ::

ጠርሙሱን ዘግታ ቀና ስትል– "ቆይ– ቆይ ... ብርቅዬ" አለና የተቀዳለትን አረቄ ጭልጥ አድርጎ "ጨምሪልኝ" አለ::

አገነበሰች::
"አቤት ተንኮል! ... "

የደንቡን ስድስት ብር አውጥቶ ከጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ::አየችው፣አየት...በጊዜ ተዋዋሉ::

ብርቄ ቀና አለች አረቄውን ቀድታለት:: እንደ ዋዛ ስድስቱን ብር አንስታ ከቆጠረችው በኋላ አንዱን ከአረቄው ጠርሙስ ስር አምስቱን በቀሚሷ ክብ የደረት ቅድ ቁልቁል ላከችው፣ ለየባለቤቱ::

"እንዴት ይወብቃል?" አለ ዋኬኔ የጨርቅ ቆቡን አውልቆ እያራገበ:: 'ድገሚ ብርቅዬ ጨምሪልኝ' ሊላት ዳድቶት ነበር:: ግን ሲያስበው፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያሰላስለው የያዘው ሰባት ብር ከሀምሳ ብዙም የሚያቀናጣ አይደለም ...።የቅድሟ አምስት ብር ስትነሣለት ደግሞ... "ትዕግስት..."አለ ከራሱ ጋር አረቄውን በስሱ ቀመስ አድርጐ"ትዕግስት..."

"እሺ ብርቅዬ ... " አለ ጨዋታ ለመጀመር አሰበና "ኑሮ እንዴት ይዞሻል ታዲያ"

"የፍጢኝ"

"ሀ! ሀ! ሀ! እንደ ሌባ?" ሲስቅ ደስ ይላል ዋኬኔ።

"ሲሰርቁ ካልተያዙ ኮ ሌብነት ይጣፍጣል..." መጋረጃውን ገለጥ አድርጋ አልጋው ላይ ዘፍ አለችና ሁለት እጆቿን የኋሊት ተመርኩዛ ትመለከተው ጀመር።

"ልክ ነሽ ችግሩ መያዙ ላይ ነው።" አረቄውን ከከንፈሩ አድርሶ መለሰው።

"ስትያዝ ደሞ የበለጠ ይጣፍጣል...።" ፊቷን ዘንበል አድርጋ ተሽከረመመች።

"ተይ ተይ እሱስ ይቅር"

"ስነግርህ?"

"ቀምሰሽዋል ልበል?"

"አዘንጨ ነዋ"

"ሀ! ሀ! ሀ! ምን? ስትሠርቂ ተያዝሽ?"

"ፍቅር"አለች ብርቄ።እግሮቿን ከነጠላ ጫማዎቿ አውልቃ አልጋው ላይ ከጭኖቿ ጐን ለጠፈቻቸውና ከጉልበቷ ወደ ቁርጭምጭሚቷ እንደገና ወደላይ ደሞ ወደ ታች ... ታሻሻቸው ጀመር፤ አግድም እያየችው ፈገግ ብላ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝም አለ ዋኬኔ ምን ማለት እንዳለበት ተደናግሮት፡፡

"እንዴት አትለኝም?" አለችው ብርቂ ፍቅር ስትሰርቅ እንዴት እንደተያዘች ለማውራት የቸኮለች ይመስል በተቀመጠችበት አልጋ ላይ ቆነጥነጥ እያለች፡፡

"እንደምን አመሻችሁ" አለ አዲስ ደንበኛ ግራ እግሩን አሹሎ፡፡

"ሸቃባ" አለ ዋኬኔ እንግዳው ገብረሚካኤል መሆኑን ሲያይ፡፡ገብረሚካኤል የቀይ ዳማ ነው፡፡ ገብረሚካኤል የሁለት አህያ ጌታ ነው፡፡ ገብረሚካኤል ተጫዋች ነው፡፡ ዋኬኔ አይወደውም፡፡ ገና ሲያየው ጉፈሩ ይቆማል፣እሩጥ እሩጥ ይለዋል፣ጥፋ ጥፋ፡፡ ዛሬ ግን የመጣው ይምጣ አስቀድሞ አምስት ብር ከፍሏል፡፡ከማንም አያንስም፡፡ "ሸቃባ"

"እንዴት ነሽ ቆንጅዬ ... አሀ! አሀ! ዋኩ ዋኬኔ በጊዜ ተጥደሀልና?"አለ ገብረሚካኤል ወደ ቤት ገብቶ ዋኬኔን ሲያይ፡፡

ዋኬኔ ዝም አለ፡፡ነገር ቢጀምር፣ቃላት ቢወራወር ቀድሞ እንደሚፈነከት ተሰምቶታል፡፡ ቆዳው ስስ ነው የዋኬኔ፡፡

ባገኘው እድል ሁሉ የበላይነቱን ከማሳየት የማይሰንፈው ደልቃቃው ገብረሚካኤል ከሶፋው



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ተዝናንቶ ተቀመጠና– "ቆንጂት ..." አለ፡፡ ብርቄም ትሁን ጠጄ፣ደጅ ይጥኑም ትሁን ዘንዬ ያገኛትን ሴት ሁሉ "ቆንጂት" ብሎ ነው ነገር የሚጀምረው፡፡ደስ ያለው ቀንማ ሴት አህያውንም "ቆንጂት" ነው የሚላት– "እሽ ... ሽሽሽ ቀስ ቆንጂት ... ጉድን ... ቆንጂት ..."

"ቆንጂት እስቲ አንድ በዬኝ"

ተቀዳለት፡፡

ቀልጠፍ ባለ አኳኋን ስድስት ብር አውጥቶ ሰጣት፡፡ተቀበለችው፡፡ ተያዩ፡፡ ብርቄ የአረቄውን ጠርሙስ ከመደርደሪያው ላይ አስቀመጠችና አን ዱን ብር ከስሩ ወተፈች ለት፡፡የተቀረውን አምስት ብር ደግሞ ወደ ቦታው፣ ወደ ስፍራው ቁልቁል ባንገቷ ላከችው፡፡

ዋኬኔን ግራ ገባው፡፡

"ሁለቴ?... እዚሁ ቁጭብዬ... ድጋሚ?... እን ዴት ነው ነገሩ? እስቲ የሚከነውን እናያለና" አለ፡፡

"እሺ ... ዋኩ 'ልጅ ይሮጣል እንጂ ...' አሉ በል እንጂ ፉት በለው ደረስኩብህ ኮ፡፡" አለ ገብረሚካኤል አጠር ብሎ ሞላ ያለ አካላቱን በሶ ፋው ወንበር ላይ እያዝናና፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"'አልሰሜን ግባ በለው' ብለዋልም'ኮ፡፡ ደሜኮ ሁለተኛ ነው፡፡አይደል እንዴ ብርቅዬ?" አለ የአ ረቂ መለኪያው ውስጥ ጉድ ያየ ይመስል መለኪ ያውን በሁለት ጣቶቹ ይዞ እያሿሿራት፡፡

ብርቂ ዝም አለች፤ ያልሰማች ይመስል፡፡

"እንግዳው ፈጠን በል በለኛ ... ቆንጅዬ ድግ ሚኝ" አለ ገብረሚካኤል አረቂውን ጨልጦ፡፡ ተቀዳለት፡፡ "ቅጂለት ለሱም ...አታስብ ዋኩ እኔ እስካለሁ ... ጠጣ እንደ ጌታህ ወፍሬጮ"

ዋኬኔ "አይሆንም"ሊል ፈልጐ ነበር፡፡ ግብዣ እዳ ነው፡፡ሁለት ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም ይዞ እዳ መግባት ደግሞ ... ግን አፈረና ዝም አለ፡፡ ተቀዳለት፡፡

"ብስ ... ስስስ" ገብረሚካኤልን አገሳው— ሳም ባው እስኪሟሸሽ፡፡ "ኤጭ...አሁንስ እነዚህ ክትፎ ቤቶች በቅባት ሊገሉን ነው"አለ በስጨት ብሎ፡፡ "እኔም አያርመኝ ... ሳይቸግረኝ ምሳዬን ክትፎ በልቼ ... አግስቶ አግስቶ ትንፋሼን ጨረሰው" ተማረረ፡፡

"ድንቄም" አለ ዋኬኔ በልቡ፡፡ቀን ምሳ ሰዓት ላይ አይቶታል—ከማማ ስንዱ ቤት በልቶ ሲወጣ— ምሳውን ሸኽና፡፡

"እንዴት መሰላችሁ የደከመኝ፡፡ ያ ወስላታ አህያ ጠግቦ ሲያሮጠኝ ዋለ ... አሁንስ ሁሉንም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰባስቤ ሽጨ አንድ ቀልበጭ ያለች ታክሲ ካልገ ዛሁ አልሆነም፡፡"

"እሰይ...እኔ ልቀልበጭ" ንድድ አለው ዋኬኔ፡፡

"ጉረኛ... ሁለት አህያ ተሸጦ ታክሲ ... ገ!" አሰበ፡፡

"ሰው እንዴት እድሜ ልኩን ጭቃ ለጭቃ ሲሮጥ ይኖራል?" አለ ገብረሚካኤል ወደኋላ ተለ ጥጦ እግሮቹን ሰተት አድርጎ ወደፊት ዘረጋና፡፡

የዋኬኔ አይኖች በጭቃ የቦኩ ጫማዎች ፍለጋ ወደ ገብረሚካኤል እግሮች አዘቀዘቁ፡፡

"ከይሲ ... " አለ ዋኬኔ በልቡ፡፡ ገብረሚ ካኤል አዲስ ወተት የመሰለ ሸራ ጫማ አጥል ቋል፡፡ "ለካስ ጫማዎቹን እዩልኝ ኖሯል ነገሩ"

"ውይ ገብርኒ ሽክ ብለህ የለ እንዴ? ... " አለች ብርቄ ገና አሁን ነው ጫማውን ያየች ለት፡፡ "ዛሬ የምርቃት ሳትለኝ መሳቀቅ የለም ... ሙት!"

"አታስቢ እንመራረቃለን" አለ ገብረሚካኤል ፀጉሩን እየደባበሰ፡፡

"ኡፍ ...ወንዶች ላይ እንደጫማ የሚያምረኝ ነገር የለም፡፡ ኡፍ ... አንዳንዶቹማ እንደ አዲስ ቤት ምርግ ቅልጥማቸው ሙሉ በጭቃ ተለውሶ ሲዞሩ ... ኡፍ!" አንገሸገሻት ብርቄን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደ ወንዱ አህያዬ?" አለ ገብረሚካኤል፡፡
"ልክ!" ብርቄ ሳቀች፡፡

ዋኬኔ ቀስ ብሎ ጉንበስ አለ፡፡ ቦት ጫማው በጭቃ ተለውሷል፡፡ "አቤት አምላኬ!" ከጉልበቱ በታች ያለውን ገላውን ጠላው፡፡እግሮቹን የኋሊት አጥፎ ጫማዎቹን ከተቀመጠበት አግዳሚ ወንበር ስር ሊደብቃቸው አሰበና ሲነቃነቅ የባሰ ዓይን እንዳይስብ ሰጋ፡፡ ለዛች ደቂቃ ምትሀተኛ ቢሆን አቤት ደስታው! ... ድራሹን ነበር የሚያጠፋው ያንን ቦት፡፡

"ዋኬ ተጫወት" አለ ገብረሚካኤል፡፡

ዋኬኔ ጨዋታ መቀየር እንዳለበት ተረድ ቷል፡፡ ገብረሚካኤል እያጠቃ ነው፡፡

"ዛሬ ቀን'ኮ ከወንዱ አህያህ ጋር ብቻህን ሳይህ ሴቲቷ ምን ሆናበት ይሆን ብዬ ... አስቤ ..." አለ ዋኬኔ በዚያ በሚያስገመግም ድምፁ የሚናገረውን ሲያስብ ቆይቶ የተሻለ ነገር ቢያጣ፡፡
"አለች አለች ... ምን ትሆናለች ብለህ ነው ... ከቤት ውላ ነው፡፡"

"ሸክሙ ቀርቶ?" አለ ዋኬኔ፡፡

"አይበቃም ብለህ ነው እስከዛሬ የተሸከመ ችው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ታዲያ አሞሩን የቤት እመቤት አድርጊአታ ለሁ አትለኝም፡፡"

ብርቄ ሳቀች፡፡ ዋኬኔን ደስ አለው፡፡

"እርግዛ ነው... ቀኗ ደርሷል፡፡ነገ ከነገ ወዲያ ሳትወልድ አትቀርም"

"ጠርጥሬአለሁ! ...ቀኑንም ይዘኸዋልና...አባት የው ማነው ይባላል?"
ብርቄ ሳቀች፡፡ ገብረሚካኤል ተናደደ፡፡

"ምነው ዝም አልክ በል እንጂ ... ቀኑን ስታውቀው አባቱ ጠፋሀሳ ...?" ዋኬኔ የአረቄውን መለኪያ አንስቶ ጨለጠው፡፡ ሞቅ አለው፡፡

"ምን ይታወቃል ብሰህ ነው እሷ እንደሆን በየወፍጮ ቤቱ ነው የምትውል" አለ ገብረሚካ ኤል፡፡
ብርቄ ሳቀች፡፡
"ቤቶች" አለ አዲስ ገበያተኛ፡፡"
"ይግቡ ... ውይ! ይግቡ አባ" አለች ብርቄ የናቷን የነፍስ አባት ከበር ስታይ ከተቀመ ጠችበት ብድግ ብላ፡፡

"የኔይቱ ... እንደምን አመሸሽ ... እንደምን አመሻችሁ ... በግዜር በግዜር ... " አሉ አባ፡፡
እነ ዋኬኔ ተነስተው ተቀበሏቸው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

አባ መስቀላቸውን ከደረቡት ጋቢ ስር ፈልፍለው አውጥተው አሳለሟቸው፡፡

"እዚህ ይቀመጡ አባቴ" አለ ገብረሚካኤል ሶፋ ወንበሩን ለአባ ለቅቆ ዋኬኔ ጉን ከጣውላው ወንበር ላይ ተዛወረና፡፡ አባ ለሱም የነፍስ አባቱ ናቸው፡፡

"የኔይቱ ...ትርሲተ ወልድ የለችም እንዴ?" አሉ አባ የብርቄን እናት በክርስትና ስማቸው እየጠሩ፡፡

"ዛሬ ስራ ነው'ኮ የምታድር፡፡"አለች ብርቄ፡፡

"አይ! አይ! አይ! የኔ ነገር ተረስቶኛልና ለካ ዛሬ አቦ ናቸው፡፡ድንቅ፡፡" አሉ አባ፡፡ "ለመሆኑ የእግሯ ቁስል ደረቀላት?"

"ኧረ ምንም አልተሻላት ... 'ሰውነቴን ሁላ ብርድ ብርድ ይለኛል' ስትል ውላ ነው በመጨረሻ በግድ ተነስታ የሄደችው" አለች ብርቄ

"ምን ሆኑ እኔ'ኮ አልሰማሁም?" አለ ዋኬኔ፡፡

"ባለፈው ሳምንት ከሰዐት ዝናብ ሲያንጠባጥብ ከውጭ የተሰጣ እህል ልታስገባ ሮጣ ስትወጣ ይሄ ደፉ ጠልፎ ጣላት" አለች ብርቄ፡፡

"ተጐድተዋል?" አለ ዋኬኔ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይ እሱስ ትንሽ ቁስል ነበር፡፡አልድን አለ እንጂ" አለች ብርቄ

"ሰበብ ... ሰበብ ነው እንጂ ሰው በገዛ ደፉ ወድቆ እንዲህ ይሆናል?" አሉ አባ፡፡ "እንግዲ ያማ ... ምን እሰራለሁ ብሄድ ይሻላል... ፈልጊ ያት ነበር ..." አሉአባ በተቀመጡበት ቆነጥነጥ ብለው፡፡

ዝም

"ልጆቼ ደህና ናችሁ ... ገብርዬ ደህና ነህ... አህዮችህስ ... ?"

"ደህና ደህና ... ብርቄ እኛ ከያዝነው ቅጅላ ቸው እንጅ" አለ ገብረሚካኤል አባ እንደማይ ሄዱ ስለገባው ተስፋ ቆረጠ፡፡

"አይ... ይጨልማል ባክህ ... አይመሽብኝም ብለህ?"

"ውጪውም ብርድ ነው ትንሽ ተጫውተው ይሂዱ" አለ ዋኬኔ እመሀል ገብቶ፡፡ ገብረሚካ ኤል ገላመጠው፡፡

"ለወይዘሮ ዘርፊሽዋል ሙቃመት ምነው አላ የሁህ?" አሉ አባ ገብረሚካኤልን በተቀመጡበት ጋቢያቸውን እያስተካከሉ፡፡

"ኧረ ከዚያው መምጣቴ ነው፡፡እንደው ባንተ ያይ ይሆናል"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ነፍሳቸው የዘለዓለም ቤት ትውረስና ያ ልጃ ቸው እንዴት እንዴት አድርጐ መሰላችሁ ሙታ መታቸውን ያወጣው:: ኧረ እንደው ስንት የተባ ረከ አለ በየቤቱ ... ድንቅ!" አሉ አባ::

ገብረሚካኤል የአባ አዝማሚያ አላማረ ውም:: ባገኙት ጊዜ ሁሉ የሙታመት ወይ የሌላ ድግስ ዜና ሳይለግሱት አልፈው አያውቁም:: ታዲያ ለነገር ነው::የዛሬ ሁለት ዓመት የሞተች ውን የባለቤቱን የአስናቀችን ሙታመት ሲደግስ "ተው ገብርዬ... እንዲህ አይደለም... ደንቡ መጓ ደል የለበትም... አንድዬ ባይልላትና ባትሰነብት የወለተ ጊዮርጊስን ሙታመት እንዲህ በቀልድ ...ዋ! አለመታደል ... "እያሉ የነዘነዙት ትዝ ይለዋል::

የዛን ጊዜ ጭንቁ አይነሳ...

ግራ ግብት ሲለው "እንዴት ይሻለኛል አባ?" ይላቸዋል::

"አታስብ ገብርዬ አንድ ገንቦ ጠላና አንድ ድፎ ይበቃል ... ተው እንጂ አንድ ሀያ እንጀ ራማ አስፈላጊ ነው ገብርዬ! ... መቼም ብታን ስም ጠቦት ነገር አርደህ ሳይበዛ ወጥ ብጤ ብታስይዝ...ዋ! የሞተ ተጐዳ...አይ የአንተ ነገር ለፍታት ትንሽ ገንዘብ ማስፈለጉማ አሁን አልተ ጀመረ..."



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይ ...አባ እኔ ይህን ሁሉ አልችልም" ሲላቸው መረር አድርገው "ያ ጉደሎ ደስ አይበለው፡፡ አሁን ማን ይሙት ለዚህ የማትበቃ ሆነህ ነው? ከወለተ ጊዮርጊስ ነፍስ አህዮችህ በለጡ? ለምን እንደጊን አትሸጣትም ገብርዬ? ... ሟች ዘመድ የለው!" ይላሉ ከንፈራቸውን ይመጡና መጽሐፉ– 'ኢታፍቅርዎ ለአለም' ሲል ለዋዛ መሰለህ? 'ወኢዘሀሎ ውስተ ዓለም' ሲል ለፌዝ መሰለህ? 'ወዮልህ ቤት ንብረቴ ብትል 'ማለቱም አይደል?"

ወዲያ ወዲህ ብሎ የተባለውንም ያህል ባይሆን እንደ አቅሙ የባለቤቱን ሙታመት አወጣ፡፡ ታዲያ ከዚያ ወዲህ የትም ያግኙት የት ስለ አንድ "ድንቅ" ሙታመት ደማቅ ስነስርዓት ሳያወሱ አይለቁትም፡፡

"የተባረከ ሲሰጥ እንዲህ ነው ...ድንቅ!" አሉ አባ "ይሄን አይነቱን ብሩክ ነው መጽሐፉ–' ወዘኒ ነበረ በተፋቅሮ ምስለ እግዚአብሔር ይነብር' ያለው፡፡"

"ልክ ነው ... ሁሉ ራሱን በወደደበት ዘመን፡፡" አለ ዋኬኔ፡፡ገብረሚካኤል ገላመጠው፡፡

"ይጠጡ እንጂ አባ ... ቆንጆ ...ማነሽ ብርቄ ድገሚያቸው ...አንዳንድ ብለን በጊዜ ወደ የቤታችን እንከተት፡፡ ልጅቱም ብቻዋን ነች፣ በጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘግታ ትተኛ፡፡"አለ ገብረሚካኤል፡፡ ሁለቱን አሰ ናብቶ ተመልሶ ሊመጣ አሰበ፡፡

"ድንቅ" አሉ አባ "በጊዜ እንውጣላት" አረ ቄአቸውን ጨለጡና ሌላ አስሞሉ፡፡

"ለዋኬኔም ቅጂለት፤ የውጪውን ብርድ አይ ችለውም አለዛ ... " አለ ገብረሚካኤል ቀልጠፍ ብሎ፡፡

ዋኬኔ ተደነጋገረው፡፡ ገብረሚካኤሪ በዘዴ እንደ ህፃን ልጅ በል በል ብሎ አዋክቦ ሊሸኘው መሆኑ ገብቶታል፡፡ 'እቆያለሁ' እንዳይልም ሰዓቱ ረፍዷል፡፡አባስ ምን ይላሉ? እንዳይወጣ ደግሞ ... እንዴት ...? የመጣው ይምጣ አባም ያሻቸ ውን ይበሉ፡፡ ምን ይመጣል? ቢበዛ ቢበዛ ...፡፡ ዋኬኔ ተጨነቀ፡፡

አባና ገብረሚካኤል ድንገት አረቄአቸውን ጨልጠው ብድግ ብድግ ሲሉ ዋኬኔ በተቀመጠ በት ሽቅብ ይመለከታቸው ጀመር፤ ተራ በተራ...

"ኧ...ኧ...እኔ ....ትንሽ እቆያለሁ...ኧ....ማነው ሰው እጠብቃለሁ" አለ፡፡

"የምን ሰው ከመሸ ወዲያ?" አለ ገብረሚ ካኤል በመገረም ዓይነት፡፡

"ኸ ...ኸ" ዋኬኔ ተጠበበ ማምለጫ ፈላለገ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ኧረ ተነስ ... ልጅቷ ትተኛበት ... አባንም አስቆምናቸው'ኮ ... በል እንጂ ..." ገብረሚካኤል አጣደፈው ።

ዋኬኔ ብልጭ አለበት፡፡ተነስቶ ገብረሚካኤልን በዛ በሰፊ መዳፉ በጥፊ ቢያቃጥለው አንጀቱ በራሰ፡፡ ግን ከዛ በኋላ "ምነው?" ቢባል ምን አደረገኝ ሊል?

"የምትጠብቀውም ሰው ካለ ከውጭ ጠብቀው እንጂ ... ከሰው ቤት ...?" አጣደፈው፡፡

"እናንተ ትቆዩ እንደሁ እኔ ልሂድ?" አሉ አባ ፂማቸውን በመዳፋቸው ሉፕሳጉ፡፡

"ኧረ ቆይ እንሸኞታለን፡፡በል አረቄህን ጨል ጥና ተነስ ... አባንም እንሸኛቸው ... ብርቄም በጊዜ ትዝጋ በሯን ... እናቷ እንኳን በሌሉበት... አይደል እንዴ አባ?" አዋከበው፡፡

"ልክ ነህ– ልክ ነህ" አሉ አባ፡፡

ዋኬኔ ተስፋ ቆረጠ፡፡ ከዚህ በኋላ መከራከር 'ቁርጡን እወቁልኝ' ነው፡፡ አባ ደግሞ ከጠረጠሩ ለነፍስ ልጃቸው ለብርቄ እናት ቱስ ማለታቸው አይቀርም፡፡ "ከይሲ!" አረቄውን አንስቶ ጨለ ጠው፡፡ አንጀቱ ተቃጠለ፡፡

"እትዬ ብ–ብ–ብርቄ አለች" አንድ ትንሽ ልጅ አንገቷን በበሩ አስገብታ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ማነው?" አለች ብርቄ ከተቀመጠችበት ተነ ስታ በሩን ከፈተችና፡፡ልጅቷ የገብረሚካኤል ጕረ ቤት የጋሽ ደርቤ ትንሿ ሴት ልጅ ነች፡፡

"አ-አባባ ልኮኝ ነው፡፡ ጋ-ጋ-ጋሽ ገብሬ ካለ ሂጂና ጥ-ጥ-ጥሪው ብሎኝ ነው፡፡" አለች ብርቄን ሽቅብ እያየች፡፡የጋሽ ደርቤ ልጅ ስትናገር ምላሷ ዳንኪራ ይመታ ይመስል ፊደላቷን ረጋግጣ ነው የምታልፋቸው፡፡

"ማነው...ምንድነው?" አለ ገብረሚካኤል ወደ በሩ ጠጋ ብሎ ፡፡

"አባባ እንዳለ ቶ-ቶ-ቶሎ ድረስ...ብሏል...አ-አ-አህያዋን ም-ምጥ ይዟታል...ብ..ብሏል" በሩጫ ተሸክማ የመጣችውን ዝርክርክ መልዕክቷን ቁርጥ ቁርጥ ከሚል ትንፋሿ ጋር አደባልቃ ዘረገፈ ችው፡፡

ገብረሚካኤል ተደናገጠ፡፡ ሊወጣ ካለ በኋላ ዕቃ እንደረሳ አይነት መለስ አለና በሹክሹክታ፥

"ገንዘቡን... አምስት ብሩን" አላት ብርቄን፡፡

"የምን አምስት ብር?"ጠየቀች፡፡ አባና ዋኬኔ ይመለከቱዋቸው ጀመር– ብርቄንና ገብረ ሚካኤ ልን፡፡

"አሀ! ... አ!" ብሎ ወጥቶ ሮጠ ወደ አህ ያው፣ እየተራገመ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ኡፍ...ፍ" ሰውነቱ መለስ አለለት ዋኬኔ፡፡ ተደላድሎ ተቀመጠ፡፡

"ትቆያለህ መሰል ...?" አሉ አባ በቆሙበት ቁልቁል ዋኬኔን እየተመለከቱ፡፡
"አ ... አዎ ትንሽ ..."
"ታመሽ እንደሁ?"
"አይ ... አይ አልቆይም"

"እንግዳው አብረን እናዘግማለን ... እግረ መንገድህን ትሸኘኛለህ" ብለው ተቀመጡ፡፡

ዋኬኔ ብሽቅ አለ፡፡ገብረሚካኤል ሲሄድ አባም ተከትለው ይወጣሉ ብሎ ተማምኖ ነበር፡፡ "በሽታ!"

"ብርቄ..."ብሎ አረቄ አስቀዳ ዋኬኔ፣ለአባም ለራሱም፡፡ ብርቄ መጀመሪያ ለአባ ቀጥላ ለእርሱ ቀድታ ቀና ስትል ሳቅ አለችለት፡፡ ደስ ደስ አለው፡፡ አሁን አባ አንድ ሁለት ብለው ሲሰለቻ ቸው ይወጣሉ ከዛ... ብርቄ...

"እርጉዝ ኖራለችና?" አሉ አባ፡፡
"ማ?" ዋኬኔ በሀሳብ ከሄደበት ተመለሰ፡፡
"የገብሬ አህያ"
"እ...አዎ"
"ሰስት ሆኑለት ማለት ነው..."አሉ አባ ከፊት ለፊታቸው ባለው ግድግዳ ላይ አይኖቻቸውን ተክለው ውስብስብ የሂሣብ ስሌት እንደሚያሰሉ አይነት፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

"እ … እ" አለ ዋኬኔ፡፡አይኑ ብርቄጋ ነው፤ የእርሷም አይን ከእርሱ፡፡ ከዛው ከሰፌው አልጋ ግርጌ ሰብሰብ ብላ ተቀምጣ ታየዋለች፣ ያያ ታል፣ይነጋገራሉ በመላ፡፡

"አሁን ድጋሚ ታረግዛለች …ምን አለ በሉኝ ዋዛ አህያ አይደለችም" አሉ አባ፡፡

"አዎ… ከበረታ" አለ ዋኬኔ አይኖቹን ከብ ርቂ ሳይነቅል፡፡ ፈገግ አለችለት፡፡ ፈገግ አለ፡፡ ሁለመናዋ ቁንጅና ሆኖ ታየው፡፡ 'ያ ነገር እኔና አንተ ብቻ የምናውቀው … ያ' –መስታወት አይ ኖቿ፣ 'በል እንጂ' … ጉጠጉጥ ጡቶቿ፣ 'እስቲ ጫፌን' – ወንዲላ ገላዋ፣… ሁሉም…

"ሀ! ሀ! ሀ! ሀ! ያለች እንደሁ ማቆሚያ የላትም" አሉ አባ፡፡

"ማ?"

"የገብሬ አህያ"

"እ…እንደባለቤቷ"

ዋኬኔ እንደገመተው አባ ሁለተኛዋን መለ ኪያ እንደሸኙ፥

"ዋኬኔ እኔ ብሔድ ይሻላል አንተ ሳትቆይ አትቀርም"አሉ ጋቢያቸውን ወደ ትከሻቸው እየሰ በሰቡ ተነሱና፡፡

ጭጭ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"በሉ ደህና እደሩ ... የኔይቱ ደህና እደሪ ... ታዲያ በጊዜ በርሽን ዘግተሽ ተኚ። ስትመጣ ንገሪያት ለትርሲት መምጣቴን" አሉ።

"እሺ" አለች ብርቄ አባን ለመሸኘት ወጥታ ከበር ቆመችና።

"እ ... ማነሽ የኔይቱ" አባ መለስ ብለው በሹክሹክታ ያወሩ ጀመር ከብርቄ ጋር። ከውጭ ስለሆኑ ዋኬኔ ምን እንደሚሉ መስማት አልቻ ለም።

ዋኬኔ ከተቀመጠበት ሆኖ ብርቄ ገልጣ ከተወ ችው መጋረጃ ጀርባ አልጋው ይታየዋል– አረን ጓዴ ባለሸንተረር ልብስ ለብሶ።ሳያውቀው ከተቀ መጠበት ተነስቶ ወደ አልጋው ሄደ።ብርቄ ተቀ ምጣበት የነበረው ቦታ ለየት ብሎ ይታያል፤ የግማሽ ክብ ቅርፅ ይዞ ጉድጉዶ– የብርቄ ቅርፅ። ዋኬኔ ቀኝ እጁን ሰደድ አድርጎ ዳሰስ አደረ ገው። እንደሞቀ ነው– የብርቄ ሙቀት። ቡጢ የሚያክል ስሜት በደረቱ ሽቅብ ቁልቁል አለ በት።ፊቱን አዞረና ጉድጓዳው ቦታ ላይ ቁጭ አለበት...።

ዋኬኔ ከውጭ የሶስተኛ ሰው ድምጽ የሰማ መሰለው። ወዲያው አዲስ መጤው ወደ ውስጥ ዘለቀ።

"እግዜር ይወድልሀል ... ?! አሁን እግዜር ይወድልሀል የምትሰራውን ስራ...?!" አምባረቀበት



t.me/OLDBOOKSPDF

በብርቱ አልጋ ላይ በተኮፈሰው ዋኬኔ ላይ፡፡ "በዚህ ዕድሜዬ አንተን ፍለጋ በየመሸታ ቤቱ ስቆረቁር ልደር?!" አዲስ መጤው የወፍጮ ቤቱ ባለቤት፣የዋኬኔ ጌታ ምርኩዛቸውን ወደፊት ገት ረው ይዘው በንዴትና በእልህ ወለሉን ወጋ አሁ ንም ወጋ፣ ድልቅ ያደርጉታል፡፡

"ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው የሰው በርበሬ ከቤት ወስዶ ማሳደር?ወይ አንደኛህን እንደዛ ወስ ላታ ሌባ እንደ ነስሮ የደንበኞቼን እህል ከቤት እየወሰድክ ሁለት ሶስት ኪሎ መቀነጣጠብ ጀም ረህ እንደሆን ቁርጡን ንገረኝና መፍትሄውን ልፈይድ ... "

"ኧረ እኔ መሸብኝና ... " ዋኬኔ ጀመረ፡፡

"ተው! ተው! ዘዴአችሁን መች አጣሁት ... ከደንበኞቼ፣ ከሰፈሩ ልታቆራርጡኝ ነው እንጂ፡፡ ከመሸ መጥተው 'በርበሬዬን ውሰድ' ሲሉኝ ሴት የዋ ከየት ላምጣው? ደግሞ 'መሸቶብኝ' ይላል፡፡ የሚመሽብህ ከሆነ ከመጀመሪያው ለምን ተቀበ ልካቸው? ደግሞስ ቢመሽ ከዚያው ከወፍጮ ቤቱ ያድራል እንጂ ያንተ ቤት የአደራ ቤት አይ ደል ..." ሰውየው በንዴትና በእልህ ይንቀጠቀ ጣሉ፡፡

"መንገድ ልቀንስ ብዬ ነው...በጥዋት ጀንበር ላደርስ..."

"ኧረ ጀንበር አትውጣልህ! እውነት ይሄ ጊዮርጊስ እንዳለ ... ደሞ 'ጀንበር' ይለኛል፡፡ ብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥፋተኛው እኔ ነኝ... ለማንኛውም ጠዋት እንነጋ ገራለን:: አሁን ቶሎ ካስቀመጥክበት ስርቻ ሄደህ የሴትየዋን በርበሬ ከቤት አድርስ... ኧከ! ...ከ! ...ከ! ምን ታደርግ... እኔ ነኝ... ምን ታደርግ..." ከፊታቸው ያለውን ሁሉ በምርኩዛቸው እየጠነ ቆሉ ዞረው ወጡ ... ሄዱ::

ዋኬኔ በቆመበት ደርቆ ቀረ::

"አትበሳጭ...አይዞህ" አሉ አባ "'ወትዕግሥት ግብር ፍፁም ባቲ' ይሏል ታገስ የኔ ልጅ::የሰው ገንዘብ መጥፎ ነው:: የኔ ልጅ ወዲያ አድርስና ተገላገል" አባ ያፅናኑት ጀመር:: "'ወንሕነኒ ይደልወነ ንትፋቀር በበይናቲነ ... '" ቀጠሉ አባ "እኛም ከትዕግስት ጋር እንፋቀር ሲል ነው ልጄ ... "

ዋኬኔ ምንም አልተናገረም:: ጨርቅ ቆቡን ከጣውላው ወንበር ላይ አንስቶ ወጣ:: ሁለት ሶስት እንደተራመደ ለብርቄ የሰጣት አምስት ብር ትዝ ብሎት መለስ ሲል ከውስጥ ድምፅ ተሰማው::

"የኔይቱ ... ነይ ወዲህ ..." አባ::

ደንገጥ ብሎ ቆመ ዋኬኔ::

"ቆይ እንጂ ... እንዴ...ኧረ ቆይ በሩን ልዝጋው ... " ብርቄ::

"ድንቅ ..." አባ—::

በሩ ከውስጥ ተዘጋ:: ተቀረቀረ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ዋኬኔ እንዴት ዞሮ መንገዱን እንደቀጠለ አያውቅም፡፡ የሰማውን ማመኑ ከብዶታል፡፡ "አባና ብርቄ?ጉድ ነው! አባና ብርቄ? ..." ይላል አሁንም አሁንም እየደጋገመ፡፡

ከፊት ለፊቱ የሚመጡ አንድ ሴትዮ "ዋኬንዬ እንደምን አመሸህ?" ሲሉት ነው ከእንቅልፉ የባነነው፡፡

"ደህና! ደህና ...ከየት ነው ...ከመሸ...ደህና?" ተደነባበረ፡፡

"አሞኝ ሰንበተ እባክህ ... ጤና ጠፉ፡፡አልቻልኩም ... በል ደህና እደር ዋኬንዬ ..." ብለውት አለፉ፡፡

ዋኬኔ ባለበት ዞሮ ይመለከታቸው ጀመር ሴትየዋን፡፡ ድንጋጤም ፍርሀትም ደስታም ሳቅም ... ሁሉም ተሻሙት፡፡

ሴትየዋ ወደ ቤታቸው ደረሱ፡፡

ሮጠ፡፡ ሮጠ ዋኬኔ፡፡ ከዚያ ስፍራ ጠፉ፡፡ ከጨለማው ውስጥ ገብቶ ተሰወረ፡፡ ሮጠ እየሳቀ—

"አባ! አባባ ቄሱ
ዳቦ ሲቆርሱ
እልም ድልቅ
አለ... ሀ! ሀ! ሀ! ..."

ታየው ቤታቸው ሲደርሱ ሴትየዋ—ትርሲት ወልዱ— የብርቄ እናት—

" ... አባባ ቄሱ
ዳቦ ሲቆርሱ....ሀ! ሀ! ሀ!"

ሮጠ ዋኬኔ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፍርሀት

ግ ... ም እያለ ከሚወርደው ዝናብ ጋር ተዳ ምሮ የሚብረቀረቀው መብረቅ፣ የሚያስገመግ መው ነጐድጓድ የምሽቱን ሰማይ እየሰነጣጠቀ፣ እየበዳደሰ፣ እየደረማመሰ ከመሬት ላይ ሊቆል ለው የቆረጠ፣ የተነሳ ይመስላል፡፡

ምሽቱ ባይገፋም አለቅጥ የሚደበላለቀው ሰማይ ዙሪያውን ጨለማ አከናንቦታል ... ፡፡ ድጋሚ ሰማዩ ከጥግ እስከ ጥግ አፉን ከፈተ ... ሰፌቱ ለቀቀ ... ተተረተረ ... ኗሱው አስደንግጦ እሱው ደነገጠ ... ጮኸ ...

በሕክምና መስጫው ክፍል ግድግዳ ላይ ከፍ ብለው የተገጠሙት ሞለል ያሉ መስታወት መስ ኮቶች ተርገፈገፉ፤ተርበተበቱ፤ በክፍሉ ጣሪያ ላይ በተርታ የተደረደሩት ፍሎረሰንት አምፖሎች እልም ድርግም አሉና ድጋሚ ልብ ገዙ ... ቦግ እልም... ቦግ ብለው መልሰው ነፍስ ዘሩ ...በሩ፡፡

"ይሄ ዝናብ ኤሌክትሪኩን ሊያቋርጠው እንዳ ይሆን ብቻ" ብላ አሰበች ሲስተር ሰሎሜ፡፡

ስራዋን አቋርጣ፣ፊቷን መልሳ ከጀርባዋ በተ ሽከርካሪው የብረት አልጋ ላይ በጀርባው የተን ጋለለውን የአእምሮ በሽተኛ ተመለከተችው፡፡ በነበረበት እዛው በብረቱ አልጋ ላይ ሳይንቀሳቀስ በጀርባው ተንጋሏል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደውጭ በተነፈሰ ቁጥር ኮረፍረፍ እያለ ገር በብ ባሉት ከንፈሮቹ መሀል አስጠሊታ አረፋ ወደ ውጭ ይወጣል፡፡መልሶ ወደ ውስጥ ሲተነፍስ ደግሞ አየር አጥቶ የሚቃትት፣የሚጨነቅ ይመስል የታች ከንፈሩ ወደላይ ተስቦ ከፊት ለፊት ካሉት ገጣጣ ጥርሶቹ ጋር ይጣበቃል፡፡ ከአል ጋው ተርፎ ሊፈስ የተቃረበው ግዙፍ ጥቁር አካሉ የተሰጠውን የዕንቅልፍ ማስተኛ መድሀኒት ተቋቁሞ፣አሸንፎ ከላይ የተደረበችለትን ስስ ነጭ የሆስፒታል ጨርቅ ገፎ ጥሎ፣አፈፍ ብሎ ራቁት ግንዱን የሚነሳ ይመስል ፍርሀት ገባት፤ አተ ኩራ ተመለከተችው፤ ገረመመችው፡፡

ከታች ከበስተግርጌ ከነጩ ጨርቅ አልፈው ብቅ ብቅ ያሉት ሰፋፊ እግሮቹ ከየቁርጭምጭ ሚታቸው ከፍ ብሎ በታሠሩበት የኘላስቲክ ቀለ በት ተከርክረው ከፉኛ ቆስለዋል፡፡

እብዱ ...የአእምሮ በሽተኛው...ይንዘፈዘፋል... ይቆይ ይቆይና እንደገና እንደ ታረደ በሬ ይነዝ ረዋል፣ይመታዋል ...፡፡ ሳይታወቃት አማተበች፡፡

"ካልጠፋ ስራ ለምኖ መኖር እያለ ሰው ከአእምሮ በሽተኞች ሆስፒታል ነርስ ይሆናል?" ትላለች ከጓደኞቿ ጋር ስትጫወት የገዛ ስራዋን እያጥላላች፡፡

በተቻላት መጠን ሀሳቧን አሰባስባ ሀኪሙ እንዲዘጋጅላቸው ያዘዟትን የሕክምና ዕቃዎች ፈጠን ፈጠን እያለች ማዘጋጀቷን ቀጠለች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

መንፈሷ ግን ሲረጋጋላት አልቻለም፡፡ አሁንም አሁንም ዞር እያለች በትከሻዋ ላይ እየተገላመ ጠች ትገረምመዋለች– ከኋላዋ በብረቱ አልጋ ላይ በጀርባው የተንጋለለውን የአእምሮ በሽተኛ፡፡ "እንደ እብድ የምፈራው ነገር የለም..." ትላለች ወሬው ሲነሳ የደስ ደስ የሞላው የሕፃን የሚመ ስል ቆንጅዬ ፊቷን ኮሶ የጠጣች ይመስል አጨ ማዳ፡፡ " ... ሽውራራው ዕድሌ አንቀዥቅዥ ከነ ርሶች ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ሲከተኝ ሰነባ ብቶ እዚህ ከእብድ ጋር ይቀላቅለኛል ብዬ መች ጠረጠርኩ? እኔማ የመሠለኝ... ሆ!... እንደ እብድ የሚያስፈራ ነገር አለ?በስመአብ!"ትላለች፡፡

ሶሎሜ ከነርሶች ማሰልጠኛ ተመርቃ፣ሲስ ተር ተብላ አሁን ያለችበት ሆስፒታል ውስጥ ማገልገል ከጀመረች አራተኛ ወሯን ይዛለች፡፡ ግን መልመድ የሚሉት ነገር ፍፁም አልነካካ ትም፡፡

"ሰው እንዴት ከእብድ ጋር ይላመዳል? ... ዘሎ ካነቀኝ በኋላ የምን መላመድ አለ ... ሆ!" ትላለች፡፡ "አንቺ ደሞ ሁሌ ፈርተሽ እንዴት ነው? መቼ ነው የምትለምጂያቸው?" ሲሏት አብ ረዋት የሚሰሩ ነርሶች፡፡

"አትፍሪያቸው ...ስትፈሪያቸው ነው ጭራሹን የሚዳፈሩሽ" ይሏታል ልምድ ያካበቱት እነ ሲስ ተር አዛሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ የቸገረኝ መፍራቴ ነውእንጂ መች የእብዶቹ መዳፈር ሆነና ... ካልፈራኋቸውማ ቢዳ ፈሩኝስ ምን ቸገረኝ ነበር" ትላለች የታች ከንፈሯን አሞጥሙጣ፡፡

አብረዋት ለሚሠሩ የስራ ባልደረቦቿ ሁሉ መሣቂያ ነች፡፡ እብድ አይታ ጥግ ስትይዝ ወይ ሮጣ ካንዱ ክፍል ስትገባ በሳቅ ፍርስ ይላሉ፡፡

"እንዲህ ሆነሽ እንዴት ልትዘልቂው ነው?" ይሏታል ከፊሎቹ፡፡ "አይዞሽ እኛም መጀመሪያ ስንመጣ እንፈራቸው ነበር...ትለምጂያለሽ" ይሏታል የተቀሩት፡፡ እሷ ግን አልዋጥልሽ ብሏታል "መልመድ ብሎ ነገር ... እብድን? ካነቀኝ ወዲያ...? በስመአብ!" ትላለች ስታስበው መላ ሰውነቷን እየነዘራት፡፡

ያለፈው ሰሞን ሁኔታው እንደማያዛልቃት ስትረዳ፣ የሚለመድ መስሎ አልታይሽ ቢላት ለአስተዳደሩ ቢሮ ማመልከቻ አስገባች፡፡ ወደሌላ ሆስፒታል አለዛም ወደ ሌላ ክፍል እራቅ አድርገው እንዲመድቧት ... አለ አይደል ...ወደ መዝገብ ቤት ... ወይ ... ላቦራቶሪ... ብቻ የትም ይሁን እብድ ወደሌለበት ...፡፡ ቢሆንም እስካሁን ምንም መልስ አላገኘችም፡፡ "...ሆ! ሰው እንዴት ከእብድ ጋር ይኖራል...?"

ድንገት ከጀርባዋ ድምፅ ተሰማት፡፡ ፈጠን ብላ ፊቷን መለሰች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው... ደነገጥሽ? አይ ያንቺ ነገር!" አለች ሲስተር አዛሉ በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ እየገ ባች:: አብረው ነው የሚሠሩት:: ስትመደብም የሲስተር አዛሉ ረዳት ሆና ነው የተመደበችው፣ ሲስተር ሶሎሜ::

"ሆ! ሆ! ..." አለች ሶሎሜ አልጋው ላይ ወደተኛው አእምሮ በሽተኛ ገልመጥ ብላ::

"ሂ! ሂ! ሂ! ..." ሲስተር አዛሉ ሳቀችባት:: " ... የተኛም ትፈሪያለሽ እንዴ ...አይ ሶሎሜ"

"እህ! ለምን አልፈራም ...እብድ መሆኑ ቀረ እንዴ ... እንዳው አያድርገውና ድንገት ቢነ ሳስ...?" ያንን ስስ የቃች ከንፈሯን አሞጠሞጠ ችው::

"ማስተኛ መድሀኒት እንደተሰጠው እያወ ቅሽ ... ?" ሳቀችባት ድጋሚ::

"ው ... ው! ... ሳቂ ሀእ ..."

"ተነስ ብትዪው ቢያንስ ለሚቀጥሉት ሁለት ሰዓታት ንቅንቅ አይልም" አለች ሲስተር አዛሉ ሰዓቷን እየተመለከተች::

"ለማንኛውም ጠንቀቅ ነው ልጄ ...መፍራት አይገልም" አለች ሶሎሜ ያዘጋጀቻቸውን የሕክ ምና መሣሪያዎች በተሽከርካሪ ትሪ ላይ ደርድራ ወደ በሽተኛው እያስጠጋች::



t.me/OLDBOOKSPDF

"በጣም ተጉድቷል አሁንስ ... " አለች ሲስተር አዛሉ ወደ አእምሮ በሽተኛው ተጠግታ የታሰረባቸው የኘላስቲክ ቀለበቶች የከረከሩቸውን፣ ያቆሰሏቸውን ቁርጭምጭሚቶቹን እየተመለከተች፡፡

"ለምንድነው ግን የሚታሠረው ... " ሶሎሜ ጠየቀች፡፡

"የባሰ ነዋ አለበለዚያ ... ራሱን ይጉዳል"

"እሱማ አደገኛ እብድ ስለሆነ... እንደሆነማ ገብቶኛል፡፡ ግን እለ አይደል ... በለስላሳ ነገር ቢታሠር ... ማለቴ ... በጨርቅ ወይ ..." ያዘጋጀቻቸውን የህክምና ዕቃዎች በትሪው ላይ እያስተካከለች ጠየቀቻት፡፡

"እየሽ አንዳንድ እብዶች አልፎ አልፎ አስቸጋሪ ይሆናሉ፡፡ ያን ጊዜ ደግሞ የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ራሳቸውንም እስከ መጉዳት ይደርሳሉ፡፡ የገዛ አካላቸውን ከወለሉ፣ ከግድግዳው ... በቃ ካገኙት ዕቃ ጋር የሚቀጠቅጡ አሉ፡፡ በአካባቢያቸው ሰው ካገኙ የሚተናኮሉም ብዙ ናቸው፡፡ ታዲያ እነዚህ በተለየ ቦታ ተከልለው ካልተጠበቁ እንደው በጨርቅ እራፊ ሸብ አድርገሽ ብትተያቸው ለራሳቸውም ለሌላውም አደገኛ ነው የሚሆኑት፡፡"

"ታዲያ አትፍሪያቸው የምትሉኝ እነዚህን ነው?" ግርም ብሏት ጠየቀች ሶሎሜ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ሂ! ሂ! ... አይ አንቺ ... ሁሉም'ኮ አንድ አይደሉም ሶሎሜ፡፡ የአንዱ ጤነኛ ፀባይ ከሌላው ጋር አንድ እንደማይሆን ሁሉ የእብዶችም እንደ ዛው የተለያየ ነው፡፡"

"እንዴት ... ? ጤነኛ ሌላ እብድ ሌላ"

"እንዴት ብዬ ላስረዳሽ ... ስልጠናችሁ ላይ አልወሰዳችሁትም እንዴ? ... የተለያዩ ናቸው ... አንዱ ምንም የማያውቅ ገና ጡጦ እንዳልጣለ ህፃን ሲስቅ፣ ሲፍለቀለቅ ይውላል፤ ሌላው ጥግ አስደግፈሽው እንደሄድሽ ብትር ቀኑን ሙሉ ከአንድ ቦታ ተገትሮ ሲተክዝ ታይዋለሽ፤ ይህ ኛው ከአምላክ የተላከ መሲህ መሆኑን እየማለ፣ እያነባ ሊያሳምንሽ ይጥራል፤ ያኛው ጥርሱን አግ ጥጦ፣ አይኖቹን ጉልጉሎ የታሠረበትን ክፍል የመዝጊያ ፍርግርግ ብረት ጨብጦ እየነቀነቀ፣ እያንገጫገጨ፣ለሀጩን እያንጠባጠበ ይጉመጅሻል ...ምን ልበልሽ የተለያዩ ናቸው፡፡"

"በስመአብ!" አለች ሶሎሜ ሳይታወቃት፡፡

"እኔኮ አንዳንዴ ለምን ነርስ እንደሆንሽ አይ ገባኝም ..." አለች ሲስተር አዛሉ ራሷን እየነቀነ ቀች፡፡ " ... ግን አይዞሽ ትለምጂያለሽ አትፍሪ ያቸው ... ከስንት አንዱ መሰለሽ አደገኛ የሚሆን ... "

"እህ! ከስንት አንዱ ቢያጋጥመኝስ ... ትቀል ጃለሽ እንዴ?!"



t.me/OLDBOOKSPDF

"አያጋጥምሽ ነው እሱማ ..." ሳቀች ሲስተር አዛሉ፡፡ " ...ግን አደገኛዎቹ ተለይተው ስለሚጠበቁ የት ብለው ያገኙሻል?" አለች በጀርባው የተንጋለለውን የአእምሮ በሽተኛ ገልመጥ ብላ ተመልክታ፡፡

"ቆይ ... ለምሳሌ ይሄ አደገኛ ነው ... አይደል?" ሶሎሜ ከንፈሮቿን ወደ አእምሮ በሽተኛው አሞጥሙጣ ጠየቀች " ... ሆ! ...አጋጣሚ'ኮ አስጠንቅቆ አይመጣም"

"አ ... ዎ ... " ሲስተር አዛሉ አመነታች፡፡ " ... ግን አየሽ የእብዶች ፀባይ እንደ በሽታው ባህሪ ሊለዋወጥ የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ ይሄን ያየሽ እንደሆነ ዛሬ ይደብተዋል ... ነገ አውሬ ይሆናል ... ይቀያየራል ...ግን እርግጥ ሲነሳበት መቼስ ... መጥፎ ነው፡፡"

"ለዚህም ነው የታሠረው ...አይደል ...በቃአ! ... ሆ!" ፌቷ ቅጭም አለ የሶሎሜ፡፡

"እሱስ ልክ ነሽ ያስፈራሉ ...ይሄ ራሱ አንዴ ሲስተር ሳምራዊትን ጉድ ሊሠራት ነበር አሉ... ዘበኞች ደርሰው አስጣሏት እንጂ፡፡ከዛ በኋላ ነው ለብቻው አንድ ክፍል ውስጥ እንዲደረግ የተወሰነው፡፡"

"እንዴት 'ጉድ ሊሠራት' ... ምን አደረጋት?" ተቻኩላ ጠየቀች ሶሎሜ፣ ለማወቅ ጓጉታ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ተይ...ተይ እሱንማ ከነገርኩሽ አንድ ቀንም አትውይ እዚህ ግቢ ... ብቻ ዋናው ነገር አለመ ፍራት ነው"

"እህ! ንገሪኝ እንጂ ... ጭራሹን አስፈራራሽ ኝከ" ወጥራ ያዘቻት፡፡

"ምኑን ልንገርሽ ...? ተነስቶበት ካጋጠም ሽው ሊጉዳሽ ይችላል ... ሊያንቅሽ፣ሊገልሽ ይች ላል፡፡ ደግሞ ሴት መሆንሽን አትርሺ ... የፈለገ ውን ቢያደርግሽ ሰው ካልደረሰልሽ በስተቀር አትታገይው ነገር አውሬ፣ አትቆጪው ነገር ደን ቆሮ ... "

"ይሽውልሻ!... በስመአብ!" ዘገነናት ሶሎሜ፡፡

ያሉበት ክፍል በር ተከፍቶ ዶክተር ዳዊት እንደሁሌው ጣደፍ ጣደፍ እያሉ ገቡ፡፡ስራ ቢበዛ ባቸውም ባይበዛባቸውም ሁሌ እንዲህ ናቸው፣ ቸኮል ቸኮል ማለት ይወዳሉ፡፡

"እቃውን አዘጋጅተሽ ጨረስሽ?" አሏት ሶሎ ሜን ገና በሩን ሳይዘጉ፡፡

"አዎ ዶክተር" አለች ቀጥ ብላ ቆማ፡፡

"አዛለች ቀለበቶቹን ከእግሮቹ ላይ አውልቂ ልኝ ... ፈጠን" ጥግ ወዳለው የእጅ መታጠቢያ ሳህን ራመድ ብለው እጆቻቸውን ይለቃለቁ ጀመር–ሀኪሙ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲስተር አዛሉ ወደ አእምሮ በሽተኛው ተጠጋታ እግሮቹ የተሸፈኑበትን ስስ ጨርቅ ወደ ላይ ሰብሰብ አደረገችና ቀለበቶቹን ማውለቅ ጀመረች፡፡

ወዲያው ሀኪሙ የእጅ ጓንቲአቸውን አጥልቀው ወደ በሽተኛው ተጠጉ፡፡ በእርጋታ አጠናቸው— የበሽተኛውን የቆሰሉ፣ ዙሪያቸውን የተከረከሩ ቁርጭምጭሚቶች፡፡

"በጣም ጉድተውቃል እነዚህ ቀለበቶች" አሉ ሀኪሙ በለሆሳስ ለራሳቸው እንደሚያወሩ አይነት፡፡በመቀስ ጫፍ የቆነጠሩትን ጥጥ ማጠቢያው መድሐኒት ውስጥ እየነከሩ ቁስሉን በጥንቃቄ መጥረግ ያዙ፡፡ ሁለቱ ነርሶች ሀኪሙ የሚፈልጉትን እቃ በተራ እያቀበሏቸው፣ የተጠቀሙበትን እየሰበሰቡ ቆሙ፡፡

ድንገት በሽተኛው በእንቅልፍ ልቡ እንደሚቃዥ ሰው ተወራጨ፡፡

"ስንት ፍሬ ነው የተሠጠው?" አሉ ሀኪሙ ካቀረቀሩበት ቀና ሳይሉ አይኖቻቸውን ብቻ አቅንተው ሲስተር አዛሉን በግንባራቸው እየተመለከቱ፡፡

"አራት ነው ...አራት ነው የታዘዘለት" አለች ሲስተር አዛሉ፡፡ ሀኪሙ እንዳቀረቀሩ ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ ሆኖም አንድ የከነከናቸው ነገር እንዳለ ሶሎሜ ጠረጠረች፡፡ ነገሩ ሁሉ አላምርሽ አላት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በሽተኛው በእንቅልፍ የተደበተ ቢሆንም እረፍት የለሽ ሆነባት፡፡ ክፉ ክፉው ታሰባት “ሆ! … ፈጣሪዬ …”

ሀኪሙ የበሽተኛውን እግሮች አክመው፣መድሐኒት ቀብተው እንደጨረሱ “ሲስተር አዛሉ … እሰሪለት” አሉና ወደ እጅ መታጠቢያው ሳህን አመሩ፡፡

ሲስተር አዛሉ የበሽተኛውን እግሮች በጥጥና በፋሻ አስራ እንደጨረሰች “ወደ ክፍሉ ይመለስ…? ዶክተር” አለች አይኖቿን በሀኪሙ ጀርባ ላይ ሰክታ፡፡

“እ … አዎ … እ … ከምግብ ጋር የሚሠጠውን መድሐኒት ጽፌ ጠረጴዛሽ ላይ አድርጌዋለሁ … እንዳይረሳ፡፡”

ሀኪሙ የክፍሉን በር ከፍተው ወጡ፡፡

ሁለቱ ነርሶች በሽተኛው የተኛበትን ተሽከርካሪ አልጋ እየገፉ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው ሕክምና መስጫ ክፍል ወጡና በረጅሙ መተላለፊያ አልፈው ምድር ቤት ወደሚያወርዳቸው አሳንሰር አመሩ፡፡ድንገት ሀይለኛ መብረቅ ጣለ፡፡ በመተላለፊያው ጣሪያ ላይ በተርታ የተሰለፉት ፍሎረሰንት መብራቶች ድርግም…ብልጭ…አሉ፡፡

“የዛሬው ዝናብ ደግሞ … ሌላ ነው” አለች ሲስተር አዛሉ በሽተኛው የተኛበትን ተሽከርካሪ አልጋ ከፊት ለፊት እየሳበች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጄኔሬተር እንዴት አያዘጋጁም፡፡ ግን ...በሽተኛ ይዞ በኤሌትሪክ ብቻ መተማመን'ኮ ..." አለች ሶሎሜ መብራት ቢጠፋ ህመምተኞችን መጠበቅ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ታይቷት፡፡

"ጄኔሬተርማ አለ ... ግን ያለፈው ሰሞን 'ተበላሸ' ሲሉ የሰማሁ መሠለኝ ... የተሠራ አይመስለኝም" አለች ሲስተር አዛሉ፡፡

አልጋው ላይ ዧ ብሎ የተንጋለለው በሽተኛ ሲነቃነቅ ያየች መሠላት ሶሎሜ፡፡

"እንቺ! ... " አለች ደንገጥ ብላ " ... ኧረ ይሄ ሰውዬ ይነቃነቃል"

"አበደ እንጂ አልሞተ ... እህእ ... ቢነቃነቅ ምን ይገርማል? ላንቺ ሲባል እብድ ሁሉ በድን መሆን አለበት ማለት ነው" አለች ሲስተር አዛሉ እያሾፈች፡፡

"ደግሞ ለምን ልብስ አይሠጠውም ... የህመምተኞች ልብስ?" ሶሎሜ ጠየቀች፡፡ በሽተኛው እራቁቱን መሆኑ ከቅድም ጀምሮ ሲከነክናት የቆየ ጥያቄ ነው፡፡

"መች እላዩ ላይ ያሰነብተዋል ... ወዲያው ነው ቀዳዶ፣በጫጭቆ የሚጥለው" አለች ሲስተር አዛሉ ተሸከርካሪ አልጋውን ወደ አሳንሰሩ በር እያስጠጋች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲስተር አዛሉ የአሳንሰሩን መጥሪያ ቁጭና በሩ እስኪከፈት መጠባበቅ ያዙ፡፡ ወዲያው በሩ ተከፈተና የበሽተኛውን አልጋ እየገፉ ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ ከውስጥ ሰው አልነበረም፡፡

ሲስተር አዛሉ ድንገት መለስ ብላ "ውይ ሶሎሚዬ ... መድሐኒት የታዘዘበትን ወረቀት ረሳሁት ... እታች ጠብቂኝ መጣሁ ..." አለችና ከአሳንሰሩ ክፍል ወጥታ ወረቀቱን ለማምጣት ሮጠች፡፡

የአሳንሰሩ በር ተዘጋ፡፡ ጠባቧን ክፍል የሞላት ደብዛዛ ብርሀን ቅፍፍ አላት ሶሎሜ፡፡ ቶሎ አለችና ምድር ቤት '0' የሚለውን ቁጥር ተጫነ ችው፡፡ አሳንሰሩ ፈልሰስ እያደረገ ከዛ ከፈራችው እብድ ጋር ይዟት ቁልቁል ወረደ፣ ወደ ምድር ቤት፡፡ብዙም አልሄዱ ድንገት ያሉበት የአሳንሠር ክፍል ተንገጫገጨች-"ገም... ገጭ... ከር... ከር... ከርሀ-ከር ..." አለችና ቆመች፡፡ባንድ አፍታ በክ ፍሏ ውስጥ የነበረው ደብዛዛ ብርሀን ውድም አለ፡፡

"ኤሌትሪክ!"

ሰውነቷ ቀዘቀዘ ... አፏ ደም ደም አላት፡፡

በጨለማው ውስጥ ገልመጥ ገልመጥመጥ ብላ ዙሪያዋን ለመመልከት ሞከረች፡፡ነገር ግን በአካባ ቢዋ ጭላንጭል እንኳን አልነበረም፡፡ሳታውቀው፣ ሳታስበው ድቅድቅ ያለ ጨለማ ዋጣት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ መዝጊያው ተጠግታ ለማዳመጥ አሰበች፡፡ ወደፊት ተራመደች– እጆቿን አስቀድማ... ተጋጨች፣ ከእብዱ እግር ጋር ተጋጨች ... እብዱ አቃሰተ!

ለጥቂት ደቂቃዎች ባለችበት ደርቃ ቀረች፡፡ እንደገና እራሷን አረጋግታ ቀስ ብላ ጥግ ጥጉን እየታከከች ወደ በሩ ተጠጋች፡፡ጆሮዎቿን መዝጊያው ላይ ለጥፋ ለማዳመጥ ሞከረች ... ተጠባበቀች ...ነገር ግን ምንም ድምፅ ልትሰማ አልቻለችም ...አሳንሰሩ በሁለት ደርቦች መካከል ታስሮ እንደቆመ ተረዳች፡፡

ድንገት ሰውነቷን ነዘራት ...ፍርሀት፡፡ ደበደበችው በሩን... አቀለጠችው፣ ጡጫ ጨብጣ ደለቀችው ... ግን እሷው ራሷ ከምትፈጥረው ድምፅ ሌላ ምንም መልስ አላገኘችም፡፡

ፊቷን መልሳ የአእምሮ በሽተኛው በተኛበት አቅጣጫ አይኖቿን አፈጠጠች ... ጨለማ...ጨካኝ ጨለማ ... ምንም አይታይም፡፡

"ሿ!" እያለ ከሚወርደው ከዝናቡ የታፈነ ድምፅና እያከታተለ ከሚጥለው መብረቅ ሌላ ዙሪያዋ ባዶ ሆነባት፡፡ ሳታስበው አይኖቿ በእምባ ተሞሉ ... "ፈጣሪዬ!"

ድንገት ከጀርባዋ በአልጋው ላይ የተኛው የአእምሮ በሽተኛ ሲያጉተመትም የሰማች መሠላት...ፊቷን መልሳ በተኛበት አቅጣጫ በደፈናው



t.me/OLDBOOKSPDF

አይኖቿን አፈጠጠች ... ደገመ! ... ትክክል ነች! ሰምታዋለች! ... ደገመ! ... በእንቅልፍ ልቡ ይሁን ወይ ነቅቶ ... ብቻ የተለየ አስጠሊታ ድምፅ አሰማ ... ልቧ ከጡቶቿ ስር ተፈራገጠ ቸባት ... ወደ ኋላ አፈግፍጋ ጀርባዋን በስተቀኝ ካለው ግድግዳ ጋር አጣበቀችና ድምጿን አጠፋች ... ጠበቀች ... ተጠባበቀች ... የአሳንሰሩ ክፍል ድቅድቅ ጨለማ ስለዋጣት የአእምሮ በሽተኛው ይነሳ አይነሳ ማረጋገጥ አልቻለችም:: መዳፏን በአፏና በአፍንጫዋ ላይ ጭና በተቻላት አይኖቿን ቡርቅቅ አድርጋ ከፍታ ተጠባበቀች... የአእምሮ በሽተኛው አስፈሪ ድምፅ ግን ተመልሶ አልመጣም::

ሲሰተር አዛሉ ያለቻት ቅዝ አላት-"ተነስ ብትይውም ለሚቀጥሉት ሁለት ስዓታት ንቅንቅ አይልም::"

ስዓቷን ወደ አይኖቿ አስጠግታ ለመመልከት ሞከረች:: ነገር ግን ድቅድቁ ጨለማ ያለርህራሄ ጋረዳት... ለመገመት ሞከረች "...'ግማሽ ስዓት?... ይበልጣል እንደዛ ካለችኝ ... ቢያንስ አንድ ስዓት አለኝ ማለት ነው ... ከዛ በፊት ኤሌትሪኩ መምጣት አለበት .... የግድ መመለስ አለበት!... ባይመጣስ? ... ፈጣሪዬ!"

ሰውነቷ ከፉኛ ይንቀጠቀጥባት ጀመር::

ደቂቃዎች አለፉ:: በአልጋው ላይ የተንጋለ ለው እብድ ድምፅ ግን ጠፋ:: 'ባይነሳ ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

እንጂ ቢነሳ እስካሁን ...' ብላ አሰበች፡፡ እርዳታ መጣራት እንዳለባት ተረዳች፡፡

በጠባቧ ክፍል ጣሪያ ላይ ለአየር ማስገቢያ ተብላ ወደተሠራችው፣ቀዝቀዝ ያለ አየር ወደም ታስገባው ክፍተት ፊቷን አቅንታ የሞት ሞቷን ድምጿን አስረዝማ 'እሪ!' አለች፡፡ የገዛ ድምጿ ተመልሶ እሷኑ አስደነገጣት፡፡ ከጣሪያው ጋር ተጋጭቶ የተመለሰው የገዛ እራሷ ዋይታ ከወለሉና ከግድግዳው ጋር ሲላተም ጠባቧ የአሳንሰር ክፍል ተናጋች፡፡

ድጋሚ ለዕርዳታ ለመጣራት ፈራች ... ስትጮህ፣ ስትጣራ፣ 'እሪ!' ስትል አጠገቧ በብረት አልጋ ላይ የተንጋለለውን እብድ የምትጠራው፣ የምታነቃቃው፣ የምትቀሰቅሰው መሠላት፡፡ ዝም አለች፡፡ ... የምታደርገው ሁሉ ተደበላለቀባት ... ለመጸለይ ፈለገች ...እንዴት እንደምትጸልይ ግን ጠፋት ... እምባዋ ብቻ ይወርድ ጀመር ... ድም ጿን አጥፍታ ታለቅስ ጀመር ... ፍርሀት አጥንቷ ገባ ... ፡፡

የነበሯት ሁለት ምርጫዎች አስፈሩዋት—ጮሀ እርዳታ መጣራትና ምናልባትም አጠገቧ አልጋ ላይ የተጋደመውን የአእምሮ በሽተኛ መቀስቀስ ወይም ድምጿን አጥፍታ ኤሌክትሪኩ እስኪመጣ መጠባበቅ ... ሁለተኛውን መረጠች፡፡ቀዝቃዛውን የብረት ግድግዳ ተደግፋ ኤሌክትሪኩ ሳይዘገይ በቶሎ እንዲመጣ በተስፋ ትጠባበቅ ጀመር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በቆመችበት ጊዜውን ለማስላት ሞከረች፡፡ እያንዳንዷ ደቂቃ ባለፈች ቁጥር በአእምሮ በሽተ ኛው አካል ውስጥ ያለው የማስተኛ መድሀኒት እየሳሳ፣እየደከመ፣እየሞተ እንደሚሄድ ስታስብ ... እብዱ ... የአእምሮ በሽተኛው እየነቃ እየተነቃቃ እንደሚሄድ ስታስብ ...ጉልበቶቿ ይንቀጠቀጡባት ጀመር፡፡ መላ አካላቷ በላብ ተዘፈቀ፡፡

አንድ ሐሳብ ብልጭ አለላት፡፡ ሰዓቷን ወደ ጆሮዎቿ አስጠግታ ያዘቻት- "ቲክ-ቲክ-ቲክ-ቲክ- አንድ-ሁለት- ሦስት- አራት-" ሴኮንዶች ደቂቃ እየሞሉ፤ ደቂቃዎች እየተነባበሩ፣እየተከማቹ ሳት ወድ በግድ እየተጠራቀሙ ሄዱ... አምስት ደቂቃ ... አስር ... አስራ አምስት... ሀያ... ኤሌክትሪኩ ግን አልተመለሰም፡፡

" ...ቲክ-ቲክ-ቲክ-ቲክ... " ሰላሳ... ሰላሳ አምስት ... አርባ ...፡፡ እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ይኾረጉደ ጉድ ጀመር ... ፡፡ ወገቧ ከወረቀት እንደተሰራ ሁሉ ተልፈሰፈሰባት፡፡

ድንገት ድምፅ ተሰማት ... "እህ ...!" አለ፤ እብዱ አቃሰተ! ቅድም በአልጋው ላይ ተንጋሎ ያየችው ግዙፍ ጥቁር አካሉ፣ እራቁት አካሉ መጥቶ ፊቷ ላይ ድቅን አለባት ... ትንፋሿን ውጣ ባለችበት ደርቃ ቆመች ... አየር መሳቧን እንኳን አቆመች ... ደገመ! የበላውን እንደሚያጣ ጥም ሰው አፉን ሲያላውስ ተሰማት ... የጨርቅ ሿሿቴ ተከተለ ... በተቻላት በጨለማው ውጥስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገላዋን ወደ ኋላ ገፍታ ከብረት ግድግዳው ጋር አጣበቀችው...፡፡

"አ-አ ... እ!" ጮኸ ...፡፡ እብዱ ተነሳ ... "አ-አ ... አ!" ጮሆ አቃሰተ እብዱ ... የተኛ በት አልጋ ተንቋቋ ተንሳጠጠ ... "አ-አ ...አ! ሲስተር!" ተጣራ ... አልጋው ተንፏቀቀ ... አሁ ንም ተንፏቀቀ ... ያች ስስ ጨርቅ እየተንኟ ኟች፣ እየተንሸራተተች ከመሬት ስትወድቅ ተሰ ማት፡፡ አሁንም በተቻላት ወደ ግድግዳው ተለጠ ፈች ... በጠፍጣፋው የብረት ግድግዳ ውስጥ ልትሰምጥ ትችል ይመስል ሰውነቷን ወደ ኋላ ገፋችው ... አጠበቀችው፡፡
"አ- ኦ...ኦ!" አጓራ፡፡

የተኛበት አልጋ ተንፏቀቀ፣ ተገፋ፣ተገፈ ተረ ... ወደፊት ተንሸራቶ ከጠባቧ ክፍል በር ጋር ሲጋጭ፣ሲላተም ክፍሏ ተናጋች...
"አ-አ ... አ!" አቃሠተ፡፡

'ጨ፟ርርር ...ር' የሚል ድምፅ ተሰማት ... ጆሮ ዎቿን አቁማ ድምጹን ለመለየት ሞከረች ... እብዱ እየተፀዳዳ ነው!ይተሻሽ ጀመር፤ ይንፏቀቅ ጀመር፤ ዙሪያውን ይዳብስ ጀመር ... ድምጿን አጥፍታ በጆሮዎቿ ተከተለችው ... ፡፡ የጠባቧን ክፍል ግድግዳ በመዳፎቹ እየዳበሰ፣ እያሰሰ፣ እያ መሰ ሲጠጋት ተሰማት ... ፡፡ ድምፁ— ኟኟቴው እየቀረበባት መጣ፡፡ ... በቀስታ ወደ ግራዋ ለመን ፏቀቅ ሞከረች ... ለመሸሽ ጣረች ...ድምፁ ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

እየተጠጋች፣ እየቀረባት መጣ ...፡፡ አሁንም ወደ ግራዋ ተንፏቀቀች ... ከአልጋው ጋር ተጋጨች... የብረቱ አልጋ ተንሸራቶ ከአንድ ነገር ጋር ተጋጨ፡፡

"አ-አ... አ!" አቃሠተ እብዱ፡፡ "...ሲስተር! ...ሲስተ ... ር!"

ደረቷ ሲዳበስ ተሰማት ... እብዱ! ...ጭኖቿን ቀዘቀዛት...

ደብዛዛ ብርሀን ጠባቧን ክፍል ሞላት ..."ገጭ ...ገጭ...ከር-ከር" አሳንሰሩ ተንሸራተተ ቁልቁል...

ተያዩ፡፡

የአእምሮ በሽተኛው ከፊት ለፊቷ አንድ እር ምጃ ያህል ራቅ ብሎ እራቁቱን ቆሟል ... ተመ ለከታት ... አፍጥጦ አያት ... አይኖቹ ደም ጉር ሰዋል ... ለሀጩ ከአፉ ወርዶ አገጩ ላይ ተንዘ ላዝሏል፡፡ ከወገቡ በታች ያለ አካሉ በገዛ እራሱ ቆሻሻ ተበላሽቷል ... እጆቹን ወደፊት ዘረጋ– እብዱ...፡፡

... ተሸማቀቀ ...

"ሲስተርዬ ...አይለምደኝም... አልረብሽም ... አትውጊኝ ... መርፌ አትውጊኝ ..." ወደኋላው ኩምሽሽ አለ፤ የአእምሮ በሽተኛው በፍርሀት እየተቁለጨለጨ ...

አሳንሰሩ ቆመ ... በሩ ተከፈተ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# መሐመድ አሊ

(1958 ____ )



መሐመድ ዓሊ በአማራ ብሔራዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን በደብረሲናወረዳ በ1958 ተወለደ፡፡ የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በወግዲ እና በቦረና ከተከታተለ በኋላ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ በባችለር ዲግሪ ተመርቋል፡፡ ከዚያም ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ተመድቦ በኤዲተርነት አገልግሏል፡፡ አሁንም በሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል በሙያው በመስራት ላይ ይገኛል፡፡.

መሐመድ ዓሊ አጫጭር ልቦለዶችን በመጻፍ ይታወቃል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለ አጫጭር ልቦለድ በመጻፍ እጁን ካፍታታ በኋላ በ1982 "ወይራ ሥር" የተሰኘ የአጫጭር ልቦለዶች መድበል አሳትሟል፡፡በልዩ ልዩ መጽሔቶች የታተሙ፤በሬዲዮ የተተረኩ ለውድድር ቀርበው ሽልማት ያስገኙ አጫጭር ልቦለዶች አሉት፡፡ ከፈጠራ ድርሰቶቹ በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መድረኮች በፈጠራ ድርሰቶች ላይ ጥናታዊ ጽሁፎችንም አቅርቧል፡፡ "ሒሳብ" የተሰኘው አጭር ልቦለዱ በዚህ መድበል ውስጥ ተመርጦ ይገኛል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሐሳብ

ጋዜጠኛው ጨፌ ረፋዱ ላይ አለቃው ቢሮአቸው ድረስ አስጠርተው ለመስክ ሥራ ካዘዙት ጀምሮ እንዳሰበ አለ፡፡ ለነገሩ በጋዜጠኝነት ሞያ ከአስር ዓመት በላይ አለው፡፡ ግን ነገረ ስራው እንደጀማሪ ጋዜጠኛ የመስክ ሥራ ያሳስበዋል፡፡ ሻይ ሲጠጣ ያስባል፣ ሲበላ ያስባል፣ ሲሄድ ያስባል፣ ምናልባትም ተኝቶም ያስብ ይሆናል፡፡ ይኸ ነገር ምናልባትም የጋዜጠኞች ሁሉ የጋራ ባህሪም ሊሆን ይችላል፣ ተራኪው አያውቅም፡፡

ጨፌ አእምሮው ስለመስክ ሥራው እያሰበ እጅና እፉ በደመ–ነብስ ምሳቸውን በልተው መርካቶ ደርሶ የተሳፈረበት ታክሲ ነጅ ጉዞ መጨረሱን ሲያረዳው ሁሉ አካሉና ነብሱ እንደ ተለያዩ ነበሩ፡፡ እዝነ ህሊናው ስለሴተኛ አዳሪ፣ ስለሸርሙጣ፣ ስለ የቡና ቤት ሰራተኛ ምንነት፣ አይነትና ልዩነት እያገዘፈ ሊያማየው እየሞከረ አእምሮው ደግሞ መረዳት እያቃተው ወረደና አቅጣጫውን በአዲስ ከተማ ት/ቤት ጥግ ባለው ጠባብ መንገድ አደረገ፡፡

ወደላይ ዘልቆ ጉልቱ አካባቢ ሲደርስ ግራ ተጋብቶ ባለበት ቆሞ ወደየት እንደሚሄድ ፀጉሩ ሁሉ አልቆ ፊተ ሰፊ ያስመሰለውን በራውን እያከከ በማሰላሰል ላይ እንዳለ "ሃይ!ያራዳ ልጅ ..." የሚል ድምፅ በስተግራው በኩል ሰማ፡፡ ድንጋጤውንና ውስጡ ያደረበትን ለመቆጣጠር እየታገለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከቀኝ ወደግራ ሰው እንደሚጠብቅ አይነት ቃኘት ሲያደርግ አይኑ አንዲት ወጣት ላይ አረፈ፡፡

ልጅቷ ከስፖርተኛ ቁምጣ ባነሰ ጥቁር ሚኒስ ከርት ተጠፍራለች፡፡ ከሚኒስከርቱ ሥር ከብር ቁካን ልጣጭ የተሰራ የሚመስለው ቀይ ሰውነቷ አይን ያልባል፡፡ ከላይ ለጨፈ የተፈጥሮ ይሁን ሰው ሰራሽ ለጊዜው ግልጽ ያልሆነለት ፀጉር እስከ ትጥቋ ድረስ አልብሶታል፡፡ ከፀጉሯ ሥር ቀጭን መስመር በመሰለ ደማቅ ቅንድብ፣ እንደ ውሃ ውስጥ እንቁ በሚያበሩት ትላልቅ አይኖችና ከላይ ወፈር ከታች ጎመድ ባለ አፍንጫ የደመቀ ክብ ፊት ይታያል፡፡ አንገቷ ላይ እንደወራጅ ምንጭ ከሚብለጨለጨው ሃብል በታች ለመፈን ዳት የንፋስ ወለብታ የሚበቃቸው የሚመስሉ ጡቶችዋን አፍኖ የያዘ፣ደረቷ ላይ አፉን የከፈተ አንበሳ ምስል ያለበት ስስ ከናቴራ ለብሳለች፡፡

መንገድ ላይ ቆሞ በመገረም ልጅቷን ሲያጠ ናት ሰውነቱ አዲስ እንደፈነዳ የጠበል ምንጭ እንፋሎት ይተፋ ነበር፡፡ በራው ላይ እንደጧት ጤዛ የኳተሩትን የላብ እንክብሎች በግራ እጁ እየጠረገ ተጠጋት፡፡እሷም ጥርሷን ገለጥ አድርጋ በአይንዋ ተከተለችው፡፡ በግራ በኩል የተከለችው የወርቅ ጥርሷ ለጨፈ ብዙ መልዕክት ያስተላ ለፈለት መሰለው፡፡ አጠገቧ ሊደርስ አንድ ሦስት ርምጃዎች እንደቀሩት ልጅቷ ፊቷን ወደ ኋላ አዙራ እየተውረገረገች በቀስታ ጉዞ ጀመረች፡፡ ቀለል ብሎት ተከተላት፡፡ እሷ ከፊት እሱ ከኋላ እየተከላት ተመራርተው ቤት ገቡ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ክፍሏ የሆድዋን ጥበት በቁመቷ ያካካሰች ትመስላለች፡፡ በራስዋ ከዋናው በር ሰፋ ብላ ወደ ውስጥ እየጠበበች እየጠበበች ትሄዳለች፡፡ መካከል ላይ በመጋረጃ ባትቋጠር ኖሮ የግራና የቀኝዋ ግድግዳዎች እየተቀራረቡ ሄደው በመጨረሻ ላይ ሳሳሙ አይቀሩም፡፡

ልጅቷ ምንም ቃል ሳትተነፍስ ከመጋረጃው ወዲህ ባለው ያረጀ ሶፋ ላይ ጨፌ እንዲቀመጥ በሚፍለቀለቁ አይኖችዋ ጋብዛው ደብል ጅን ቀድታ አቀረበችለት፡፡ ጨፌ ሰውነቱን ብርክ ብርክ አለው፤ ልቡ ብቻዋን ደረቱ ውስጥ ስትደ ልቅ ተሰማው፡፡ ልጅቷ ተመልሳ ፊቷን በስተቀኝ በኩል ባለው የመጋረጃ ጠርዝ አዙራ የሆነ እቃ ስታንኳኳ አይኑን ዳሌዋ ላይ ተክሎ ወደ ውስጥ ኪሱን አሰበው፡፡ ለጊዜው ከምሳ የተረፉ ስድስት ብሮች አገኘ፡፡ እውነት ይሆን? አለና ሊያረጋግጥ ቀስ ብሎ እጁን ኮቱ ኪስ አስገባ፡፡ የእጅ መዳፍ የምታህል ጠፍጣፋ ነገር ተቀበለው፡፡ “ምንድነው ደግሞ ይኸ?” አለ ለራሱ፡፡ በመጠኑ ከኪሱ ወጣ አደረገና የሰላች አየው፡፡ የጋዜጠኛ ቴፕ ነበር፡፡ በራሱ ለራሱ በውስጡ ሳቀ፡፡

“ሰው እንዲህ መሆኑን ሲያውቅ ለምን ከቤቱ ይወጣል? ካለበት በገመድ ተጎትቶ አልመጣ! ኤጭ—፡፡ በህይወቴ ፈሪ ወንድ አልወድም ይደብ ረኛል” እያለች የተበረዘ ለስላሳ ይሁን ሌላ ብቻ ጨፌ ሊረዳው ያልቻለ ቁመቱ አጭር ሆዱ ሰፊ በሆነ ብርጭቆ ይዛ ከፊት ለፊቱ ካለው ሶፋ ላይ በቁሟ ወደቀች፡፡ የስፖርት ቁምጣ በመሰለ ሚኒ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስከርት ሥር ያለው የሰውነቷ ክፍል ለጨፌ ግልፅ ሆኖ ታየው፡፡ አይኖቹን ወደቀረበለት ብር ጭቆ ሰበራቸው፡፡

"እኔ እንጃ! ብቻ ስንት ሺህ ብር አውጥቶ ለሚገዛው እቃ በአምስት፣ በአስር ሳንቲም ሲከራ ከር ጊዜ የሚያጠፋ ሰውና ስሜቱ እየፈለገ ራሱን ደርሶ አይናፋር የሚያስመስል ወንድ ሳይ ያቅረ ኛል" አለች ልጅቷ፡፡ አነጋገሯ ለጨፌ ወይም ለራሷ ወይም ለሌላ እሷን ለሚታያት ለጨፌ ግን ስውር ለሆነበት ሰው ይሁን አይታወቅም፡፡

ጨፌ የግድ ከቀረበለት ጅን በሀይል ሳበለ ትና መልሶ አስቀመጠው፡፡

"ይቅርታ ወንድም አላስመረጥኩህም፡፡ ቤት ውስጥ ያለው ይኸ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ቢሆንም ለፈሪ ፍቱን መድሃኒት ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ደረቅ ጅን የሞተ የሚያስነሳ፣የፈራን የሚያጠነክር ልዩ ወተት ነው" አለች፤ ጨፌ ሲጠጣ የሰውነቱን መሸማቀቅ አይታ፡፡

"አዎን ቆንጆ ክኒን ነው" ሲል ሀሳቧን መቀ በሉን መሰከረላት፡፡ልጅቷ መጠጧን በአንድ ትን ፋሿ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ወደ ውስጥ አስገባችና ስዓቷን እያየች "ታዲያ እንዴት ነው? ወንድም?" ስትል ጠየቀችው፡፡

"ስለ ምኑ?" ሲል ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰ ላት፡፡ ለነገሩ ለጨፌ የልጅቷ ጥያቄ ግልጽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር:: ግን ግን በብዙ ምክንያቶቹ ዝግጁ አልነ በረም::

ርቃኑን የቀረ ፍም የመሰለ ቀይ የግራ እግ ሯን አንስታ ሌላኛው ላይ እያነባበረች፤ በአንገቷ ወደ መጋረጃው እየመለከተች "ምን ልበልህ? ልብስ እጠብ ወይስ ውሃ አሙቅ?" አለችው::

"እኔ ለሱ አልመጣሁም"አላት::ምንም እንኳ በእዝነ–ህሊናው የሠራ አካላቱ ሁሉ ከእርሷ ጋር ቢሆንም መናገር የሚችለው ይኸንኑ ነበር::

"ታዲያ ቀጠሮ ልትወስድ ነው?" ስትል ንግ ግሯን በሳቅ አጅባ ጠየቀችው::

"ጋዜጠኛ ነኝ" አላት::

"ሁና! እሱ የራስህ ችግር ነው:: ለኔ እንኳን ጋዜጠኛ ለምን ፕሬዚዳንት አትሆንም! ወይስ ጋዜጠኛ ስሜት የለውም?":: እንደ ማፈር ብሎ "እንደሱ ሳይሆን ..." አለና ለምን እንደመጣ ተረከላት::

ስዓቷን አየችና "በቃ የኛ ጋዜጠኞች መጨ ረሻ ይኸው ነው ማለት ነው" አለች::

"ማለት የፈለግሽው አልገባኝም?"

"ባገሪቱ ሥራ ጠፍቶ እኛ ጋ ስትመጡ ገር ሞኝ ነው:: ለማንኛውም ይኸ እኔን አይመለከ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትም፡፡ የፈለከውን ጠይቀኝ" አለችው ሰዓቷን እያየች፡፡

ደስ እያለው ከኪሱ ቴፑን አወጣ፡፡

"እንግዲህ መጀመራችን ነው ልብ በይ" አላት፡፡

"ልብ ብያለሁ" አለችው፡፡

"ወደዚህ እ-ወደ- እ-ሴ- - -ተኛ አዳሪ" ብሎ ምን ብሎ እንደሚጨርሰው ግራ ተጋባና ቀና ብሎ አያት፡፡

"ሴተኛ አዳሪነት ካሻህም ሽርሙጥና አትለ ውም፤ምን አስፈራህ፡፡እኛ ደስ ብሎን እየኖርነው አይደል! 'አንቺ ሽርሙጣ' ሲሉን እንዴት እንደ ምንደሰት ባየህ!" አለችው፡፡

"ኖ ኖ አልፈራሁም፡፡ ቴፕ መስራቱን እያረ ጋገጥኩ ስለነበር ነው፡፡ እና ወደዚህ የ—የሴተኛ አዳሪነት ኑሮ እንዴት እንደገባሽ ባጭሩ ለአድማ ጮቻችን ብትገልጭልን" አለ፡፡

"የምን አድማጮች" አለችው እየሳቀች፡፡

"በሬዲዮ ስለሚቀርብ ነው" ሲል አስረዳት፡፡ እግረመንገዱንም በመገናኛ ብዙሀን ለህዝብ እንደ ሚያቀርበው እንድታውቀው ስለፈለገ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

"መልካም ለነገሩ ሴተኛ አዳሪ መቼ እንደሆንኩ አላውቀውም፤ ላውቀውም አልፈልግም" አለችው፡፡

"ለምን?"

"አንተን ለምን ይመስልሃል? አንድ ሰው ለምን ጋዜጠኛ ይሆናል?"

"በአጋጣሚ ወይንም ወዶት ሊሆን ይችላል" ሲል መለሰላት፡፡

"ታዲያ በአጋጣሚ ወይስ ወድጀው ልበልህ?"

"እሱንማ የምታውቂው አንቺ ነሽ"

"እንደማላውቀውማ ነገርኩህ፡፡ አንተ ማወቅ ያለብህ ወድጄውም ይሁን በአጋጣሚ ሴተኛ አዳሪ ወይም ሽርሙጣ መሆኔን ነው፡፡"

"ኖ! ኖ! እንደሱ አይደለም፡፡ የኔ እ ...በነገራችን ላይ ስምሽን አልነገርሽኝም"

"ሳትጠይቀኝ እንዴት ልነግርህ እችላለሁ?" አለችው እየሳቀች፡፡

"ልክ ነሽ፣ መጠየቅ ነበረብኝ፣ ይቅርታ፡፡ አሁን ልትነግሪኝ ትችያለሽ?"

"ከጠየከኝ አዎ፣ ፀደንያ እባላለሁ"



t.me/OLDBOOKSPDF

እንግዳ ስም ነበር፡፡ ጨፌ ቃሉን ደጋግሞ ጠራውና "ፀደንያ ነው ያልሽኝ?"ሲል ጠየቃት፡፡

"አዎን፣ ፀደንያ" ስትል መለሰችለት፡፡

"እንዲህ አይነት ስም ስሰማ የመጀመሪያዬ ነው፡፡ ለመሆኑ ምን ማለት ነው?" አላት፡፡

"ስሜ መሆኑን እንጂ ትርጉሙን እኔም አላ ውቀው፡፡ ለኔስ ስምህን አትነግረኝም፡፡"

"ጨፌ" አላት፡፡

"ጨፌ-ጨፌ ምን ማለት ነው?" አለችው ፈገግ ብላ፡፡

"እኔም አላውቀው! ስሜ ከመሆኑ በስተቀር" ሲል መለሰላት፡፡

"ብድር መከፈሉ ነው?"

"አይደለም ፀ-ፀደኒያ! ...ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስና ቅድም እንዳልኩሽ መንግስት የሴተኛ አዳሪዎችን ችግር አስተማማኝ መፍትሔ ለመስ ጠት ለሴትኛ አዳሪነት መነሻ የሆነውን ማህበራዊ ቀውስ ማወቅ ይፈልጋል፡፡የችግሩ ምንጭ ታውቆ ካልተዳፈነ የቱንም ያህል ጥረት ቢደረግ ተመ ልሶ ያው ነው" ሲል እንዴት ወደዚህ ሕይወት እንደገባች እንድትነግረው የፈለገበትን ምክንያት ሊያስረዳት ሞከረ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"አይመስለኝም፡፡ለምን መሰለህ፤ የሴተኛ አዳሪነት መነሻው ከተዳፈነ አገሪቱ መተዳደሪያ፤ ታጣለች፣ባለስልጣኖቹም ይደኸያሉ" አለችው፡፡

"እንዴት" ሲል በመገረም ጥያቄ አቀረበላት፡፡

"አየህ፣ሴተኛ አዳሪዎች ከሌሉ እኛን የሚፈልጉ የውጭ አገር ሰዎች ስለማይመጡ ከቱሪዝም አትደምቅም፤መንግስትም እርዳታ አያገኝም፤ባለስልጣኖቹም የገቢ ምንጫቸው ይደርቃል፡፡ ይኸን ደግሞማንም አይፈልግም፡፡እብድ ቢሆን እንኳ፡፡"

"ዐደንያ ትክክል አይደለሽም፡፡ መንግስት..." ብሎ ሀሳቡን ሳይጨርስ፦

"የኔ ወንድም ሌላ ጥያቄ ካለህ ጠይቀኝ፡፡ ያልኩህን በሚመለከት የፈለከውን ማለት ትችላለህ፡፡ መብትህን አልከለክልህም፡፡ ግን ለኔ አይደለም፡፡ይቅርታ!" አለችና ሰዓቷን አየች፡፡

"መልካም ካልፈለግሽው ይቅር፡፡ ለመሆኑ በቀን ከስንት ሰው ጋር ትተኛለሽ?"

"እኔ እንጃ፣አላውቀውም፡፡ ከአንድ፣ከሁለት፣ ከአስርም ሰው ጋር ሊሆን ይችላል፡፡ልልህ የምችለው ገንዘብ የሚከፍል ወንድ አግኝቼ መልሼ አላውቅም፡፡"

"መቶም ቢሆን"? አላት እየሣቀ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከተገኘ ለምን ሚሊዮን–ቢሊዮን አይሆንም፡፡"

"መልካም፤ የወቅቱን ሁኔታ መቼም ከኔ ይበልጥ ታውቂዋለሽ፡፡ኤድስ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ነው፡፡ ባንቺ በኩል እንዴት ነው የምትከላከይው?"

"ይኼን ያህልም አስቤበት አላውቅም፡፡ የኔ ሥራ የደንበኞቼን ፍላጎት ማርካት ከዛም ፍሉስ መቀበል ነው፡፡ በሽታ ፈርቶ ኮንዶም መጠቀም የፈለገ ይጠቀማል፤ ያልፈለገም እንደምርጫው ይስተናገዳል፡፡" አለችና ራሷን ነጠር አድርጋ ፀጉሯን ወደ ኋላ መለሰችው፡፡

"ይኼኮ የህይወት ጉዳይ ነው?"አላት ስቅጥጥ እያለው፡፡

"ባይገርምህ እኔ ለህይወቴ ይኼን ያህል ተጨንቄ አላቅም፡፡ እስካለሁ ድረስ ገንዘብ ማግኘት አለብኝ፡፡ ከሞትኩም ተገላገልኩ፡፡ እንደኔ አይነቱ ለህይወቱ ሳይሆን ለእለት ጉርሱ ነው የሚያስበው፡፡ መሆን ያለበትም ያ ነው፡፡ ለህይወቱ አስቦ ገንዘብ ፈልጐ መኖር አይችልም፡፡"

"እንዴት"

"እንዴት አትበለኝ፡፡ አንተ ጋዘጠኛ እንጅ ፖሊስ አይደለህም፡፡ ደግሞ እንዴት?ለምን? የሚባሉ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የላቸውም፡፡ ግን ልንገርህ፤ለህይወቱ ማሰብ ያለበት የተሟላ ቤትና



t.me/OLDBOOKSPDF

ንብረት— ስልጣን ያለው ሰው ነው፡፡ ሴተኛ አዳሪ ሆነህ ለህይወትህ ሳስብ ማለት ያስቃል፡፡ ለሴተኛ አዳሪ ገንዘብና ህይወት አብረው አይሄዱም፡፡ አንድ ጊዜ ሴተኛ አዳሪ ከሆኑ ገንዘብ ማግኘት ወይም መሞት ነው፤ በቃ ከዚህ ውጭ ሞተው እየኖሩ መሞት ያስቸግራል፡፡"

"ፀደንያ..."

"ስለዚህ በቃ፡፡ ሌላ ጥያቄ አለህ?"

"እሺ! በዚህ አጋጣሚ ልጅ ወልደሻል?"

"በአጋጣሚ ስላረገዝኩ ወለድኩት" አለችው፡፡

"እንደገባኝ የወለድሽው ወንድ ይመስለኛል"

"አዎን ወንድ ነው፡፡"

"ስንት አመት ይሆነዋል?"

"ዘጠኝ ወይም አስር ዓመት ሳይሆነው አይቀርም፡፡"

"ያኔ በእርግዝናሽ ወቅትና ከወለድሽው በኋላ እንዴት ነበረ ያሳለፍሽው?"

"ያለፈ ነገር ባትጠይቀኝ ደስ ይለኛል" አለችው ፊቷን ከስክሳ፡፡

"ለዚህ ጥያቄ ብቻ እመልስልሃለሁ፡፡ያኔ እንዳሁኑ አልነበርኩም፤ተራ ለማኝ ነበርኩ፡፡ በየመንገዱ፣በየፊርማታው፣በየቡና ቤቱ፣ የሚለምኑ አይተሃል አይደል? ልክ እንደነሱ ነበርኩ፡፡

"ደግሞ ብዙ ለማኝ ጓደኞች ነበሩኝ፡፡ ሁላችንም በየግል ምክንያት ነበር ለልመና የተሰማራነው፡፡አንዷ የእንጀራ አባቷ ካልደፈርኩሽ ብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስላስቸገራት ተማራ ከቤት የወጣች ነበረች፡፡ አንዷ ደግሞ እናቷ ለማኝ ሆነው ወለዷትና አብ ራቸው ስትለምን አድጋ ኋላም እናቷ ሲሞቱ ልመናቸውን ወረሰች፡፡ሌላዋ ደግሞ አባቷ ጦር ሜዳ ሄዶ ይሞታል፡፡እናቷ ጡረታ ቢጠይቁ 'እኛ አገሩን ለከዳ ሰው ጡረታ አንሰጥም' ብለው መለሷቸው፡፡ የሚተዳደሩበት ሌላ ገቢ ስላልነበ ራቸው ደካማና በሽተኛ እናቷን ለመርዳት ስትል ልመና ላይ ተገናኘን፡፡ ሌላዋም እንደዚሁ ከትው ልድ አገሯ ረሀብ አባሯት እዚህ አዲስ አበባ ከነ ጋዴ ጋር መጥታ ልመና ተሰማራች፡፡ ብቻ ምን ልበልህ ሁላችንም ስንለምን ተገናኝተን ተዋደ ድን፡፡ ቀን የትም ዞረን ማታ ተሰባስበን ያገኘነ ውን ተካፍለን በልተን በየውሃው ቱቦ ሥር ወይም አጥር ጥግ ያገኘንበት ቦታ ስንጫወት ቆይተን ተቆላልፈን እንተኛለን፡፡

"ታዲያ አንድ ቀን ሳላውቀው ከማላውቀው ሰው አረገዝኩ፡፡ያኔ ምንም አልመሰለኝም፡፡ እንደ ውም ጌጥ ይመስለኝ ነበር፡፡ ኋላ ጊዜው ሲገፋ ድካም ያዘኝ፡፡ቢሆንም ያየኝ ሁሉ ያዝንልኝ ስለነ በር በዛ ያለ ገንዘብ አገኝ ነበር፡፡ቱቦ ስር ሌሊት ወለድኩ፡፡ ሲነጋ ጓደኞቼ መንገድ ዳር ወስደው 'የማሪያም አራስ' አሉ፡፡ ብዙ ገንዘብ አገኙ፡፡ እዚያው ቱቦ ሥር አረሱኝ፡፡" አለችና በሀሳብ ባህር ውስጥ ሆና የቦዙ አይኖችዋን ቴፑ ላይ ተክላ "ቀሪውን ብንተወው ይሻላል፤ላንተም ለኔም አይጠቅምም" አለችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን በማለቷ የጨፌን ልብ ደስ አላት፡፡ ታሪኳ እርሱንም ረብሾት ነበር፡፡

"ይበቃል" አላት ፈጥኖ "በነገራችን ላይ እነ ዚያን ጓደኞችሽን አሁን ታገኛቸዋለሽ?" ሲል ጥያቄ አቀረበላት፡፡

"አይቻቸው አላውቅም፡፡ ምናልባትም ሞተው ወይም ቱጃር ሆነው ወይም ከኔ ያነሱ ሆነው ወይም በሽተኛ ሆነው ወይም አልፎላቸው ይሆናል፡፡"

"ያኔ ልጅሽን ራስሽ እየለመንሽ አሳደግሽው ወይንስ ምን አደረግሽው?"

"ለትልቅ ሰው ነው ልጅ የሚጠቅመው፡፡ እሱን እያሳዩ ሲለምኑበት ያምራል፡፡ለወጣት ሴት ግን ገቢ ቢዘጋ እንጂ አያስገኝም፡፡በዚህ ምክን ያት ለአሳዳጊ ሰጠሁት፡፡"

"ጉዲፈቻ ማለትሽ ነው?"

"አይ አይደለም፡፡ በሳምንት አስርም ሃያም ብር እንዳገኘሁ የምሰጣቸው ባልቴት ሴትዮ አገ ኘሁና እንዲያሳድጉልኝ ሰጧቸው፡፡ እሳቸውም ልጁን በጣም ይወዱት ስለነበር ብዙም አልተቸ ገርኩም፡፡"

"አሳዳጊም ገንዘብም ባታገኚ ኖሮ እንዴት ታደርጊው ነበር?"


t.me/OLDBOOKSPDF

ፀደንያ ፈገግ አለችና "አንቄ እገድለው ነበር ልበልህ?! በጊዜው ከልመና ወጣሁና ሴተኛ አዳሪ ነቱን ተያያዝኩት፡፡የገንዘብ ችግር አጋጥሞኝ አያ ውቅም፡፡ ባይሆን አንድ ነገር ልንገርህ፡፡ እኒያ ባልቴት ሴትዮ ልጄን ለሌላ ለማኝ የቀን ኮንት ራት ሰጥተው ሲለምኑበት አገኘሁዋቸውና በን ዴት አናታቸውን ለሁለት ከፈልኩት፡፡ ታዲያ ከዚያስ እንዳትለኝ እሺ?"

"እንደዚያ ከሚሆን ለምን ልጅሽን በሞግዚ ትነት ለሚያሳድጉ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ለመስጠት አልሞከርሽም?"

"ማ! እኔ ፀደንያ! ቢለምኑኝም አልሰጣቸውም ነበር" አለችው ኮስተር ብላ፡፡

"ለምን?"

"ጀመርክ እንግዲህ ይኸን 'ለምን' ብሎ የጅል ጥያቄህን፡፡ ግን ለመጨረሻ ግዜ ልንገርህ፡፡ የኔ የለማኝዋ፤ የሴተኛ አዳሪዋ ልጅ የማንም ሴባ ሀብት መለመኛ፤ ኑሮ ማድለቢያ፤ ቤት መስሪያ አይሆናትም፡፡ ህፃናትን ሰብስበው በፍርፋሪ ዳቦ እያኖሩ እነማን እንደሚጠቀሙ አውቃለሁ፡፡ ሲፈጠር ጀምሮ እድል ፊቷን ያዞረችበትን ልጅ ያለጥቅም የሚረዳ ወይም የሚያዝን ያለ እንዳ ይመስልሀ፡፡" አለችና ስንቷን አየት አድርጋ "እንግዲህ አይበቃህም?" አለችው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ እኔም እየጨረስኩ ነው፡፡ ሌላ ሥራ ብታገኚ ከዚህ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት መውጣት አትፈልጊም?" አላት፡፡

"ለምን እወጣለሁ?! ምን አጣሁ፡፡ ወይስ ወንዶች ባገር አለቁ!" ስትል በማሾፍ መለሰችለት፡፡ ከንግግርዋ "የለማ" የምትል ትመስላለች፡፡

"እንዲህ አይነቱ ኑሮ ለጊዜው ቢያኖርሽ እንኳ ቢያንስ ከሀይማኖት አንፃር ሲታይ የሚወደድ አይደለም?"

"እሱ ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ሴተኛ አዳሪዎች የተጠሉት ገና ሲፈጠሩ ነው፡፡ እግዜር ስንት ሃይል፣ ጥበብና ችሎታ እያለው ይኸን ከመረጠልን ሃላፊው ማን ይመስልሃል" ስትል ሰውነቷን ዘና አድርጋ ጠየቀችው፡፡

"እንዲህ አይነቱ ችግር እንኳ ሰው ሰራሽ ነው" ሲል መለሰላት፤ ስለ ፈጣሪ ያላትን አመለካከት ሊያስብበት ከብዶት ነበር፡፡

"ሰዎችንስ ማን ፈጠራቸው?ለማንኛውም እሱ የኔ ችግር አይደለም፡፡እኔ ወንዶችን እያስደሰትኩ ገንዘብ ከማግኘት አልፌ ስለሌላ ነገር መፈላሰፍ አልፈልግም" አለችው፡፡

ጨፌ በንግግሯ ተደንቆ ፈገግ አለ፡፡ የምትሰጠው መልስ ሁሉ እሱ ለሴተኛ አዳሪ ካለው ግምት ሺህ ግዜ በልጦ ታየው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምነው፤ ምኔ አሣቀህ?" ስትል ጠየቀችው፡፡ "አይ፤የአስተሳሰብሽ ነገር ገርሞኝ ነው"አላት፡፡

"ሴተኛ አዳሪዎች የማያስቡ፤ እንጉል የሴላ ቸው እድርገህ ትገምት ነበር ወይስ ጭንቅላታ ቸው ጭናቸው ውስጥ ይመስልህ ነበር?"

"ሳይሆን፤እ-አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ነው የቀ ረኝ፡፡ አንቺ የመንግስት አካል ብትሆኚ ለሴተኛ አዳሪዎች ምን ታደርጊ ነበር?"

"እኔ የመንግስት ባለስልጣን ብሆን? አገሬ ውስጥ ሌላ የትም አገር የሌሉ፤እጅግ ድንቅ የሆነ የወሲብ ጥበብ ያላቸው ቆንጆ ቆንጆዎች ስላሉ፤ እድሜ ሳይጫንዎት፤ሞት ሳይቀድምዎት አሁኑኑ ወጥተው ይጐብኟቸው ብዬ ለዓለም ከበርቴዎች ጥሪ አቀርብ ነበር" አለችው በሽሙጥ፡፡

"ፀደንያ እውነቴንኮ ነው የጠየኩሽ፡፡"

"ወይም ደግሞ በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ የሚገ ኘው የሴተኛ አዳሪዎች ቁጥር ከዘጠና በላይ ቀን ሷል" ብዬ ተፈላጊ እንዲሆን አደርግ ነበር፡፡

"ምናለ ሽሙጡን ትተሽ ቀና ነገር ብታ ስቢ?"

"ሰው' ኮ ማሰብና መናገር ያለበት መሆን በሚችለው ልክ ነው – ጋዜጠኛው፡፡ አሁን ማይ ሙት ፀደኒያ የመንግስት ባለስልጣን ሆና የሴተኛ አዳሪዎችን ችግር ለመፍታት የምትበቃ ይመስ


t.me/OLDBOOKSPDF

ልሃል? ወይስ በአሁኑ እደሜዬ የሴተኛ አዳሪዎች ንቅናቂ የሚል ድርጅት መስርቼ እግዜርን፣ ተፈ ጥሮን፣ሰውን እታገላለሁ እንድልህ ትፈልጋለህ?"

ጋዜጠኛው ጨፌ እና ሴተኛ አዳሪዋ ሳይግ ባቡ ምልልሱን ጨረሱ:: ጨፌ እንዴት አድርጎ ፕሮግራም መስራት እንደሚችል ማሰላሰሉን ቀጠለ:: ሲያስጨንቀው የነበረ ግዳጅ ወደ ሌላ ጭንቅ አሸጋግሮ ጣለው::

"ሒሳቡ ስንት ነው?"አላት ኪሱን እየደባበሰ፣ ቶሎ ከቤቱ ወጥቶ ለብቻው ማሰብ ነበረበት::

ፀደንያ ሰዓቷን አየችና– "በቃ ከኔ ይቅር ሀምሳ ብር" ስትል መለሰችለት::

"እንዴ?ሒሳቡ—ሒሳቡ" አለ ጨፌ ደንግጦ:: "ስንት ነው የጠጣነው?"

ፀደንያ ፈገግ እንዳለች "የመጠጡ አስር ብር ነው:: የሌላውን ደግሞ አርባ ብር አድርጌል ሃለሁ:: አዲስ ባትሆን ኖሮ ስልሳ ነበር::" ስትል መለሰችለት::

"ሌላው ደግሞ የምንድነው?" አላት ይበልጥ ደንግጦ::

"ሌላውማ" አለች በድጋሚ አይኖችዋን ሰዓቱ ላይ ተክላ "እዚህ ቤት ስትገባ ስምንት ሰዓት አልነበረም?" ስትል ጠየቀችው:: "አሁን ደግሞ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልክ ለአስራ አንድ ሩብ ጉዳይ ሊሆነው ነው፡፡ አየህ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ሦስት ወንዶች አስተናግድ ነበር፡፡ የሦስቱ ጊዜ ሒሳብ ሲደመር ስልሣ ብር ይመጣል፡፡ ላንተ ግን አርባ ብር ያደረኩልህ አዝኘልህ ነው" አለችው አቅርባለት ለነበረው ጥያቄ ራስዋ እየመለሰች፡፡

"ታዲያ እኔ ምን አደረኩ? አብሬሽ አልተኛሁ?" አላት አይኑ ላይ የተለያዬ ህብረ ቀለማት ብልጭ ድርግም እያሉበት፡፡

"እሱ የኔ ችግር አይደለም፡፡ለኔ አብረኸኝም ተኛህ አልተኛህ ለውጥ አያመጣም፡፡የቀን ሥራ ዬን ካንተ ጋር እንዳጠፋሁ ማወቅ አለብህ!! አየህ ከወንድ ጋር ካልተኛሁ ገንዘብ አላገኝም፡፡ ገንዘብ ካጣሁ ደግሞ ፀደንያ የለችም፡፡ ጊዜውን ደግሞ ካንተ ጋር አሳለፍኩ፡፡ እናንተ ራሳችሁ 'ጊዜ ወርቅ ነው' ትሉ የለ! ወርቁ ቢቀር ገንዘቡ ይቅር ብኝ ትላለህ?" አለችው እየሳቀች፡፡

ጨፌ በግራ እጁ የግራ ጉን ጉንጩን ደግፎ በቀኝ እጁ ድምፅ መቅረጫውን እያሻሸ፣ አይኖቹን ፀደንያ ጭን ላይ ቡዝዝ አድርጎ ተክሎ በአ ይኑ ህሊናው ኪሱን መዳበስ ያዘ፡፡ ከምሳ መልስ ስድስት ብር፣ ትላንት የነበረው ሦስት ብር ... አገኘ፡፡

"ምን ማድረግ ይሻላል?" ሲል እንደ ድንገት ጠየቃት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከመከፈል ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል፡፡ተጨ ማሪውን ከቻልክም ይዘኸኝ መተኛት" ስትል መለሰችለት፡፡

"እንደሱ ሳይሆን፤ ያለኝ ዘጠኝ ብር አይሞ ላም" አላት፡፡

ፀደንያ በረዥሙ ሳቀችና "እሱ የራስህ ችግር ነው፡፡ ፀደንያ ግን ጊዜዋን ያጠፋችበትን ገንዘብ ዋን ማግኘት አለባት" አለችው፡፡

ጩፌ የግዱን ሳንቃውን አላቆ "እሱማ ማግ ኘት አለብሽ፡፡ችግሩ የኔ ገንዘብ አለመያዝ ነው" በማለት በደከመ ድምፅ በልመና መልክ መለ ሰላት፡፡

"ለገንዘቡ ብዙም አትቸገር" አለችና ወደእሱ ተንጠራርታ መቅረፀ ድምጹን ከእጁ ላይ መንጨ ቀችው፡፡"ገንዘብ ሳይዙ በመምጣት አንተ የመጀ መሪያው አይደለህም፡፡ሌላ ቀን ይዘው እንዲመጡ ቃል አስገብቼ ይሄዳሉ፡፡ ባይሆን ሲሄዱ አስተማ ማኝ እቃ ያሲዛሉ" አለችው፡፡

"እና?" አላት በደመነፍስ፡፡

"አንተንም አምንሃለሁ፡፡ ጋዜጠኛ ይዋሻል ሲባል እንጂ አይታመንም ሲሉ አልሰማሁም፡፡ ይኸን" አለችው መቅረፀ ድምፁን እያሳየችው፡፡ "ገንዘቤን ይዘህ እስክትመጣ እኔ ጋ ይቆያል" ብላው ከመቀመጫዋ ተነሳች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

. “በፍፁም አይሆንም፡፡ ሊ-ሊሆን አይችልም” ሲል እሱም ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ተነሳ፡፡

ፀደንያ በሁኔታው ሳቀችና “ቀልዱን ለሬዲዮ ንህ አቆየው፡፡ ይልቅስ” አለችው የእጇን ስዓት ለእርሱ ለማሳየት እየሞከረች “ስዓቱ ሒሳቡን እን ዳይቆጥርብህ፡፡”



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሰለሞን አያሌው

(1952 — )



ሰለሞን አያሌው በ1952 በደቡብ ጎንደር ደብረታቦር ከተማ ተወለደ፡፡የ1ኛና የ 2 ደረጃ ትምህርቱን በደብረታቦር፣ በጎንደርና በአዲስ አበባ ከተማዎች ተከታትሏል፡፡ ከዚያም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በቋንቋዎችጥናት ተቋም በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ዘርፍ ትምህርቱን ተከታትሎ የባችለር ዲግሪውን ተቀብሏል፡፡ ከተመረቀ በኋላ መምህር፣ በክልል 14 ትምህርት ቢሮ የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት ሐላፊ ሆኖ ሠርቷል፡፡ አሁንም በሜጋ የኪነጥበባት ማዕከል በሙያው በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

ሰለሞን አያሌው እጅግም ለህዝብ ያልቀረቡ ወጥ ድርሰቶችና የትርጉም ሥራዎች አሉት፡፡ የተወሰኑ አጫጭር ልቦለዶቹን ለውድድር አቅርቦ ሽልማት አግኝቶባቸዋል፡፡ ለዚህ በአጫጭር ልቦለዶች መድበል የተመረጠው "ሌላው አባወራ" ልቦለድ ባህል ሚኒስቴር አዘጋጅቶት ለነበረው ውድድር ቀርቦ ሽልማት ያስገኘለት ወጥ ድርሰቱ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሌላው አባወራ

አመት በአል ነው፣ የቅዱስ ዮሐንስ ዋዜማ ለት፣ የአዲስ አመት መዋለጃ ምሽት፡፡ እስከዛሬ እንደሚያደርገው ሁሉ በዚህች ዕለት ዕንቁጣጣሽን መጠጥ ቤት ሄዶ፣የነገውን እንቦቀቅላ አመት መለኪያ ጨብጦ፣የጠርሙስ አንገት አንቆ፣ሲጋራ ለኩሶ መቀበል አላሰኘውም፡፡ ባለፉት ዓመታት ተመላልሶ ያመሸባቸውን ቡና ቤቶች በራፍ ማየት አስጠልቶታል፣ የነአልማዝ፣ የነአለምነሽ፣ የነከበቡሽ እንግዳ መሆን አልፈቀደም፡፡ ምናቸውም አንገሽግሾታል፡፡የአልማዝ ዳሌ፣ የዓለምነሽ ፍልቅልቅነት፣ የከበቡሽ ልጥፍ ባይ ሰውነት አልናፈቀውም፣ የነወይዘሮ እቴነሽ፣ የነእትዬ ጌጤ፣ የነማማ ውዴ ቀልድና ደረቅ ፈገግታ ዛሬ አላሳሳውም፡፡ ሂድ ሂድ ውጣ ውጣ አላለውም፡፡ ና! ና! ብሎ እንደሌላው ጊዜ አልጠራውም፡፡

የሚያደርገው ጠፍቶት፣ ሁሉም መና ሆኖበት ከቤቱ ቁጭ ብሏል፡፡ ባለቤቱ ለምለም የእንቁጣጣሽን ዋዜዋ ለማስዋብ ባለ በሌላት አቅም ሽር ጉድ ትላለች፡፡አይናገርም አይጋገርም፡፡ ቁጭ ካለ በት ወንበር ሁኖ ቤቱን እንደንግዳ ይማትራል፡፡ አዲስ ቤት ...ይታየዋል፤አዲስ ሽታ ያውደዋል፡፡ ከለምለም ጋር ሰባት የአዲስ አመት ዋዜማዎች ሲያሳልፍ እንደዛሬው ዋዜማ ላዲስ እይታ፣ላዲስ መአዛ ስሜቱ አልታደለም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዛሬ ማንም ምንም ቢመጣ ከቤቱ የሚያ ስወጣኝ ሀይል አይኖርም" አለ ለብቻው፣ለራሱ ቃል ገባ፣መሃላ፡፡

"ከዘነበ ጋር ቀጠሮ አለኝ እሱም በርግጥ ይመጣል ግን ዛሬ ... ዛሬ ቤቴን አለቅም፣ አን ዲት እርምጃ ፈቅ አልልም፡፡"ነጎደ በሃሳብ ከራሱ ጋራ ሙግት ገጠመ፣ እሰጥ አገባ፡፡

"ቢራ እየጠጡ፣ አረቄ እየተጎነጩ፣ ጭስ ስበው ጭስእየተፉ አምሽቶ ሌሊት የቤት በር ማንኳኳት እስከመቼ" ይላል፡፡

"አንድ ክፍል ውስጥ ታጉሮ፣ ቤትን ትቶ ጎጆን ረስቶ፣ልጅን ዘርን ገፍቶ፣ካርታ መቀጥቀጥ ... እጅ ማንቀጥቀጥ ፋይዳ ቢስ መላ የለሽ ሕይ ወት" ያወግዛል እራሱን፡፡
ውጩ ደንገዝገዝ ብሏል፡፡

ለምለም ተፍ ተፍ ትላለች፡፡ ቂጤማውን፣ ዕጣኑን፣ ሰንደሉን፣ አበባ ቆሎውን፣ ቂጣውን፣ ቡናውን የቅዱስ ዮሐንስ ልማዳዊ ሽርጉዷን ተያ ይዛዋለች፡፡ የባሏ የአሸናፊ እንግዳ ነገር እሷንም አሳስቧታል፡፡

"ዛሬ ምን ሁኗል? እንዴት አስችሎት በዚህ ሰዓት፤ በዚህ ዕለት እቤት ቁጭ አለ" ትለዋለች የልጅዋን አባት በሆዷ፡፡
"ቤቶች" ዘነበ መጣ፤ ማድያታሙ አጭሩ ወፍ ራሙ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ግባ ... ግባ ቤት ለእንግዳ" አለ አሸናፊ፤ የለምለም ባል፡፡

ከማድቤት ወደ ጓዳ፣ከጓዳ ወደ ሳሎን የምት መላለሰው ለምለም የዘነበን ድምፅ ሰማች፡፡

"በቃ እንግዲህ ተያይዘው ሊሄዱ ነው ምን በደል ነው እቴ" ስትል አሰበች፡፡ ዘነበ ቤት ውስጥ ገብቶ ቆሟል፣ በትክክስ ቁጤማ ላይ ባዲስ ሽታ እየታወደ፡፡

"ቁጭ በል እንጂ" አለ አሸናፊ፡፡

"የምን መቀመጥ አመጣህ? እነ አሰፋ ቤት ሄደን እንሰየም እንጂ"

ያሰፋ ቤት ለካርታ ጭዋታ አመቺ ነው፡፡ እየተጫወቱ ረጅም ጊዜ ቢቆዩበት የሚከፋ ሰው የለበትም፡፡አሸናፊና ጓደኞቹ በዚህ ቤት ተሰብስ በው ካርታ ሲጫወቱ፤ በቅርብ ካሉ ቡና ቤቶችም መጠጥ አስመጥተው እየጠጡ ጊዜአቸውን ያሳል ፉበታል፡፡

"ቁጭ በል፤ምን መሰለህ ..." አለው አሸናፊ መርዶውን እንዴት እንደሚነግረው እያሰበ፡፡

"ምን መሰለህ አሞኛል ዛሬ ብርድ ... ብርድ ይለኛል ..."

"እና አልሄድም እንዳትለኝ ብቻ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እዎ እንደሱ ነው ብርድ ብ...ርድ ይለኛል፣ ያተኩሰኛል! ምን እንደሆንኩ አላውቅም ... ቁጭ በል ... እስቲ ... አረፍ በል ዘነበ"

ለምለም የዘነበንና ያሽናፊን ውርክብ ትሰማ ለች፡፡ ሰራተኛዋ ከሄደች ጀምሮ ለብቻዋ ደፋ ቀና ትላለች፡፡ የስድስት ዓመቱ ልጃቸው መላ ኩም እንደ ጓዳ እንደ ሳሎን ይመላለሳል፡፡

"እንዴ ... ዘነበ ባያመውስ በዛሬው ቀን እን ሂድ ይባላል! በዘመን መለወጫው ዋዜማ ውጭ ይመሻል?እዚሁ ቁጭ ብላችሁ ተጫወቱ፤ ጠላ ውም አረቄውም ለዛሬ አያንስም፡፡ይልቅ አንተም ቁጭ በል ጠላ ላምጣ፡፡" አለች ለምለም በዘነበ ሀሳብ ላይ ቅሬታዋን ለመግለጽ እየሞከረች፡፡

"ብንሄድ ይሻላል ለምለም፤ ያሰፋስ ቤት ቢሆን ቤታችን አይደለም እንዴ ... ደግሞም ከነ ለማ ጋርም ተቀጣጥረናል፡፡ መቅረት የለብንም፤ አይዞሽ ሌላ የምናደርገው የለም– ቁጭ ብለን ካርታ ከመጫወት ሌላ" አለ ዘነበ፡፡

"አሸናፊ ዛሬ የፈለገው ቢሆን የትም አትሄ ድም፡፡እነለማም ቢሆኑ ከፈለጉህ እዚሁ መምጣት ይችላሉ፡፡ይልቅስ ጋቢ ላምጣልህ"

"አሞኛል ዘነበ፤ ይልቅ ቁጭ በል፡፡ እንዳል ኩህ አሞኛል ... ብርድ ... ብርድ ይለኛል ... ትኩሳት ይሰማኛል ... ቅፍፍ ... ፍፍ ብሎኛል፡፡ ዛሬ ከቤት አልወጣም፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለብርዱም ሆነ ለትኩሳቱ እቤት መዋሉ መድሐኒት ሊሆንህ አይችልም:: ይልቁንስ ያልተ ለመደ ሰበብ ከማብዛት ጨክንና እንሂድ:: እነለ ማን ስትቀጥራቸው ለምን እንደነበር አትርሳ:: እነ እትዬ ጌጤ ወይም እነ እማማ ውዴ ቤት ጎራ ብለን አንድ ሁለት መድሀኒት እንወስዳለን" አለ ዘነበ እንደቆመ::

"የዛሬው ህመሜ በአንድ በሁለት ...የምወጣው አይነት አይደለም ዘነበ:: ውስጤን የሚሰማው ብርድና ትኩሳት የተለመደ አይደለም:: እቤቴ ብውል ይሻለኛል" አለው::

ለምለም ጠላ በጠርሙስ ከብርጭቆዎች ጋር በትሪ ይዛ መጣች::

"ቁጭ በል ዘነበ" አሉ ድንገት ባንድ ላይ ባልና ሚስት የተማከሩ ይመስል::

"ሰው ቀጥረን፣ እንመጣለን ብዬ ... እንዴት ቁጭ እንላለን አሸናፊ ... ጥሩ ነው እንዴ ይሄ ነገር ለምለም?!" አላቸው ዘነበ እንደተገተረ::

"ሲያመውስ ... አሞታል ...እኔም እኮ በሆዴ አሸናፊ ምን ሁኗል ዛሬ ስል ነበር ... ልጠይቀው ስል ነው አንተም የመጣኸው ... በል ጋቢውን ልበስ ተሸፋፈን"ብላ ጋቢውን አለበሰችው "ይልቅ ቁጭ በል ዘነበ ሲያመው ሲሆን ለበሽታው መፍ ትሄ ይፈለጋል እንጂ እንዴት እንውጣ ይባላል? ያውም በዛሬ ቀን ... ታምር ነው ይሄስ! ቡናም



t.me/OLDBOOKSPDF

አፈላለሁ" እያለች ሁለተኛውን ብርጭቆ ጠላ ልትቀዳ ስትል ዘነበ፡-

"አልጠጣም ... ሰው ጠብቁኝ ብየ እዚህ አል ጠጣም" አለ በቁሙ ማዲያታም ፊቱን ደበልጥ እያሻገረገረ፡፡ ለምለም በግድ ቀዳችለት፡፡

"ከፈለግህ አንድ ... ጠጣና ትሄዳለህ ... የናስፋ ቤት ካለበት እግር አውጥቶ አደሮጥ... ቆረጣጠመኝ ... ቁርጥማት ... ሎፍ ... እነለማም አንዴ ከተሰየሙ ስዓት እላፊ ነው የሚገላግላ ቸው፤ አያመልጡህም ... እኔ ልተኛ መሰል ... ትከሳቱ ባሰብኝ ብርድ ብርድ ..." ብሎ ሳይጨ ርስ ዘነበ ካፉ ቀማው፡፡

"የዛሬው ሁኔታህ አላማረኝም ... የማትሄድ ከሆነ ቶሎ መሄድ አለብኝ፤ ይጠብቁናል ... ኧ... ይጠብቁኛል" ብሎ ጠላውን በቁሙ ጨለጠው፡፡

ለምለምም "አሞታል ዛሬ፤በጤናው አይደለም ...ፊቱ ሁሉ ተለዋውጧል፤ ትከሳቱም ጨምሯል" አለች የአሸናፊን ግንባር አንዴ በመዳፏ አንዴ በእጇ ጀርባ ሙቀቱን እየለካች፡፡ ዘነበና አሸናፊ ተያዩ፤ አስተያየታቸው ለሁለቱም አዲስ ነበር፡፡

"ከቸኮልክ ... በቃ ... ሂድ፤ እኔ ...መውጣት ቀፎኛል፡፡"አለው አይኑን ከዘነበ ላይ ሳይነቅል፡፡

"መልካም ካመመህ ... ከመሰለህ እ ... ንዳ ልክ ... ብቻ ብንሄድ ጥሩ ነበር"አለው ወደ በሩ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያመራ ዘነበ፡፡ ደህና እደሩም ሳይል ወጥቶ ሄደ፡፡

"መቼ ጀመረህ አሸናፊ? ግንባርህ እኮ ያተኩ ሳል ... ጠላውም ይቅርብህ ... ሽፍንፍን ብለህ ተኛ" አለች ለምለም፡፡

"ዛሬ ... አሁን ... ድንገት ነው የጀመረኝ፤ እቤት ስገባ ... ቤቴን ሳየው አዲስ መሰለኝ፤ቁጤ ማን እንደዛሬ አስተውየውም ደስ ብሎኝም አያ ውቅም ለምለም፡፡"

"እንዴት?ቤት ደግሞ ያማል ... እ... ያተኩ ሳል ... ብርድ ብርድ ይላል"አለች ለምለም ግራ በገባው መልክ ቀይ ውብ ፊቷን ቅጭምአድርጋ፡፡

"እኔ ሳልሆን... የታመምኩት... ደባሌ ነው... ከዚህ ቤት ውስጥ ያለው ሁለተኛ አባወራ" አለ ጋቢውን እያመቻቸ ደርባባው አሸናፊ፡፡

ለምለም ይበልጥ ግራ ገባት፡፡

"ጠረጠረኝ እንዴ ...ከሱ ሌላ የደረብኩ መሰ ለው" አለች በሆዷ እንደጨነቃት፡፡ወዲያው በጥ ርጣሬ እንደተወጠረች፤ ቆሎውን፣ ቂጣውን አዘጋ ጅታ አሸናፊ ፊት ቡና ለማፍላት አስባ ወደ ጓዳዋ ገባች፡፡

"መላኩ" አለ አሸናፊ ወደ ልጁ ፊቱን አዞሮ፡፡መላኩ ከሳሎኑ መስኮት ጥግ ካለች ትንሿ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠረጴዛው ላይ ደብተሮቹን ዘርግፎ ወረቀት እየቀደደ ያጥፋል፡፡"ምንድነው የምትሰራው? ደብተርህን ለምን ትቀዳለህ?" ሲል ጠየቀው፡፡

"ቅርፅ ስራና አምጣ ብለውኝ ነው፤ የሰፈር ጓደኞቼ" ብሎ መለሰ፡፡

"የምን ቅርፅ?"

"የመርከብ...አባዬ የወረቀት መርከብ ... ደሞ እችልበታለሁ አይደል አባዬ" አለው የምን ቅርፅ እንደሆነ የማይለይ የተጣጠፈ ወረቀት ለአሸናፊ እያሳየው፡፡

"በል በደንብ ስራ፤ወረቀት አታበላሽ፤ ባንድ ሉክ ብቻ ለመስራት ሞክር፤ ስትጨርስ ታሳየኛለህ" አለው፡፡

መላኩም ወደ መርከብ ስራው ተመለሰ፡፡

ለምለም ረጅም ቀጭን ሰውነቷን ከበርጩማዋ ላይ እጥፍጥፍ አድርጋ ቁጭ እያለች "ያልከው እኮ አልገባኝም፤ ምንህን ነው ያመመህ አሸናፊ?" ብላ ጠየቀችው፡፡ የሆነ ነገር ሆዷን ይበላት ጀምሯል፡፡

"ማንነቴን ለየሁት ለምለም፤ ያመመኝም ይኸው የራሴ አዲስ እውቀት ነው" አለ፡፡ ለምለም አይን አይኑን ባልተረጋጋ መልክ አየችው፡፡'ይቃዣል እንዴ' ስትል ራሷን ጠየቀች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“በእኔ ላይ ሌላ ሰው ተደርቦ ባንድ አልጋ ላይ ሶስት ሁነን እስከ ዛሬ ማደራችንን፣ እስካ ሁን መኖራችንን ዛሬ ለየሁት፤ አሁን ደረስኩበት ... ለምለም ... ማለቴ ...” አሸናፊ ወደ ውስጥ ከራሱ ጋር መነጋገር የጀመረ ይመስላል፡፡

“እኔ ልጅት ... እኔ ለምለም ...ማንም ቢሆን ...እኔ ካንተ ሌላ እንዴት ሆኖ... እንዴት አሸናፊ ...እንዴት...እንዲህ...እኔን”አለች፤ ሁለመናዋ ይን ቀጠቀጣል፡፡ፀጉሯ በንዴት ይርገፈገፋል፡፡ አይኗ በፀፀት ፈጧል፡፡

“አንቺ አይደለሽም...ለምለም ጥፋተኛው እኔ ነኝ...ለምለም...ሁሉንም እያወኩ፣ እራሴን እየደለ ልኩ፣ እኔን እየሸነገልኩ የማይሆን ትዳር የተዳ ርኩ፣ የማይዘለቅ ጎጆ የወጣሁ፣ክቡር ቃልኪዳንን ያፈረስኩ...እኔ ነኝ... ለምለም”

“አባዬ ... እ ... እማዬ ... አባዬ ... አባዬ! ተመልከት አሁንስ መርከብ አልሆነም”አለ መላኩ ቅርፁን አንስቶ እያሳየ፡፡ሁለቱም ወደ እሱ ተመ ለከቱ፡፡

“ተጣሟል መላኩ አስተካክል ... አፍር ሰውና እንደገና ሌላ ስራ” አለ አሸናፊ፡፡ መላኩ በቁጭት መርከቡን አፈረሰው፤ሌላ መርከብ መሥ ራት ጀመረ፡፡

ሀሳቧ ሁሉ በአሸናፊ ህመምና ህመሙ በሚያ ናግረው እንግዳ ነገር፣ ዱብዕዳ ቅዠት ተተብት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቧል፡፡የከሰል ምድጃውን የሚያራግበው እጇ ምን እንደሚሰራ አታውቅም፤ እሳቱ ደብዘዝ ብሏል፡፡ ያቀረበችውን ነገር በሙሉ ዘንግታዋለች "በርግጥ አሞሃል ዛሬ ... ምን እንደምትለኝ ...ልትለኝ የፈ ለከው ነገር ... የዛሬው ነገርህ አልገባኝም ...ተኛ አረፍ በል...በጤናህ አይደለም...የምትለኝን ሁሉ የምትናገረው ... እኔ ካንተ ሌላ... በስመአብ..." ሁለመናዋን ሰበቃት፡፡

"ለምለም በርግጥ አሞኛል ... ጤና አይደ ለሁም... ጤና ለመሆን ... ኸ ... መታመም ... መታመም ... ኸ ... አ ... ጤና ለመሆን" ጋቢ ውን ተከናንቦ ከተቀመጠበት የወንበር ድጋፍ ወደ ጠረጴዛው ተጠግቶ በክርኖቹ ተደገፈ፡፡ "እኔ ዘነበን፣ እኔ አሰፋንና እኔ ለማን ጓደኞቼ አድርጌ ... ከበደ... የሚነግረኝን፣ የሚመከረኝን፣ ትክክለ ኛውን ነገር የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብዬ ለዚህ... ለዚህ ሁሉ ነገር በቃሁ፡፡"

"የመቸው ከበደ! አ ... ሸ ... ና ... ፊ... ስለኔ ከ ... ከበደ ምንም አይነግርህም ...የት አይ ቶኝ? በሰው ወሬ!...ትልቅ ሰው ይመስለኝ ነበር... እኔን ከማን ... ከየትኛው ሰው ጋር አየ ... የ... ኳኋት ... አለህ?" ስራዋን ሁሉ አስተዋት፡፡ ማራገቢያውን መሬት ላይ ጥላው ረጃጅም ክንደ ቿን ካከረታተመቻቸው ጉልበቶቿ ላይ አደራርባ አሸናፊን በፀፀትና በንዴት እያየችው 'አሞት መሆን አለበት እንጂ እንደዚህ አይነት ነገር በፍፁም' የሚል ሃሳብ ይመጣባታል እንደገና ያሳ ዝናታል፡፡ 'ምን አገኘው ዛሬ?' ትላለች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምለም ... ቆሎውን ቁይው፤ ለምለም ... በድየሻለሁ ... ህመሜን እንድነግርሽ ... ቡናውን አፍይው"

"ሁል ጊዜ ማምሽት ... ኧ ሁሌ መጠጣት... አሁንም ማጨስ ... ነጋ ጠባ ቁማር መቀጥቀጥ ትርፉ ይሄው ነው ... ደሞ ይሄን ሁሉ እኔ በታግ ስኩ ... አንተ እንደገና..."

"በድየሻለሁ...ቡናውን... ቆሎውን... ለምለም"

"እሱስ ያድንህ እንጂ እቆላዋለሁ ግን ... በሰው ... በከበደ ወሬ እኔን ..." ብላ ቡናውን ብረት ምጣዱ ላይ ማጠብ ጀመረች፡፡ የምድጃው እሳት አመድ ለብሷል፣አራገበችው፡፡ እሳቱ ሳቀ፡፡ ከሰል ጨማምራ ብረት ምጣዱን ጥዳ መቁላት ጀመረች፡፡ ለምለም ቡናውን በሃሳብ ታማስላለች "ደሞ ከሱም ብሶ..." ያሰኛታል፡፡

"አባዬ ...አባይ ተመልከት ...መርከብ...እማይ ትዋኝበታለች አይደለ?" አለ በኩራት፡፡ መላኩ መርከብ በመስራቱ ፊቱ በደስታ ተውጧል፡፡

"እዎ ግን እንዳያሰምጠኝ ... አታድነኝም መላኩዬ" አለችው፣ ያሸናፊ የህመም ንግግር ባቀ ሉት አይኖቿ በናትነት እያየችው፡፡ ለምለም እን ዲህ ስታይ ልዩ የሆነ የደስደስ አላት፡፡

"እንደገና ሥራ፤ ጫፉ ላይ ... ተንሻፏል" አለው አሸናፊ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“አሁንስ የመጨረሻዬ መርከብ ነው” አለና መርከቡን አፈራረሰው፡፡

ቡናው በመዓዛው ቤቱን አወደው፤ አሸናፊ ሰውነቱ ተፍታታ፣ ቀለለው፡፡ ተንጠራራ፡፡ ቡና ሸቶት ቢያውቅም የዛሬው ማታ መዓዛ ግን ቡናን እንዲያደንቅ አስገድዶታል፡፡ ጀበናውን ጥዳ ቡና ውን ሙቀጫው ውስጥ ከታ ከነዘነዘናው ይዛው ወደ ጓዳ ገባች፡፡ ድው ... ድው ... ይላል ሙቀ ጫው፡፡ የአሸናፊ ንግግርም የለምለምን ልብ ከቡ ናው ጋር ቅርጭም ... ድቅቅ ያደርገዋል፤ አብሮ ያስወቅጣታል፡፡

ስትመለስ የረሳችው ነገር ትዝ አላት፡፡ ቆሎው አልተቆላም፣ ቂጣው አልተጋገረም፡፡ ጀበ ናውን አውጥታ ብረት ምጣዱን ጣደች፡፡ ተቆላ፤ ቂጣው ተጋገረ፡፡ ቡናው ተፈላ፤ ሰንደል ተለኮሰ፤ ስኒ በረከቦት ቀረበ፤ አቦል ቡና ተቀዳ፡፡ በቤቱ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ለአሸናፊ አዲስ ሆነ በት፡፡ ህመሙ፣ ትኩሳቱ ቁርጥማቱ ከቡናው አቦል ... በረካ... ቶና ጋር ተሸኝቷል፡፡ መላኩም ቂጣውንና ቆሎውን በላልቶ እንደጨረሰ-

“አሁን ልተኛ አባዬ ... መ ... መርከቡን ነገ እሰራዋለሁ”አለ ሲያፈርስ ሲሰራ ድክም ብሎት፡፡

“ራትክን ሳትበላ መላኩዬ፤ ቆይ ላቅርብልህ... የኔ ጌታ” ብላ ልትነሳ ስትል፡-

“በቃኝ እማዬ ጠግቤያለሁ” አለ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዋ ... ሌሊት ይርብሃል ... ብላና ተኛ" ሲል ተናገረው አሸናፊም፡፡

"በቃኝ አባዬ ... እማዬ ጠዋት ቀስቅሽኝ፤ መርከቡን እንደገና እሰራዋለሁ"ብሎ ወደ መኝታ ቤታቸው ገባ፡፡

"አሁንስ አልተሻለህም?ትኩሳቱ አለቀቀህም? ... ራት ላቅርብ"አለች ለምለም፡፡

"መሻልስ እየተሻለኝ ነው ... ግን ሁለት አባ ወራ ላንቺ አንድ ገላ አይሆንም ...ሁለት አባወራ ላንድ ቤት አያስፈልግም፤ ዛሬ አንዳችን ይለይል ናል፡፡ ላንድ ገላ አንድ ነው ... ላንድ ሚስት ... አንድ ባል ... አንድ ትዳሩን አክባሪ፣ ጎጆውን ጠቃሚ፣ ልጁን ተንከባካቢ ሌላ አባወራ፡፡ ባልሽ ቁማርተኛው፣ ያኛው ባልሽ ቁማርተኛው ሰካ ራሙ፣ ትምባሆዋሙ ዛሬ ተይዟል እጅ ከፍንጅ ይዥዋለሁ፡፡በዛሬው እለት በዚህ የአዲስ አመት ዋዜማ ይሞታል፤ ይቀበራል፤ ዳግም ላይነሳ" ለምለም አቅለሸለሻት፡፡ የጠጣችው ቡና የበላችው ቂጣና ቆሎ ሆዷ ውስጥ ተላወሰ፡፡ ንዴት፣ ብስ ጭት ጥርጣሬ ... ልቧን አጥወለወለው፡፡ ሳቧ በግምባሯ ግጥም አለ፡፡ የምትናገረውን አትቆጣ ጠረውም፡፡

"የታታ ... መምህ ... መስለህ ... የልብህን ተናገርክ አይደል፡፡ በ-በቃህ አሸናፊ ይልቅስ ታመህ ... አታታሳምመኝ ... አድ ... ድነኝ ... አሸ...ና...ፊ ...በጣም እዝናለሁ፡፡ካንተ ሌላ... እ...



t.me/OLDBOOKSPDF

እ ... ኔኔን ከቁማርተኛ ... ሰካራም ... ትምባሆ መጣጭ ... ጋር ጠሬ ... ጠር ... ከኝ ... ከበደ... ከበደ ... ነገረህ ... ከሆ ነም ... ደግ ... ስማ ደግ ... አደረ ... ኩ" ልብሷ ከሰውነቷ ጋር ይን ዘፈዘፋል፤ አሸናፊ የሚለውን ለመስማት ጆሮ ነስቷታል:: ብቻ ትናገራለች:: ቁማ ትንዘፈዘፋ ለች::ጎሊናዋ አዳዲስ አረፍተ ነገሮች መፍጠሩን አቁሞ ይደጋግማል:: አፏ ምላሷም ያንኑ ይከላ ልሳል "ደግ ... አረኩ ... ደግ ... አደረኩ እኔ... እኔ ... ካ ... ንተ ... ወዲያ ... ያ... በቃ ደግ... አደ ... ረኩ"::

አሸናፊ መካከለኛ ቁመቱን ከወንበሩ አላቆ ወደምትንቀጠቀጠው ምስኪን ባለቤቱ ተጠጋ:: በክናዶቹ ተጠመጠመባት:: ለምለም ባቀፋት ክና ዶች ውስጥ ሁና በንዴት ትንፈራገጣለች::እንደ ምንም ብሎ ወደ ሶፋው አስጠጋት::ረጅሙ ሶፋ ላይ ይዟት ዘፍ አለ:: አቅፎ አባበላት፤ ሊያቀዘ ቅዛት ታገለ:: "አስጨርሽኝ ለምለም ... የምልሽ ይገባሽ፤ስሚ!በድየሻለሁ፣ይቅርታሽን አትንፈጊኝ"

ለምለም ከሰመመን ነቃች፣ ከንዴቷ ሰከነች፤ ባሸናፊ መማጠን በረደች::

"እየገደልከ...ታድነኛለህ...እ... የወጋህ ታረሳ... ሳኛለህ...ምን ሁነሃል ዛሬ ቀን እ...ን...ተ...ሰው?"

"ስሚኝ ለምለም ዛሬ ገዳዩ ሚቱም ... እኔው ነኝ::የዚህ ቤት ሁለት አባወራ ያልኩሽም... ራሴ ነኝ:: አንደኛው እኔ ... የስከዛሬው ... የእስካሁኑ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰካራም፣ ቁማርተኛው፣ ሲጋራ መጣጩ ... አሸ ናፊ-አ ... ሽናፊ፣ የነ ዘነበ፣ የነ አሰፋ የ... የነ... ሊ...ለማ ጓደኛ... አ... ሀ... ሀ... አ ... ሀሀሀ ... ኃላፊነት የሞላኝ ግን ... ግን ... ኃላፊነት የማይሰማኝ፡፡

"ሌላው አባወራም እኔው ነኝ ... እስካሁን በደባልነት ከኔ ጋር የነበረው ... ያለው የዛሬው አዲሱ አሸናፊ በዚህ ቤት ውስጥ ሶስተኛ ሰው የነበረው ... ለምለም ትሰሚኛለሽ ... ያሁኑ የዋዜ ማው ያዲሱ አመት ... አዲሱ አሸና፣ የነለማ ጓደኛ ሳይሆን ... አ ... ሀ ... ሀሀሀ ... የትልቁ የቁምነገረኛው፣ ያስተዋዩ የከበደ ጓደኛ ነኝ፡፡ ተቀበይኝ ለምለም ... ማሪኝ ለምለም" ብሎ አሸ ናፊ ከሶፋው ተነስቶ ጉልበቷ ላይ ባንገቱ ተደፋ፡፡

"አታ ... ታስጨንቀኝ ... አሸናፊ፡፡ በቃህ ... የተጎዳኸው አንተው ራስህ ነህ ... አንተን ጎድተህ የበደልከው ቤተሰብህን ነው... መጀመሪያ የጎዳኸውን አንተን ... ይቅርታ ጠይቀው ... ለሱ ለዚህ ላሁኑ ... አንተነትህ... ተንበርከክለት... ለሱ ቃል ግባለት ... አሸናፊ" በማለት ከጉልበቷ ቀና አደረገችው፡፡

"ለተጎዳው እኔነቴ ... ለበደልኩት ትዳሬ ... ጎጆዬ ካሣ የምከፍለው በደለኛውን ... ከሃዲውን እኔነቴን በመሰዋት ነው ... ዛሬ ... የዛሬ አዲሱ አሸናፊ ያኛውን ያጠፋዋል ... ይገድለዋል ... ለምለም፡፡ ራሴን በራሴ ገደልኩት ... ለምለም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የድሮ እኔነቴን ዛሬ ቀበርኩት፡፡ለወደፊት ብሩህ ሕይወታችን መድህን ... ለጋብቻችን ክቡርነት፣ ታላቅነትና አለኝታነት፡፡”

ለምለም ከሶፋው ተነስታ ያቀራረበቻቸውን እቃዎች አንስታ ከሶፋው ላይ ቁጭ ያለውን አዲሱን አሽናፊ ወደ ምግብ ጠረጴዛው ጠራችው...



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፍሬ ህይወት ተሰማ

(1963 ―― )



ፍሬ ህይወት ተሰማ በ1963 ተወለደች፡፡የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህ ርቷን እንደጨረሰች አዲስ አበባ ንግድ ስራ ኮሌጅ ገብታ በሴክሬታ ሪያል ሳይንስና በኦፊስ ማኔጅመንት በዲፕሎም ተመርቃ በሙያዋ በመ ስራት ላይ ትገኛለች፡፡

ፍሬ ህይወት በፈ ጠራ ድርሰት በአንባቢ ያን ዘንድ አትታወቅም፡፡ ገና መጻፍ የጀመረች ወጣት ፀሐፊ ናት፡፡ ከጅምር ሥራዋ ይህን መና ገር ይቻላል፡፡ የታሪክ አወቃቀርዋ፣ የቋንቋ አጠ ቃቀምዋ ወደ ማህበራዊ ህይወት ዘልቃ የበሰለ ጭብጥ ይዛ ስትነሳ ተስፋ ያላት ፀሐፊ እንደም ትሆን ይመሰክርላት ይመስለናል፡፡ በዚህ የአጫ ጭር ልቦለዶች መድበል “አውራሪስ” የተባለው አጭር ልቦለድ ድርሰቷ ይገኛል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# አውራሪስ

ባለቤቱ መጀመሪያ የተሸነፈችለት በውበቱና በሽቅርቅርነቱ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ እንደውበቱ የምትጠላው ነገር የለም፡፡ከሁሉ በላይ ደግሞ ግዴለሽነቱ ያበሽቃታል፡፡የሴቶቹ አይን ዞሮ ዞሮ እርሱው ላይ ነው-እርሱም ካገባ በኋላ እንኳ በአ ይኑ ሴት መሸኘት አልተወም፡፡ ኃላፊነት ሲሰ ማው፣ ልጅ ሲወልድ ይተዋል ብትልም በቀን ሁለቴ ሸሚዝ መቀየሩን፣ ጸጉሩን ሲወጣ ሲገባ ማበጠሩን፣ ሽቶ መለቅለቁን፣ በዓይኑ መከተሉን ልትታገሰው አልቻለችም፡፡ፊቱ ላይ ጢም ማቆጥ ቆጥ ከጀመረ፣ ከረባት ካላሰረ፣ጫማው እንደመስ ተዋት ካላበራ እንዲሁ ያነጫንጨዋል፡፡ እርሷም ስታምርና ስትኳኳል ነው ፍቅሩ የሚያገረሽበት፡፡ ካልሆነ ዞር ብሎም አያያት፡፡ "ልጅ አትውለጂ ከወለድሽ ትወፍሪያለሽ፣ታረጂያለሽ" ብሎ ከልክ ሏት ከአንድ በላይ ሳይወልዱ ቆይተዋል፡፡

ፈልጋው ሳይሆን ሁኔታው አስገድዷት የሌለ ባትን አመል መነጫነጭ መጀመሯ ነበር የባሰ ቤቱን እንዲጠላ ያደረገው፡፡ጭራሽ የሱ ሴቶች ቤቷ ሲደውሉ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት የፍቺ ጥያቄም ለማቅረብ ፈልጋ ነበር፡፡ግን ፈራች፡፡ ካለምንም ማመንታት እሺ እንደሚላት እርግጠኛ ናት፡፡ሌላው የሚያጽናናት ነገር ለየትኛዋም ሴት የጠለቀ ፍቅር እንደሌለው ማወቋ ነው፡፡ እርሷ ንም ቢሆን ሊያገባት ፈልጎ አልነበረም የተጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቡት፡፡ በዚያ ላይ 'አንቺን ካልበደልኩሽ ፍቅር ካልነፈግኩሽ የትስ ብሔድ ምን አለበት? እበቃች ኋለሁ' የሚል የሚያሳብዳት ፈሊጥ አለው፡፡ እና ሰሞኑን የምታደርገው ጠፍቷታል፡፡

ስልኩ ሲንጫረር ለማንሳት ስትሄድ ቀድሞ አነሳው፡፡ ከንፈሯን እየነከሰች አጠገቡ ቆመች፡፡ የሚደወለው ስልክ ሁሉ የርሱ ይመስላታል፡፡ግድ አልነበረውም፡፡

"ሃይ! ሃይ! ስዊት ሽርት" አለ፡፡ ሴቶቹን ሁሉ እንዲህ ነው የሚላቸው እርሷንም፡፡ "ደህና-ደህና ... ዛሬ መደወሌ አይቀርም ነበር ... ሪሊ... ምን ችግር አለ? ተያት ባክሽ ...በቃ ማታ እመ ጣለሁ ማታ ... ልክ ሁለት ሰዓት ... ባ-ባይ!"

አንጀቷ እየደበነ በንዴት ስትመለከተው መኖ ሯን እንኳን ሳያይ ወደመስተዋቱ ሄዶ ጠጉሩን ከነካካ በኋላ ጃኬቱን መልበስ ጀመረ፡፡

"ጌታቸው-ለመሆኑ ሰው መስዬ አልታይህም? ንቀት ነው አይደል?ጥሩ ሚስት መሆኔ፣ትዳሬን መውደዴ ሲያስንቀኝ ይገባል? ለመሆኑ በዕሁድ ምድር የት ልትሄድ ነው?" አለችው የለበሰችውን ፒጃማ ከርሱ ሸክ ማለት ጋር አስተያይታ እንባ እየተናነቃት፡፡

"ለመሄድ ዕሁድን የመሰለ ቀን አለ'ንዴ?" አላት ምንም እንዳልነበረ ዓይነት ምስሉን በፊገ ግታ እያስተዋለ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዳንተ መሆን አቅቶኝ አይደለም፡፡ ትዳሬ ንና ልጄን ብዬ እንጂ" አለችው በዕልህ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ፡፡

"እንደፈለግሽ ሁኚ፡፡ ትዳራችን ምን ይሆናል ብለሽ ነው? ሰራተኛም ሞግዚትም አሉ አይደል? ብቻ እንዳታድሪ፡፡ ሚስት ውጪ ስታድር ያስጠላል" አለና ከቆዳ ጃኬቱ ጋር የሚመሳሰለውን ቡናማ ከረባቱን አስተካከለው፡፡

"እንደዚህ አልክ?" አለች በትዝብት እያየ ችው፡፡"እሺ!እኔ ደግሞ የማደርገውን አውቃለሁ፡፡ እንዲህ እንደቀለድክብኝ አትቀርም"አለች በጥላቻ ከግር እስከራሱ በግልምጫ እያነሳችው፡፡

"ነገርኩሽኮ፡፡ ለውጥ የግድ ያስፈልግሻል፡፡ አንድ ዓይነት ነገር፤ ሰው—ቤት-ልብስ-መኪና ... ብቻ ሁሉም ነገር ተደጋግሞ ሲታይ እንዴት እንደሚያስጠላ ለውጡን ስታይ ነው የምታው ቂው፡፡ በጧት እየተነሳሽ መጨቃጨቅሽንም ታቆ ሚያለሽ፡፡ ይልቁንስ ዛሬ እንዴት ነኝ?" አላት በእርካታ ራሱን በመስተዋቱ ውስጥ እየተመለ ከተ፡፡

"ደደብ ነህ!"አለችው እየተጠጋችው፡፡ "አታ ስብም፡፡ የያዝነው ትዳር እንጂ ቀልድ አይ ደለም፡፡ ካልበረደልህ መጀመሪያውኑ ለምን አገባ ሽኝ?" አለችው ፊቷ ግሞ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንጋባ ብለሽ ወጥረሽ የያዝሺኝ አንቺ። ገና ነን እንጨፍር ስልሽ መጠንቀቅ ሲገባሽ አረ ገዝሽ" ትከሻውን በግዴለሽነት ሰበቀ።

በመጋባታቸው ደስተኛነት እንደማይሰማው ሁሌም ሳይጨነቅ መናገሩ አዲስ ነገር አልነበረም -ለርሷ።

"ብቻ በሽታ ይዘህብኝ እንዳትመጣ አንተ የራስህ ጉዳይ ... ውጭውጭ እንዳልክ አንድ ቀን ውጭ እንደምትቀር የታወቀ ነው።"

አቋረጣት። "አ! ኖ! ኮኒ። ጥንቁቅ መሆኔን እያወቅሽው? ይልቁንስ እኔ የምፈራው ላንቺ ነው። ልምድ ስለሌለሽ ተጠንቀቂ" አላትና ጉንጯን ሊስማት ተጠጋት። ባለ በሌለ ኃይሏ በጥፊ አጮለቸውና "ልክስክስ! ወራዳ!" አለችው።ለርሷ የሚያሳያት ፍቅር ምን ጊዜም የኔ ነው እንድትል ቢያደርጋትም ስልክ ቤት ድረስ ማስደወሉና ፊቷ ማነጋገሩ ጭራሽ ከማንም ጋር ብትሄድ ጉዳዩ እንዳይደለ ሲነግራት ራሷን መቆጣጠር አልቻ ለችም።

"እንዴ" አለ ፊቱን እያሻሸ "ምን ነካሽ? በዕ ሁድ ቀን ሰው ትለክፊያለሽ እንዴ?በቃ ዛሬ የተ ረገመ ቀን ነው የሚሆነው-የኔ እመቤት በዱላ ሳታገላብጭኝ ልውጣልሽ" አላት ወደበሩ እየ ሄደ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"ታያለህ ደግሞ-እኔ ቆንጂት አይደለሁም" አለች ከኋላው እየተከተለችው:: "ባልሰራልህ ምናለች በለኝ-ባለጌ!" አለችና ከፍቶት የወጣውን በር ገፍትራ ዘጋችው::

በዕሁድ ቀን በዚህ ዕድሜዋ መዘናናት ስት ችል ብቻዋን ባዶ ቤት መዋሏ አንገበገባት:: ጭራሽ እፊቷ መቃጠሩ ሳያንሰው አንቺም ሂጂ ማለቱ ለርሷ ያለውን ግዴለሽነት በግልጽ አሳ ያት::በገነች::ከተጋቡ ጀምሮ ጸባዩ እንዳለ ነው:: ገንዘብ ካለው ያንበሸብሻታል:: ቤቱ አይጉድ ልም::በፍቅር በኩል ቀርቧትም ርቋትም አያው ቅም:: የጸባዩ አለመለወጥ ያስገርማታል:: በራሷ አዘነች:: ምን ለማድረግ እንዳሰበች ባትወስንም ዛቻዋን ቀጥላለች::"ቆይ ግዴለም ባልሰራለት::"

ከዮዲት ጋር ያሳለፈውን ውሎ እያስታወሰ ከምሽቱ ሁለት ስዓት ወዳለው ቀጠሮው ተጣ ደፈ:: ዮዲት እንጋባ እያለች ስትጨቀጭቀው መዋሏ አሳቀው:: "ምስኪን!" አለ በሆዱ::ሚስት እንዳለው አልነገራትም:: ሴቶች ወንድን በሞኖ ፖል የመያዝ ጉጉታቸው ያስገርመዋል:: ብቻ እነርሱን ዕድሜ ልክ በውጪ እንጂ ማግባት እንደማያስፈልግ የሚስቱን ራሷን መጣል ከዮዲት ጣፋጭ መዓዛ፣የጸጉር አሰራርና አለባበስ ጋር አስተያይቶ ማግባቱን አማረረ::

ከሰናይት ደግሞ ሚስቱ ትሻለዋለች:: እንዲ ያውም ሺህ ጊዜ:: ለለውጡና ሁልጊዜ ደግሳ ስለ ምትጠራው እንጂ ሰናይት ዘንድ መሄድን እንኳ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይወደውም፡፡ 'ሚስትህ ምን ትልሃለች? ምን ታደርግልሀለች? እንዴት ነች?' ማለቷ ያናድደዋል፡፡ ዝም ብላ መደሰት አትችልም፡፡ ካለ 'ሚስትህ' ወሬ የላትም፡፡ቆንጂት እንኳ ባሏን ተጋርታ የርሷን ያህል አትብከነከንም፡፡ ዛሬ ግን አምርራለች፡፡ካለ ነገሩ ቀናተኛ ሴት አይወድም፡፡ ለማናቸውም ፍቅርም ጥላቻም የለውም፡፡ ይቀር ባል ይደሰታል—ሲበቃው ይርቃል፡፡ የሚያናድደው ግን እነርሱ ተደስተው መራቅ አለመቻ ላቸው ነው፡፡

ማምሻቱ የታወቀው የሰናይትን ሰፈር ጭርታ ሲያይ ነበር፡፡ከዋናው መንገድ አስር ደቂቃ ወደ ሚያስኬደው ኮረኮንች ሲ.ታጠፍ ጨለማው የባሰ ተሰማው፡፡ ሰዓቱን ለማየት ሞከረ፡፡ አልቻለም፡፡ ከሁለት ሰዓት እንዳለፈ ግን ገምቷል፡፡ዮዲት አለ ቅም ባትለው ኖሮ ይህን ያህል እንደማያመሽ አሰበ፡፡ ጨለማና ኮረኮንች አይወድም፡፡ የመኪና ውን ቀለም ለማስለወጥ ጋራዥ ካስገባት ወዲህ ኮረኮንች እንደሸሸ ነው፡፡ ሰናይትም ጋ ይህንኑ ፍራቻ ከቀረ አስራ አምስት ቀን ሊሆነው መሆ ኑን በማስላት ራሱን በሃሳብ ጠመደ፡፡

መንገዱ አላልቅ አለው፡፡ ትከሻውን ቀፈ ፈው፡፡ ሁሌም ጨለማ መንገድ ላይ የሚቀፈው ነገር አለ፡፡ መመለስ አማረው፡፡ ግን ብዙ ሳይ ሄድ እንዳልቀረ ገምቶ ወደፊቱ ቀጠለ፡፡ ከኋላው ኮቴ ሲሰማ ዞር ብሎ ተመለከተ፡፡ምንም የለም፡፡ እርምጃውን አፋጠነ፡፡ ከፊቱም ጥላ ያየ መሰ ለው፡፡ ሰሞኑን የማጅራት መቺዎች ወሬ ከሌ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላው ጉልቶ ይሰማል፡፡ አይንኩት እንጂ የፈለ ጋቸውን እንደሚሰጣቸው ለራሱ ቃል ገብቶ እጆቹን ከኪሶቹ አውጥቶ እያፋተገ ወደፊቱ በፍ ጥነት ተራመደ፡፡ ከፊቱ የሰናይትን ቤት በር ሲያይ ደስ አለው፡፡ አዕምሮውን በሃሳብ ለመጥ መድ ፈልጐ ሰናይት ያንን በሚያክል ቤት ውስጥ ብቻዋን መኖሯ ሊያስገርመው ፈለገ፡፡ ከፊቱ ወደርሱ የሚመጣ ቅርጽ በጨለማው ውስጥ ታየው፡፡ ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡መናገር ፈለገ፡፡ አልቻለም፡፡ቀረቡት-ከኋላም ከፊትም፡፡ በደመነብስ እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ "የምትፈልጉትን ልስጣ ችሁ" አለ እየተንተባተበ፡፡ "ሁሉም ነገር... ይኸው" አለ የአንገት ሀብሉን ለመፍታት እጁን ወደአንገቱ እየሰደደ፡፡

ከኋላው እግሩን ተጠልፎ ዘፍ ብሎ ወደቀ፡፡ እጆቹ ግራና ቀኝ ተዘረጉ፡፡ መጮህ አልቻለም፡፡ ወገቡ ሹል ድንጋይ ላይ እንዳረፈ ተሰማው፡፡ ሆዱና ፊቱ በርግጫ ተነረቱ፡፡ የሚመቱት ሰዎች የሚናገሩት ነገር ነበራቸው፡፡ ሊሰማው ግን አል ቻለም፡፡ ከሳዱን ጨምድደው አነሱት፡፡ መልሰው አየር ላይ እንዳለ ለቀቁት፡፡ አንዳች ነገሩ እንደ ተሰበረ ገባው፡፡ መተንፈስ አቃተው፡፡

"...ዛቻው የቀልድ እንዳይመስልህ" አለው አንዱ-ድብደባው ለጊዜው ጋብ ብሏል፡፡ "እየቀ ለድክ ያለኸው በሰው ልጅ ሕይወት ነው፡፡ በንቀ ትና በግዴለሽነት የምታበላሸው የሰው ሕይወት እንዳንተው ዋጋ አለው"



t.me/OLDBOOKSPDF

እጁን ለሁለት ይዘው አንጓውን አጠፉት፡፡ እንደተጋደመ በስቃይ ሲጮህ አፉን አፈኑት፡፡ ፊቱን ደጋግመው በጡጫና በርግጫ ደበደቡት፡፡ "በዚህ ሁኔታ የምትቀጥል ከሆነና ቶሎ ካልወ ሰንክ ሆድህን በዚህ ነው የምናምሰው" ጩቤ እንዳሳዩት ገመተ፡፡ አይኑን ለመግለጥ ሞከረ፡፡ እግሮቹንና ኮሌታውን እንደያዙ ከግንብ ጋር አላተሙት፡፡-ራሱን ሳተ፡፡

*  *  *

"አስደበደበችኝ ጠዋት– ስትዝት ነበር" አላት እንደነቃ፡፡

ሰናይት ሲያመሽ ቤቱ ደውላ አለመግባቱ ሲነገራት ውጪ ልትጠብቀው ስትወጣ ነበር የሚያቃስት ድምጽ የሰማችው፡፡ ስትጠጋ እርሱ መሆኑን ስታውቅ በጩኸት ሰዎች ጠርታ ተረዳ ድተው ሀኪም ቤት ከወሰዱት በኋላ ነበር ቤቷ ያስተኛችው፡፡

"ማን? ሚስትህ?" አለችው ፊቷ በጥላቻ ኮሶ እንደመሰለ፡፡ ራሱን አወዛወዘላት፡፡

"ይቺ እርኩስ ምን ልሁን ብላ?እንዴት ባንተ ትጨክናለች? ለምን አትፈታትም?" አለችው–ቢፋ ታላት በክብር ቤቷ እንደምታስገባው አስባ፡፡

ዝም አላት-ማሰብ አልቻለም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት በማስገባቱ በኩል ያገኟት ጉረቤቷ "ለመሆኑ እንዴት ነው?" አሉ ወደአልጋው ጠጋ ብለው እያዩት:: ፊቱ ከአይኑ በስተቀር በፋሻ ተሸፍኗል::

"ምንም አይል" አለች ዘመዴ ነው ብላ መዋሸቷን እያሰላሰለች::

"ኧረ እንኳን እግዜር አተረፈው:: የአውራ ሪስ ቡድን ይሆን እንዲህ ያደረገው?" አሏት በሰፈሩ ውስጥ የታወቀውን የተደራጀ የሌቦች ድርጅት ስም አስታውሰው "አለመግደላቸውም ተአምር ነው:: ከነርሱ እጅ መትረፍ መቼም የማይታሰብ ነው::" አሉ እዚያው ሰፈር በየምክንያቱ የጠፋው ንብረትና ነፍስ እየታሰባቸው:: "ለመሆኑ ዘርፈውታል?"

"ኧረ እነርሱ አልመሰሉኝም ጋሼ:: አንድም ነገር አልወሰዱበትምኮ" አለች ሚስቱን ብታገኛት እንደምትቦጫጭቃት ለራሷ እየማለች::

"አዬ– ባለመውሰዳቸው ነው ብለሽ? አንዳንዴኮ ሰውም ቀጥሯቸው ልክ እንደታዘዙት ያደርጋሉ:: አዬ ልጄ እነርሱኮ በመጻፍና በፊልም ያዩትን እየሞከሩብን ነው" አሉ ሰውየው በምሬት ፊታቸውን ከስክሰው::

ጌታቸው ራሱን ነቀነቀና ለመናገር አፉን ሲከፍት ሁለቱም ተጠጉት:: "ጠዋት ስት ...ስት



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝት ነበር ... ምናልባት ከፍላ ... ቸው ይሆ...
ና... ል..." አለና አይኑን ጨፈነ፡፡

"ይሆናል ይቺ ርኩስ" አለች ሰናይትም በን
ዴት እየተቃጠለች፡፡

"ማን ናት?ቂመኛ አለህ እዚህ ሰፈር?" አሉ
ሰውየው በመገረም አስግገው፡፡

"ሚ ... ሚስቴ"

ሰናይት ጉረቤቷን አፈረቻቸው፡፡ የሰፈሩን
ሰው ፈርታ ነበር በማታ የምትቀጥረው፡፡ ብዙ
ነገር ሳያወራ ልታሰናብታቸው አሰበችና "በሉ
ጋሼ እግዜር ይስጥልኝ-ይሂዱና ይረፉ፤ችግር ካለ
እጠራዎታለሁ፡፡መሽቷል፡፡ አምስት ሰዓት ሊሆን
ነው" አለቻቸው፡፡

"በይ ልጄ እግዜር ይማርልሽ-የውሻ ቁስል
ያርግለት፡፡ ጠዋት እየዋለሁ" አሉና በትዝብት
እያዩዋት ተነስተው ወጡ፡፡

"ጌታቸው" አለችው ሰውየው እንደወጡ አላ
ስችል ብሏት፡፡ "ለመሆኑ ያቺ ሚስትህ ምን
ብላህ ነበር?"

ጌታቸው ትክት አለው፡፡ እንኳን አሁን በደህ
ናውም ጊዜ 'ሚስትህ' ስትለው ደስ አይለውም፡፡
ዝም አላት፡፡ የቆንጂት በርሱ ላይ መጨከን ግን
አስገረመው፡፡ሚስቱ ሩህሩህና ቻይ እንደሆነች


t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር የሚያውቀው፡፡ 'ትዕግስቷ ሞልቶ ፈሷል ማለት ነው' ሲል አሰበ፡፡ ልታስገድለው እንዳልፈ ለገች ግን ገባው፡፡ ጩቤው ማስፈራሪያ እንደሆነ አልተጠራጠረም፡፡ ቀልድ ብሎ የያዘው ነገር ችግር መፍጠሩ አሳሰበው፡፡ 'በዚህ ከቀጠልክ እንገ ድልሀለን...አሁኑኑ ወስን' ብለውታል፡፡ፈርቶ ደስ ታውን ማጣት አልፈለገም፡፡ እርሱ መታሰር አይ ፈልግም-በቃ፡፡ ለውጥ ይፈልጋል፡፡ ሰናይት ጋር እንዳይቀር ደግሞ የባሰ ቅናተኛ እንደሆነች ያው ቃል፡፡ ከእንግዲህ ያለውን ጊዜ ከቆንጂት ጋር ብቻ ማሳለፉን ሲያስበው አስጠላው፡፡ ከመሞት ሳይሻል አይቀርም፡፡ ብዙ ማሰብ አልቻለም፡፡ ስሜቱ ተፈረካከሰበት፡፡ የሚቀለውም ሆነ የሚጨ ብጠው ሃሳብ አጣ፡፡

"ጌትሽ...አመመህ እንዴ?" አለችው ፊቱን መከስከሱን አይታ፡፡

"አይ አሁን ደህና ነኝ" አላት ፈገግ ለማለት እየሞከረ፡፡

ሰናይት ለጓጓችለት ጥያቄ መልስ ስላልሰጣት አንጀቷ አርሮ "ሚስትህ ምን ብላ እንደዛተችብህ አልነገርከኝም'ኮ" አለችው፡፡

"አፍ ... ፍ! እባክሽ ተይኝ በቃ! አስደበደበ ችኝ፡፡ ቀ ... ቀናች፡፡ በቃ ሄደሽ ተኚ ምንም አትጠይቂኝ" አላት ስልችት ብሎት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰናይት ግን ትዕግስት አልነበራትም፡፡ የጌታ ቸውን ሚስት በስድብ ልትገሽልጣት ስልክ ትደ ውልና ሁለቴ መጥራት ሲጀምር ባልታወቀ ኃይል መልሳ ትዘጋዋለች፡፡“ፍቺው አይፈልግ ሽም” ማለት አማራት፡፡ጌታቸውን የመሰለ፣ ሁሌም ፍቅር የማያልቅበት ቆንጆና ሽቅርቅር ባል የምታስደበድብ እርኩስ ስለሆነች አሁኑኑ ሄዳ ብትገድላትና የራሷ ብታደርገው ተመኘች፡፡ ሚስቱን እንዲህ አስደርጋው ባይፈታትም ከእን ግዲህ ግን ቤቱ እንደማይሄድ እርግጠኛ ነች፡፡

መኝታ ቤት ሶፋ ላይ ኩርምት ብላ ለመተ ኛት ብትሞክርም እንቅልፍ ሲወስዳት ግን ዘጠኝ ሰዓት አልፎ ነበር፡፡

* * *

“ጌታቸው...ጌትሽ” አለች ሰናይት፡፡ በእጇ ፖስታ ይዛለች፡፡

“እፍ ...እህ ...እ ...እ ...እቤት? ምንድነው?” አለ ለመንጠራራት ፈልጎ ቁስሉ አላንቀሳቅስ ስላለው በስቃይ ፊቱን አጨማደ፡፡

“ማን እዚህ እንዳለህ እንደነገራቸው አላው ቅም፡፡ይኼን ፖስታ ስጪ ብለውኛል ብሎ አንድ ልጅ ሰጠኝ” አለችና አሳየችው፡፡ “ያቺ ደደብ ሚስትህ ትሆናለች– ምናልባ ልታስፈራራህ” ፊቷን አጨፍግጋ ፖስታውን አቀበለችው፡፡ “ታመው ለተኙት ሰውዬ ነው ያለኝ”



t.me/OLDBOOKSPDF

"አድራሻ የለውም?" አላት፡፡

"የላኪውም የተቀባዩም የለውም—ባዶ ነው"

"ክፈቺና ስጪኝ እስኪ" አላት ለመክፈት ሞክሮ ሲያቅተው፡፡

ሚስቱ የላከችውን ፖስታ መክፈቱ ብስጭቷን አናረው፡፡ከፍታ ደረቱ ላይ ወረወረችለት፡፡

ማንበብ ጀመረ፡፡

*"ጤና ይስጥልን*

*ትናንት ማታ ስለፈጸምነው ስህተት በጣም እናዝናለን፡፡ትዳሩንና ቤተሰቡን በትኖ ከተራ ሽርሙጣ ጋር የሚማግጥ ዳኛ ፍርድ ልንሰጥ ታዘን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአለባበሳችሁ መመሳሰል ስህተት ፈጽመናል፡፡ በእርግጥ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ አዲስ አይደለም፤ ያጋጥማል፡፡ በተረፈ የአጋጣሚ ጉዳይ እንጂ ሥራችን እንከን ኖሮት እንደማያውቅ ልና ረጋግጥልናዎት እንወዳለን፡፡*

*ምንጊዜም ታዛዥችዎ*
*አውራሪስና ጓደኞቹ*
*ወረቀቱ ይቃጠል*

"ስህተት?" አለ ጌታቸው እጁ እየተንቀጠቀጠ፡፡ ብሞትስ?አለና ደብዳቤውን ለሰናይት አቀበላት፡፡

"ሚስትህ አይደለች'ንዴ"አለችና ተቀብላ አነበበችው፡፡የጽሁፉ ይዘት አቀዘቀዛት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"የአውራሪስና ጓደኞቹ ስህተት!"አለ በቀስታ ለራሱ:: "ምን ጊዜም ታዛገርችዎ? ቂ ... ቂ ... ቂ ..." ለመሳቅ ሞክሮ አቃተው::ፊቱ በስቃይና በንዴት ተጨማደደ:: 'ውጭ ውጭውን እንዳልክ አንድ ቀን ውጭ እንደምትቀር የታወቀ ነው' የሚለው የሚስቱ አባባል ሳቁን ነጥቆት ይስቅበት ጀመር::

በማግስቱ ሰናይት ሰፈር የዕድር ድንኳን ታየ -ዳኛው ቤት::


t.me/OLDBOOKSPDF

# ቱሉ ፎርሳ

የ "ቱሉ ፎርሳ" ደራሲ አይታወቅም፡፡ ይሁን እንጂ "ቱሉ ፎርሳ" በ1968፤ በነሐሴ ወር በጎህ መጽሔት ታትሞ ለንባብ የበቃ አጭር ልቦለድ ነው፡፡ ታሪኩ ከሚያነሳው ማህበራዊ ጉዳይና ለህትመት ከበቃበት ጊዜ አንፃር ሲታይ ልቦለዱ በ1966 ህዝባዊ አመፅ ዋዜማና በ1968 ለንባብ ከበቃበት ጊዜ መካከል እንደ ተጻፈ ለመገመት ይቻላል፡፡

"ቱሉ ፎርሳ" ከአተራረኩ ማራኪነት፣ ከቋንቋው ምናባዊነት ጋር የዘመን አሻራም ውስጡ ስላለበት ለዚህ መድበል ተመርጧል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ቱሉ ፎርሳ

ቱሉን ማን የማያውቅ አለ? እናንተ አታውቁትም እንዴ? ቱሉ ይሄ ማካሮኒ ፋብሪካ ውስጥ የሚሰራው እኮ ነው። አ ቱሉን ማን የማያውቅ አለ?

ቱሉ ሠላሳ አንድ ዓመቱ ነው። ወይም ወደ ዚያ ግድም ነው። እና የቱሉ ቁመት ረጅም ነው። የቱሉ እጆች ትላልቅ ናቸው። የቱሉ ክንዶች ጠንካሮች ናቸው። የቱሉ መዳፎች ሻካራ ናቸው።ቱሉ ከማካሮኒ ፓስታና ፓስቲኒ ፋብሪካ ውስጥ ወፍጮ ክፍል ነው የሚሠራው። ወፍጮ ክፍል ስድስት ዓመት ሰርቷል። የፋብሪካው ባለ ቤት ሙሴ ጋሌብ ናቸው። ጌታ ጋሌብ እዝች አገር (ይችው የኛይቱ የምንላት) ሲገቡ ቤሳቢስቲን አልያዙም። እዚህ ከገቡ በኋላ ነው ይኸን ሁሉ ያፈሩት፤ ያን ሁሉ ቪላ ሠርተው የሚያከራዩት፤ ያን ሁሉ ሱቅ የከፈቱት። ጌታ ጋሌብ የናጠጡ ዲታ ናቸው።አቤት ሠራተኛ ሲፈራቸው። ጌታ ጋሌብ ሽማግሌ ናቸው። አጭር፣ መላጣ ባርኔጣ የማይለያቸው አማርኛ አቀላጥፈው የሚያውቁ ዕድላም ሰው ናቸው። ስለአበሻ ሲናገሩ "አበሻ ሥራ አይወድም። አበሻ ሰነፍ ነው። ለዚህ ነው ሀብታም የማይሆነው — እንደኔ" ይላሉ።

ቱሉ ፎርሳ በወር ሠላሳ አምስት ብር ያገኛል። ያ ደመወዝ ነው። ቱሉ ፎርሳ ሲሏችሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፎርሳ ያባቱ ስም እንዳይመስላችሁ:: አይደለም::
የወፍጮ ቤቱን ሥራ አታውቁትም እንዴ? ስንዴ
በካሚዮን ይመጣል:: ከካሚዮን ወደ መጋዘን
ይጋዛል::ከመጋዘን ወደማንጠርጠሪያው የወንፊት
ሞተር ቤት ይወሰዳል::ከዚያ ይታጠባል:: ከዚያ
በሞተር ይደርቃል:: ከስንት ጣጣ በኋላ ይፈ
ጫል:: ዱቄቱ በጆንያ እየታሰረ ወደቡኮ ክፍል
ይተላለፋል:: ይህን ሁሉ የሚያደርገው የሰው
ትከሻ ነው::ካሚዮን ሲመጣ ካቦው ሰው ይጠራል
እንዲያወርዱ፤ “አንድ ሁለት ፎርሳ፤አንድ ሁለት
ፎርሳ፤ አንድ ሁለት ፎርሳ ... ” ከመኪና ላይ
ኩንታሉን እየተሸከሙ ወደ መጋዘን ትንንንን...

እና በሥራ ቱሉን የሚያህል የለም:: ኩን
ታል ተሸክሞ ሲበር ጭብጥ ላባ የያዘም አይመስ
ልም::ሁልጊዜ በጩኸት “አንድ ሁለት ፎርሳ...”
ይወዳል:: ለዚህ ነው ቱሉ ፎርሳ ተብሎ የቀረው
እንጂ ያባቱ ስም ሆኖ አይደለም::

የቱሉ ሚስት ጠንፌ ነው የምትባለው:: እን
ጀራ ለመግዛት ጉልት የሄደ ሁሉ ጠንፌን ያው
ቃል:: መሸት ሲል ወደጉልት ብቅ ያለ ሁሉ
ጠንፌና የእንጀራ ሰፌዷን ይለምዳል:: መሸት
ሲል የቀን ሠራተኞች ወደቤታቸው ይመጣሉ::
እግረ መንገዳቸውን እንጀራ ይገዛሉ ሲመሽ የእን
ጀራ ገበያ ይደራል::

“እስኪ እንጀራው?” ይላል ጠጋ ይልና::
“ይኸው ወርቅ የመሰለ እንጀራ” ይባላል::
“ጤፍ ነው ቅይጥ?” ይላል ላፋ::



t.me/OLDBOOKSPDF

"ንጹሕ የበቆ ጤፍ" ተብሎ ይነገረዋል።

ጠንፌ ዘንድ ግን ብዙዎቹ እንዲያ ብለው አይጠይቁም። ብዙዎች ስለሚያቋት ዝም ብለው ነው የሚገዟት። አንዳንዴ ከተጠየቀችም፥

"ጤፍ ነው?"
"ትንሽ ዘንጋዳ አለበት"

የቀን ሠራተኞች ላፋቸው ነው የሚጠይቁት። ያገኙትን ነው የሚገዙት። የሚገርመው ነገር የቀን ሠራተኞቹ ወንደላጤዎች ናቸው። የቀን ሠራተኞቹ ወጥ አይሠሩም። የቀን ሠራተኞቹ ብዙ ሆነው በትንሽ ቤት ውስጥ ነው የሚኖሩት። ታዲያ ለምን ዳቦ (ሞፎ) ገዝተው አይበሉም?ሞፎ ወጥ አያስፈልገውም።ሞፎ የወንደላጤዎቹ ምግብ ነው። ግን የቀን ሠራተኞቹ ከዳቦ ይልቅ እንጀራን ይመርጣሉ።ደረቅ እንጀራ ማላመጥ ደስ ይላቸዋል። ምናልባት የቀድሞ ቤታቸውን፤ የወትሮ ትዳራቸውን የሚያስታውሳቸው እየመሰላቸው ይሆናል። እንጀራ የወደፊቱ የተስፋ ምልክት እየመሰላቸው ይሆናል።

ጠንፌ አንድ ሃያ አምስት ዓመት ይሆናታል። ጠንፌ ከሁለት ዓመት በፊት ቱሉ ፎርሳን አገባች።በፊትማ ከአያቷ ጋር ስትኖር የመንደር እንጀራ ጋጋሪ ነበረች። እንጀራ መጋገር እንዴት ያለ ሥራ መሰላችሁ? አንዱ ቤት ሰላቢ ነች ይላሉ፤ ሌላው ቤት ማገዶ አይመክታትም ይላሉ፤ሌላው ቤት እንጀራ ታወፍራለች ሌላውም



t.me/OLDBOOKSPDF

ታሳሳለች ... ጣጣ ነው።በመጨረሻ አያቷ ሲሞቱ ጋግሮ ከማብላት ይልቅ (በሶስት ብር ተቀጥሮ) ጋግሮ መሸጥ ይሻላል ብላ በነጋዴነት ተጠቃለ ለች።ከቱሉ ጋር የተዋወቁት በእንጀራ ደንበኝነት ነው። ሆሆይ ይሄ ደግሞ እራሱን የቻለ ታሪክ እኮ ነው።

ታዲያ ጠንፌ ወንድ ልጅ ወለደች። ልጁ ደሞ ጤና የለውም፤ እሷንም ጤና ነሳት እቴ። የእንጀራ ንግዱም አላዋጣ አለ እንደዱሮ። ርካሽ ዱቄት ፍለጋ መንከራተት አለ፤ ማገዶ ፍለጋ አገር ጥሎ መሄድ አለ። ... ኸረ ስንቱ። በዚህ ላይ ልጇ ጤና የለው።

ባሎች ሁሉ ሚስቶቻቸውን ይማታሉ።ባሎች ሁሉ ይሰክራሉ። ቱሉ ግን አይማታም፤ አይሰክ ርም፤ ከጠንፌ ምንም አይደብቅም። አምላኩ ጠንፌ ናት። ያለ ጠንፌ ምን ሕይወት አለው ና! ጠንፌም ባሏን ትወዳለች ታከብራለች።

– ጠንፌ

– አቤት

– ዛሬ ደመወዝ ተቀብዬ ከጓደኞቼ ጋር ጠላ ቤት ገብቼ ስልሳ ሳንቲም አጠፋሁ።

– ደግ አረክ።

ጠንፌ ቀና ብላም አታየው። ጠንፌ ለቱሉ፤ ቱሉ ለጠንፌ የተፈጠሩ ይመስላሉ። ትሳሳለታ ለች።

– ጠንፌ ዛሬ ደመወዝ ተቀበልኩና ስመጣ ሉካንዳ ቤት ገብቼ የሃምሳ ሳንቲም ሥጋ ገዛሁልሽ።



t.me/OLDBOOKSPDF

– ጥሩ አረክ::
– ከዚያም በፊት አማረኝና አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጣሁ፡፡ ምነው ጠንፌ ከፋሽ እንዴ?
– እኔቴ

ቱሉ ሚስቱን ትኩር ብሎም አያያት፡፡ የም ትሚሚ ይመስለዋል፡፡ ይሳሳላታል፡፡

ታዲያ ልጁ እየዋለ እያደር ይታመም ጀመር፡፡ በተወለደ በአሥር ወሩ የጠና ሕመም ታመመ፡፡ ይቃትት ጀመር፡፡ ያጣጥር ጀመር፡፡

"ሀኪም ቤት ውሰጂው" ይላሉ ጎረቤቶች፡፡
"የትኛው ሀኪም ይሻላል?"
"አሮጌው አውሮፕላን ማቢያ ያለው ጥሩ ነው፡፡"

"እሺ እስቲ" ትላለች ጠንፌ፡፡ ለባሏ ግን አትነግረውም፡፡ምን ብላ ትንገረው? የቤት ኪራይ አሥራ አራት ብር፤ የቤት ጣጣ ሌላውን ይወጣ ዋል፡፡ምን ብላ ትንገረው? እንጨቱ ውድ፤ እህሉ ውድ፤ የኩራዝ ጋዝ እንኳ ካቅሙ ዱሮ በሁለት ፍራንክ የሚሸጠው ዛሬ በአራትም ፍራንክ አይ ገኝ፡፡ ሁሉ ቀጥሏል፡፡ የረከሰ ቢኖር የሰው ነፍስ ነው፡፡ ታዲያ ምን ብላ ትንገረው?

ልጁ ጠናበት፡፡ የሰው አፍ ደግሞ አይጣል ነው፡፡ "በቅሎ ግዙ ግዙ፤ አንድ ጨው ላያግዙ" ማለት ያ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እረ ባካችሁ ሀኪም ውሰዱት?" አሉ አንድ ቀን ማታ ሊጠይቁ የመጡ የመንደር አሮጊት፡፡

"የትኛው ይሻላል?" አለች ጠንፌ፡፡
"የውሬሏ፤ ጥሩ ናት ሲሉ ሰምቻለሁ"
"እውን የውሬሏ ጥሩ ናት ሲሉ ሰምቻለሁ"
"እንዲህ እንዳትመስልሽ፤አሁን የዝች የቀለሟ ልጅ ታማባት፤ እንዲያው በጠና ተይዛባት እዛ ሄዳ እንዲያው ባንድ መርፌ አዳነቻት፡፡ ደሞ ዋጋዋ ትንሽ ነው፡፡ ሁለት ብር ከፍሎ ካርኔ መቁረጥ ነው — በቃ፡፡

ጠንፌ ልብዋ ስንጥቅ አለ፡፡ የውሬሏ ሀኪም ሁለት ብር፡፡

ሲመሽ የታመመው ሕጻን ከቶውንም ጡት መሳብ ተሳነው፡፡ ያ የፈራችው ሊመጣ ነው፡፡ ወልዶ መቅበር ላይቀርላት ነው፡፡ አዬ ሰው መሆን፡፡

— ቱሉ?
— ምን አልሺኝ ጠንፌ
— ሁለት ብር አለህ?
— እይ አሁን?... እንዴት? እኔ? ሁለት ብር ነው ያልሺኝ?
—አወን ሁለት ብር ለውሬሏ ሀኪም የሚከፈል፡፡
— ሀኪም ቤት መሄድ ያስፈልጋል?
— አወን በጣም አሞታል፡፡ አታየውም ትኩሳቱን?


t.me/OLDBOOKSPDF

— እ... ይሁን... ነገ ጠዋት እበደራለሁ፤ ግዴ ለም ጠንፌ አታስቢ፡፡

ሕጻኑ መቃተቱን ቀጠለ፡፡ከቶውንም ማልቀስ እያቃተው ሄደ፡፡ ጠንፌ ለባሏ የሚበላውን ሰጠች ውና ልጅዋን አቅፋ ቁጭ አለች፡፡

— እንብላ እንጂ ጠንፌ?

— እኔ ስበላ ነው የዋልኩት እባክህ፡፡ የሴት ነገር ስቀምስም ስበላም ጠገብኩ፡፡ ቱሉ የቀረበለ ትን የእንጀራ ፍርፋሪ በኩራዙ ብርሃን አስተዋ ለው፡፡ ትናንት ከፊቱ የተነሳው የሻገተ እንጀራ ነው፡፡ጠንፌ ዋሸቻለች፡፡ ጠንፌ ምንም አልቀመ ሰችም፡፡ጠንፌ ጠሟን ልታድር ነው— ለሱ ብላ፡፡

ጠንፌ ልጇን ታቅፋ በዓይኗ አንቅልፍ ሳይ ዞር ነጋላት፡፡ቱሉ ብር ሊበደር ወደፋብሪካ ሄደ፡፡ በሽተኛ ሕጻን፤ ምስኪን እናት፤ የምስኪን እናት እንባ በትንሿ ጎጆ ውስጥ ቀሩ፡፡

ቱሉ ጠዋት ተነስቶ ወደ ፋብሪካ ሄደ፡፡ ፈቃድ ተቀበለ፡፡ በደንቡ መሠረት ፈቃድ የወ ሰደ ደመወዝ የለውም፡፡ቢሆንም መቼስ ምን ይደ ረጋል? ልጅህ ሞቷል ና ቅበር ከመባል ልጇ ሞቷል ኑ አቃብሩኝ ማለት ይሻላል፡፡ጠዋት ሠራ ተኞቹ ወደሥራ ተሰማሩ፡፡ "አንድ ሁለት ፎርሳ አንድ ሁለት ፎርሳ ..." እንዴት ያለ ዘፈን ነው? ሠራተኞች ጆንያውን ተሸክመው ይበራሉ፡፡ጆንያ ተሸክሞ በዝግታ መራመድ እራስን መጉዳት ነው፡፡ መሮጥ ነው የሚበጀው፡፡ ማን ዝግ ብሎ?



t.me/OLDBOOKSPDF

ያውስ ካቦው "ዳይ፤ ዳይ፤ ዳይ፤ ሲል መቼ ፋታ ይሰጣል፡፡ ቱሉ እንደ እንግዳ ሠራተኞቹን ቆሞ አስተዋላቸው፡፡እንደ ጅል ተመለከታቸው፡፡ጠጉራቸው ዱቄት ለብሷል፡፡ ግንባራቸው ዱቄት ተለቅልቋል፡፡ ልብሳቸው ዱቄት ተነስንሷል፡፡ ቁልቁል ወደ አንገታቸው የሚንቆረቆረው ላብ ፊታቸው ላይ ትናንሽ ጅረቶች የሠሩ ይመስላሉ፡፡ ጫንቃቸው ጉብጥ ያለ ይመስላል፡፡ ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ ይላል፡፡ ሰዎች በጣም ይሠራሉ፡፡ያም ሆኖ ጌታ ጋሊብ አስተያየት ሲሰጡ "አበሻ ሥራ አይወድም፤ ሰነፍነው፡፡ለዚህ ነው እንደኔ ዲታ የማይሆነው" ይላሉ፡፡ሠራተኞቹ ለብዙ ዘመናት ሙሉ ቀን ሲሰሩ ነው የሚውሉት፡፡ ዲታ ግን አልሆኑም፡፡ ከቶውንም መናጢ ናቸው፡፡ ቀደም ብሎ ብድር የጠየቃቸው ሠራተኞች ሁሉ ሁለት ብር የላቸውም፡፡ አበበ እንዲያውም የሞፎ ዋጋ መክፈል አቅቶት ዱቤ ተከልክሏል፡፡ከላላ ትናንትና የጎማ ጫማውን ሸጠ ነው ራት የበላው፡ እርገጤም የቤት ኪራይ መክፈል ተስኖት ሲባረር ነው፡፡ ተክሌ የኮሸ ሲጋራ መግዣ ፍራንክ አጥቶ ያዛጋል፡፡ ሁሉም ምስኪን ነው፡፡ ሠራተኞቹ ብዙ ይሰራሉ፡፡ ብዙ ገንዘብ ግን አያገኙም፡፡ ማንን ይጠይቋል? ማንን ይለምኗል?

ቱሉ በሙሉ ሠራተኞቹን በብድር ጥያቄ አዳርሶ ሳይሳካለት ቀረ፡፡ማንም ገንዘብ የለውም፡፡ ገንዘብ ያላቸው ምናልባት የቢሮ ሠራተኞች ናቸው፡፡ እነርሱ ቢሮ ደግሞ "ያለ ሥራ መግባት ክልክል ነው" ደግሞ ከቢሮ ቢሮ ሲንጠለጠል ጌታ ጋሊብ ቢያዩትስ? በካልቾ ብለው ከሥራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያውኑ ያበሩታል። ቱሉ ከፋብሪካው አጥር ሲወጣ ችግሩን ለዘበኛው ለበቀለ አዋያቸው። አቶ በቀለ ምንም እንደሌላቸው ይልቁንም በሌት ዘበኝነት የብርድ መከላከያ አሮጌ ካፖርታቸውን ማስጣፊያ ገንዘብ በማጣት እትት ሲሉ እንደሚ ያድሩ አዋዩት። አልሆነም።

ሁለት ብር ቢያገኝ ኖሮ ልጁ ይታከም ነበር። ሁለት ብር ቢኖር ኖሮ ምናልባት ልጁ ይድን ነበር። የውሬሷ ሀኪም እጅዋ መድኃኒት መሆኑን ጠንፌ ሌሊት ነግራዋለች። ሁለት ብር ከየት ይመጣል?

ቱሉ ወደቤቱ መመለስ አፈረ።ጠንፌ ትጠብ ቀዋለች። ሁለት ብር ይዞ ይመጣል ብላ። ልጁ ሊሞት ነው። ሁለት ብር ሊያድነው ይችላል። ሁለት ብር ከየት ይመጣል?

የለበሰው አሮጌ ቱታ ምንም ዋጋ አያወጣ። ከመኪና ጎማ ውዳቂ የተሰራው አሮጌ መጫሚ ያው ስሙኒም አይሸጥ። አቤት ድህነት፤ መልኩ ምንኛ አስቀያሚ ነው?ቱሉ ምድር ሰማይ ዞሮበት አውራ ጎዳናውን ተከትሎ ሲንገላወድ ከፀሐይ ቡና ቤት አጠገብ ደረሰ። ፀሐይ ቡና ቤት የወይ ዘሮ ፀሐይ ንብረት ነው። ከመንገዱ ዳር አምሮ የተሰራ ቤት ነው። መኝታ ክፍሎች አሉት። የአበባ መደብ አለው፤ምግብ ቤት አለው። ፀሐይ ቡና ቤት ተራ ሰው አይገባም። ሠራተኞች በውጭ ሲያልፉ የቤቱን ድርጅት ከማድነቅ በቀር ገብተውም አያውቁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቱሉ ከፀሐይ ቡና ቤት ግቢ ሰተት ብሎ ገባ፡፡ወደ ጓሮ ዞረ፡፡አንድ ምግብ አቅራቢ ትኩር ብሎ አየው፡፡

- የኔ ወንድም፣ ወይዘሮ ፀሐይ አሉ?
- አወን አሉ፡፡ ማን ነው የፈለጋቸው?
- ተልኬ ነበር ብቅ ብታስደርግልኝ፡፡
- ማን ነው የላከህ?
- የለም እዚህ ላይ ያሉ ዲታ ናቸው፡፡

ምግብ አቅራቢው ገብቶ ወይዘሮ ፀሐይን ጠራቸው፡፡ ወይዘሮ ፀሐይ ቆንጆ ናቸው ይባላል፣ ወፍራም ናቸው፡፡ ጉንጫቸው ብርቱካን ይመስ ላል፡፡ ገና ብቅ ሲሉ ቱሉ ተንደርድሮ እግራቸው ስር ወደቀ፡፡

"በንብረትዎ፣ በትዳርዎ ሲሉ ይለመኑኝና ሁለት ብር ያበድሩኝ፡፡ እንዲያው ደፈረኝ አይበ ሉና ሁለት ብር ስለነፍስ ብለው ልጄ ታሞብኝ .."

"ሂድ ወዲያ!" አሉና እሜቴ ፈንጠር ብለው ቆሙ፡፡ "የማንም ዕብድ መጫወቻ አደረገኝ እንዴ! እከከከ ሌባ ቀጣፊ ሥርተህ አትበላም? እንዲህ ነችና ፀሐይ ..." እንደ ወፈፌነት አደረጋ ቸው፡፡ ዘበኛው መጣና፣ "ሰውዬ ቀስ ብለህ ውጣ ሳትደበደብ" አለው፡፡

ቱሉ ዓይኑ ረጠበ፡፡ ቅልጥሙ ካደው፡፡ ይንቀ ጠቀጥ ጀመር፡፡ እየተገላመጠ ከግቢው ወጣና ካጥሩ ስር ኩርምት አለ፡፡ ዘበኛው መጣ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

— ስማ ሰውዬ ምን ሆነሀል?
— ፍርሀት ይዞኛል
— ቤት የለህም?
— አለኝ፡፡ ቤት ነው? እ ... የኔ ቤት እ...
— ሰክረሀል መሰል

ቱሉ ደረቅ ሣቅ ያዘው፡፡ ከቶውንም ይንፈቀ ፈቅ ገባ፡፡ አፈፍ ብሎ ተነስቶ ቆመ፡፡
— ሃሃ ሃሃሃ እኔ? እኮ እኔ ልሰክር?

ቱሉ ሽቅብ ይሮጥ ጀመር፡፡ እየሳቀ፡፡ እንደ ሰከረ ሰው ለብቻው እየፈነደቀ፡፡ ምን ይታወቃል ሰክሮ ይሆናል? እየሮጠ ወደቤቱ ሄደ፡፡ ከደጃፉ ቆመ፡፡ ፀጥ አለ፡፡ ለንቦጩን ጣለ፡፡ ማልቀስ ቃጣው፡፡ ልጁ ሞቶ ይሆን? ወይስ ገና ሞቶ አላ በቃም፡፡ እንደ ደህና ሰው ወደቤት ገባ፡፡
— ቀናህ ቱሉ?
— እ ምን አልሺኝ? የት? መቼ?
— ብሩን አገኘህ?
— አዎን
— ጎሽ እንካ ልጁን ያዝልኝ፡፡ ከማማ ወደሬ ቤት ጃንጥላ ተውሼ ልምጣ፤ ፀሐዩ ገሮአል፡፡
— ካዛንችስ ሀኪም ቤት ልትሄጂ?
— አዎን
— አይ አትሂጂ ጠንፌ፤ ጠንፌ አትሂጂ ምንም ዋጋ የለው፡፡ እኔ እ... እኔ አውቀዋለሁ፡፡ ዋጋ የለውም፡፡

— ምነው? ለምን ዋጋ የለውም?



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ስመጣ አሁን እዛጋ እንትን አገኘኝ፡፡

— ምን?
— ይሄ ምንድነው ስሙ? ት ...ትልቅ ሰው፡፡ ጠጉሩ በ ... በጣም ትልቅ፡፡ትልቅ ትልቅ ቃልቻ አገኘሁ፡፡ ዋዋ ... ዋና ባ...ባሕታዊ መስቀል ሁሉ የያዘ ትልቅ አ ... አዋቂ፡፡
— ታዲያ ምን አለህ?
— አትድከም አለኝ
— አትድከም?
— አ ... አወን፡፡ ልጁ አ ... አይ አይ ... አይድንም አለኝ፡፡

ጠንፌ ከመሬቱ ላይ ልጅዋን እንደታቀፈች ሟሟች፡፡ በክንድዋ የታቀፈችውን ሕፃን ገለጥ አድርጋ ፊቱን አየችው፡፡ ትኩሳት የጠበሰውን ጨቅላ በትኩስ እንባ ቀቀለችው፡፡ ተንሰቀሰቀች፡፡ "ልጄ ልጄ ወይኔ ልጄ" ብላ በተሸነፈ ድምጽ አለቀሰች፡፡

ቱሉ ቤቱን ጥሎ ወጣ፡፡ ራቅ ብሎ ከምድሩ ላይ ቁጭ አለ፡፡

"ወይኔ ወይኔ ልጄን በላሁ፡፡ነፍሴን በውሸት ሸጥኩ — ወይኔ ወይኔ" አለ፡፡ ይነደው ጀመር፡፡ ቱሉ ዋሽቶም አያውቅ አለዛሬ፡፡ አይሆንለትም፡፡ ያየውን አላየሁም ያለበት ጊዜ ነበር፡፡ ሳያይ አየሁ ያለበት ጊዜ ግን ያለዛሬ ... ቱሉ እንባ አልወጣውም፡፡ አንጀቱ ግን ተንሰፈሰፈ፤ ቁጭ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ ወባ እንደያዘው ይንዘፈዘፍ ጀመር:: በሌሎ ሮው እያሰበ እራሱን ረገመ::

— ቱሉ ፎርሳ ምነው ወደክ እንዴ?

— እእ ... እኔ አወን:: የለም አለሁ::

— በል ተነሳ:: እንካ ትንሽ ገንዘብ

— ገንዘብ? ምንድነው እሱ ጋሽ ምትኩ? ል... ልጄ ሞተ? የድር ገንዘብ ነው እንዴ?

— ምንድነው የምትለው ቱሉ ፎርሳ? ትቃዣ ለህ ልበል? እንካ ሃያ ብር፤ የሠራተኛ ማህበር ብድር ነው:: ወደፊት ትከፍላለህ::

— ማ ... ማህ ... ማህበር? የ ...የኛ ማህበር? ለኔ ለ ... ለኔ ነው ሃያ ብር::

— ኋላ ትፈርማለህ::አሁን እቸኩላለሁ:: ወደ ፋብሪካ ልመለስ ነው:: ጠፍቼ ነው የመጣሁት ልሰጥህ::

ቱሉ ብቻውን ቀረ::እሱና ሃያ ብሮች::አንድ ቀይ አንድ ብጫ፤ አምስት አረንጓዴ ብሮች— የሚሰራው ጠፋው:: ፊቱን ጠረገው:: ቆጠረው "አልማለሁ ልበል?" አለ ለራሱ እራሱን አርገፈገ ፈው:: "የለም ሕልም አይደለም" እየሮጠ ወደ ቤቱ ገባ:: ጠንፌ ከልጅዋ ጋር ተኮራምታ ትንሰ ቀሰቃለች:: በሩን በርግዶ ዘሎ ገባ::

"ጠንፌ ጠንፌ" ብሎ ተጣራ:: ቀና ብላ አየችው:: ፊቷ ንፍሮ ይመስላል::

— እንሂድ ጠንፌ

— የት?

— ሀኪም ቤት፤ የውሬሏ ሀኪም እጅዋ መድ ኃኒት ነው ብለሽ የለም?


t.me/OLDBOOKSPDF

– የለም ዋጋ የለውም ከንቱ ነው፡፡
– ለምን ዋጋ የለውም?
– ልጁ ከሞት አይድንም
– እንዴት አወቅሽ?
– ያ ያገኘሁው አዋቂ ሰው አይድንም ብሎህ የለ?
– እሱን ተይው አያውቅም
– ያውቃል ቱሉ፡፡ ሰውዬው ያውቃል፡፡
ቱሉ ደነገጠ፡፡ በገዛ ገመዱ እንደተተበተበ ገባው፡፡

"ስሚ ጠንፌ በመጨረሻ ያለኝ እኮ ሀኪም ቤት ከሄደ ይድናል ነው" አላት፡፡
"የት ሀኪም ሂዱ አለ?"

"የውሬሏ ሀኪም ቤት– የካዛንቺሷ ሀኪም ቤት" አለና ሃያ ብር አጠገብዋ አስቀመጠ፡፡ ቀና ብላ አየችው፡፡ ለመጠየቅ ጊዜም የላት፡፡ ወደ ሀኪም ቤት ጠንፌና ቱሉ ልጁን ይዘው በረሩ፡፡

በሶስተኛው ቀን ሕፃኑ እንደልብ ይጠባ ጀመር፡፡ዳን ያለው መቼም አይሞት፡፡ብቻ ከልጁ መዳን ጋር በቤቱ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ እንደቀድሞው መነጋገር መጨዋወት ቀረ፡፡ ሁለቱም ተፈራሩ፡፡ ጠንፌ ባሏን ሰረቅ አርጋ ታይና ቁና ትተነፍ ሳለች፡፡ ለመጠየቅ ትከጅልና መልሳ ጥያቄውን ትውጠዋለች፡፡አንድ ማታ ከራት በኋላ ድፍረቷን ሁሉ ሰብስባ፡
– "ቱሉ" አለችው፡፡ድምጽዋ ፀጥታውን ሲሰ ብር ቤቱ የፈረሰ ያህል ሆነ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

– ቱሉ
– ምነው ጠንፌ?
– አንድ ነገር ልጠይቅህ?
– ምንድን ነበር ጠንፌ?
– ሃያውን ብር ከየት አመጣኸው ቱሉ?
ድንገት በሩ ተንኳኳና ተከስተ ገባ፡፡መሽቷል፣ ሦስት ሰዓት ሊሆን ነው፡፡
– እንዴት አመሻችሁ ሕፃኑስ ደህና ዋለ?
– ደህና ነው፣ አሁንማ ተሻለው፡፡ምንም አይለው፡፡
– ጥሩ ጥሩ፡፡ እንኳን ተሻለው ጃሪ ፡፡ እኛማ በቀደም ደንግጠን፡፡
– አረፍ በል ጋሽ ተከስተ!
– የለም ልሂድ፣ እቤትም አልደረስኩ፡፡ ገና ከስብሰባ መውጣቴ ነው፡፡
– ስብሰባ? እስካሁን የሚያቆይ?
– አወን እባክህ ሰሞኑን አንድ ትዕዛዝ መጥቷል፡፡
– የምን ትዕዛዝ?
– ማህበሩን አፍርሱ የሚል
– ማህበሩን? ማን? የ ... የት? ... እ... እንዴት? ማ ... ማን አባቱ?
– ከሚኒስቴሩ ነው አሉ፡፡
– እኮ ለምን?
– ሙሴ ጋሊብ ሠራተኞችን ሥራ አስፈታች አባለገ ብለው አመልክተው ነው ይባላል፡፡ ብቻ ገና ነው እስኪ እንሰማው የለ? በሉ ደህና እደሩ እቸኩላለሁ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

ተከስተ ፋብሪካ ውስጥ ሜካኒክ ነው፡፡ ተከ ስተ የሠራተኛ ማህበር ፀሐፊ ነው፡፡ ተከስተ ማለፊያ ሰው ነው፡፡ ተከስተ ከቱሉ ቤት ወጣ፡፡ ቱሉ ከበራፉ ላይ ቆሞ በጭለማ ውስጥ የሚወዛ ወዘውን የተከስተን ቅርጽ ትኩር ብሎ ያየው ጀመር፡፡ ከባሻገር ያዲስ አበባ የኤሌክትሪክ ብር ሃን እንደጧፍ ሲንቀለቀል ይታያል፡፡ ከላይ ከሰ ማይ ከዋክብት ይፍለቀለቃሉ፡፡ እነሱም እንደ ጧፍ ናቸው ይባላል፡፡ ከዚያ ዳር የቱሉ ሁለት ዓይኖች አለወትሮአቸው በሲቃ ተጉልጉለው እሳት የሚተፉ ይመስላሉ፡፡ ከኋላው ደግሞ ጋዝ ያለቀባት የቱሉ ኩራዝ ብልጭ ድርግም ትላ ለች፡፡

ቱሉ ሁለት እጆቹን በኃይል ጨብጦ ስሩ እየተግተረተረ፤ጥርሶቹን ነክሶ ጡንቻው እስኪነፋ ድረስ ካማጠ በኋላ፥

"ይቺ ማህበር ነፍሴ ቆማ አትፈርስም" አለ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

